

# በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ሲነገር የኖረው ትንቢት

"በምስራቅ ባለች ታላቅ ሀገር በርሷ ላይ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ጦርነት ይነሳል፣ ከጥቂት ሰወች በስተቀር በርሷ የሚተርፍ የለም።" ራዕየ ሳቤላ

''ትንቢትን አትናቁ ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ''

**1ኛተሰ 5:20**

**ሰምተው የተገበሩት ከሞት ሊድኑበት፣ ንቀውት ለሚሞቱት፣ በማይቀረው ፍርድ ጊዜ ''አልሰማንም ነበረ'' ቢሉ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ፣ ዛሬ በአምላክ ፈቃድ እርስዎ ጋር የደረሰ መልእክት**

## ትውልዱ ተጠራጣሪ ነውና፣በቃል የተነገሩት አእላፍ ትንቢቶች ሳይካተቱ፣በቅዱሳት መፅሀፍት ሰፍረው ያሉት ብቻ በጥቂቱ የተጠቀሱበት ፅሁፍ

**"ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ቃሌ ግን አያልፍም።" ማቴ 24:35፣ሉቃ 21:33፣ማር 13:31 ሁሉም ላይ ተደጋግሞ የተፃፈ ፅኑ የስላሴ ቃል**

**ሙሉው ሳይፈፀም ይህ የመጨረሻው ሰፊ ጥሪ ነው!**

ማስታወሻ፡-

- መልዕክቱን በጥንቃቄ ያንብቡ
- በጋዜጣ በመጽሔት አትሙት፣ አሰራጩት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ልቀቁት፡፡
- ፋክስ አድርጉት፣ ኢሜይል አድርጉት፣ በድረገጾቻችሁ ልቀቁት፣ በፖስታም ላኩ፡፡
- ለሌሎች ሲሰጡ ሁሉንም ገጾች ይስጡ፡፡ አይቀንሱ ፤ አይጨምሩ ፤ አያያሻሽሉ ፡፡ ይህን የሚያደርጉ አለቅጣት አይታለፉምና !
- መሪ ሆነ ተመሪ ሁሉም የሚመዘነው እንደመጸፀቱና እንደቅን ተግባሩ ነው፡፡
- በጎ ሥራም የሚጀመረው ከትንሹ ነውና !

መልካም የመረዳት ንባብ ይሁንልዎ !

# በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ሲነገር የኖረው ትንቢት

**ትውልዱ ተጠራጣሪ ነውና፣ በቃል የተነገሩት አእላፍ ትንቢቶች ሳይካተቱ፣ በቅዱሳት መፅሀፍት ሰፍረው ያሉት ብቻ በጥቂቱ የተጠቀሱበት ፅሁፍ**

**"በምስራቅ ባለች ታላቅ ሀገር በርሷ ላይ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ጦርነት ይነሳል፣ ከጥቂት ሰወች በስተቀር በርሷ የሚተርፍ የለም።"**
ራዕየ ሳቤላ

**ከሁሉ በላይ ታላቅ ሀያል ንጉስ፣ ፈጣሪ እውነት አለ ይሆን? ዛሬ ምናችን ነው? በሀገራችን ምን ብንተራመስ፣ ምን ጭንቅ ቢይዘን፣ ከሀሳባችን አስገብተነው እናውቅ ይሆን? ዛሬ የሁላችንም ሀሳብ በሆነው የሀገር ትግላችን ይህንን ሀያል አካል ዋጋ ወይ ቦታ ሰጥተነው እናውቅ ይሆን? ነው? የለም ነው የምንለው?**

**እንዴት ሆኖ? ለነገሩ አይደለም ምእመኑ፣ ቤተክርስቲያኒቱም እንኳን ስንት ጭንቅ ህዝቡን ሲይዘው፣ ክፉ ቀን ሲመጣ፣ መንገድ ሲጠፋን ምህላና ሱባኤ እንኳን ጠርታ አታውቅም። ተጠራ ቢባል እንኳን በዙሪያዋ ካሉ ካህናት በቀር መጠራቱን እንኳን የሚሰማ የለም፤ ይህ ሁሉ ምእመኖቿ የሌላ እምነት የሆኑ ይመስል አታስተባብራቸውም፤ ትታቸዋለች፣ አርቃቸዋለች፤ እረፍት በሌለው ስውር የጠላት ስራ ተዳከማለች፣ ግድ ከማይሰጣቸው ልጆቿ በስውር ጠላት ጥፋቷን ያፋጥነዋል፣ እኛም ግድ የለንም፣ እሷ ለኛ ጥቅም እንጂ በመሰረቱ እኛ ለሷ እንዳልሆንን ዘንግተን ጨለማ ወርሶናል፣ በጋራ ወደአምላካችን በጭንቃችን ጊዜ እንኳን ለመፍትሄ ቆመን ተጣርተን አናውቅም።**

ሁላችንም የዘመኑ የኢትዮጵያ ሰዎች ሀይማኖትን “ለምግባር ማሳመሪያና ለሳይኮሎጂ ጥሩ የሆነ ነገር” ብለን ያዝነው እንጂ የአምላክን መኖር እውነትነት ተቀብለን አውቀን አምነን የያዝነው ነገር አይመስልም። ሐቁን ያዘው፣ አይመስልም ሳይሆን አይደለም።

እውነት አምነን ቢሆንማ፣ እንዴት ሁሉን የሚችል ሀያል አካል አለ ብሎ የሚያምን ሰው በሀገሩጭንቅ በስጋት ሆኖ መፍትሄን በሚመኝበት ሰአት ወደዚህ ሁሉን የሚችል አካል እርዳታ ሳይጠይቅ፣ እሱን ከግምት ሳያስገባ እንዲሁ ተግባሩ ሙሉ በትርኪምርኪ የስጋ ልፊያና ፖለቲካ ዙሪያ መርመስመስ ይሆን ነበር?

እርዳታ መጠየቁን ተወውና፣ እንዴት "ከሁሉ ነገሬ የማስቀድመው፣ ሀያል የሁሉ ፈጣሪ የሆነ አባትና ንጉስ አለኝ" ብሎ የሚያምንና የተቀበለ ሰው፣ ሁሉ ትግሉና ጉዞው ይህንን ጌታውን ይመቸው/አይመቸው፣ ለአንዲትም ቅፅበት ሀሳብ ሳይሆንበት፣ ሊያቋቁም የሚጥረው ስርአት “ከሁሉ ሚቀድምብኝ ጌታዬ” ብሎ የተቀበለውን የጌታውን ህግ አክብሮ ለመኖር ይረዳኛል? ወይስ ያስከዳኛል ብሎ ሊያስብ ገድ አይሰጠው?፣ ያም ከሁሉ የቀደመ መስፈርቱ ሊሆነው አይቻለውም?

እውነት፣ ሀቁ ይነገር ከተባለ እምነት የሚባል ነገር ስለሌለን ነው እንጂ። እውነታው ያ ነው። ባፋችን እንበል እንጂ፣ በህይወትና ኑሯችን፣ ባጠቃላይ እንቅስቃሴያችን እግዚአብሄር ከሁሉ ኋላ የሚመጣ፣ ተጨማሪ ነገር ስላደረግነው እንዲሁም በተግባራዊው ህይወታችን አንዳችም ቦታ ሳንሰጠውና የሱ መኖር/አለመኖር በኑሯችንና ስራችን የማይንፀባረቅ እንደ ምናባውቲ ቲዮሪ አልፎ አልፎ የምንጠቅሰው ለሳይኮሎጂ፣ ለምክር ብቻ በሚመስል መልኩ የምንጠቀምበት ወይ ደግሞ ቤተክርስትያን ስንሄድ ብቻ ስዊች ኦን አድርገን ስንመለስ በቀረው ህይወታችን ፍፁም ስዊች ኦፍ የምናደርግበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

ሙሉ ህይወታችንን ተወልደን ያደግነው በዚሁ ዘመን በመሆኑ፣ ከዚህም ዘመን አኗኗር ሌላ አይተንም ስለማናውቅ ራሳችንን አወዳድረን ከሰው የተፈጠረበት አኗኗር ስተናል/ቀርበናል የሚለውን ልናውቅ አንችል ይሆናል። ነገር ግን የቀደሞችን አኗኗር የተዘገበውን፣ ያባቶቻችን ከእግዚአብሄር ጋር አኗኗር የተፃፈውን ሁሉ ለማየት ገድ ሰጥቶን አያውቅም እንጂ ምን ያክል በአስፈሪ ደረጃ ፈጣሪ አስቦ ከፈጠረን የአኗኗር ሁኔታና የሱ ልጅነት ህይወት እንደራቅን ማየት በቻልን ነበር።

ዛሬ ኢትዮጵያውያን ከልባችንና ታሪካችን በተቃራኒ እግዚአብሄርን ከህይወትና ስራችን እጅግ አርቀን እንደ አህዛብ በስም ብቻ በማያዝ፣ ጭራሽ መሬት ላይ እንደሚታየው ማንም ሳያስገድደን ልጆቻችን ስሙን በአደባባይ መጥራትን እንዲሸማቀቁበት ለሚያደርግ ትምህርት እንዲሁም አስተዳደግ አሳልፈን ሰጥተን፣ ትልቁንና ዋናውን የአለም አካል የሆነውን ፈጣሪ ከህይወታችን አስወጥተንና ክደን፣ በስጋችን እኛ ለሁሉ ብለን፣ ከሁሉ አልፎም የአምላክን ስም በአደባባይ መጥራትን የሚጠየፍና የሚያስጠይፍ የአስተዳደር ርእዮትና መዋቅር ባልገባን መልኩ ተቀብለንና አውጀን የማይፈታ ቅዠት፣ ትርምስና ግራ መጋባት ውስጥ እንገኛለን።
ተቀበልነው አልተቀበልነው የሀገሪቱም ሆነ የአለሙ ሁሉ ባለቤትና አድራጊ ባለስልጣን እሱ ነውና በዘመናችን የሚፈፀመው የሚሆነውን የገለጠላቸው ተናግረውት፣ እንዲሁም በበዙ የትንቢት መፅሀፍት ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

ይህ ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው "የኢትዮጵያ ትንሳኤ" ተብሎ በብዛት የሚታወቀውን ጨምሮ የብዙ ነገሮች መፈፀሚያ የሆነው ጊዜ ፍፁም ስለመቅረቡ ምስክር ይሆነን ዘንድ የተፃፉት ምልክቶችን ስንመለከታቸው፣ ጊዜው እጅግ እጅግ መቅረቡን እየመሰከሩ ብቻ ሳይሆን ያለፍነው እስኪመስል ድረስ በገሀድ ተፈፅመዋል።
ለመሆኑ እነዚህ ማንን/የትኛውን ትውልድ ይገልፃሉ?

እስኪ የተፃፉትን ቃል በቃል እንመልከታቸው...
" ነጋድያን: ወዲያና: ወዲህ: ብለው: እንዳይነግዱ: የባህር: ወደብ: ይዘጋባቸዋል፣ የዚያን: ጊዜ: ንብረት: ብላሽ: ነው" ፍካሬ ኢየሱስ
በዚያ ጊዜ ወደብ አልባ መሆናችን፣ ረብህ የሌላቸው እቃዎች መወረራችን ቀድሞ ተነግሯል
"ባህላቸውን: ይለውጣሉ፣ የያዙትን: ይጥላሉ፣ ያላዩትን: ይናፍቃሉ፣ ሰብአዊ: ባህሪያቸውን: በእንሰሳ: ባህርይ: ይለውጣሉ፣ ነውርን: ይንቃሉ፣ ኃፍረታቸውን: ይገልጣሉ. . . እግዚአብሔር: ኃጢያታቸውን: ስለታገሳቸው: እንደሌለ: ይቆጥሩታል፣ በስራቸው: የጎሰቀሉ: በሀሳባቸው: የረከሱ: ናቸው።" ፍካሬ ኢየሱስ

በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ *"እርሱም አለ፦ ፊቴን እሰውርባቸዋለሁ ፍጻሜያቸው ምን እንደ ሆነ አያለሁ፤ ጠማማ ትውልድ፥ ያልታመኑም ልጆች ናቸው።"* ብሎ እግዚአብሄር የተናገረውቃል፣ ልጆቹ የሆንን ግን የረሳነው የዛሬዎቹን እኛን በደንብ ይገልፀናል።
" የሀገር: ፍቅር፣ የወገን: ክብር: አይሰማቸውም፣ የአባት: እናታቸውን: ምክር: አይቀበሉም: ተውን: ልቀቁን: እንኑጥ: እንፈርጥጥ: ይላሉ". . . "እድሜያቸው: ያጥራል፣ በወጣትነት: ዘመናቸው: ይቀሰፋሉ" ፍካሬ ኢየሱስ

ከአገላለፁ እንደምንረዳው ራእዮቹ በተፃፉባቸው ጊዜያት ከነበረው የእምነት እሴቶችና ስብእና ጋር እያወዳደሩ እንደሆነ ይጠቁማል በጥንት ኢትዮጵያውያን ዘንድ የነበሩትን ወርቃማ እሴቶች ዛሬ ላይ ያለን አናውቃቸውምና፣ የኛን ትውልድ የገለፁበት መንገድ እንዲሁ በባዶ እየወቀሱን መስሎ ሊሰማን ይችላል። የጥንት ኢትዮጵያውያን ይህ በአምላክ የተወደደ ባህል፣ ስነልቦናና አኗኗራቸው እንዲሁ አፈታሪክ፣ እራስንም በባዶ መካብ ይሚሉ ነው ይኖራሉና ነገር በምስክር ይፀናል እንዲል የጥንት ከኛ መዛግብት ውጪ ባሉ በዘመኑ በታዘቡ የውጭ ምስክሮች እንኳን እንደገለፁት ሆሜር እውቁ የግሪክ

ባለቅኔ "የኢትዮጵያ ሰወች በጉልበት ኃያላን፣ በውበት የተደነቁ፣ በጠባይ ጭምቶች ትህትናን የተሞሉ..." ብሎ ሲገልፃቸው፣

ታላቁ የምእራባውያን የታሪክ አባት የሚባለው ግሪካዊው ሔሮዳይተስ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሲገልፅ "እጅግ ያማሩ ሕዝቦች ያሉባት፣ ርህራሄያቸው እንደ እግዚአብሔር የሆነ፣ ምንም መንገደኛ የሚበላው የማያጣባት ፣ በእድሜያቸው ከ100-130 አመት የሚኖሩ፣ ነውርና ክፉ ነገር በሀገራቸው የተጠላ፣ የጤና ምንጭ የሚሆኑ ውሆች ያሏቸው፣ እነሱን በጠጡ ጊዜ ሰውነታቸው የሚታደስ (ፀበል?) " በማለት ድንበሯም አልፎ እስከ ነጭ አባይ እንደነበረ ጠቅሶ የኢትዮጵያን ህዝብ አኗኗርና በእምነታዊ ኑሯቸው ያገኙትን የአምላክ በረከትና ቅርበት ይመሰክራሉ።

ይህ ፍልስፍና፣ እምነትና በእንቁ ማህበራዊ እሴቶች የተገነባ ማንነታችን እንዲሁ የተወሰኑ አናሳ ጥቃቅን ህዝቦች ለአጭር ጊዜ የነበራቸው ማንነት ሳይሆን፣ እጅግ በግዙፉ የሰራ፣ ለረዥም ጊዜ በታላቅ ግዝፈት ተተግብሮ የተኖረበት፣ የሰው ልጅና አእምሮው በልዕልና ላይ ደርሰው በሰፊውና በቀጣይነት ሊኖሩ የሚችሉበት ታላቅ ስርአት ነውንጂ። ለዚህም ምስክር የሚሆኑን፣ ኢትዮጵያውያን በአናሳነት ተወስነው የቆዩ ሳይሆኑ በታላቅነት ሲሄዱ የነበሩበት መሆኑ ነው።

የዘመኑ ትውልድ ማንነቱን ይቀበለውም አይቀበለውም፣ በዚህ ማንነት የቀድሞው አክሱም መንግስት በዘመኑ "የምድር 5ቱ ምሶሶዎች" ከተባሉት ታላላቅ መንግስታት ዋናው ነበር። ይህቺን ምድር ካስተዳደሩ ታላላቆቹ 5 ነገስታት ዋናው ተብሎ ነበር የሚጠቀሰው። ብሎም አለማቀፍ ታሪክ እንደሚናገረው ከዛ በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት ታላቅነታቸው ከዛ በእጅጉ የጨመረ እንጂ የቀነሰ አልነበረም።

በመፅሀፈ ነገስት እንዲሁም በትንቢተ ኢሳያስ ተደጋግሞ "የኢትዮጵያው ንጉስ ቲርሐቅ" ተብሎ የተጠቀሰው ታላቅ ንጉስ ኢትዮጵያን አልፎ በግብፅም በመንገሱ ታላላቅ ፈርኦኖች ከሚባሉት ዋናው ሆኖ በታሪክ ተዘግቧል።

ይህም የኢትዮጵያውያን የራስ ማኮፈስ ወሬ ሳይሆን ከኛ ይልቅ በሌላው አለም የተዘገበ ነው። መቼም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ልጆች በውጪዎች ካልተነገራቸው አለማመናቸው እጅግ አሳዛኝ፣ የማትገባቸውን ሀገር ላይ የተወለዱ ቢያስመስላቸውም፤ እነሱ ከፈለጉ ለቀዋት ሊሄዱ ይችላሉ እንጂ ታሪክ እንደሆነ ታሪክ ነው፤ ለዘላለም ፅኑ ሀቅ ነው።

ይህ ሐቅ በመሆኑም የዚህ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ታላቅነት ከአፍሪካውያን ይልቅ የራሳቸውን በማግነን በሚታሙት የውጭ ሀገራት ሰወች ሳይቀር ሊካድ ያልተቻለው ሀቅ ነው።
የተባለው ታዋቂ የግሪክ የጂዎግራፊ አባት ስታርቦ በፅሁፎቹ ይህ ንጉስ አልፎ እስከ አውሮፓ ክፍሎች ድረስ በእጁ ያስገባ መሆኑን እንደዘገበ "Starbo" በሚል ርእስ የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ባሳተመው ፅሁፍ ላይ ማግኘት ይቻላል።

አልፎም በሌሎች ፅሁፎች ይህ ታላቅ ንጉስ ብሎም በስፔን ምድር እስከሚገኘው "የሄርኩሊስ ምሶሶዎች" እስከ ሚባሉት ቦታዎች የተቆጣጠረ ታላቅ ንጉስ እንደነበረ በ1975 የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ "Before Color Prejudice: The Ancient View of Blacks" በሚል ባሳተመው ፅሁፍ ላይ ማግኘት ይቻላል።

አልፎም በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ የአሶር ንጉስ ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት በተነሳ ጊዜ፣ ህዝቅያስን ባስጨነቀ ጊዜ በነቢዩ ኢሳያስ በኩል ወደእግዚአብሄር ባለቀሰ ጊዜ እግዚአብሄር ኢየሩሳሌምን ከወረራ ለማትረፍ ቢፈልግ ከደቡብ በአሶር ንጉስ ላይ ያስነሳው ይህንን ታላቅ

ንጉስ ነበር። ይህንንም ሲገልፅ በመፅሀፍ ቅዱስ ሁለት ቦታዎች ላይ "የኢትዮጵያ ንጉሥ ቲርሐቅ ሊወጋህ መጥቶአል የሚል ወሬ በሰማ ጊዜ ደግሞ ወደ ሕዝቅያስ መልእክተኞችን ላከ..." ብሎ ይህንን እስከ ሶሪያ ድረስ የዘመተ የኢትዮጵያ ታላቅ ንጉስ ይገልፀዋል።

" በዚያን ጊዜ: አሉባልታ: ትእቢት: ስድብ: ራስን: መውደድና: ማክበር: መማለጃ: ተቀብሎ: ፍርድ: ማጣመም፣ ገንዘብ: መቀማት፣ ወንድምን: መግደል". . . "ድንበር: ማፍረስ፣ ወሰን: መግፋት". . . "ፍቅር: ከነሳቸው: ይርቃል።" ፍካሬ ኢየሱስ

" በዚያን ጊዜ: ለብዙ: ክብር: የታጩ: በማዕርግ: በሹመት: ያደጉ: በከፍተኛ: ደረጃ: ላይ: የሚገኙ: ሁሉ: አደራቸውን: ይዘነጋሉ፣ ሀገራቸውን: ይከዳሉ፣ መህላቸውን: ያፈርሳሉ፣ ከባለሚልነታቸው: ይወጣሉ፣ ከማዕርግና: ሹመት: ጓደኞቻቸው: ይለያሉ". . ."ባለስልጣኖች: ከአመፀኞች: ጋር: ይተባበራሉ:". . ."ክፉ: ስራቸው: በተገለፀባቸው: ጊዜ: ይፀፀታሉ" ፍካሬ ኢየሱስ

" በዚያን ጊዜ: የምድረበዳ: አውሬዎች: ቦታቸውን: ትተው: ወደከተማ: ይገባሉ። አውሬ: የተባሉ: ባሕታውያን: ናቸው። ባሕታውያን: ነን: ሲሉ: የብትሕናውን: ስራ: አይሰሩም፣ ፆም: ፀሎት: ሌሊት: መንቃት: የለባቸውም". . ."ወንድማቸውን: ባለንጀራቸውን: አይወዱም: እንደ: ዓለማዊ: ሰው: የዚህን: ዓለም: ሹመት: ይሻሉ: " ፍካሬ ኢየሱስ

" ውሀ አሻቅቦ: ይፈሳል። ውሀ: አሻቅቦ: ይፈሳል: የተባለው: የማይገባቸው: እኔ: እነግስ: እኔ: እነግስ: የሚሉ: ናቸው።" ፍካሬ ኢየሱስ

ካገላለፃቸው ዘመናችንን ከኛ ከኖርንበት የተሻለ ያውቁታል ብንል ሐሰት አይሆንም
" ከሴቶችም : ሽብቶ፣ ጥርስ አውጥቶ ይወለዳል። የሚጣፍጠውም ውሀ ይመራል፣ ወዳጆችም እንደጠላት ድንገት እርስበርሳቸው ይጋደላሉ።" ፍካሬ ኢየሱስ

ልጆች በብዙ ነገር ነቅተው፣ እንደልጅ ሳይሆን እንደአዋቂ ሆነው እንደሚወለዱ፣ ፊት ፊት እንደሚሉ በምሳሌ ይገልፀዋል

" የእግዚአብሄርን: መኖር: ይዘነጋሉ". . . "ገንዘባቸውንና: ወርቃቸውን: የሚያከማቹበት: ከፍተኛ: ሳጥን: ለማዘጋጀት: ይፋጠናሉ: ነፍሳቸውንም: ለብዙ: ዘመን: የሚበቃሽ: የደለበ: እህል: የተከማቸ: ገንዘብ: አለሽና: እንግዲህ: ዓርፊሽ: ብዪ: ጠጪ: ደስም: ይበልሽ: ይሏታል። ነገርግን: ባላሰቡበት: ሰዓትና: ጊዜ: ሞት: ነፍሳቸውን: ነጥቆ: ይወስዳታል። ያደለቡትና: ያከማቹት: ሀብት: ለማንም: ይሆናል። እግዚአብሄርን: ያላሰበ: በባለጠግነቱም: ብዛት: የተማመነ: ዕድሉ: እንዲህ: ይሆናል።" ፍካሬ ኢየሱስ

ይሄም ሁላችንም የምናምነው የተለመደ ሐቅ ነው። ከመደበኛው ህዝብ እግዚአብሄርን ከትርፍ ጊዜ ርእስ አሳልፎ የሚያስብ ማንም የለም። እንደተገለፀው ሁላችንም ሩጫችን ለልጆቻችንም እንደባህል የህይወት አላማ ብለን የምናስተምረው እንደምንም በሁሉ ተሯሩጠን የባንክ አካውንታችንን መሙላት ነው። መመኪያም የህይወት መለኪያም የምናደርገው እንደተጠቀሰው በገንዘብ ጎተራችን (አካውንታችን) ያለንን የገንዘብ መጠን ነው። ውጤቱም አልቀረ፣ እንደወጡ መቅረት፣ በአደጋ፣ በተኛንበት፣ "ባላሰቡት ሰአትና ጊዜ" እንዳለው በሞት መወሰድን ፍፅም ተላምደነው የለተለት ነገር ሆኗል፣ ገንዘቡም ለማንም ይሆናል። ገዢዎቻችንም ለምን ይሁን በሽታ ይሆን ቆሞ ላየ ግራ እስኪገባ ድረስ ዘለአለም ኗሪ እንኳን በማይዘርፈው መጠን ለማመን የሚያዳግቱ ገንዘብ መጠኖች

ያለእረፍት ሲያግበሰብሱ ኖረው፣ ጥቂት ስንኳ ሳይነኩለት ለማንም ሲሆን አይተናል።

እነዚህ ከብዙዎቹ የተፃፉ መግለጫዎች ጥቂቶቹ ቢሆኑም በብዙ መልኩ ወደኛ ያመለክታሉ። ከራሱ፣ ከማንነቱ፣ ከአእምሮው የተጣላ የአመፅ ትውልድ አፍርተን፣ ማንነቱ መንገዱ ምኞቱ ይሄ ነው ለማይባል ላፈራነው ምስኪን ትርምስምስ ትውልድ ይኸው ዛሬ ባለ ድንቅ የባህልና እምነት ታሪክ፣ ብዙ መለኮታዊ ምስጢራት ማህደር የሆነች ሀገርን ከሁሉ በላይ የራሷ ዘመን የማይለውጠው የማይተዋት መንፈሳዊ ባለቤት ያላትን ሀገር እነሆ ሊወዳት ይችል ዘንድ ለማያውቃት ትውልድ ለፍፁም ጥፋቷ የሚሆን ርክክብ ላይ አድርሰናታል። እሷስ የማትጠፋበት ፅኑ ቃልኪዳን አላት፣ ማ እንደሚጠፋ ግን የምናየው ይሆናል

የመፈናቀል፣ የጥላቻ፣ የሞት ዜና፣ የዘረኝነት፣ የቃጠሎ፣ የፍጅት፣ የሀገራዊ ውጥረት ዜና አስጨነቃችሁ? ዛሬ ይሄ አስጨነቃችሁ?

ከፍቅር በራቀ፣ እግዚአብሄርን በረሳ በዛሬው አካሄዳችን ስንቀጥል አይቀርምና፣ ፅኑ የማያልፍ የትንቢት ቃሉ ገና የሚሆነውን እንዲህ ነው የሚለው።
"በምስራቅ: ባለች: ታላቅ: ሀገር: በርሷ: ላይ: ሶስት: ቀንና: ሶስት: ሌሊት: ጦርነት: ይነሳል፣ ከጥቂት: ሰወች: በስተቀር: በርሷ: የሚተርፍ: የለም።" ራዕይ ሳቤላ

ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ብሎ በምሳሌ አስቀምጦታል፣ እንደ ንሰሀና መመለሳችን ሶስት አመትም፣ ሰላሳም፣ እንደ እስራኤላውያን ሺም ልናደርገው ስልጣኑ በኛው ይመስላል።

ምናልባትም እዚህ ጋር ሰላሳ አመት ሲባል ቀልድ መስሎን ሊታየን ይችላል። ርቀን ሳንሄድ እዚህ ሶማሊያ በጦርነት መሀል፣ መንግስት ሳይኖራት ከ ሰላሳ አመታት በላይ መኖሯን አንርሳ። ያውም አንድ

እምነት፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባህል ያላቸው ህዝቦች ሆነው። በራስ ሹፈታችንን ትተን ቆም ብለን ማሰብ ይኖርብናል። አላሰቡም ተብሎ የሚቀርልን መከራ የለምና

"በዚያን ዘመን : የሚጣፍጠው: ውሀ፣ የሚጥመው: እህል: መራራ: ይሆናል፣ ህዝብ: እርስ: በርስ: ይተላለቃል" "ደግሞ: በክንፍ: የሚሰበሰብ: አሞራ: እልካለሁ፣ እሱም: ኔየየየሚፒ: በግና: ፍየል: ባንድ: ቀን: የሚገድል: ነው። ከነዚያውም: የተዘጋጀ: የለም። በግና: ፍየል: ያልኋቸው: ፃድቃንና: ኃጥአን: ናቸው።" ፍካሬ ኢየሱስ

"በዚያን ጊዜ አንዱ: ከምእራብ: ሌላው: ከምስራቅ: ሲመጡ: ይገናኛሉ፣ "ወዴት: ትሄዳላችሁ?": ይሏቸዋል: "ወደምእራብ: መሄድ: እንወዳለን": ይላሉ: "ወደምእራብ: አትሂዱ: በዛ: መከራ: አለና": ይላሉ፤ "እናንተስ: ወዴት: ትሄዳላችሁ?": "ወደምስራቅ: መሄድ: እንወዳለን": ይሏቸዋል፣ "ወደምስራቅ: አትሂዱ: ብዙ: መከራ: አለና": ይላሉ። ራዕይ ሳቤላ

በጦርነት ብቻ አያበቃም፣ ከፍተኛ ረሀብ ቸነፈርና ችጋር እንደሚመጣ ቃሉ ይናገራል። በዛሬ ቀን የቆምን ቢያንስ በረሀቡ ሳይሆን በጦርነት እንኳን ለመሞት ፀሎት ያስፈልገናል። በጦርነት መሞትን እድለኝነት የሚይስብል በረሀብ ስቃይ የሚመጣ የከፋ ሞትም አለና። በመፅሀፍ ቅዱስም በሰይፍ የመጣ ሞት በረሀብ ከመሞት ይሻላል ተብሎ ተፅፏልና።

አባቶቻችን ሰምተዋቸው የማያውቋቸው አዳዲስ እጅግ ወራሪና ፈጣን ገዳይ በሽታዎች በሀገራችን ይገባሉ። (ምልናባትም በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ በመሰራጨት ላይ ያሉት አዳዲስ ገዳይ በሽታዎች ፍንጭ ሊሆኑን ይገባናል።)

"የሞቱትን ሰወች ንሁዳን ከቡራን ናችሁ እስኪሏቸው ድረስ ችግርና ሀዘን ይሆናል" ራዕይ ሳቤላ

እውነቱ ይህ ነው።

በሀገራችን እግዚአብሄርን ባገለለ መልኩ፣ የሱን ሀሳብና እርዳታ፣ አብሮነት ሳንጠይቅ በምድራዊ ፖለቲካ ስጋዊ ትርምስምስ፣ እሱን አርቀን የምናደርገው የዘረኝነትና ስጋዊነት ሩጫችን ሁሉ መዳረሻው ያ ነው። ቆርጠን ለስጋዊ ግባችን መጠሪያ ካደረግነው "የኢትዮጵያ ትንሳኤ" በፊት የሚሆነው ይህ ነው።

አይ እምነተቢስነት፣ ከትንቢቶቹ "ትንሳኤ" የምትለውን ቃል ብቻ መርጦ ይዞ በየሚዲያው፣ በየቦታው እየጮሁ ባለቤቱንና ባለቃልኪዳኑን እግዚአብሔር ግን ረስቶና ከድቶ በየቦታው መለፈፍ ቁጣና መከራውን ቢያፀናውንጂ ከዚህ ሁሉ መከራ ከቶ አያድንም። በብልጣብልጥነት የሚሆን ነገር የለምና፣ በተለይ ክርስትያን ነን የምንል ህዝቦች ከቅዱሳን መፅሀፍቱ መልካም መልካሙን በመምረጥ፣ የሚያስፈራንን መተው ከመከራ ፅናት ያለፈ ምንም አያተርፍልንም። ሌላ ለማንም ተብለው አልተፃፉምና፣ አላማቸውም ስለትንሳኤ ሊያስጎመዡን ሳይሆን ለኛው በፍቅርና ቸርነት ተፅፈው ቀድመን አውቀን ከዚህ ከሚመጣው ፅኑ ፍርድና መከራ እንድንድን መድህኒት ይሆኑልን ዘንድ የተፃፉ ናቸውና

እንደለመድነው መልካም መልካሙን በመምረጥ ይህን ቃል ብንንቅ፣ እሳቱን መጥቶ ካላየን አናምንም ብለን ብንሸሽ በኛው ስልጣን በራሳችን ላይ ሰነፍን እንጂ፣ በማንም አልፈረድንም ጊዜው ደርሷልና፣ ይህን መልእክት ያየን ብዙዎቻችንም በቸልተኝነትና ልባችን መደንደን ምክንያት ምንም ሳንዘጋጅ እንጠፋለንና፣ ከሞታችን በኋላ በፍርድ ጊዜ የኛው ንግስታችን ንግስተ ሳባ ሳይቀር እንደምትቆምብን መፅሀፍ ይጠቁማል

"ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና" **ማቴ 12:42**

"የነነዌ ሰዎች በፍርድ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና" ሉቃ 11:32

ከእኛው ምእመኑ ጋር ቤተክርስትያናችንም ጭምር እጅግ በበብዙ ስውር በትሮች ብዛትና የሰወችም ችግር በመዳከሟ አብረን ለዚህ የእውቀት ክፍተት ደረስን እንጂ፣ እጅግ በበዙ ቅዱሳት መፅሀፍትና ገናም ባለልቦና ሰው አግኝተው ከግእዝ ያልተተረጎሙና ለህዝብ ባልደረሱ የቤተክርስቲያኒቷ የብራና ቅዱሳት መዛግብት በብዛት የተፃፈ ጉዳይ ነው።

ጥንት በራሳቸው ዘመን መልካም ቀን ቢሆን፣ ያ ሳያዘናጋቸው ጥበበኛ አባቶች በፍቅር ተነሳስተው ለሚመጣው ትውልድ በመጨነቅ በልመና በራእይ ያዩትን ዛሬ እንድንበት ዘንድ የተፃፉ ብዙ አሉ። በልዩልዩ ዘመናት በመልአክት አንደበት ተነግረው (በተለይ በ ቅዱስ ዑራኤልና ራጉኤል ተነግረው) የተፃፉም ብዙ አሉ።

ከሁሉ በላይ መልሰን ልንወደው ያልተቻለን ሁሉን አፍቃሪ አምላክ ለይቅርታና ንስሀ ጊዜ ሳይሰጥ ጥፋት እንዲሆን አይፈቅድምና በብዙ ትንቢቶች፣ ድርሳናት፣ ገድላት፣ ራዕዮች፣ ትርጓሜዎች... ከነዛ ግማሹ ከ 1600 ሌላው ከ 500 አመታት በፊት በልዩልዩ ዘመናት፣ ብዙዎችም ከሀገራችን ውጪ በነበሩ ታላላቅ ነብያት ተነግረው የቀኑ ነዋሪዎች ተረድተን እንድንባቸው ዘንድ ጥንት ተተርጉመው የተላኩ ሁሉ ሳይቀር በሚገርም ተዋህዶ በአንድ ቃል በቅርቡ ስለሚመጣው ሁሉ ይተነብያሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ለኛው ታስቦ፣ በንስሀ ተዘጋጅተን በልመና ፀንተን፣ ለመዳን ፈቃደኝነታችንን ለአምላክ አሳይተን ከሁሉ ያድነን ዘንድ ነውንጂ፣ ሌላ ምንም ጥቅም የላቸውም።

የእስራኤልን ህዝብ አምላክ ከሞት ሊያድናቸው ቢፈልግ ለፈቃዳቸው ነበረ የሰጣቸው። በግብፅ ምድር መቅሰፍቱን ሲልክ አስቀድሞ ነግሮ መዳን ከፈለጉ በበራቸው ላይ በደም ምልክት እንዲያደርጉ ነበር የጠየቃቸው፣ ዘፀአት 12:13

"ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።"

ብሎ ነበር የነገራቸው፣ ለሱ ለመለየት አቅቶት ሳይሆን፣ እነሱም ፍላጎትና ትብብር ሲኖራቸው ብቻ እንደሚድኑ ለማሳየት ነውንጂ። በሀዲስም የታመመውን ሰው " ልትድን ትወዳለህን?" ብሎ እንደጠየቀው።

ዛሬም ይህ ጥያቄው ለኛም ቀረበ፣ ከሀጢያታችን በንሰሀ ታጥበን ያድነን ዘንድ በፀሎት እንተጋ ዘንድ ልጆቹ ነንና ቀድሞ ሊያሳውቀንና ሊያድነን እድል ይሰጠን ዘንድ ነው እንጂ፣ እኛ አልንም/አላልንም ቃሉ እንደሆነ እንድማያቆም የውሀ ጅረት ቀጥ ብሎ ፀንቶ ይፈፀማል፣ በዘመን ፀንቶ ይፈሳል፣ አይቀሬ ነውና፣
ከትንቢቱ ክፍል አንዱን ያለፈና የተፈፀመውን አካል ለአብነት ብናይ፣ ካለፈው ጀምሮ እንዴት በድንቅ መልኩ ቃል በቃልሲፈፀም እንደቀጠለ ያሳየናል።

ጥንት ቅዱስ ራጉኤል ለልብነ ድንግል እስካሁኑ ዘመን ድረስ የሚሆነውን የተናገረውን የትንቢት ቃል ላይ ተፈፅመው ካለፉት ውስጥ ለምሳሌ እንመልከት
ቃል በቃል ፅሁፉ ይህንን ይመስላል...
. . .

"በቃል: ወይም: በንባብ: የምነግርህን አስተውል፣ ነገርግን እነርሱንም በምስጢር እፅፍልሀለሁ አለውና እንደሚከተለው ፃፈለት።

የፅህፈቱም: ቃል: እንዲህ: የሚል: ነው: ሚ: ይሸጣል: ገ: ይነግሳል: ፈ: ይሞታል: ያ: የተባለው: ግን: ቸር: ፃድቅና: የታመነ: ያባትህ: የአብርሀም: አምላክ: የእግዚአብሔር: ሀገር: በሰላም: ተጠብቃ: ትኖር: ዘንድ: እስከፈቀደ: ድረስ: በሀገሩ: "

. . .

"ይህም: ሆኖ: በኋለኛው: ዘመን: ሚ ከተሸጠበት: ይመጣና: ነግሶ: በዙፋንህ: ላይ: ይቀመጥ: ዘንድ: የፈጣሪያችንን: እናት: ይለምናታል፣ ይማልዳታል።" ድርሳነ ቅዱስ ራጉዔል

. . .

**ቃሉ እንዴት እንደተፈፀመ እንመልከት ፡-**

መቼም እኛ ታሪካችንን ባንፅፍ፣ የነጮቹ መርማሪዎች በራሳቸው ሰወች የዘገቧቸው እንደ Richard K. P. Pankhurst, Worldstatsmen, The British Academy, Crown Council of Ethiopia, wikipedia በመሳሰሉ ባሉት ያለውን ብንመለከት

ከተፈፀመ በኋላ ሲፈታ (አመተምህረቱ በውጪዎች የተፃፈ ነው)
ሚ ይሸጣል: አፈፃፀም
ሚ - ሚናስ (የንግስና ስም አድማስ ሰገድ)
Emperor Menas of ethiopia (1559–1563)
During Ahmad ibn Ibrahim al-Ghazi's invasion of Ethiopia, Menas had been captured but treated well as a valuable prisoner.This clemency came to an end in 1542, when the Imam, desperate for help from his fellow Muslims, included Menas in an assortment of extravagant gifts to the sultan of Yemen

Richard K.P. Pankhurst, The Ethiopian Royal Chronicles (Addis Ababa: Oxford University Press, 1967)
wikipedia -- Menas of ethiopia ትንቢቱ ተፈፅሞ፣ በ "ሚ" የተወከለው ሚናስ የልብነድንግል ልጅ በ ግራኝ አህመድ ተይዞ ታስሮ በስጦታ መልክ ለየመን ሙስሊሞች መሰጠቱ በታሪክ ተዘግቧል

ገ ይነግሳል: አፈፃፀም
ገ - ገላውዲዎስ (የንግስና ስም አፅናፍ ሰገድ)
Emperor Gelawdewos of ethiopia (1521-1522)
His reign was dominated by the struggle with Ahmad ibn Ibrahim al-Ghazi during the Abyssinian–Adal war until Ahmad's defeat and death in the Battle of Wayna Daga on February 21, 1543.

Richard K.P. Pankhurst, The Ethiopian Royal Chronicles (Addis Ababa: Oxford University Press, 1967) George Wynn Brereton Huntingford, The historical geography of Ethiopia from the first century AD to 1704, (Oxford University Press: 1989), p. 135
wikipedia -- Gelawdewos of ethiopia
ትንቢቱ ተፈፅሞ፣ በ "ገ" የተወከለው ገላውዲዎስ የልብነድንግል ልጅ ነግሶ ግራኝን ድል በወይናደጋው ጦርነት ድል ማድረጉ በታሪክ ተዘግቧል
ፊ ይሞታል: አፈፃፀም
ፊ - ፊቅጦር (ለንግስና ሲጠበቅ የነበረው የልብነድንግል(የዳግማዊ የዳዊት) ልጅ)
Fiqtor Lebna Dengel Son of Dawit(another name of Lebna Dengal) ( -1522)

Both Ethiopia and Dawit suffered heavily from these assaults. The monastery of Debre Libanos was burned, and the establishments on the islands of Lake Tana looted. Dawit's eldest son Fiqtor was killed at Zara in Wag by a lieutenant of Ahmad on April 7, 1537

Sihab ad-Din Ahmad bin 'Abd al-Qader, Futuh al-Habasa: The conquest of Ethiopia
Taddesse Tamrat, Church and State in Ethiopia (1270 - 1527) (Oxford: Clarendon Press, 1972), p. 301.
wikipedia -- Lebna Dengel
ትንቢቱ ተፈፅሞ፣ በ "ፊ" የተወከለው ፊቅጦር ሲሆን ለንግስና ሲጠበቅ የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ እንደተተነበየው መሞቱ በታሪክ ተዘግቧል

ያ : ሲተረጎም
ያ - ያዕቆብ (1597–1603) መልአከ ሰገድ በሚል የንግስና መአረግ አባቱን ሰርፀ ድንግል(1563–1597) ተክቶ ኢትዮጵያን አስተዳድሯል። ታሪኩም በሰፊው ተዘግቧል።

"ሚ : ከተሸጠበት ይመጣና..." የሚለው ሲተረጎም
ከላይ መሸጡን ያመለከተው ሚናስን ሲሆን የሚለው፣ የአምላክ ቃል አያልፍምና ለንግስና የተጠበቀው ፊቅጦር ሞቶ፣ ይልቅ ያልተጠበቀውና ከ እጅግ መንሻ ጋር ወደ አረብ ምድር የተሸጠው ሚናስ ባልተጠበቀ ሁኔታ አድማስ ሰገድ በሚል ስም ለንግስና በቅቶ ከ 1559 እስከ 1563 በኢትዮጵያ ነግሷል።
ያለፈው በቅዱስ ራጉኤል የተገለጠው ትንቢት ክፍል እንደሚመለከተው በሚያስገርም ሁኔታ ተፈፅሞ እንደ እድልም በውጪ ታሪክ ዘጋቢዎች ጭምር በምስክርነት ተጠናክሮ ተዘግቧል። የአምላክ ፅኑ ቃል ነውና፣ ቀሪውም ክፍል እንደዚሁ የሚፈፀም ይሆናል።

ቀሪውም ክፍል በዛው መልኩ ቃል በቃል የሚፈፀም ይሆናል።

ዛሬም ያለንበት የሀገራችን ችግር ሁኔታ አዲስ ክስተት መስሎን እንዳንሸወድ። ሁል ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ከእግዚአብሄር መንገድ በወጣን ጊዜ አርባ አርባ አመት የተግሳፅ ጊዜ ይሰጠን ነበረ። በዮዲት ጉዲት፣ በግራኝ አህመድ፣ በሱስንዮስ ... ሁልጊዜ እውነተኛው ጠባቂያችን ወደ ገደል ራቅ፣ ወጣ ብለን ስንሄድ በዘንጉ መለስ፣ መለስ ያደርገናልኮ፤ ሁልጊዜ ያለ የነበረ የሚቀጥልም ጠበቃ ማንነታችን ነውና፣ የረሳነው ኢትዮጵያዊነት ማለት ይህ ከአምላክ ጋር በፍቅር ልጅነት ያለው ቅርርብ ነውና።

ዛሬም ከንጉሱ ውድቀት አንስቶ ኢአማኒነት በመንግስት ታውጆ በፅኑ መከራና ስቃይ በአረማዊነት የነበርንበት ቅዠት ጊዜ የኢሠፓ ደርግ 17 አመትና፣ የዚህኛውም ቆይታ ሲደማመር 40 አመቱ በኛ ቀን አቆጣጠር ከ 2007 ዓ.ም ወዲህ ማለፉ ታይቷል።

የዛሬው ለየት የሚለው እንደቀድሟችን በንስሀና ፀፀት ተመልሰን፣ በእግዚአብሔር ተመክተን ጊዜው እንዲያጥርልን አልሆንንም እንጂ በኛ ያባሰው ዛሬ በእምነት ምግባር ደክመን እንዳንጠቀምበት ሆነን፣ ትንቢታዊ መልእክቱ በድሮ ዘመናት ስንት እንዳልተነገሩ፣ ዘመኑም እንዳልተናፈቀ፣ ያውም የመረጃ ልውውጥ እንደዛሬው ሳይሆን እጅግ ከባድ በነበረበት ዘመን በሰፊው ታውቆ የነገስታትን ስም እስከማስቀየር እንዳልደረሰ፣ (ለምሳሌ አፄ ቴዎድሮስ መጠሪያ ስማቸው የነበረውን ካሳ የሚለውን ስም በነዚህ ትንቢቶች በተተነበየው ገና ወደፊት በሚመጣው ፣ከላይ እንደተጠቀሱት ነገስታት ሁሉ የስሙ ምልክት "ቴ" ፣ "ቶ"  ተብሎ በብዙ ትንቢቶች ወደሚታወቀው ቴዎድሮስ ቀይረው ነበርና)፣ የዚህን ያህል ለዘመናት በትውልድ እንዳልተናፈቀ፣ በዛሬ ዘመን ግን በልዩ ልዩ የውጪና ስውር መንፈሳዊ ሴራዎች አማካኝነት በተጠና የመፅሀፍት ምዝበራ፣ ውድመት፣ ማሸሽ፣ እንዲሁም ሀገራዊ አጀንዳ ቅየራ፣ ቤተክህነት ድረስ በገቡ ስውር እጆች ጭምር ወዘተ ለኛ መዳኛ የተፃፉልንን

የአምላክ መልእክቶችና ትንቢቶች ፈፅመን እንዳንሰማና በንስሀ እንዳንዘጋጅ ሆነናል። ቃሉ መፈፀሙ ላይቀር ነገር፣ በሚያሳዝን ሁኔታ ምንም ባልሰማንበት በጨለማ በተወረወረ ፍላፃ ልንወጋ ተይዘናል።

የሚገርመው ይኸው ሁኔታችን ሳይቀር በትንቢቱ እንደዚህ መፃፉ ነው።

" . . . ከነዚያውም: የተዘጋጀ: የለም። በግና: ፍየል: ያልኋቸው: ፃድቃንና: ኃጥአን: ናቸው።" ፍካሬ ኢየሱስ

ቤተክርስትያንም በተለያዩ ክስተቶች፣ ስውርም፣ ግልፅም ሰውሰራሽ ችግሮች እንድትሸከምና እንድትዳከም ሆናለች። እጅግ ጥቂት ከስንት አንድ ብርቱ ቅዱሳን አባቶች ቢኖሩም፣ በየቦታው ያሉ መሪዎቿ አይደለም ለህዝባቸው ተጨንቀው ዘመኑንና በማሰብ የአምላክን መልእክቶች በመከታተል ልጆቻቸውን ሰብስበው ህዝቡን ሊያነቁ ይቅርና፣ እራሳቸው እንኳን ለዘመኑ ሰለባ ሆነው፣ በስውር መንገዶች በሌሎች ተፅእኖ ወድቀው፣ የውድቀታችን ፈታውራሪዎች ሆነው ይታያሉ። ቀኑ ላይ ደርሰናልና ስለእነሱም ሳይቀር እንዲህ ተተንብዮ ነበር

"ከመነኮሳት: ማህበር: ሆነ: ከካህናት: ወገን: እንዲሁ: ወንዶችና: ሴቶችም: በመልካም: ስራ: አይሄዱም፣ ፃድቃን: ይመስላሉ: በውስጣቸው: ግን: ተንኮለኞችና: ሐሰተኞች: ሴሰኞችም: ናቸው።" ድርሳነ ቅዱስ ዑራዔል

"ቁራ: ቀሚስ: ወዳንገቱ: ያጠልቃል። ቁራ: የተባለ: ቁራ: አይደለም: ቄስ: ነን: የሚሉ፣ መንፈስ: ቅዱስ: ያላደረባቸው፣ ወደቤተክርስትያን: የማይሔዱ፣ ይህንን: አለም: የሚወዱ. . ." ፍካሬ ኢየሱስ

እንዲህ የተገለፀው ሁሉ ከተፈፀመ፣ በብዛትም ከታየ ቆይቷል። እንዲህ ያለ ፅኑ መንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ ገብተናል። ነገር ግን መንፈሳዊ አይናችን በመታወሩ ሊታየን አይቻለንም። በዚህም ምክንያት ይታየን ዘንድ መንፈሳዊ ውድቀታችን ስጋ ለብሶ እንዲቆም እንዲለብስ ይሆናል። ውድቀታችን በስጋ ተተርጉሞ እንመለከተዋለን። ፍፁም መናወጥ፣ እልቂት በሀገራችን ይነግሳል። ከጦርነትም የጨቀየው ረሀብ እጣፈንታችን ይሆናል። በሀገሪቱ ብዙዎች ይወድቃሉ፣ ከብዛታቸው የተነሳ ለቀብር እንኳን አይታደሉም። የርስበርስ አንዱ በሌላው መነሳት ብሎ ሲገልፀውም ክፋቱን ያመለክተናል። ይህንኑም ሊከውኑ ቸኩለው ይመስላል የሀገራችን ዘረኞች ከቀንቀን መካረርና ወደፅንፍ መዳረስ  ቀጥሎም የኛን ሀገር መከራ የሚያስናፍቅ ፅኑ ቀውስና መከራ በአለም ሀገራት ይከተላል፣ እርስበርስ ይወድቃሉ፣ ወደኛም ሀገር ሊሰደዱ ይነሳሉ

ከላይ የተባለው ሁሉ መከራ ካለፈ በኋላ፣ ምድር ከፀዳች በኋላ፣ ያኔ ነው ትንሳኤ የሚሆነው፣ ባሁኑ አያያዛችንም ብዙዎቻችን አናየውም እውነትን የት እንደብቃት? ምን ይደረግ? ግን መራር እውነታው ይህ ነው።

እውነታው ይህ ነው - ለብዙዎቻችን ለብዙዎቻችን ሀጢያተኞች "ትንሳኤ" አይደለም ከፊታችን ያለው ፤ "በረሀብ ጦርነት ረዥም ስቃይና ጉስቁልና ሞቶ ያለመቃብር መበተን" ነው። በትንሳኤ በታላቂቷ ኢትዮጵያ ልንኖር አይደለም፣ ይልቅ ቀባሪ ካጡ ሬሳዎች አንዱ መሆን እንጂ በከንቱ "የኢትዮጵያ ትንሳኤ" ብለው ትንቢቱን እንደሚመቻቸው ቆርጠው በባዶ በስጋዊ መንገድ አራግበው ብዙውን ከሀቁ አሳቱት።

ጥቂቶች ግን ይተርፋሉ  ትንቢቱም ቀድሞ የተፃፈበት ምክንያት ሁሉ አንብበው ከነዚህ መሀል ለመሆን ይችሉ ዘንድ ነውና ትንሳኤውም ከዚያ በኋላ አሀዱ ብሎ ይጀምራል ፡፡

"ከዚህ በኋላ በምስራቅ: በኩል: ታሪካዊና: ደገኛ: የሆነ: ንጉሥ: ይነሳል፤ እሱም: ፈቃዴን: የፈፀሙትን: ከመከራ: ያተረፍኳቸውን: የሚሰበስብ: ነው" ፍካሬ ኢየሱስ

"የአንበሳ: ልጅ: ከምስራቅ: ይመጣል፣ በዚያ: ዘመን: ምድር: ላይ: የፈረሱ: ሀገሮች: ይታነፃሉ፣ ታቦት: ትተከላለች፣ በዓለሙ: ሁሉ: በዘመኑ: ጥጋብ: ይሆናል". . . ራዕየ ሳቤላ

**እጅግ እስከቅርብ ጊዜ ሳይተረጎም በግእዝ ቋንቋ ብቻ ይገኝ የነበረው በሮም መቶ ቅዱሳን በአንድ ሌሊት በአንድነት የተገለጠላቸው ራእይ ትርጓሜ የራዕየ ሳቤላ መፅሀፍ ላይ የተዘገበው**

## "የስሙ: ምልክት: ቴ: ተብሎ: የተመለከተው: ይነግሳል"

## በድርሳነ ዑራኤል የተዘገበው

ከ አንድሺ ስድስት መቶ አመታት በፊት በስክንድርያ ግብፅ ቤክተርስትያን በማነፅ ላይ በነበሩበት ጊዜ ለእግዚአብሄር ክብር በወርቅና ብር አስጊጠው በሰሩ ጊዜ ስለክርስስቶ ፍቅርና እምት ነበሰማእትነት ያለፈው ቅዱስ ፊቅጦር በትንቢት መንፈስ ተመርቶ "ይህንን አታድርጉ፣ ከዚህ በኋላ እስላሞች የሚነግሱበት፣ ሀገሩን ሁሉ የሚይዙበት ጊዜ ይመጣልና ለወርቁ ብለው ያፈራርሷታል"፣ ብሎ ቢናገራቸው በፅኑ ሀዘን ሆነው እንደዚያ ከሆነማ ለምንስ ጭራሹኑ እናንፃለን? ቢተክዙ አይዟችሁ፣ ይህቺ ቤተክርስትያን ፀንታ ትቆያለች፣ ከዘመናት በኋላ እግዚአብሄር በኢትዮጵያ ሀገር ክርስቶስን የሚወድ ንጉስ ያስነንሳል... ብሎ አልፎም ተሻግሮም ከሰራዊቱ ጋር በዛቺ ሀገር እንደሚመጣ፣ በጊዜው በሮም ከሚነውሳ ንጉስ ጋርም በእስክንድርያ የአባ ሲኖዳ መታሰቢያ በሆነችው ቅድስት

ቤክተርስትያንም ተገናኝተው የሚሆነውን ጭምር፣ ሌሎችም ብዙ ትንቢቶች ነግሯቸው ነበር። ከዚያም በኋላ በደስታ ሆነው ያቹን ቤተክርስትያን በነገራቸው መልክ አነጹት።

ጊዜም አለፈ፣ ከሶስት መቶ አመት በፊት ነግሯቸው ነበርና በመንፈስ ቅዱስ ቃልም መሰረት በ ሰባት መቶ ክፍለ ዘመን በአምር የተመራ የአረብ ሙስሊሞች ካሊፌት ጦር ግብፅን ተቆጣጠረ፣ ህዝቡም ተቀየረ። ቀሪውም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተነገረ ቃል በዚሁ መልኩ ይፈፀማል። እግዚአብሄር ከኢትዮጵያ ንጉሱን ያስነሳል፣ በአእላፍ ቅዱሳኑም የተነገረው ትንቢት ይፈፀማል።

የዘመኑ አዋቂ ትውልድ እጅግ በሹፈት "ከዚህ በኋላ ንጉስ?" እያለ በንቀት እንደሚያፌዝ ጥርጥር የለውም። ወይ ከመንፈሳዊው ወይ ከምድራዊው ካንዱም ላይሆን ባክኖ ቀረ እንጂ፣ የምድራዊውም ሳይንስ አባቱ Einstein እንኳን "The fourth world war will be fought with stones and sticks" ብሎ ፍንጭ ሰጥቶት ነበር። ሶስተኛው ላይ የሚፈፀመው እልቂት ከህሊና በላይ በመሆኑና ፍፁም ጠረጋ በአለም በመከናወኑ ምክንያት ከዚያ በኋላ የነበረው ሀያልነት፣ ስርአትና ሁኔታ ሁሉ እንደሚቀያየር መስክሮ ነበር። ከአለም አቀፍ ጦርነቶች ሶስተኛውን ግን ለየት የሚያደርገው የእግዚአብሄር ሰይፍ ፍልሚያውን መቀላቀሉ ነው።

አንዱን ከሌላው ጠቅልሎ፣ የሚያወድም፣ ያልፈጠራትን ምድር ከነፍጡሮቿ የሚያወድም በማይከስም መርዝ፣ ዳግም እንዳይኖሩባት እንኳን በጨረር በሚበክል፣ ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ የጥፋት ትጥቅና ኃይልን በእብሪትና ፉከክር እጅግ እጅግ አብዝቶ የታጠቀው የሰው ልጅ፣ ምድርንና ተፈጥሮን ሊደመስስ በተነሳበት ጊዜ የታጋሹ አምላክም ፅዋ እንደሚሞላ፣ ፍጡራኖቹንና ድሀ ልጆቹን ሊታደግ በቁጣው እንደሚነሳ መገመት ቀላል ነው። በቃሉ የፀናች ተፈጥሮ ሳይቀር በአስፈሪ አውሎ ነፋስ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በውሀ መጥለቅለቅ ወዘተ በመላው አለም ላይ በትሯን እንደምታፀና

መገመት አያዳግትም። የሰለጡኑት ሁሉ ምድር በተነሳችባቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሄር ተስፋ ምድር መግባት ምኞታቸው እንደሚያደርጉ ብዙዎቹም እንደማይሆንላቸው የተነገረውም ይፈፀማል።

በዚህ የሰፈረው፣ በመዳረሻው የተገለጠው ሁሉ የሚፈፀምበት ቀንና ሰአት በአንድ አምላክ ዘንድ ብቻ የሚታወቅ ነው። ከኛም መሀል ማንም ስልጣን ኖሮት በዚህ ጊዜ ነው ብሎ መናገር የሚቻለው የለም። ነገር ግን ለሰው ይገለጥ ዘንድ የሰፈሩት ምልክቶችና፣ የሀገራችን ሁኔታዎች ቀኑ እጅግ ስለመቅረቡ ይጮሀሉ።

ከረዥም ጊዜ ወዲህም በሀገራችን በአሁኑ ወቅት እንደሚታየው ለእፎይታ የሚሆን የነፃነት ጊዜንም የተሰጠን ይመስላል፣ ለአምላክ እግዚአብሄርም የመጨረሻው እይታው ይመስላል። ከምናማርርባቸው ነገሮች ተላቀን በነፃነት ቆመን ሳለን ወደአምላካችን የመቅረብና የመመለስ ወይም የመራቅና ከቀሪው አለም የመደባለቅ ዝንባሌያችንንም የምናሳይበት ጊዜ ይሆናል። ባሳየነው ዝንባሌና በነፃ ሳለን በቀየስነው መንገድ፣ ልንመስል ልንከተል ልንሆን በመረጥነው ወገን መሰረት ፍርዳችን ቢፀና መከራከሪያ እንዳይኖረን ራሳችን ምስክር እንሆናለን። በዚህም መሰረት ጊዜ የሌለን በመሆኑ የመከሰቻ ቀኑ ለራሱ ሲቆጥር፣ እኛ ለራሳችን ዝግጅትና መንፈሳዊ ብርታት በመትጋት እንዘጋጅ።

ይሄ ሁሉ "ዉይ! ጥንት የተባለው ሊደርስ ሳይሆን አይቀርም፣ እግዜር ያለው ይሁን እንግዲህ" ብለን እንደዝናብ ተጠልለን የምናሳልፈው ነገር አርጎ ማሰብ ትልቁ ፈፅሞ የተሳሳተ የብዙዎች አዝማሚያ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ እንዲሁ ተቀምጠን የምንጠባበቀው ሳይሆን፣ እስራኤላውያን በበራችሁ ላይ የደም ምልክት አድርጉ መቅሰፍቱም አልፏችሁ ሌሎችን ይመታል እንደተባሉት ለኛም "መዳን ከፈቀድክ ይህንን አድርግ" የሚል መመሪያ ያለበት የተለዩት የሚቀሰፉበት ሁሉንም የሚፈትን፣ የሚዳብስ ከባድ ሁኔታ ነው። ለረዥም ጊዜ ሁሉም የሚካፈሉት፣ የከፋ ረዥም የእርስበርስ አድካሚ አፍሳሽ

ጦርነት የምንካፈልበት፣ በዚህም አብሮ ከጦርነት የረከሰና የከፋ የሆነው የረሀብ እልቂት በረዥም ጊዜ የምንንጠባጠብበት፣ በአባቶቻችን ዘንድ ያልታወቁ ልዩ ልዩ ተዛማጅ በሽታዎችና ቸነፈር በሀገራችን ገብተውና ፈንድተው በተባለው ደረጃ ድረስ ሰው የሚጨርሱበት እንዲሁ በቸልተኝነት ያልቆመ መልክ ነው ከፊታችን ያለው።

ስነልቦናችን የፈጣሪ መኖር ክህደትን በስውር መንገድ አንግሶ ውስጣችንን ለራሳችን ባዳ አድርጎት እንጂ፣ መቼ ይህ አይነት መቅሰፍት ሊሆን የማይችል ክፉ ፈፅሞ የማይፈጠር ጠንካራ መቅሰፍት ሆነና? ከሺዎች አመታት በፊት የአለም ህዝብ ቁጥር ጥቂት በነበረበት ወቅት እንኳን፣ በ ኢዮርብዓም ዘመን ግማሽ ሚሊዮን እስራኤላውያን በቁጣው ሲወድቁ የነበረው እግዚአብሄር ዛሬም አለ፤ ያኔ ከሶስትሺ አመታት በፊት አሮን ጥናውንና እጣኑን ይዞ ሮጦ እስኪደርስ ባለችው ቅፅበት እንኳን አስራ አራት ሺህ ሰው ሲያልቅ የነበረው አምላክ ነው ዛሬም ያለው ነገም የሚኖረው አምላካችን፣ በሀገራችን ያለውን ታቦተ ፅዮን በተዳፈሩ ጊዜ የአምስት ሺዎች ትንፋሽ በተቋረጠ ጊዜ የነበረው፣ በዘመናት የማይቀያየረው እግዚአብሄር ነው ዛሬም ያለው። ራሳችንን ልዩ አድርገን ብንስል ብንታበይ፣ ጊዜም እንደዥረት ይፈሳል፣ ቀንም ታሪክ ይሆናል፣ አምላክ እግዚአብሄርም ፀንቶ ይቀጥላል።

በጥንት የአምስትመቶ አመተአለም ፋርስ ስልጣኔና ነገስታት በነበሩበት ዘመን የነበረ በዳንኤል ስለነሱ የተፃፈው ትንቢት ተፈፅሞ ታሪክ ሆኖ ሲያልፍ ያን ሁሉ አብሮ ላሳለፈ እግዚአብሄር እኛም የተለየን አይደለንም፣ እንዲሁ ታሪክ ሆነን አልፈን ቀጥሎ ብዙ ክፍለዘመናት ይቆጠራሉ። ስለዚህም ቆም ብለን የተፈጠርንበትን ምክንያት መርምረን፣ እውነት ላይ እንቁም፣ እንችላለንና ከጥፋታችን ራሳችንን እናድን።

ቀን ይቀየራል፣ መዝሙረኛው ዳዊት እንዳለው " ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉና እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ። ገና ጥቂት፥ ኃጢአተኛም አይኖርም ትፈልገዋለህ ቦታውንም አታገኝም።ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፥ በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል። ኃጢአተኛ ጻድቁን ይመለካከተዋል፥ ጥርሱንም በእርሱ ላይ ያንገጫግጫል። እግዚአብሔር ይሥቅበታል፥ ቀኑ እንደሚደርስ አይቶአልና። " ክፉዎች ተጠርገው የደጎች ዘመን ይመጣል።

ከሀሳዊው መሲህ መምጣት በፊትም ማቴዎስ በወንጌሉ "ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል" ብሎ እንደተናገረው መልካም የእግዚአብሄር ዘመን በአለም ላይ ይፀናል። ዛሬም ምናልባትም ሰይጣንም መቼም ስራ አይፈታምና ንጉስ ነኝ፣ እንዲህ ነኝ፣.. እንደዚህ ነኝ እያሉ የሚነሱ በሀገራችንም ይመጡ ይሆናል። ነገር ግን የተባለው ፅኑ መከራ ሁሉ ሳይቀድም፣ ክፉዎች ሳይጠረጉ የተባለው ሁሉ አይሆንምና፣ የምመጣውም ንጉስ ቢሆን እንዲህ ነኝ ብሎ መለፈፍ የሚጠበቅበት ሳይሆን እግዚአብሄር ያለበሰው ግርማ የሚገልጠው ይሆናል።

ከበታች ያሉትን ፅሁፎችንም ሁሉን አንብበህ ተማርባቸው።

# ምን ላድርግ?

አንባቢ ሆይ፣ ከተባለው ትንሳኤ በፊት በማይቀረውና የሚመጣው መከራና የሚወድቁም ሆኑ የሚተርፉ፣ በአጠቃላይ በሚከተለው ጥፋት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ማንም የትኛውም ቢሆን የተለየ እድል አያገኝም ሁሉም በእኩልነት በየራሱ ይመዘናል እንጂ እስከዛሬ ምን እንስራ፣ በምን ህይወት እንኑር፣ በቸልተኛ እምነት፣ በጥፋት፣ በርኩሰት ህይወት ወይ በመልካምነት እንዴት ይሁን ማንም፣ ሁሉም ሰው ከእውነተኛ ንሰኃ ፊት ፍፁም እኩል ነው። ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች እኩል እድል አለን።

**የእግዚአብሄር እጅግ ድንቅነቱ፣ ዛሬ አንድ ልጁ በእውነተኛ ፀፀት በንሰሀ ይቅርታን ቢለምነው፣ በአምላካዊ ችሎታው ነገ ጥፋቱን ሲደግመው እየታየውም ቢሆን ዛሬን በፍቅር ይቅር ማለቱ ነውና።**

**ቆሽሾ የማይፀዳ፣ ፀድቶ መልሶ ማይቆሽሽ የለምና፣ በንሰሀ ፊት ሁሉ እኩል የሚታይ ነውና ይህ መልክት ለሁሉም ነው።**

ይህን የምታነበው ስምህ ማነው?
ዘርህ ምንድነው?
እምነትህ ከየትኛው ይሆን?
ሀብታም ከሚባሉት፣ ወይስ ደሀ ከሚባሉት?
ስራህስ ምን ይሆን?

በአእምሮህ መልሰህልኝ ሊሆን ይችላል፣ ልሰማህም አይቻለኝም፣ ብሰማህም ከቶ ረብህ የለውም።  ምክንያቱም እነዚህ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ሁሉ በፊታችን ከቆመው በማይቀረው ቃል ከሚጠብቀን ክስተት የተነሳ ፈፅሞ ምንም ጥቅምና ዋጋ የላቸውም።

በፊታችን ከሚጠብቀን እውነት መሰረት ብቸኛው ዋጋ ያለው ጥያቄ ይህ ነው።

በፍካሬ ኢየሱስ "ለቀብርና ምድሪቷን ለማፅዳት ሰባት ወር ይፈጅባቸዋል" ተብሎ ተፅፏልና ነገ በማያልፍ ቃሉ የተነገረው፣ ከብዛታቸው የተነሳ ተበትነው በምድር አውሬና አሞራ እየተቦጨቁ ወዳድቀው ለመቀበር ተራቸውን ከሚጠብቁት አከሬኖች መሀል ነው የምንገኘው? ወይስ "እግዚአብሄር ያተረፋቸውን ጥቂቶች የሚሰበስብ ንጉስ ይነሳል" ተብሎ ከተነገረላቸው በህይወት አምላክ ካተረፋቸው ጥቂቶች መሀል? ቤተሰቦቻችንስ? ዘመዶቻችንስ?

የጭካኔና ጨለምተኝነት የሆነና የማይፈፀም ውሸት መሰለ አይደል? አይ ወገኔ፣ ምነው ሀገር ሰላም በሆነበት፣ ድንገት በጠዋት መላው ህዝብ የሰው ልጅ ቁርጥራጭ በጥቁር ፌስታል ሲለቀም እዚሁ ከደጃፋችን አውሮፕላን በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ አላየንምን? መቶ ሀምሳ ሰባት የማይተዋወቅ ሰው የአካል ክፍላት መለየት ስላልቻሉ የተለያየው ተለቅሞ ሙሉ ሙሉ ሲመስል በአንድ እየተደረገ እንደ አንድ ሰው ሲቀበር አልመሰከርንምን?

እግዚአብሄር ምን ሊያሳየን ነው ይህ ፈቃዱ ሆኖ በመሀል ሀገራችን የተከሰተው? ይህ ሁሉ ነፍስ ያለፈበትን ያለፈበት ክስተት ሲፈጠር ሁለት ቀን አውርተን እንዲሁ እንዳልተፈጠረና እንዳላየን መስራት መብታችን ነው።

እንደው ወደልባችን እንመለስ ዘንድ ጥቂቶች ቀድመው የምድር ህይወታችንን ከንቱነትና ቀን ሊያመጣ የሚችለውን ልብ እንድንል ምናልባትም የነገ የጋራ እጣፈንታችንን እንዳላሳዩን በምን እርግጠኛ ሆነን? ነው አንተ ፃድቅ እነሱ ኃጥአን ስለሆኑ ይህ ለነሱ ተገባ ብለህ ነው ያሰብከው? **ታዲያ ከኛ ምን ይጠበቃል?**

*ይህ መልዕክት ከንቱ ፍርሀትና ጭንቀት ለመንዛት አይደለም የተለቀቀው። ይቻላልና እንድንበት ዘንድ ነውንጂ። ከኛ የምትጠበቅብን እጅግ ኢምንት ፍፁም ቀላል ናትና።*
***ድሮም ቢሆን የሁሉ ባለቤት የሆነ ታላቅ አምላክ ከኛ ከቶ ምን ይፈልግና።***

ከላይ ከተጠቀሱት ከምንወድቀውም ሆነ ከምንነሳው ወገን ለመሆን ዛሬ ሁላችንም እኩል መብትና ስልጣን አለን። ዛሬ ቀኑን መልካም የሚያደርገው ነገሮች ሁሉ ተወስነው ያለቁ ሳይሆኑ ዛሬ ልንወስናቸው ስለምንችል ነው። ግን ዛሬ ምን ያህል ወራት፣ ቀናት፣ ሰአታት፣ መቼ ይሁን ከባለቤቱ ውጪ ጠንቅቆ የሚያውቅ ባለመኖሩ ጊዜ ባይሰጠውም።

ከቀኑ በፊት በእውነተኛ ፀፀት ንሰሀ በመግባት፣ ራሳችንን በማንፃት ጊዜው እስኪደርስ ከሚመጣው ሁሉ ምህረት ለማገኘት እየለመኑ የሚቆዩ የእግዚአብሄር ልጆች ቀኑ በደረሰ ጊዜ በእሳት ማእበል መሀል ቢሆኑ እንኳን ከጠጉራቸው አንዲቷን ሊነካ የሚቻለው ከቶ ማንም አይኖርም።

***"በዚያን፡ ጊዜ፡ በዚህ፡ መፅሀፍ፡ ቃል፡ የተጠበቁ፡ የፆሙ፡ የፀለዩ፡ ጥቂት፡ ሰዎች፡ ይተርፋሉ።"ፍካሬኢየሱስ***

***"እርሱ፡ ከአዳኝ፡ ወጥመድ፡ ከሚያስደነግጥም፡ ነገር፡ ያድንሃልና። በላባዎቹ፡ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም፡ በታች፡ ትተማመናለህ፡ እውነት፡ እንደ፡ ጋሻ፡ ይከብብሃል። ከሌሊት፡ ግርማ፥ በቀን፡ ከሚበርር፡ ፍላጻ፥ በጨለማ፡ ከሚሄድ፡ ክፉ፡ ነገር፥ ከአደጋና፡ ከቀትር፡ ጋኔን፡ አትፈራም። በአጠገብህ፡ ሺህ፡ በቀኝህም፡ እሥር፡ ሺህ፡ ይወድቃሉ፡ ወደ፡ አንተ፡ ግን፡ አይቀርብም። በዓይኖችህ፡ ብቻ፡ ትመለከታለህ፥ የኃጥኣንንም፡ ብድራት፡ ታያለህ። አቤቱ፥ አንተ፡ ተስፋዬ፡ ነህና፡ ልዑልን፡ መጠጊያህ፡ አደረግህ። ክፉ፡ ነገር፡ ወደ፡ አንተ፡ አይቀርብም፥ መቅሥፍትም፡ ወደ፡***

ቤትህ: አይገባም። በመንገድህ: ሁሉ: ይጠብቁህ: ዘንድ: መላእክቱን: ስለ: አንተ: ያዝዛቸዋልና: እግርህም: በድንጋይ: እንዳትሰናከል: በእጆቻቸው: ያነሡሃል። በተኵላና: በእባብ: ላይ: ትጫማለህ: አንበሳውንና: ዘንዶውን: ትረግጣለህ። በእኔ: ተማምኖአልና: አስጥለዋለሁ: ስሜንም: አውቆአልና: እጋርደዋለሁ። ይጠራኛል: እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም: ጊዜ: ከእርሱ: ጋራ: እሆናለሁ: አድነዋለሁ: አከብረውማለሁ።"መዝሙረዳዊት

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።"መዝሙረዳዊት

የአምላክ ቸርነት እጅግ ብዙ ሆኖ ሳለ ለምንጠፋው ምን ተብሎ ይነገርልን ይሆን?

ይህንን ቃል ሰምተው የተኙ፣ ሳይዘጋጁ ከፊታችን ያለው ጥርጊያ እንዳሉ ያገኛቸው የተባለውን ሁሉ ይቀበሉታል፣ ቃሉን ሰምተው ለዳኑት የነበረውን ፅዋ ጭምር ይሻሙታል። ይህችንም አሁን የምታነባትን ፅሁፍ ባያነቧት በተሻላቸው ነበር። ለመስማታቸው አፍ አውጥጥታ ምስክር ሆና ትናገርባቸዋለችና። ላንተም የሚደረገው ነገር እጅግ ቀላል ነው።

አሁኑ ነገ ዛሬ ሳይሉ ትልቁንና ዋናውን ብቸኛ ዝግጅት ማድረግ፣ እሱም "አንዲት ንስሀ መግባት"፣ ከሀጢያት ነፅቶ በእምነት መገኘት፣ የራቅነውን አምላክ ለማወቅና ለመቅረብ መጣር። ቢቻል የንስሀ አባት ጋር ዛሬ ነገ ሳይሉ ንስሀ መግባት፤ ሰበብ ሆነኝ እንዳይሉም በርቀትና ሌላም ሀሳብ እጅግ አዳጋች መስሎ ከታየህ፣ መገናኘት ካልቻልክ ያልፈለግከው ሰበብ እንዳይሆን አሁን በመነሳት በአቅራቢያ ካለ ካህን እስከዛ ንስሀ ተቀበል፣ ቅድሚያ ሰጥቶም እያሰቡ ወዲያውም የንስሀ አባት ጋር እንደተገናኙ ንስሀ መግባት። በየዕለቱም ተግቶ ከሚመጣው መከራ ሁሉ ይቅርታንና ምህረትን ከሚወደን አምላክ ዘንድ መለመን።

ልቦና የለንም እንጂ በቃ ይህቺው ናት። የሁሉ ባለቤት ፍፁም ጌታ ቀድሞስ ከኛ ደቃቆች ምን ይፈልግና? ብርቱ ሰብሳቢ አጥተን እንጂ፣ ሱባኤና ምህላ ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ የሚታወጅበት፣ ምእመኑ በአንድ ድምፁን እንዲያሰማ የሚሆንበት ጊዜ አሁን ነበር። ሀገር እንዲህ ባለችበት ጊዜ እንጂ ታዲያ ከቶ ለመቼ ነበር? አይደለም በዚህ ሀገር እንዲህ ፈተና ላይ በሆነችበት፣ ድሮ ዝናብ በቆየ ጊዜ እንኳን በህብረት ምህላ ተወጥቶ እዛው መልስ ሳያገኙ፣ ሳይረጥቡ አይመለሱም ነበር።

ዛሬም እያንዳንዳችን በጋራ በመወያየት፣ በመሰባሰብ ከምንጊዜውም በላይ በጋራ ፀሎትና ምህላ በህብረት ልንፀና ይገባናል። ከሁሉ እለታዊ የቤተክርስትያን ስብስባችን ካህናትን በማስተባበር በምህላ አምላካችንን ልንማፀን ይገባናል። ከሁሉ በላይ ከምድራዊ ፖለቲካ መፍጨርጨርና ዘር ክፍፍል ራሳችንን አርቀን፣ በፍቅር በእግዚአብሄር ልጅነት ድልድይነት ክፍፍሎችን እየተሻገርን በአንድላይ ሆነን ብቻ ወደአምላካችን ልንጣራ፣ ልናለቅስ ይገባናል።

በየትኛውም የቤተክርስትያን አገልግሎት ቋሚ የህብረት ፀሎትና ምህላ በማፅናት ቢያንስ ልብ ገዝተን በዚያ ተገኝተን የምንለምነውን ከሚመጣው ሁሉ በይቅርታው ይሰውረን ዘንድ እንዲራራልን ልንማፀነው ይገባናል። ትኩረታችን ይህ ሊሆን ይገባዋል።

በመፅሀፍ ቅዱስ "ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ" ብሎ የተናገረው የእግዚአብሄር ቃል ምናችን ነው?

ኢትዮጵያ ምንድነች? ትእዛዙን የጠበቁ ቅዱሳን ቃልኪዳን ምድርነቷ ምናችን ነው? ስለቃልኪዳናቸው ብሎ እንዲምረን አምላካችንን ካልለመነው? አቡነ ተክለሀይማኖት ምናችን ናቸው? 27 አመት በዱር በዋሻ ቆመው ፀልየው የተቀበሏቸው ቃልኪዳኖችን ምነው

ተውናቸው? ሀገራችን ቤተክርስትያናችን በእሳት መሀል ሲቆሙ፣ ሞታችን በፊታችን ሲመላለስ ያላሰብናቸው ቃልኪዳኖች፣ ያልጠራነው አምላካችን ስላልካድነው ነውን?

ስለዚህም ያባቶቻችንን አምላክ፣ ፈጣሪያችን ክርስቶስን አይደለም ከሚወዳት እናቱ፣ እንደ ቅዱስ ዮህንስ ከጫማው ጠፍር ስር ወድቀን በትህትና በለቅሶ ልንማፀነው ይገባናል።

በጭንቅ ጊዜ ካልጠራናት ድንግል ማርያም ምናችን ናት? ውድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወዳት እናቱ፣ ከእናትም ቤት እንኳን ያልነበራት ድሀ እናቱ፣ ስታድግ በቤተክርስትያን፣ ከዛ ቢያስወጧት በእጣ በቅዱስ ዮሴፍ ቤት፣ ልጇን ወልዳም በበረሀ በስደት፣ ቆይቶም አንድ ልጇን ቢገድሉባት ለደቀመዝሙሩ ወደቤትህ ውሰዳት ብሎ ባደራ ስለሰጣት ውድ እናቱ ብሎ እንዲምረን በትህትና ልንለምነው ይገባናል። እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ ብሎ በተናገረው ፅኑ ቃሉ መሰረት አይተወንምና

በዚህ ጊዜ የሁላችንም ሩጫ መሆን ያለበት በመሰባሰብ፣ በየጊዜው እርስ በርስ በማስተባበር ለጋራ ንሰሀና ከቻልናቸው ጋር በህብረት በፀሎት በመትጋትና በጋራ እጃችንን ወደእግዚአብሄር በቻልነው መንገድ ሁሉ ለመዘርጋት ነው ልንሯሯጥ የሚገባን።

በዙሪያችን በተለያዩ አጋጣሚዎችም የምንገናኝ ሁሉ አማኞች ሁሉ በመሰባሰብ በመተሳሰር ሌሎችን በማሳወቅ፣ መልእክት በማድረስ፣ በማስተባበር ከሁሉ በላይ ምንም ቢመጣ እንኳን ቢያንስ ለነፍሳችን ድኅነት ስንል በፀሎትና ንሰሀ መትጋት ይኖርብናል።

ዘር፣ ብሄር፣ ምን ምን ሳንለይ በመጠራራት፣ በመሰባሰብ "ለሀገር እድገት" ተብሎ ለሚወራው ሳይሆን ለራሳችን ለየግላችን ከሞት መትረፍ ስንል የግድ ልንተባበር ይገባናል። እንዲሁም ሆኖ ከዳንን ትልቅ ነገር ነውና። ካልሆነም እንዲሁ ወገን ወገን ይዘን ተከፋፍለን

ያለነው እንደሆነ በሰላሙ ጊዜ ለበላይነት እንፎካከር ይሆናልንጂ ጊዜው ሲከፋ ከየትኛውም ወገን ቢሆን "ለጥፋት ያንሳል" የሚባል ከቶ አንድም የለምና፣ አዎን ከቶ አንድም ቡድን የለምና፣ በመሀል ማንነታችን ሳያድነን ልንጨፈለቅ ያልን ነንና ከቅዠታችን ባነን ወደአምላካችን በአንድነት ልንሯሯጥ ይገባናል።

በዱር እንኳን ነፍስ የሚጋልብ ሰደድ እሳት በተጨሰ ጊዜ ነብሩ ከድኩላው፣ አንበሳው ከጎሹ፣ ከቀበሮው፣ ከጥንቸሉ ሁሉ እየተጋፋ ይሸሻል፣ እንዲህም ሆኖ ከነሱ ብዙው አይተርፍም። እኛም ቢያንስ በቅርበት በዙሪያ አብረን ያለነው ከጥላቻ መርዝ መፅዳት ካቃተን፣ ሞቱ ባይቀርልን እንኳን፣ ቅጣቱ በምድር እንዲያልፍልን ልንለምን ይገባናል። ቢያንስ የስቃይ ሞትን ተቀብለንም ቢሆን ነፍሳችን ይተርፍ ዘንድ ልንማፀን ይገባናል። እንደተነገረው የሞት ፈረሰኛ በጦርነት ብቻ ሳይሆን ከባድ ረሀብና እጅግ የፈጠነ ወረርሺኝ ይዞ በመሀላችን ሊገኝ አስቀድሞ ተነግሯልና።

የመከራው ጊዜ በደረሰ ወቅት ብዙዎች የረሱትን አምላክ ፍለጋ ይጮሀሉ፣ አያገኙትምም። በቸልተኝነት ይህንን ጊዜ ብናልፈው፣ ይህንን ማንቂያ ብንዘነጋው እግዚአብሄር ከዚህ በፊት ጥሪውን ሰምተው ላልተመለሱት፣ በንቀት ቸል ላሉት እንዲሆን የተናገረው ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ቃል ያስተጋባባቸዋል።

**"በጠራሁ፡ ጊዜ፡ እምቢ፡ ስላላችሁ፥ እጄን፡ በዘረጋሁ፡ ጊዜ፡ ማንም፡ ስላላስተዋለ፥ ምክሬን፡ ሁሉ፡ ግን፡ ቸል፡ ስላላችሁ፥ ዘለፋዬንም፡ ስላልፈቀዳችሁ፡ እኔም፡ ስለዚህ፡ በጥፋታችሁ፡ እስቃለሁ፡ ጥፋታችሁም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ አላግጥባችኋለሁ። ድንጋጤ፡ እንደ፡ ጐርፍ፡ በደረሰባችሁ፡ ጊዜ፥ ጥፋታችሁም፡ እንደ፡ ዐውሎ፡ ነፋስ፡ በመጣ፡ ጊዜ፥ ጭንቅና፡ መከራ፡ በወረደባችሁ፡ ጊዜ። የዚያን፡ ጊዜ፡ ይጠሩኛል፥ እኔ፡ ግን፡ አልመልስም፡ ተግተው፡ ይሹኛል፥ ነገር፡ ግን፡ አያገኙኝም። እውቀትን፡ ጠልተዋልና፥ እግዚአብሔርንም፡ መፍራት፡ አልመረጡምና፡ ምክሬን፡ አልፈቀዱምና፥ ዘለፋዬንም፡ ሁሉ፡ ንቀዋልና፡**

ስለዚህ: የመንገዳቸውን: ፍሬ: ይበላሉ፥ ከራሳቸው: ምክር: ይጠግባሉ። አላዋቂዎችን: ከጥበብ: መራቅ: ይገድላቸዋልና፥ ሰነፎችንም: ቸልተኛ: መሆን: ያጠፋቸዋልና። የሚሰማኝ: ግን: በእርጋታ: ይቀመጣል፥ ከመከራም: ሥጋት: ያርፋል።"
**መፅሀፈምሳሌ**

**የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ ይህ ፅሁፍ ሰው መንገዱን አስቦ ባላቀደው መንገድ እርስዎ ዘንድ ደርሷልና፣ ለሎች ሀላፊነታቸውን በመወጣታቸው ይህ እርስዎ ጋር በመድረሱ፣ እርስዎም በቅንነት ለሌሎችም በማድረስ ሀላፊነቱን ያሳልፉ፣ በመክሊትዎ በችሎታዎ ሁሉ ያግዙ። ይህንን ተመልክቶ በንሰሀ ወደአባቱ የሚመለስ ይኖራልና፣ የሚወደው የጠፋውን ልጁን ያገኘው የእውነት አባትም ዋጋዎን አይረሳም። ከራስዎም እንዳይዘናጉ።**

በኮምፒውተርዎ ዴስክቶፕ ላይ "Ethiopia" በሚል ፎልደር ተቀምጦሎታል። እንደፈቃድዎ ለሌሎችም ያድርሱ

ልኡል እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን !

ለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።

## መልካም የመገለጥ ንባብ ይሁንላችሁ...

# ለአማራ ምድር ነዋሪዎች

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ከቃሉ አንዲቷም ፈፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

አምላክ ሁሉን ህዝብ ሲያይ በእኩል አይን ነው። ራሳችንን በወገንተኝነት፣ በጎጥ፣ በሀብት፣ በምን በምን ብንከፋፍል እዚሁ ለኛው ይሆናል እንጂ፣ የእግዚአብሄርን አይን ልንጋርደው ወይም ተፅእኖ ልናሳድርበት ፈፅሞ አይቻለንም።

በሚመጣው ሁሉ በእግዚአብሄር ፍርድ የሚቀሰፈውም ሆነ የሚድነው እያንዳንዱ ግለሰብ የሚመዘነው ዘመን በማይለውጠው በነበረው በሚኖረው አምላካዊ ሚዛኑ ነው እንጂ የኛ የቡድን ወይ የዘር መለያ ወይ ጎራ በሱ አይን ፊት እንደሌለ ነው የሚሆነው። አንዴ በሱ ፊት ተመዝነን ከወደቅንና ለቅጣት ከተወሰነብን ምን አለም ቢሰለፍ፣ ምን ተአምር ቢሰራ የሚያድነን ከቶ ሊኖር አይችልም፤ ደግሞ በዛው መጠን በሱ ፊት አንዴ ተመዝነን ከተመረጥን ምን እሳት ቢዘንብ፣ የእልቂት መአበል መሀል ብንገባ ከቶ የሚነካን ሊኖር አይችልም።

ይህል ትልቁ ሀቅ በመሆኑ፣ በዚህ መሰረት ምን ስጋት ውስጥ፣ ምን ከበባ ውስጥ ብትገባ፣ ምን ጠላት ቢነሳብህ ቀድመህ ዞረህ ልታየው የሚገባህ የቀረህን ጥይት ወይ የአባሪህን ዝግጅትና ትጥቅ፣ ወይ የምሽግህን ስፋት አይሁን። ይልቁንስ ከመደራጀቱና መታጠቁ በፊት ቀድመህ ልታየው የሚገባህ ከጥንት ጀምሮ መከታ ሆኖ ያኖረህን፣ አንተነትህን የመሰረቱት አባቶችህን ያላሳፈራቸው የሀያላን ጌታ አብሮህ መሆን አለመሆኑን ነው።

ለአባቶችህ እንዳደረገው ዛሬም የአምላክ ሰራዊት ከጎንህ እንዳይሰለፍ ምን ሊያርቀው እንደሚችል ቀድመህ ፈትሽ። ከአንተ ጋር ምን

አፀያፊ ነገር እንዳያሸሻቸው ዙሪያህን፣ ውስጥህን መርምር።

የምትኮራበት ነገር ሁሉ፣ የኢትዮጵያ የክብር ታሪክ ሁሉ መሰረትና ማዕከል፣ አላማም ጭምር አንድ እሱ እግዚአብሄር ነበርና።

ለዘመናት ሊደፍሩህ ሳይቻላቸው ሲነኩህም ተዋርደው የወደቁት የውጭ ጠላቶች ዛሬ ይህን ታሪክህን እንዳትደግመውና እንዳይዋህድህ ፈርተው ከታሪክህ ይህንን መልክህን ቆርጠው አውጥተው አስረስተው፣ ትልቁን ትጥቅህን አስፈትተው በባዶ እጅ ሙሉ ትውልድ ሊማግዱ እየተሯሯጡ ነው።

ግን ከኬንያው፣ ከአረቡ ወይ ከግብፅ ከጣልያን ወይ ከቱርክ ከደርቡሹ ጦረኛ ከቶ በምን ተለይቶ ነበር የሐበሻው ኃያልነት? እውነት በቃ እንዲሁ ጀግንነትና ስልት? ለሱ ለሱማ እንደቻይናዎቹ የጥንት ወታደሮች በብዛትም ሆነ በልዩ ስልጠና፣ በማርሻል አርት፣ በዉሹ የተጠበበ... የተጠበበ ሰራዊት ከቶ ማን ነበረው? እሱስ ቢሆን በትንሿ ጃፓን የዘመናት አሰቃቂ ቅኝ ግዛት ከመውደቅና ባርነት መች ታደጋቸው? አይደለም የኛን ከግብርና ተነስተው የሚዘምቱትን አባቶቻችን? ሳትዘነጋው ወይ ሳትተካው አልቀረህም መሰል?

ያንን ልዩነት ነው ሊያስረሱህ የሚተጉት። ብረትና ባሩድንማ ከግልብፅና ከቱርኮች አለፍ ካለም ከጣልያኖች በላይ አትርፎ አብዝቶ የተሸከመው ከቶ ማን ነበረ?

ታዲያ የቱ ነበረ ልዩነትህ? በአለም ካሉ ሀገራት ሁሉ ከሩሲያ በስተቀር በብቸኝነት ለማንም ወድቆ የማያውቅ ያደረገህ? ጌዴዎን ማሰሮና የቀንድ መለከት ብቻ ይዞ ወጥቶ አምላክ ሙሉ የምድያምን ሰራዊት ላይ ድልን አልሰጠውምን?

እነሱ ባያስተምሩህ፣ ከታሪክ ትምህርትህ ቢቆረጥ በስራቸው ያከበርካቸው ምኒሊክ ሰይፍ ላይ በጉልህ የተቀረፀውን ፅሁፍ ምነው

ሄደህ ከቤተመዘክሩ አላየኸው? “የምኒሊክ ሀይሉ እግዚአብሄር ነው” የሚለውን?

ወይ ታሪክ ራቁቱን ሲቀር! ግንድ መነሻውን አይተን እንዳታቆጠቁጥ ቅጠሉን ብቻ ሲተረት እንዲኖር ሲደረግ! ስንቱን ታሪክ መሰረቱ ተረሳ፣ ተጠፋ!

ሌላውስ? የቋራው ካሳ ብቻ ወይስ የማህበረስላሴ ገዳሙ ካሳ? አፄ ቴዎድሮስ የሚለውን ስም ከየት፣ በነማን ተምረው ለምንስ መረጡት?

ዳዊት ደጋሚውና ራሱን ከንጉስ ዳዊት ጋር የሚያስተያየውና በሱ መልክ ራሱን የሚያንፀው ቴዎድሮስ? ወይስ የሕዝቅኤልን ትንቢት ሊፈፅም፣ ኢየሩሳሌምን ነፃ ሊያውጣ፣ ልጆቿን ሊሰበስብ የተነሳው፣ ሌላም በመልአኩ ቅዱስ ዑራኤል የተነገሩትን ሊፈፅም፣ አልፎም ስንትና ስንት እስከዛሬ በትክክል እንኳን ተረድቶ የሚያውቃቸው የሌሉ ረቂቅ ህልሞችን ይዞ የተነሳው ቴዎድሮስ ወይስ እንዲሁ ሽፍታው ቴዎድሮስ? ከማህበረስላሴ መነኮሳት ጋር የነበረው ቃልኪዳንስ? አፅማቸውስ ካረፈበት ስለምን ወዴትስ ተቀበረ?

በአድዋስ ዘመቻ ከምኒሊክ ሰራዊት ፊት ቀድሞ የሚመራው ምን ነበረ? ለምን የጊዮርጊስ ታቦት ተመረጠ? የጦር ጀግኖች የክብር ሽልማቶች፣ ይሰራዊቱ አርማ ስለምን ነበረ በቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል የሚቀረፀው?  ቢያንስ በጣም ታወቁ ከተባሉት ታሪኮች እንኳን እነኚህ ሁሉ ስለምን ተነጠሉ?

ሁሌም ከነበረን ሀያል ታሪክ ጀርባ ዋናው ታላቁና ቀዳሚው ትጥቅ እግዚአብሄር ነበረ። ያ ብቻ ነበረ የሐበሻው ልዩነት። ልብነድንግል ቁጥር ስፍር የሌለው ሰራዊት ይዞ ስለምን ክፉኛ ወደቀ? ልጁስ ገላውዲዎስ በተቃራኒው የጠላቱን ሩብ ያህል ይዞ እንዴት ታላቅ ድልን አገኘ?

ሌላው ቢቀር ሁልጊዜ የማትለይህ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ስለምን ይሆን ስሚ ሰንደቅ አላማ የተባለው?

ሰንደቅ አላማ? ምን ትርጉም አለው? የንጉስ ስም እንደነበረ ማን አስተምሮህ ይሆን? በሳባውያን ፅሁፎች እንደተፃፈው የአለምን ክፍል እስከ አንድ ሶስተኛ ያከል ያስገበረው ንጉሰነገስት ሰንደቅ አላማ ስሙን ዘወትር ሳያውቁት ከመጥራት ያለፈ ማን በሙሉ ታሪኩ ያስታውሰው ይሆን? ከኛ ጠፍተው በውጭ ሀገራት እንኳን የተገኙት የእግዚአብሄርን ስም ሳይጠቅስ የማይሆንለት የተፃፃፋቸው የጥንት ደብዳቤዎቹስ ለዛሬ ኢትዮጵያውያን ይደርሱ ዘንድ ማን ተርጉሚቸው ይሆን?

አንተስ ዛሬ በችግር ውስጥ ባለህበት ጊዜ ምን ያህል ትልቁን ትጥቅህን አምላክህን ይዘኸዋል?

ንብ አበባ ባለበት እንዲሰፍር፣ በየትኛውም ጊዜ እግዚአብሄር በመሀል የሚገኘው ፍቅርና እምነት ባለበት ነው። በመሀልህ የሚገኝ ወንድምህን አንዱን ከሌላው ለይተህ ያየህ፣ ምን ቢወድቅ ቢነሳ በማይቀይረው መስፈርት ከፍቅርህና ማህበርህ በለየኸው ጊዜ፣ ያኔ በፈቃድህ አምላክህን እንዳይቀርብህ እንደገፋኸው፣ ሀቁን፣ እውነቱን እወቀው።

የሁሉ ነገር ከልካይ ዘረኝነት ባለቀ ጊዜ ወደ አማራው ሊገባ እየታገለ ይገኛል።

**ከዘረኛ በላይ ክፉና እጅግ ወንድሙን የሚጠላ የዲያቢሎስ ፈረስ የለም። ዘረኛ በነገሰበት በትኛውም የሀገራችንም ሆነ የአለም ስፍራ**

**ፍቅር ሰላም ተዋህዶ እምነት ምልክታቸውም አይኖሩም። ይህ የሚታየው ሀቅ ነው።**

ከየትኛውም ዘር ብትሆን፣ ምንም ምክንያትም ብትሰጠው ይህንን የተላበስከው ዕለት የደነበረ ፈረስ ላይ የታሰረን ገመድ በአንገትህ ፈቅደህ እንዳስገባኸው እወቀው። የእግዚአብሄርም ቁጣ ዘራቸውን ሳይጠይቅ ዘረኞችን ሁሉ ይመታል።

አምላክ ሁሉ ነገር ያለው ሆኖ ሳለ ከኛ የሚጠብቃትን አንዲቷን ነገር ፍቅርን የሚሰብር፣ አምላክን (እስከዛሬ መከታ ሆኖ ያኖረህን ትጥቅ) የሚያርቅ ፀያፍ ነገር በመሀልህ ሊያስተጋባ ዳር ዳር እያለ ነውና ፈጥነህ ይህንን ሰደድ እሳት ደርሰህበት ግታው። ለምታገኘው ወንድምህም ሁሉ አሳውቀው።

የክርስቶስ ሌላው መጠሪያው የሆነውን ወንድማዊ ፍቅርን ከመሀልህ አስወጥተህና ከፍለህ እግዚአብሄርን የሚያፀይፍ ነገር ካንተጋር ኖሮ ፈፅሞ አብሮህ ሊገኝ አይችልምና ከእይታህና ከጠበቅከው ፍፁም ውጪና በላይ በሆነው ፅኑ መቅሰፍት አወዳደቅህ የከፋ ይሆናል። ቀድሞም አሁን ያለንበት ሁኔታ የኛ ጉዳይ ሳይሆን ቀድሞ የተነገረ የሚጠበቅ፣ ውጤትና ደረጃውም ከኛ ያለፈ ነውና፣ ለምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ አምላክን አስቀድመን ከዛ የኛን ድርሻ መታገል ይኖርብናል።

ዘር ለቅሞ ከራስ መሀል ለይቶ በመደራጀት ስም ወደጥፋት መስመር ቀድሞም ጠንካራ የነበረውን ህዝብ እየወሰዱት ነውና ፈጥነህ ቀድመህ ልትመልሳቸው ይገባሀል። መደራጀቱስ ምን ጥፋት ሆነ? ግን ከመሀልህ አንድ የዋህ የእግዚአብሄር ሰው ተነስቶ ወዳንተ ቢመጣ የሚያገለው አደረጃጀት ከሆነ ፍፁም አምላክህን ካንተ የሚያርቅና እጣህ በሰይፍ ብቻ እንዲሆን የሚያደርግህ ነው።

መቼስ የትኛውም ህብረተሰብ እንዲህ ነህ ብለው ለይተው ቦድነው

ሲያጠቁት ማንም ቢሆን እራሱን ለመከላከል መሰባሰቡ የማይቀር ነው። ጠላት ከፊት ቢገፋህ ወደኋላ ስትሸሽ የምትወድቅበትንም ጭምር አስቦ ነውና በታቀደልህ መንገድ ገብተህ ትልቁን ትጥቅህን እንደፈለገው አትፍታለት። ሀይልና መከታ ሆኖ ያኖረህ ዛሬም ለምንም ብሎ ጥሎ የማይጥልህ አምላክህን አታርቅለት። ይህም ስለሚታወቅ አውቀህ ትድንበት ዘንድ ነውና ቅዱሳን አባቶችህ ነብያት ዛሬ ባይደርሱልህ እንኳን ልጃቸው ዛሬ አንብበህ እንድትድንበት ስለዚህ ቀን ፅፈው ያኖሩልህ።

ቆይ ግን ለመሆኑ፣ ማንነት ማለት ራሱ ምን ማለት ነው? እንዲሁ እንደፈለጉ በየጊዜው የሚቀያየር ነገር ነውንዴ? ትላንት የሆንከው ዛሬም የሆነው ነገም የምትሆነው ፅኑ ነገር ነውንጂ? ካልሆነማ እንዴት ማንነት ይሆናል?

የአማራ ክልል ህዝብ ከኢትዮጵያዊነት ከፍያለም ከኢትዮጵያዊነት ዝቅም ያለ ማንነት አልነበረውም፣ የለውም። ታዲያ እንዲህ ነህ ተብሎ ተለይቶ ሲጠቃ፣ አሁንም ለታቀደ ጥፋት ኢላማ ተደርጎ ሲነሱበት ተባብሮ መቆሙ ግድ ቢሆንበትም፣ እንደሚታየው ወደባሰ ፍፁም ውድቀት ዝቅ በሚያደርግ፣ ከመጀመርያውም የሁሉ መንስኤ የሆኑት በክህደት ፀንተው አጋንንት በህቡእ አንድነት ሚመራቸው የውጪ ጠላቶች እቅድ ሙሉ በሙሉ በሚፈፅምላቸው፣ እግዚአብሄርንም አፀይፎ በሚያርቀው መልኩ ፈፅሞ መሆን የለበትም።

ከመጀመሪያውኑ የዚህ ሁሉ መነሻና የጠላቶች መዳረሻ ግባቸው አምላክን አክባሪነት የሆነውንና በአምላክም የተወደደውን ባለ ቃልኪዳኑን ኢትዮጵያዊነት ማጥፋት ነበርና።

ከሁሉ በፊት፣ እንቁ ኢትዮጵያዊና የእግዚአብሄር ህዝብ የነበረው

የትግራይ ምድር ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱና በእምነቱ ምክንያት ቅድሚያ ኢላማ ተደርጎ እግዚአብሄርን በጠላ ርዕዮት እንዲመረዝ ተደርጎ፣ ድንገት የተነሳ ዘረኝነትና ጥቅመኝነት ያወረው ቡድን በዛ መልካም ህዝብ ላይ ነግሶና ሰልጥኖበት ህዝቡ የኔ ብሎ እንዲያየውም በተለያዩ ስነልቦናዊና የጥቅም ውስብስብ መንገዶች ስራ እየተሰራበት ሙሉ ህዝብ ለመለወጥ ባቀደ መንገድ አዲስ ትውልድ ያውም ኢትዮጵያዊነት ምኑም የማይመስለው፣ ለእግዚአብሄር ያለው እይታና ቅርበት፣ ከምእራባውያን ቸልተኛ ህዝቦች ያልተለየ የሆነ፣ ኢትዮጵያን እንደውም ከማንም በላይ የሱም አባቶች ጠብቀው ባቆዩት የአምላክ ቃልኪዳና፣ ታሪካዊና መንፈሳዊ ማንነቷ ሳይሆን የሚያውቃት እንዲሁ ማንም ተነስቶ ገነጣጥሎ ሊያፈርሳት የሚቻለውና የራሱ አባቶች ሳይቀር ያቆዩት መንፈሳዊ መሰረት የሌላት አድርጎ የሚያስብ ትውልድ እንዲፈጠር ጫና እየተደረገ ኖሯል።

ከሰሜን ከኤርትራ ጀምሮ በጊዜ ወደታች እየወረደ ኢትዮጵያዊነትን እያጠበ መምጣትን አቅዶ የሚሰራው ክፉ ጠላት ዛሬ አንተ ላይ ቢደርስ በተመሳሳይ አንተም ያንኑ ደግመህ ስታሳካለት ማየትን ያህል የሚያም ነገር የለም።

ከጥንትም ሰንሰለቱ ሆኖ ያያያዘን እግዚአብሄርን ሁሉም ቢረሳው እንዲህ መለያየት ሰፈነ እንጂ፣ በስነልቦናና እምነት፣ በድህነት ፍቅር ፍፁም አንድ የሆነህን ህዝብ ጋር ማን ይለይህ ነበር? ፈጣሪህን ልትይዘው ይገባህል! አንድ የሚያደርግ የፍቅር ሰንሰለት እሱ ነውና።

በምንም መልኩ ልትበገር የማትችለውን ኢትዮጵያን ሊንድ ይቻለው ዘንድ ከትግራይ ምድር ኢትዮጵያውያን ጋር ያላችሁን የጋራ ማንነታችሁን ሊያጠፉ ጠላት አቅዶ እንዳደረገው፣ በወንድምህ ላይ ዘምቶ ካንተ ቢለየው፣ ልታዝንለት፣ ወንድምህ ፈልጎ ያመጣው ሳይሆን ያንተውም መልክ በሆነው በኢትዮጵያዊነቱና እምነቱ ምክንያት ለጥፋት ነውና በእንባ ልትፀልይለት እንጂ፣ ልትፈርድበት

ፈፅሞ አይገባህም!

ሀገሩን ከ 83 ወዲህ በግፍ የገዛው ባንተ ስም ካንተ ወገን ተነስቶ ቢሆን ኖሮ ተመሳሳይ ተግባርና ሁኔታ ባንተ ይሆን እንደነበረ እውነት ሀቅ ነውና በነሱ የሆነ የወገንተኝነት ፈተና ባንተም ፀንቶ በተመሳሳይ መልኩ ይታገልህ፣ ይፈትንህ እንደነበረ ፍፁም ሀቅ ነውና ስለውሸት ፈፅመህ እንዳትመፃደቅ። ዛሬ በትግራይ መሬት እንደሚሰበከው በከፊልም በአዲሱ ትውልድ እንደሰፈነው በተራነት እግዚአብሄርን መዘንጋት፣ በመሳሪያ ትጥቅና ወገንተኝነት ተማምኖ፣ በፉከራ፣ በመሳሪያ ታጋይነት ትርክት፣ ከንቱ ከሁሉ የበላይነት ስብከት የትእቢት መንፈስ ተጠምቆ የእግዚአብሄርን ህልውና መዘንጋትን መሰረት ያደረገ የምእራባውያን የብልፅግና፣ ስልጣኔ መንገድ ምኞት ሰክሮ ስለ እግዚአብሄር አንዳችም ሀሳብ ሳይኖረው በአባቶቹ በእምነት በክብር ተጠብቀው በኖሩ የእግዚአብሄር ቃልኪዳኖች ምድር ከእግዚአብሄር ጋር እንደገነት እንደ ፅዮን መኖር ሳይሆን በግንጠላ ሲንጋፖርነትን የሚቃዠ ትውልድ እንዲፈጠር ከባድ እንቅስቃሴ ይደረጋል። ነገር ግን እግዚአብሄር ዛሬም አለ፣ በአለም የሚሆነውም በኛ በብናኞች ባለቅፅበት እድሜ ፍጡራን ሳይሆን በሱ ይፀናል።

በአሁን ጊዜ በመሀልህ የተነሳውን ከእግዚአብሄር የሚያርቅ ነገር ሁሉ ቀድመህ ተዋጋው። በመሀልህ የኔ ዘር ነው ልዩ፣ የኔ ዘር ነው ባለታሪክ፣ የኔ ዘር ነው ኢትዮጵያን ያቆየ የሚሉ ትእቢትና ማግለልን ቀላቅሎ የሚከፋፍል፣ እግዚአብሄርን አፀይፎ ከመሀልህ የሚያርቅ ነገር ሁሉ አጥፋ። ይህ ሁሉ አነጋገር ባላዋቂው ትውልድ የመጣው ህዝቡ በእምነቱ ደክሞ እግዚአብሄርን ረስቶ ሳለ ድንቅ ታሪኩን ቢመለከት፣ ዛሬ በረሳው እግዚአብሄር የተደረገው ተግባር ሁሉ ባለቤት ባዶ ሆኖ ቢታየው ለራሱ ወስዶ የሚናገረው ነውና። ኢትዮጵያ ለሺ ዘመናት ስትጠበቅ በአክሱም ፅዮን፣ በደብረሊባኖስ፣ በምሁር ኢየሱስ፣ በላሊበላ... በአራቱም ማእዘናት ባሉ ኢትዮጵያውያን ፀሎትና ምህላ፣ አምላክን በችግር ጊዜ ሁሉ

ብትለምነው፣ በኑሯቸው በእምነት ቢገዙለት፣ በፍቅር ምስጋና መኖርን ባህላቸው ቢያደርጉት፣ እሱም ልጅነታቸውን ቢቀበል ነውና ባላረፍንበት ዘመናችን ሁሉ ጠላት ቢነሳብን እግዚአብሄርን ተማምነን ከእርሻላይ ተነስተን ጦርና ጋሻ ይዘን ብንወጣ፣ መድፍና ጥይት ይዞ፣ የተደራጀ ስልጡን ጦር ሁሉ ከእግራችን ጫማ በታች የጣለልን፣ እንጂ በመላው አፍሪካ ግብፅን ጨምሮ ከቶ መች ሳይዋጋ ለቅኝ ግዛት፣ ለባርነት እንዲሁ ራሱን የሰጠ ነበር?

ታዲያ ዛሬም በዘር ቡድን ለይተው ቢያጠቁህ እንዲህ ነህ ብለው ቢነሱብህ አይሆንም ብሎ መደራጀትና ለመከላከል በጋራ መቆም አማራጭ የሌለው ትክክለኛ ቢሆንም፣ ስለምን አጥብበው የሰጡህን ትለብስላቸዋለህ? ቢሰጡህ ይበልጥ የሚያደክምህንና ያባቶችህን ትጥቅ እግዚአብሄርን ይሚያስፈታህ ይሆን ዘንድ ነውና። ስለምን/ስለማንስ ብለህ የማያሳፍርህ ብቸኛ መከታ አምላክህን አጋርነት ትተህ እሱን ከመሀልህ የሚያርቅ ዘር ቡድን ላይ ራስህን ልትመድብ ትፈቅዳለህ? ቀድመህስ ስለማን ብለህ ነው አምላክህን የያዝከው? ዛሬስ የምትለቀው?

አደረጃጀትህ ማንኛውም በመሀልህ የሚኖር አንድ የዋህ መልካም አሳቢ የእግዚአብሄር ሰው ሊቀላቀልህ ቢያስብ፣ በማይቀይረው መስፈርት ዘር ቆጥረህ እንድታገለው የሚያደርግ ፈፅሞ አይሁን። እውነት ለምሳሌ ፃድቁ አቡነ አረጋዊ እንኳን መጥተው አብሬህ ልሁን ቢሉህ አሻፈረኝ ብለህ ልታገላቸው ድረስ መርከስ ቀላል ሆነልህ?? በዚህ መሰል አሰራር አምላክህን ልታፀይፈውና ልታርቀው ግድ የሌለህ ነህን? እሱ ካንተጋር ይሁን አይሁን ግድ የሌለህ ኢአማኒ ሆነህ በስጋ በመርመስመስ ገባዥ የማያስፈልገው የአጋንንት ማደሪያ እንደሆኑት ዘረኛ ታጣቂዎች ሆንክ? ይህንንስ እንዳታደርገው። ከምንም በላይ ለድል ቅድሚያ የሚሰጠው የእግዚአብሄር አብሮ መኖር ነውና።

እንዲህ ነህ ተብለህ ለጥቃት ኢላማ የተደረግከው መደራጀት አለብኝ ካልክ፣ ቢጠብ ቢጠብ የአማራ ክልል ህዝብ አደረጃጀት እንጂ የአማራ ዘር ብለህ አላስፈላጊ ክፉ መንገድ ውስጥ አትግባ።

አብረውህ ያሉትን ማንኛቸውንም የማይለይ፣ ክልል ሚጠብ ሚሰፋ በመሆኑ ሌሎች በአንድነት ሀሳብ ያመኑ በግብለሰብም ሆነ በህብረት መጥተው የሚቀላቀሉህ፣ ሀይልም የሚሆኑልህ፣ እግዚአብሄር ሊባርከው የማይጠየፈው የፍቅር አንድነትን ተላብሰህ ለማደግ ለመበርታት ቁም። እኛ ዘር ተማምነን ጎራ ይዘን ብንቆም፣ አምላክም አንዱን ለይቶ የሚደግፍበት ምክንያትም አይኖረውም፣ ከሁላችን ርቆ በሰይፋችን ስንተራረድ እንከርማለን እንጂ። ከክልሉም ውጪ ያሉ የአማራ ዘር ተብለው የሚገፉ ወገኖች፣ የአማራ ክልል ህዝብ ልጆች ናችሁ ተብለው ነውና፣ ለነሱም ብትቆም ይህ አደረጃጀት ያስችልሀል። የዥንጉርጉር ልጆቹ አባት እግዚአብሄርንም ይዘህ ድልን ትለብሳለህ።

እንዲያ ካልሆነ ግን በራስህ እጅ እግዚአብሄርን ገፍተህ እንዳስወጣኸው እወቀው። ለነገሩ ክርስቶስ እራሱ በስጋ ተገልጦ ከመሀላችሁ ልገኝ ቢል ምን ዘር ብለህ ልታስገባው ነው? ትመልሰዋለህንጂ። ይህ እውነተኛው የጉዞህ መልክ ነውና አይግረምህ። ከተለያዩት የዘረኞች ጎራማ ያንተ ለምን ተለይቶ አብሮህ ይሆናል? ነው ወይስ በዚህ በታሪክህ ከባድ ጊዜ እሱን አትፈልገውም? ሌላኛው ሳይጠሩት የሚመጣው ጋባዥ የማይፈልገው ርኩስ መንፈስ ግን መገኘቱ አይቀርም። ምንጊዜም በመሀል ነግሶ ዘረኞችን አንድ አይነት አድርጎ በሚዲያው እንደሚታየው እንደውም በብዛት የተማሩ ምሁር የሚባሉትን ሳይቀር አእምሮ አውርዶ የሚያስደነግጥ አፀያፊ ንግግርና ተግባር ላይ ሲውላቸው ተመልክተሀል።

በዘረኝነት ግር ብለው በወጡ ሰወች መሀል ለሰው አእምሮ የሚከብድ አሰቃቂ ነገር ሁሉ የሚከሰተው ስለምን ይመስልሀል?

እያንዳንዱን ሰው በተናጠል ብትጠይቀው ከቶ ሊያደርገው የማይችለውን የሚጠየፈውን ነገር በተሰበሰቡ ሰወች መሀል ተደጋግሞ ሲደረግ ለምን ይመስልሀል? በየግል ያላቸው የተሻለ ሰብአዊ አእምሮ ጠፍቶ በጋራ አንድ የሚያደርጋቸው ሰው በቁሙ የሚያስቃጥል፣ ዘቅዝቆ የሚያሰቅል፣ በስለት የሚቆራርጥ በስቃይ የሚደሰት አዲስ አእምሮ በአንድነት ይላበሳሉ እንጂ፤ በዛ የቡድን መንፈስ ላይ መሪነቱን የሚቀዳጀው መሀል ለመግባት ግብዣ የማይፈልገው ክፉ መንፈስ፣ እያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ እንደፈለገው ተመሳሳይ ሀሳብ የማስቀመጥ፣ ትእዛዝ በመስጠት ማስተባበር የሚያስችለው መናፍስታዊ ተፈጥሮውን በመጠቀም አንድ የጋራ አእምሮ አስይዞ በየግላቸው የሚጠየፉትን ቡሀላም የሚፀፀቱትን፣ እንደሌላ ሰው የሚኮንኑትን ተግባር እንዲሁም ሌላም ያለንግግር የተቀናጁ ጥርጣሬዎች፣ ድንጋጤዎች፣ ፍርዶች፣ ያንድላይ ሀሰተኛ ፍረጃዎች በአንድነት ያለንግግር ተግባብተው አሰቃቂ ተግባሮችን በአንድ አእምሮ ያሰራቸዋል።

ሌላም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ማንኛውም ሰው ክርስቶስ የሚቃወመውን ነገር ሲያደርግ፣ የፍቅር ፍፁም ተቃራኒ የሆነውን ዘረኝነትን ሲሰብክ፣ ራሱን ጋብዞ የሚመጣ መንፈስ ምሁሩን አእምሮ አልባ እስኪመስል ድረስ ተቆጣጥሮ ክፉ ክፉ ያናግረዋል፣ ያሰራዋል። የዚህ አይነት ክፉ ወንድምን ከሌላው መክፈልና ለይቶ ጥቅመኝነትን መስበክ ደግሞ አንዴ ባለቤቱ መንፈስ ከገባበት ነገሩን አራማጁ ሰው እንዳቀደው አማራና ሌሎች፣ በሚለው ክፍፍል ፀንቶ የሚያበቃና በዛው የሚቀጥል ሳይሆን አንዴ የክፍፍልና የወገንተኝነት መሪ መንፈስን ጋብዘው ካስገቡት ልክ ከላይ እንደመቱት መስታወት ከዋናው ስንጥቅ መስመር ተከትለው ሌላ የበዙ ክፍልፍሎችን የሚፈጥር ሆኖ ስንጥቁ እስከጥጋጥጉ እንደሚዛመት፣ አማራ እና ኦሮሞ፣ ወይ አማራና ትግሬ የሚል ክፍልፍልን አራግበው ከላይ ራሳቸውን የከፈሉበት መንፈስ ወርዶ የቅማንት፣ የአገው፣ የሸዋ ወዘተ እያለ እየቀጠለ መጨረሻ የሌለው ነቀርሳ መንፈስ መሆኑ የሚወራ

ሳይሆን በተግባር የሚታይም መገለጫው ነው። ቀድሞስ ቢሆን በዚህ መህል የሚነግስ መንፈስ ከዛ ዘር ወይ ከሌላው ዘር ምን የተለየ ጉዳይ አለውና? በቻለው መጠን የልዩነትና ባላንጣነትን፣ ወገን ለይቶ ጥቅመኝነትን መንፈስ አንግሶ ፍቅርን እስከተቻለው መጨረሻዋ ቅንጣት መስበር ነውንጂ። በፍቅር የሚመሰለውን ክርስቶስ የወንጌል ህሉ ጭምቅ መልእክት በፅኑ መዋጋት ነውንጂ።

ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው "ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።"

ምን ባለመንፈሳዊ ፀጋ ባለቤት፣ ምን ባለቅዳሴ፣ ባለማህሌት ብንሆን፣ ያ ሁሉ በዜሮ ተባዝቶ እምነት ከሌላቸው ሀጢያተኞች ጋር በአንድ ላይ እንድንቀሰፍ ያደርገናል።

ስለዚህ ምንም ቢጠብ ቢጠብ፣ ቢያንስ አብረውህ በክልሉ ያሉ ወንድሞችህን ለይቶ የማያገል አድርገው። ቦታ ሊሰጡ የማይገባቸው ከንቱዎች በመልካም ሰብአዊ ፍቅር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መህል አጥብበው ከፍለው "አማራ ክልል" የተባልክ መሆንህን አትርሳ! የአማራ ክልል ኢትዮጵያዊ መሆንህን አትርሳ ! አማራ ክልል ተብለው የተከለሉ ኢትዮጵያውያን!

# የአማራ ክልል ኢትዮጵያዊ !!

ነኝ ብለህ ልትናገረው የሚገባህ ያ ነው ያንተ መጠሪያ። ከዚያ አታጥብበው። ለልጁ “ተመልከት ያንተን ንብረት” ብሎ የአክሱምን ሀውልት የሚጠቁም፣ “ተመልከት የርስትህን ጫፍ” ብሎ ከካርታ ላይ ኦጋዴንን የሚያሳይ፣ እሱ ራሱ እንዲህ ተብሎ ከአባቶቹ የተረከበውን እንዳባቶቹ ታግሎ ጠብቆ ለልጁ ሙሉ መብትና ባለቤትነትን የሚሰጥ ነህ። ወደፊትም ኢትዮጵያን የሚያድነው ኢትዮጵያዊ እንዳትሆን ከቶ ምን ያንስሀል?

ጀግንነትና ሀይል አንሶህ ነውን የበታችነት የተጠናወታቸው፣ መቼም የማያሸንፉ፣ በተጎጅነት ትርክትና ሮሮ ሲያላዝኑ ሀያል ጉልበታቸውና ጊዜያቸውን ሲጨርሱ እንደሚታዩት ዘረኞች፣ ከዘረኝነት የሚገኝ ሀይልን ለመላበስ የምትሯሯጠው? ነው ወይስ እግዚአብሄር የለም ብለህ ክደሀል? ወይ በቃ ፈፅመህ ክደሀል? ታዲያ እሱን ይዘህ በፍፁም ስነልቦናዊ ሀይልና እምነት የዳዊትን ሀይል መላበስን ትመርጣለህ እንጂ። ቀድሞስ ቢሆን መቸ ደካማ ሆነህ ነው የሰነፍ ዘረኝነት ሀይልን ልትይዝ ራስህን የምትከፋፍለው?

በግፍ ጥቃት ለይተው ቢገፉህ፣ የሚገባህን ሊነጥቁህ ቢነሱ፣ በዚህ ክልል ላለን ኢትዮጵያውያን ይገባናል በል፣ አማራ ብላችሁ ለይታችሁ የምታጠቋቸውን ለራሳችሁ በከለላችሁትም ያሉትን እኔዎች እከላከላለሁ በማለት ቁም እንጂ ይህን ሁን ብለው የሰጡህን አጥብበህ ይዘህ ራስህን በክፉ መንገዳቸው አውለህ ውስጥህ ያሉትን ኢትዮጵያውያን እንደገና ዘር ብለህ ሳትከፋፍል በፍቅርና ጠንካራ አንድነት እግዚአብሄርን ይዘህ ይህን አንድ የሚያደርግ በሌላም ክልሎች ያሉ መሰል አስተሳሰብ ካላቸው በዙሪያህ ያሉ ኢትዮጵያውያን ጋር በአደረጃጀትም ሆነ በስፋት እያደግክ በዘረኛ ጠላቶችህ ላይ ባልፈለጉት መንገድ ክፉ መንፈሳቸውን የሚሰብር አምላክህን ይዘህ ተነሳባቸው።

እምነታችን ደክሞ ከእግዚአብሄር ህግጋትና መመሪያ ብንርቅ እንኳን ከአደባባይ ታሪክ መማሩን ማን ጋረደን?

አሁን በኢትዮጵያ ያለው መልክ አሜሪካ በክፍፍልና አደጋ ውስጥ ሆና የነበረበት ሚሊዮኖች የሞቱበት የእርስበርስ ጦርነት ከነበረበት ወቅት ተማር። አንድነትን የሚያቀነቅኑት ቡድኖችና መገንጠልን የሚሰብኩት ዘረኞቹ ቡድኖች በተዋጉበት ወቅት እጅግ ብዙዎች በዙሪያው የነበሩት ከያሉበት ወደ አንድነቶቹ ቡድኖች መቀላቀል ይችሉ ነበር። ከተገንጣዮቹም ወገን ብዙ መረጃዎችንና ሀይሎችን በመያዝ በሂደት ወደአንድነት ሀይሎቹ መቀላቀላቸው ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው። የተገንጣዮቹ ጥቁር አፍሪካዊ ባሪያዎቻቸው ሳይቀር በመኮብለል ወደዛኛው ሀይል ይቀላቀሉ ነበር። ይህንንም ያስቻለው አቃፊነታቸውና ይህንን ታላቅ ነገር ያስቻለ አደረጃጀታቸው ነበር። በዚህም መሰረት በአብርሀም ሊንከን የሚመራው የአንድነት ሀይል ድል አድርጎ ያሁኗ ሀያሏ አሜሪካ እንድትመሰረት መንገድ ከፍቷል።

ዛሬም አንተ ራስህን አቃፊ ሆነህ፣ በፍቅርና አንድነት ከሌሎች ጋር በመዋሀድ፣ ከዘረኞች ጎራም ጭምር ወደ አንድነት የሚመጡ የሚቀላቀሉበትን መንገድ በመያዝ ኢትዮጵያውያን በጋራ በፍቅር አምላካቸውን ይዘው ድል የሚያደርጉበትን መንገድ ልትከተል ይገባሀል። ራስን በዘር ቆልፎ ለውድቀህ መሯሯን አስቀድመው የተዘጋጁለት የመረጡልህ መንገድ ነውና በሚሰፋና የሚያድግ እንቅስቃሴ በርትተህ ተገኝባቸው። እግዚአብሄር የሚጠላውን ዘረኝነት፣ ጥቅመኝነትና መከፋፈልን በውስጥህም ሆነ በውጪ፣ ከየትኛውም ጎራ ይሁን ፈፅመህ ተዋጋው።

ሀይል ለሚሆኑህ ለሌሎች መልካም ኢትዮጵያውያን ውሱንና ዝግ

ሆነህ፣ ጠላት ያዝ ያለህን ይዘህ ሳይሆን ማደጊያ መስፈያ የሆነውን ኢትዮጵያዊነት እንደፈለጉ የማይቀያየር እውነተኛው የማይቀየር ማንነትህን አፋፍመህ ይዘህ ራስህንም ላለመጣል ለጥቃት አማራ በሚል የተለዩትን ኢትዮጵያውያንም መጠበቅ ከአላማዎቹ ውስጥ አንዱ ዋና አላማው የሆነ አደረጃጀትን ይዘህ ለታላቅ ድል የሆነ የጀግና ጋባዥ ትግል አድርገው። ክልሉ ውስጥ ያሉትን ሌሎች ወንድሞችህን ጭምር የሚያገል ዘር ቆጠራ ውስጥ ገብተህ አምላክህን አታርቀው! ካሉት የዘር ጎራዎች መሀል የኔን ዘር መርጦ ይቀርባል ብለህ ክብሩን ዝቅ እንደማታደርገው ይታሰባል።

ዛሬ ያለን ትውልዶች መንገዳችን እግዚአብሄርን ያሳዘነ ነውና፣ የእግዚአብሄር ትንቢቶች እንደተናገሩት ከባድ ጊዜ ከፊታችን ይጠብቀናል። አንተም ይየትኛውም ዘር ይሁን፣ ዘረኝነትን እንዲስፋፉ ፈቅደህ ለሚመጣው መቅሰፍት በግንባርህ ላይ የእርድ ምልክት አታድርግ። ምን ጠላት ለይቶ ቢነሳብህ የአባቶችህን ትጥቅ ከፊታህ ብቻ ነውና የምትወድቀው እግዚአብሄር ከመሀልህ እንዳይቆም ከሚያደርግ፣ ጠላትም ይህንን አውቆ ሊነዛብህ ከሚታገለው ዘረኝነት ራስህን ጠብቅ።

ዘረኝነት በትንሹ ተብሎ ሊወሰድ የማይችል ስካር፣ አንዴ መንከባለል ከጀመሩለት እዚህ ጋር አቆማለው የማይሉት ቁልቁለት መሆኑን ማንም የማይክደው ተፈጥሮው ነውና ስለራስህ ስትል አትላበሰው፣ በሙሉ እንቅስቃሴህ ተጠንቅቀህ በሩቁ ያዘው።

አንተ አልከም/አላልከም/ተቃወምከም/ደገፍከም ዘረኞች ሁሉ ይጠፋሉ። ጥንት በክፋት ተጠምደው የነበሩ የኔፍሊም ልጆች የነቢዩን ማስጠንቀቂያና የንሰሀ ጥሪ ችላ ብለው በርኩሰታቸው ቢቀጥሉ “ቅዱስ ገብርኤል ሰይፉን ሰጣቸው” ተብሎ እንደተፃፈና እርስበርስም በፍፁም ውድቀት እርስበርስ እንደተበላሉ ሁሉ፣ ጎራ ጎራ ይዘው በጥላቻም ሆነ በራስወዳድነት የተሰለፉ የዛሬ ዘረኞች ከየትኛውም ዘር ይሁኑ እርስበርሳቸው እንዲሁ ፍፁም መተላለቅን

ይቋደሳሉ፣ የእሳት ሰይፉን ይዘው መራራውን የመከራ ሞት ፀዋ አንዱ ለሌላው ይጋታሉ።

በንግርትም ጭምር በሱ ዘመን እንኳን የሰው የእንጨት ጠማማ አይጠብቀውም እንደተባለው ክፉ ዘረኞችም ሆኑ የሀጢያት ሰወች ከትንሳኤው በፊት በሚበላው እሳት ከስመው ይቀራሉ።

አይደለም ዘረኝነትን ጨምረህበት፣ እንዲሁ የምንኖረው የሀጢያት ኑሮ እንኳን ሩጫችን ከሚመጣው የእግዚአብሄር ቁጣ ባላተረፈን ነበር።

ከሚመጣው ከተነገረው መከራ የሚተርፉት ጥቂቶች መሀል ሁን። ከመከራ በኋላ በሚሆነው ትንሳኤ የሚመጣውን ዘመን ዳዊት በትንቢታዊ መዝሙሩ "ኢትዮጵያውያን ከፊቱ ይመራሉ" ከተባሉት ከመሆን ይልቅ ሌላ ዘረኛ ማንነትን መላበስን ከመረጥክ፣ ያንተው ምርጫ ነው። በቃል ንግርት እንኳን "በሱ ዘመን እንኳን የሰው የእንጨት ጠማማ አይጠብቀውም" እንደተባለው ወንድሙን ለይቶ የሚያርቅ ክፉ ዘረኝነትን ከሚሰብኩት፣ ከሚከራከሩለት ጋር ቀድመህ ከምድር ለመፀዳት፣ ለመጠረግ አትፋጠን።

ይልቅ ታሪክ እንደዘገበው፣ በዘመኑ በጎበኙን የውጪ ፀሀፊዎች ማስታወሻ እንደተዘገበው የኢትዮጵያውያን መለያ የሆነው፣ የጀግንነት፣ ከአህዛብ ሁሉ የበላይነትና የአምላክ ወዳጅነት ስነልቦናን ያላበሳቸው ምስጢር ሁሉም አዘውትረው የሚደግሙት የተዋሀዳቸው መዝሙረ ዳዊት ነበር። አንዳንድ ኢትዮጵያን ጠል ፀሀፊያን እንኳን ያንጓጠጡን መስሏቸው "ከመዝሙረ ዳዊት ሌላ መፅሀፍ የማያውቁ፣ በቃላቸውም ብዙዎቹ ሙሉውን የሚደግሙት" በማለት ዘግበው ነበረ የባህል ፍልስፍናና ኢትዮጵያዊ ስነልቦናችን ምንጭ የሆነው መዝሙረዳዊት መሆኑን ዛሬ ላለነው ምስክር ይሆን ዘንድ የዘገቡልን። በአምላክ መታመን፣ በችግርና ማንኛውም ፍልሚያም ቢሆን እግዚአብሄርን ሀይል ማድረግን የተማሩበት፣ የአፄ

ቴዎድሮስ መሳሪያ፣ እንዲሁም የሀበሻ ጀግንነትና ማንነት ምንጭ ይህ የተዋሀዳቸው መዝሙረዳዊት ነውና ዛሬም አንተም ይህንን መፅሀፍ አንሳው! እውነተኛ ሀይልህን ጀግንነትን ተላበስ።

እውነትም በመፅሀፍ ቅዱስ ማንም ባልተገለፀበት ቃል፣ ፈጣሪ ራሱ በቃሉ " እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ " ብሎ የመሰከረለት ቅዱስ ዳዊት ተከትሎ እንደ እግዚአብሄር ልብ ለመሆን የሚጥር ህዝብን መሆንን ያክል ክብር በምድርም በሰማይም ከቶ እንዴት መታደል ነው !!

ቅዱስ ዳዊት ጠላት፣ ሰልፍ በበዛበት ጊዜ፣ ሀብት ሆኖ ድልን ያለበሰውን አምላኩን የተማፀነባቸው መዝሙሮች፣ በእግዚአብሄር መተማመንን፣ እሱን ሀይል ማድረግን የሚያላብሰውን ይህን መፅሀፍ በዚህ ጊዜ አንተም ያዘው።

አንዷ 7 መስመር የምታሞላ ናትና በዕለት 5 ምዕራፍን ብቻ ከልቦናህ ሆነህ ብታነብ ለዚህ ዘመን ስልቹ ሰው እጅግ ቀላል፣ ግን ፍፁም ሀያል ተግባር ነውና ከአባቶችህ ስነልቦና፣ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት፣ ከሀበሻ ተአምራዊ ጀግንነት እንደቀድሞህ ተዋሀድበት !

ሁሉ ህይወትህ የአምላክ ፈቃድ እንዲነግስበት ፍቀድ፣ አምላክህን ልጅ ሁነው፣ አባትህ ነውና እመነው፣ የአምላክን ፈቃድ መኖርን ራስህን አለማምደው።

መኪና ስትሳፈር እንኳን "በሰላም አስገባኝ" አትበለው፣ ይልቅ እስቲ ደፍረህ አምነኸው "ፈፅሞ ያንተው ፈቃድህ ይሁንልኝ" በል፣ ፈቃዱን ማስቀደምን፣ መቀበልን ተለማመድ ! ! ! "ፈፅሞ ፈቃድህ ይሁንልኝ፣ ግን ከተቻለ የይቅርታና ቸርነትህ እንዲሆን እለምንሀለሁ" ብለህ አምነኸው ራስህን ስጠው፣ ፈቅዱ ሞትህም ከሆነ በደስታ ለመቀበል እስካልቻልክ እውነተኛ እምነት የለህምና ራስህን በዛ መንገድ

አንፀው፣ ይህንን ሳትረሳ በመኪናም ሆነ በስጋትህ ጊዜ አትዘንጋው፣ ራስህን ወደአምላክህ አለማምደው። አባት ሆኖ ሳለ ደካማ ልጁ አምኖት ከእግሩ ስር ሲሸጎጥ ልቡ ችሎ የሚጎዳ፣ ችሎም ዝም የሚል አባት የለምና፣ እሱስ እንደሆነ ከኛ ልጅነትን እንጂ ጎሎበት ለሱ ልንሰጠው የምንችል እሱም የሚፈልገው አንዳችም የሌለው ደግ አባት ልጁ ሁንለት እንጂ ሁሉን እንዳይሰጥህ ቀድሞስ ምን አጋጅ ምክንያት አለውና?

የብዙ ገንዘብ እጣ ሊወጣልህ ቢል፣ "እባክህን አምላኬ ያንተ ፈቃድ ብቻ ይሁንልኝ፣ ለኔ ፈቃድህ እሱ ከሆነ ባዶ እጄን እንድትመልሰኝ፣ አንዳችም እንዳላገኝ አብዝቼ እለምንሀለሁ፣ አገኝ ዘንድ ፈቃድህ የሆነውን ግን ስጠኝ" ብለህ ፈጣሪህን ማመኑን የህይወትህ መርህ አድርገው።

በህይወትህም፣ በድልህም፣ ዳዊትን መስለህ ኑር።

የሀገራችን መፃኢ ሁኔታና ውጊያው ባይንህ ያየኸው፣ ነው ብለህ የምታስበው፣ የተዘጋጀህለትና የጠበቅከውን መልክ የያዘ፣ በዛም የተወሰነ ሳይሆን፣ ይልቅስ የራስህ አባቶች ጭምር ከጥንት በትንቢት አውቀውት፣ ሲጠብቁት የኖሩት ውጊያውም የምድራውያን ጎሳዎች ተራ ግጭት ሳይሆን የእግዚአብሄር የቁጣ አይኖች ወደሀገራችን የሚመለከቱበት፣ ከህሊናህ በላይ የፀና፣ የእግዚአብሄር ፍርድ የሚገለጥበት በመሆነውና በምድር ፋክክራችን ታውረን ልክ ከታላቅ ጎርፍ መንገድ ስር ቆመው ትኩረታቸው እርስ በርስ ላይ አድርገው ጨርቅ የሚጓተቱ ሁለት ሰወች አይነት ሁኔታን አትላበስ። የነሱ መሸናነፍ ምን ሊሆናቸው? ትልቁ አስፈሪ ጎርፍ በነሱ ላይ እንደሆነ ልብ ይገዙ ዘንድ ማን በነገራቸው። የሚመጣው ክስተት አንተ ባሰብከው ውሱንነት የሚታይ ሳይሆን የእግዚአብሄር ክንድ ወይ ባንተላይ ወይ ካንተጋር ከሁለት አንዱን ይዞ በፅኑ የሚቀስፍበት፣ ከባድ ጊዜ መሆኑን ልብ በል። ከእስራኤላውያን መሀል ጎሳ ለይተው ሰልፍ በወጡ ጊዜ ለእግዚአብሄር በአንድነት መገዛት ይሻለናል

ብለው፣ አምላካቸውን ይዘው የወጡትን በሀይላቸው የተማመኑት በድንገት አዘናግተው ጦር አዙረው ከበባ ውስጥ በከተቷቸው ጊዜ፣ ይሁዳውያ በእግዚአብሄር ታምነው ያባቶቻቸውን አምላክ ከሁሉ ትጥቃቸው አምነው አስቀድመው ይዘው በመውጣታቸው ከበባውን ሰብሮ በአንዲት ሰአት ግማሽ ግማሽ ሚሊዮኖችን እንደመታ አስታውስ። በማይቀረው ምታደርገው ምድራዊ ዝግጅትህም ሁሉ የዳዊት አምላክ ሀይል ይሆንህል። የመጣውን የዘረኝነትና ዘር ቆጠራ መርዝ ራስህን ከወጋኸው ግን፣ አምላክን አታስፈልገኝም በራሴው እሞክረዋለሁ ካልክ ምርጫው ያንተ ነው። የሀጢያተኞችና ዘረኞች፣ ባጠቃላይ የጠማሞች መደምሰሻ ጥፋታቸውና ሞት እንደሆነ በፊታችን ገፁን አበርትቶ ፀንቶ ቆሚልና በግንባርህ ላይ የትኛውን ምልክት አድርገህ እንደምትጠብቀው ምርጫው ያንተ ይሆናል።

ለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።

# ለትግራይ ምድር ነዋሪዎች

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ አንዲቷም ፊፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም

አምላክ ሁሉን ህዝብ ሲያይ በእኩል አይን ነው። ራሳችንን በወገንተኝነት፣ በጎጥ፣ በሀብት፣ በምን በምን ብንከፋፍል እዚሁ ለኛው ይሆናል እንጂ፣ የእግዚአብሄርን አይን ልንጋርደው ወይም ተፅእኖ ልናሳድርበት ፈፅሞ አይቻለንም።

በሚመጣው ሁሉ በእግዚአብሄር ፍርድ የሚቀሰፈውም ሆነ የሚድነው እያንዳንዱ ግለሰብ የሚመዘነው ዘመን በማይለውጠው በነበረው በሚኖረው አምላካዊ ሚዛኑ ነው እንጂ የኛ የቡድን ወይ የዘር መለያ ወይ ጎራ በሱ አይን ፊት እንደሌለ ነው የሚሆነው። አንዴ በሱ ፊት ተመዝነን ከወደቅንና ለቅጣት ከተወሰነብን ምን አለም ቢሰለፍ፣ ምን ተአምር ቢሰራ የሚያድነን ከቶ ሊኖር አይችልም፤ ደግሞ በዛው መጠን በሱ ፊት አንዴ ተመዝነን ከተመረጥን ምን እሳት ቢዘንብ፣ የእልቂት መአበል መሀል ብንገባ ከቶ የሚነካን ሊኖር አይችልም።

ዛሬ ትግራይ ተብሎ በተከለለው ክፍል የሚኖሩ ጥንት ኢትዮጵያውያን፣ ለዘመናት ፀንተው ሳይናወፁ፣ ኢትዮጵያዊነት ከነሙሉ መገለጫውና በሙሉ መልኩ የተላበሱት፣ እግዚአብሄር በሚወደው የዋህነትና ፍቅር በእምነት ልጆቹ ሆነው የሚኖሩ፣ እሱም ለክፉ ጠላት አሳልፎ ሊሰጣቸው የማይፈቅድ ለኢትዮጵያዊነት መሰረትና ምሶሶ ከሆኑት ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው።

ከጥንት ኢትዮጵያ ልጆች ጋር “እንዲህ ያለ ኑሮ እንኑር” ብለው የሆነ

ማንነት ለመያዝ አቅደው የኖሩ ሳይሆን፣ በእምነት ከፈጣሪያቸው ተዋህደው በስሩ በፍቅርና እውነተኛ እምነት የኖሩበት ባህልና አኗኗራቸው ኢትዮጵያዊነት የሚል ስም የተሰጠላቸውና እስከዛሬም በሙሉ መልኩ ልንላበሰው የምንመኘውን ማንነት የሰጡን ህዝቦች መሀል ዋነኞቹ ናቸው።

ይህንን ማንነታቸውንም ተላብሰው ሳሉ ምንም ጠላት ቢነሳባቸው አምላካቸውም አሳልፎ ላይሰጣቸው፣ እነሱም ከቶ ላይወድቁ መሆናቸውን ከኛ በላይ የተረዱት የውጪ ጠላቶችና መንፈሳዊ አለሙን መኖር ከደውለት በስውር ሚመራቸው ዲያቢሎስ ቀድመው ይህንን ሀይላችንን አውልቀው ራቁታችንን የሚያስቀሩበትን መንገድ ሲፈልጉ ቆይተዋል። ያም ውጊያቸው ብዙ ትውልድ እየተሻገረ እጅግ የበዛ ዋጋ አስከፍሎናል።

በዚህም አላማቸው መሰረት በእምነቱ ፀንቶ ኢትዮጵያዊነቱን ጠብቆ የኖረው የትግራይ ምድር ኢትዮጵያዊ ቀድሞ ኢላማ ውስጥ ገብቶ ከባድ ዋጋን ከፍሏል። ባልታሰበ መንገድ ከሱ ጋር ፈፅሞ ሊሄድ የማይችል እግዚአብሄርን በጠላ መጤ ርዕዮት እንዲመረዝ ተደርጎ፣ ባላሰበው መልኩ ድንገት ከራሱ መሀል ነፃ አውጪ በሚል ስም በውጭ መንግስታት እርዳታና ስለላ መንገድ ጠረጋ በስውር በእጅጉ የሚደገፍ የነበረ ታጣቂ ቡድን ዘረኝነትና ጥቅመኝነት ክፉኛ ያወረው ማህበር ከመሀሉ ወጥቶ፣ ልክ ዛሬ በየቦታው እንደሚታዩት ዘረኛ ቡድኖች እንደተለመደው ብሶትን በመቀስቀስና ተጎጅነትን በመስበክ ቀላል ስነልቦናዊ መንገድ ፈጣን ተከታይና ወዳጅ አፍርቶ በዛ መልካም ህዝብ ላይ ነግሶና ሰልጥኖበት እስከዛሬ እየኖረ ይገኛል። ህዝቡንም ወይ ከአምላኩ፣ ወይ ከኑሮ ደረጃውና ሀብት፣ ወይ ከሀገሩ እንዳይሆን አድርጎ በአየርላይ ተንሳፎ ያቺ ምድር ሌላ ሰው የሌላት ይመስል በባዶ እኔነኝ መድሀኒታችሁ እያለ ነግሶበት ይገኛል።

ይህም ሳይሆን ጉዳቱ፣ ዋናው ነገሩ ከዛ ምድር ነዋሪ የክፍለዘመናት ታሪክ ፈፅሞ ውጪ በሆነ መልኩ ከአምላኩ የተለየ፣ በመሪነት

ራሳቸውን ያነገሱበት ሰወች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ስብከትና ምኞት፣ የሚዘረጉት ርዕዮትና አስተምህሮ፣ ባህል፣ እንዲሁም ተግባር ሁሉ ተተኪው ትውልድ ከልጅነቱ ጀምሮ ሰፊ/ሙሉ ጊዜውን ውሎውና አስተዳደጉ ከክቡራን ከአባቶቹ ይልቅ በሚገባባቸው የትምህርት ተቋማትና ሚዲያዎች አማካኝነት በማሳለፉ አዲስ እንደተመሰረተ ምድር ልጆች ኢአማኒነትን የተሰበከ፣ ካባቶቹ አምላኩን ያላወቀ፣ ያባቶቹን ሳይሆን በሌላ አዲስ ማንነት የተላበሰ፣ ስነልቦናው በክርስቶስ መቅረቢያ ፍቅርና አንድነት የተሰበከ ሳይሆን ዘር ለይቶ ፉክክርና ወገንተኝነት፣ ከሌሎች ክርስትያን ወንድሞች ጋር በጠላትነት የሚያስተያይ በሆነ መልኩ የተቀረፀ፣ የህይወት ምኞቱና ግቡም አባቶቹ ከምንም በላይ አክብረውና ዋጋ ሰጥተው ባቆዩለት ፀንተው ቢኖሩባቸው እንቁ የሆኑ የአምላክ ቃልኪዳኖች የተላበሰችዋን የቃልኪዳን ምድር ሳይሆን በግንጠላና ምድራዊ ምኞት ላይ የፀናች ሲንጋፖርነትን በቁሙ የሚቃዥ፣ መዳረሻው ከአምላኩ የራቀ የሆነ እንግዳ ትውልድ እንዲፈራ ሆኗል። ከመሀል ሻል ብሎ አምላክን የሚጠራው ቢኖር እንኳን ጠዋት ማታ በሚሰበከው ዘረኝነት ተመርዞ የክርስቶስ በመሀል መገኛ መልክ የሆነው ፍቅርን አጥፍቶ አምላኩ ከመሀሉ ፈፅሞ ሊገኝ እንዳይቻለው እንደዘረኝነትና ጥላቻ አፀያፊ ነገርን እንዲላበስ ይተጋሉ።

ይህም ተፅእኖ በገጠሩ ውስጥ በሚኖሩ የዋህን እንዲሁም ደግሞ እድሜያቸው ትልልቅ በሆኑት አማኝና ኢትዮጵያዊ አባቶችና እናቶች ላይ የደረሰ ሳይሆን፣ ከልጅነቱ ጀምሮ በህፃን አእምሮ በዚህ መልኩ ሲመረዝ ያደገ አሁን በወጣትነትና ከዛ በታች ባሉት፣ እግዚአብሄርን በማያውቁት ላይ ግን በተወሰነ መልኩ ተፅእኖው ያይላል።

በዚህም መልኩ ለዘመናት ያኖረውን ትጥቁን አምላኩን ጥሎ፣ ብረትና ባሩድን በማስጨበጥ፣ በየትኛውም ዘርፍ ለሚመጣ ጠላት ሁሉ ራቁቱን እንዲቆም ሊያደርጉት ጠላቶች ብዙ እየለፉ ኖረዋል።

የፈጣሪን መኖር ፈፅሞ ካልካዱ በስተቀረ፤ ያ ሀያል ፈጣሪ መኖሩ

እየታወቀ፣ ፈጣሪ በሰራው አለም ላይ ሆኖ ያለ ሀያሉ እርሱ አካልነት ማቀድና ያለ እሱ መነፅርነት ነገሮችን ማየት ምን ያህል የበታችነትና ውድቀት መሆኑ ላንተም የሚጠፋህ አይመስለኝም። ምን ጠላት ቢነሳ፣ ምን ክፉ ቀን ቢመጣ እግዚአብሄር አብሮ ካለ ሌላው ጠላትህ ምን ቢል፣ ምን ቢለፋ፣ ከቶ ምን ዋጋ ሊኖረው?

አንተም አምላክህን ከሁሉ ይልቅ አስቀድመህ መያዝህን አትዘንጋ፣ የመጀመርያ ሀሳብህም፣ ቅድሚያ የምታየውም የመጀመርያ መተማመኛህ እሱ ይሁን።

ፈፅመህ ዘር የቆጠረ፣ የሰውልጆችን በማይቀይሩት ማንነታቸው ካንተ የሚለይ ክፉ አደረጃጀትን በማንውኛም መንገድ አትቅረበው፣ ከልጆችህ አእምሮም ፈጥነህ አፅዳ። ከሌሎች ድሀ ኢትዮጵያውያን ጋር በአንድነት የአምላክህ ልጅ የምትሆንበትን፣ አምላክ ከመሀልህ የሚገኝበትን የአንድነት መንገድን ብቻ የምትከተል ሁን። በየትኛውም የመቃቋም ማህበርህም ሆነ ድርጅትህ ዘርን ቆጣሪ ሳይሆን የሰው ልጅን በቀና አስተሳሰቡ ብቻ አቃፊ ሁን፣ ድልም የሚከተልህ ያ ሲሆን ብቻ ነው። እውነት ግን ፃድቁ አቡነተክለሀይማኖትን ወይ ክርስቶስ ሰምራ እንኳን እንደው ሊቀላቀሉህ ቢመጡ አሻፈረኝ ልትላቸው ድረስ የሚነግርህን የዘር አደረጃጀትን ይዘህ ልትረክስ ቀላል ሆነልህ? ለመሆኑ ክርስቶስስ ቢመጣ የየትኛው ዘር ብለህ ልታስጠጋው ኖሯል? ትመልሰዋለህንጂ። እንዲህ ባለ ፍፁም እብደት መሆንንስ በየትኛውም መንገድ አርቀው፣ እኩይ ድንበሮችን አልፈህ በህብረት ከሌሎች የእግዚአብሄር ልጆች ጋር መዋሀድን ምርጫህ አድርገው። ከዛ ውጪ የሚመራህ ለፍፁም ጥፋትህና ለሞትህ ካልሆነ የትም መዳረሻ ሊኖረው በተፈጥሮው አይቻለውምና።

ከፊታችን የሚጠብቀን መከራና መቅሰፍት ሁሉ ድንገት የመጡና በኛ ባሰብናቸው መሹለክለኮች ልንወጣቸው የምንችላቸው ያጋጣሚ ክስተቶች ሳይሆኑ ከዘመናት በፊት ቀድመው የታወቁ፣ ክፉኛ የሰፋ

እልቂታቸውና ውጤታቸው የተፃፉ፣ ከኛ ይልቅ በአባቶችህ ከነዛሬ ሁኔታችን በድነብ የታወቁና ለሁላችንም ልጆቻቸው እንድንባቸው ዘንድ የተፃፉልን፣ ካለአምላካችን ፈቃድ ማንኛችንም ቢሆን በእጅስራችንና መፍጨርጨራችን አንዳችንም ልንሻገራቸው የማንችላቸው በመሆናቸው ነው።

እጅግ አስከፊ የሚያደርገውም፣ ከእውነተኛው የዘመናት ተግባሮቻችን በተቃራኒ መንፈሳዊ አይናችንን ከድነንና ዘግተን የምናደርጋቸው የለተለት መፍጨርጨሮች እያባሱብን፣ ከግርፋታችን ቀድመው ይበልጥ አምላካችንን አርቀው ራቁታችንን እያስቀሩን በመሆናቸው አንተም ከዚህ ራቅ።

አምላክህን ያዝ እንጂ፣ እሱ በመሀልህ እንዲገኝ ዘር መልክ ሳትለይ ፍቅርን አንግሰህ በየዋህነት ፈጣሪህ በመሀልህ እንዲገኝ ጋብዘው እንጂ፣ አምላክ አንተን ሊያጠፋ የመጣብህ ጠላት ዘሩ፣ ቀለሙ፣ ምድሩ ለሱ አይታየውም። የሰይጣን መንፈስ ግብር ይዞ የተነሳብህ ጠላትህ ካንተም መሀል ይሁን ከሌላው እኩል አንድላይ ከስሞ፣ ይጠፋል።

ራስህን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ሳትለይ ፍቅርና ክርስቶስ ብቻ የጋራ ማእከልህ ሊሆን ከሚችለው ከየትኛውም ጋር በአንድነት ቁም። በታሪክህ አሳፍሮህ የማያውቅ፣ እውነተኛው ትጥቅ የሆነውን እግዚአብሄር በመሀልህ እንዲገኝ ትጋ፣ ንብ በአበባ መአዛ እንዲገኝ ክርስቶስም እምነትና ጥንት ተላብሰኸው የኖርከው የዋህ ወንድማዊ ፍቅር ባለበት ነውና የሚገኘው ያንን ተላብሰህ በመሀልህ ጋብዘው።

**ከዘረኛ በላይ ክፉና እጅግ ወንድሙን የሚጠላ የዲያቢሎስ ፈረስ የለም። ዘረኛ በነገሰበት በትኛውም የሀገራችንም ሆነ የአለም ስፍራ ፍቅር ሰላም ተዋህዶ እምነት ምልክታቸውም አይኖሩም። ይህ የሚታየው ሀቅ ነው።**

ከየትኛውም ዘር ብትሆን፣ ምንም ምክንያትም ብትሰጠው ይህንን የተላበስከው ዕለት የደነበረ ፈረስ ላይ የታሰረን ገመድ በአንገትህ ፈቅደህ እንዳስገባኸው እወቀው። የእግዚአብሄርም ቁጣ ዘራቸውን ሳይጠይቅ ዘረኞችን ሁሉ ይመታል።

ጠላትህ ይሄ ነው የሚሉህን ፈፅመህ አትስማቸው። ደግፈህ አትሰለፍላቸው። በእግዚአብሄር መንገድ ብቻ ሆነህ ቁም፣ ከየትኛውም ቢሆን የዲያቢሎስ ፈረስ አንተን ጠላት አድርጎህ ቢነሳብህ ግን ከዚህ ፀድተህ አምላክህን እስከያዝከው ድረስ ፈጣሪ አምላክ ፍፁም ድልን ያለብስሀል።

አዲስ ማንነት፣ አዲስ ሀገር ቅዠት ውስጥ ገብተው ሊማግዱህ የሚርመሰመሱትን በሙሉ ለአምላክ ስጣቸው። እውነት ሊቀየር አይችልምና።

የትግራይ ምድር ነዋሪ ሁሉ ከኢትዮጵያዊነት ከፍያለም ከኢትዮጵያዊነት ዝቅም ያለ ማንነት አልነበረውም፣ የለውም።

ቆይ ግን ለመሆኑ፣ ማንነት ማለት ራሱ ምን ማለት ነው? እንዲሁ እንደፈለጉ በየጊዜው የሚቀያየር ነገር ነውንዴ? ትላንት የነበርከው ዛሬም የሆንከው ነገም የምትሆነው ፅኑ አንተነትህ ነውንጂ? ካልሆነማ እንዴት ነው ራሱ ማንነት የሚሆነው?

የትግራይ ምድር ነዋሪ ከኢዛና ከ ሳይዛና ቡሀላም ከአብርሀ ወ አፅብሀ፣ የተለየ ማንነት አለውን? ከቅዱስ ያሬድ የተለየ ማንነት አለውን? ከ አቡነ አረጋዊ የተለየ ማንነት አለውን? ማንስ ተነስቶ ይህንን አጥፍቶ አዲስ ሌላ የሚያለብሰው? እንደው ከነዚህ የከበረ ማንነትስ እንዴት ብሎ ይሆን ሊሰጣቸው የሚሰብከው? ከነዚህና

ሌሎችም ታላላቅ የምድራችን ምሶሶዎች የራቀ ማንነት የለውም።

ይህንንም ስለሚያውቁት ይመስላል በአዲሱ ትውልድ ያልበሰለ ልቦና ላይ ያተኮሩት፣ ለአማኙም ህዝብ መደለያ ብለው ብለው የፈጠሩት፣ ለራሳቸው የማያምኑበትን እምነት እንደ ፕሮፓጋንዳ ለመጠቀም፣ "ትግራይ ናት ኢትዮጵያ የምትባለው፣ ይህቺ ምድር ናት ባለቃልኪዳኗ...፣ ተገንጥለን እኛ ነን ባለተስፋዋ ምድር..." የሚል በእሳት የመጫወት አይነት ከፉ መንገድን ከመጓዝ ወደኋላ አላሉም።

የዚህ አይነት እምነት የጎደለው የክፋት ዘመቻ አራማጆችን ሞታቸው ከደጃቸው ፊት ስለቆመ ለነሱ ጆሮ ቢሰጧቸውም አይጠቀሙም። ጣራቸው ቢበዛ እንጂ እነዛ ሁሉ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ያፈለቀችን ምድር ሳያካትቱ ቆርጠው ምን አይነት ኢትዮጵያ ይሆን ሊፈጥሩ የሚናገሩት? የኢትዮጵያ ምድር የተባረከችው በቅዱስ ዑራኤል አይደለምን? ክርስቶስ በስደት ጊዜ ድንግል ማርያምን ርስት ሀገርሽ ብሎ አዙሮ ያሳያት ምድር አይደለችምንዴ ኢትዮጵያ ማለት? ቅዱስ ዑራኤል ይህ ምድር የቅዱሳን መፍለቂያ ይሆናል ብሎ ትንቢት የተናገረባቸው ቦታዎች ካልያዘች ምኗ ነው ኢትዮጵያ? ቅድስት ማርያም በመከራ በስደት ጊዜ ያረፈችባቸው፣ የአስራት ቦታዎቿን ያልያዘች ስለየትኛዋ የቃልኪዳኗ ኢትዮጵያ ይሆን የሚያወሩት? ተክለሀይማኖት በየአቅጣጫው ዞረው ማስተማራቸው ምን ይሆን ትርጉሙ? በደቡብ ከወላይታ ባሻገር ሩቅ አልፈው የሰበኩባቸው ቦታዎችን ያልያዘች ኢትዮጵያ የትኛዋ ነች? አክሱም ፅዮንን፣ ደብረሊባኖስን፣ ላሊበላን፣ ዋልድባን ያልያዘች አንድ ኢትዮጵያ ስለየትኛዋ ኢትዮጵያ ነው የሚያወሩት?

አብርሀ አፅብሀ በሀገሬ እምነት ላቅና ብለው ቢነሱ በገዛ ምድራቸው በጎጥም መርጡለማርያምን አላቆሙም? አሪትን ከሀዲስ አስማምተው፣ እንደንጉስ ሶሎሞን እንደዳዊት አምላክ በህልምና ራእይ እየተገለጠላቸው በሀገራቸው እየተዟዟሩ የእግዚአብሄርን መቅደስ፣ ገዳማቱን አልመሰረቱም? እነሱ ሀገሬ ብለው የለፉበትን

ምድር ርስታቸውን ለማን ትተኸው ነው አንተ ሌላ ማንነትን የምትላበሰው? ያባቶችህን ምድር የሚጠየፍና ሌላ የሚል በአዲስ ማንነት ሰፍቶ ሸሽቶ ጠባብ ቅፅር ይዞ ሊያጠብህ የሚኮላተፍ ክፉ ዘረኛ የደከመ መንፈስ እንዴት ልትቀበለው ይቻልሀል?

ሁሉ በፍቅር ተቀብለውት በኢትዮጵያ ምድር ከአፅናፍ እስከአፅናፍ ዜማው እንደጊጊዮን ዥረት ዘመን ሳይሽረው የሚፈሰው የአክሱሙ ጥኡመ ዜማ ቅዱስ ያሬድ ማንነት አይደለምንዴ ያንተ እውነተኛ ማንነት? የአክሱሙን ንጉስ አሰናብቱኝ ብሎ ሙሉ እድሜውን ሊያሳልፍባት፣ ለድጓው መድረሻ በምኞት የመረጥኳት ሀገሬ ብሎ የሄደባት፣ እንዳትከለክለኝ ማልልኝ ብሎ ንጉሱን አስምሎ ጥሎ የሄደባት ርስቱ ጣና አይደለችምንዴ? ከሱ የተለየ ምን ማንነት ይዘህ ይህችን ምድር የኔ አይደለችም ልትላት ይቻልሀል?

በመላው ምድሯ በኢትዮጵያዊነትና በእምነት ከሚኖሩ፣ ያባቶቻችን ልጆች ሆነው ባንድነት ክርስቶስን የሚያፈቅሩ እንቁ ወንድሞችህ ጋር በምንህ ትለያለህ? ከመሀልህ ተነስቶ በስምህ ተንኩሶ አሁንም ጠላት አድርጎ የሚስልብህን ቡድን ተሻግረህ በማህበር ከክርስቶስ ወንድሞችህ ጋር በአንድነት ቁም። በአንድነት ከሚመጣው ከፋትና ጥፋት እንዲሁም መከራ ሁሉ ያድንህ ዘንድ በመሀልም ይገኝ ዘንድ በፍቅር ሆነህ በአንድነት በፀሎት ተግተህ አምላክን ተማፀን።

በትግል በወደቁ የትግራይ ምድር ታጋዮች ስም ብሶት በመቀስቀስና ዘወትር ደጋግሞ በማላዘን ልብህንና ትውልድህን ዘላለም ልግዛህ የሚልህን ክፉ ዘረኛ ቡድን እጅህን አትስጠው። ከጥንት ወንድምህ የኢትዮጵያ ልጅ እንዲለይህ አትፍቀድለት። መሞቱንማ ማንስ ያልሞተው አለ? አንተን በብሶት አሳቦ ሊገዛህ ተነሳብህ እንጂ።

ዛሬ የጎንደር ገንዘብ የውጪዎች እስኪመስል ድረስ በደርግ ግፍ በውጪ በስደትና ሞት ተገፍቶ የተበተነው፣ “የዛሬን ማርልኝ የነገን አልወልድም” ተብሎ እስኪለቀስ ወጣቱን ሲጨርስ አልኖረምን?

ባድመ ተወረረች፣ የሰሜን ኢትዮጵያውያን ጠላት ተነሳባቸው ሲባል ሀገሬ ብሎ፣ ወንድሜ ብሎ፣ ለገበያ እንደወጣ ጭምር ከቤቱ ሳይመለስ በዛው ሄዶ የወደቀው የአማራ ምድር ኢትዮጵያዊ አልነበርምን?

በደቡብ በምስራቅ ጠላት ኢትዮጵያውያንን እየገደለ ኦጋዴንን ያዘ ቢባል፣ ያለመደበኛ ቅጥር ተነስቶ የዘመተ ነፍጠኛ የገበሬ ልጅና ሚሊሻ፣ በዛውም ላይመለስ የወደቀ ማን መታሰቢያ እንኳን አደረገለት?

ወገንህን ብቻ ሟች አድርጎ ብሶት እየቀሰቀሰ በሞትህ ተንተርሶ ለዳግም ሞት ሲጋብዝህ፣ አንዳች ገድ የማይሰጠው ነፍስህን እቃው ሊያደርግ ሲያሴር አንተም አብረኸው አትደግፈው። እድል አያገኘምንጂ፣ ከቤትህ ግርግዳ ላይ የተለጠፈው ጭቃ እንኳን ከጥንት ጠላት በየቦታው በመጣ ቁጥር፣ ድንበር በተገፋ ቁጥር እየሄደ ሲሞት የነበረው የስንት የአማራ ምድር ኢትዮጵያዊ ደምና አጥንት አርሶት እንደኖረ በመሰከረ ነበር። የጎንደርንም አፈር ዘግነው ቢጠይቁት ደርቡሽ ሲነሳባት ሄዶ የተሰዋ የስንት የትግራይ ምድር ኢትዮጵያዊ ደም እንደያዘ በመሰከረ ነበር። በአድዋ ያለን ዛፍ ችለህ ብትጠይቀው ጠላት ትግራይ ምድርን መንካቱ ሲሰማ ልጆቻቸውን ጥለው ለወንድማቸው የመጡ የስንት የአማራና ሌሎችም ወገኖች አጥንት በስሩ እየዳበሰ እንደሆነ በነገረህ ነበር።

ሌላው ያልወደቀ ይመስል ከቶ ያንተን ብቻ ለይቶ በገዛ ደምህ ባሪያው እንዲያደርግህ፣ ከእግዚአብሄር እንዲያርቅህ ስለምን ትፈቅድለታለህ? ያለፈው ደም ሳይደርቅ ለአዲስ እልቂት በዘረኝነትና በክፋት ሲያቀልምህ እሺ አንዳትለው፣ በታጋይነት ጀብዱ ትእቢት፣ በዘረኝነት ተሞልተው አምላክን አርቀው ክፉ መንፈስን የተላበሱ ክፉዎችን ተዋቸው፣ ልጆችህን መልስ።

በአንተም ሆነ በሌላውም በኩል የአማራም ሆነ የኦሮሞ የየትኛውም ዘረኞች እንዲሁ በአንድላይ ይከስማሉ። በፍቅርና ኢትዮጵያዊነት ሆነህ አምላክህን ብቻ ያዝ።

ካንተም መሀል ይሁን ከነሱ ዘርን መርጠው ፍቅርን አጠልሽተው የተነሱ ሁሉ በአንድነት ያልቃሉ። ክፉ የሆነ ከወንድማማቾች መሀል አንዱን ሌላ አንዱን ዘሬ በማለት የተለየ ጥቅመኝነትን የሚሰብኩ ሁሉ የያዙት ዘር ከየትኛው ይሁን ከየትኛው ያ በአምላክ ፊት አይታይም፣ በአንድነት ይጠፋሉ። ኢትዮጵያዊነቱን ተፀይፎ የቆመ በአንድላይ ይወድቃል። አንተም በቅዱሳን ቃልኪዳን የቆመውን ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ ላይ ጠላት አድርገህ ራስህን አታስቀምጥ፣ በታሪክ ጥሩ መጨረሻ ኖሮት አያውቅምና።

ዘረኞች ዘሬ ብለው ከያዙት ዘር ሳይሆን መዝሙረኛው "ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይመራሉ" ብሎ የተናገረላቸው ዥንጉርጉር የፍቅር ህዝብ ተለይተው ምንም ሳይሆኑ በእሳት ወላፈን መሀል ቆመው ይታያሉ። ሌላው አልቆ እነሱ ይቆማሉ። ቀኑ ቅርብ ነውና ከነሱ መሀል ራስህን አትጣው። ልጆችህንም አስተምራቸው። የመፅሀፍ ቅዱሱ ቃል ወይ እውነት ወይ ሀሰት ነው። ከሁለቱ ውጪ የለውም። ሀሰት ወይ እውነት እንደምትል እምነትህን አንተው ታውቀዋለህ። ይሄም የዳዊት ትንቢታዊ ቃል ሳይፈፀም የሚቀር አይሆንም።

ጥንት በክፋት ተጠምደው የነበሩ የኔፍሊም ልጆች የነቢዩን ማስጠንቀቂያና የንሰሀ ጥሪ ችላ ብለው በርኩሰታቸው ቢቀጥሉ "ቅዱስ ገብርኤል ሰይፉን ሰጣቸው" ተብሎ እንደተፃፈና እርስበርስም ፍፁም ቅድቀት እንደተበላሉ ሁሉ፣ ጎራ ጎራ ይዘው በጥላቻም ሆነ በራስወዳድነት የተሰለፉ የዛሬ ዘረኞች ከየትኛውም ዘር ይሁኑ እርስበርሳቸው እንዲሁ ፍፁም መተላለቅን ይቋደሳሉ፣ የእሳት

ሰይፉን ይዘው መራራውን የመከራ ሞት ፀዋ አንዱ ለሌላው ይጋታሉ።
በንግርትም ጭምር በሱ ዘመን እንኳን የሰው የእንጨት ጠማማ አይጠብቀውም እንደተባለው ክፉ ዘረኞችም ሆኑ የሀጢያት ሰወች ከትንሳኤው በፊት በሚበላው እሳት ከስመው ይቀራሉ።

“ማንነት” ማለት ምን ማለት ነው? እንዲሁ እንደፈለጉ በየጊዜው የሚቀያየር ነገር ነውንዴ? ትላንት የሆንከው ዛሬም የሆነው ነገም የምትሆነው ፅኑ ነገር ነውንጂ? ካልሆነማ እንዴት ማንነት ይሆናል?

እግዚአብሄርን የረሱ ስልጣን እጅግ ያፈቀሩ ታጣቂዎች በቅድስና እምነትና በመልካም ሰብአዊ ፍቅር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መሀል በደረቅ መሬት አጥብበው ከፍለው “ትግራይ ክልል” የተባልክ መሆንህን አትርሳ! የትግራይ ክልል ኢትዮጵያዊ መሆንህን አትርሳ ! ትግራይ ክልል ተብለው ከኢትዮጵያውያን መሀል የተከለሉ ኢትዮጵያውያን!

# የትግራይ ክልል ኢትዮጵያዊ !!

ነኝ ብለህ ልትናገረው የሚገባህ ቀድሞን የነበርከው ያ ነው ያንተ መጠሪያ። ከዚያ አታጥብበው። ትግራይ ምድር ላይ ቤቱን የሰራ ኢትዮጵያዊ፣ ለልጁ “ተመልከት ያንተን ንብረት” ብሎ የላሊበላን ውቅር አብያተክርስትያናት የሚጠቁም፣ “ተመልከት ያንተን ሀብት“ ብሎ ጣናን፣ አባይን የሚጠቁም፣ ተመልከት የርስትህን ጫፍ” ብሎ ከካርታ ላይ ኦጋዴንን የሚያሳይ፣ እሱራሱ እንዲህ ተብሎ ከአባቶቹ የተረከበውን እንዳባቶቹ ታግሎ ጠብቆ ለሚወደው ልጁ ሙሉ ሙብትና ባለቤትነትን የሚሰጥ ነህ። አባቶቹ ደማቸውን ከፍለው የገዙትለትን ጥሎ የሚሸሽ ሳይሆን ወደፊትም ኢትዮጵያን የሚያድነው ኢትዮጵያዊ እንዳትሆን ከቶ ምን ያንስሀል?

አንተ ራስህን ሁን፣ ለአምላክ ክልሉ ተከፍሎ አይታየውምና በሌላም ያሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች፣ ባንተም መሀል ያሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች በሙሉ በዚህ ተለይተው ይጠፋሉ። የትኛውንም ዘር ይልበሱ፣ በክፋት ለይተው ያንን አግንነው ለአቃፊ ክርስቶሳዊና ወንድማማቻዊ ፍቅር ኢትዮጵያዊነት ጠንቅ የሆኑት በሙሉ ይፈረድባቸዋል ለጥላቻና ጥፋት የጋለባቸውም አጋንንት የዚኛውን ባሪያውን ሙት ትቶ ለአላማው ሌላ ፍለጋ ይሄዳል።

አንተ የነበርከውን መጀመርያም ያንተ ማንነትህ የሆነውን ና ወንድሙን በከንቱ ለይቶ የማይጠላ ክርስቶስ በመሀል ለመገኛነት የሚመርጠውን በዥንጉርጉርነት መሀል ክርስቶስ/ፍቅር ያስተሳሰረው ኢትዮጵያዊነትን ተላበስ። በንሰሀና ፀሎት ከአምላክህ ተግተህ ቅረብ። ጠላቶችህም በሙሉ በፅኑ ይወድቃሉ። እውነት የአምላክ እግዚአብሄርን መኖር ያመንክ ከሆንክ እሱ የወደደውን የዳዊት ስብእና ተላበስ፣ የአባቶችህ አምላክን ይዘህ በእሳት ማእበል ውስጥ ከፀጉርህ አንዲንም ሳይነካት ተጠብቀህ ኑር። መመኪያህን በስጋ ጀግንነት፣ በመሳሪያ ታጣቂነት፣ በወገን ሳይሆን በእግዚአብሄር አድርግ።

የተተነበየው የሚመጣው መከራና እልቂት አሻፈረኝ ብለው በተነሱ ዘረኞች መሀል እንዲቀር፣ የነሱ ጉዳይ ይሆን ዘንድ፣ አንተ ራስህን አንፃ አድን። ሀገርን ለማዳን በከንቱ ምድራዊ ፖለቲካ ልፊያ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሄርና በሱ መንገድ ላይ ትጋ። እውነትም አለና፣ እንደ ልጁ፣ እጄን ያዘኝ በለው። ድህነት ከሀጢያት ለነፁት እንጂ የሆነ ፖለቲካ አቋም ለያዙት አይደለምና፣ በንሰሀ ታጥበህ ራስህን ከሀጢያት ጠብቀህ ዘወትር ድህነቱንና ይቅርታውን በመለመን ተዘጋጅተህ ኑር። ስለዘራቸው፣ ስለ ፖለቲካቸው ሳይሆን ስለ ፍቅርና እግዚአብሄር ልጅነታቸው ከሚተርፉ ጥቂቶች መሀከል ሁን።
ለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።

# ለኦሮሞ ምድር ህዝብ

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ አንዲቷም ፈፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

አምላክ ሁሉን ህዝብ ሲያይ በእኩል አይን ነው። ራሳችንን በወገንተኝነት፣ በጎጥ፣ በሀብት፣ በምን በምን ብንከፋፍል እዚሁ ለኛው ይሆናል እንጂ፣ የእግዚአብሄርን አይን ልንጋርደው ወይም ተፅእኖ ልናሳድርበት ፈፅሞ አይቻለንም።

በሚመጣው ሁሉ በእግዚአብሄር ፍርድ የሚቀሰፈውም ሆነ የሚድነው እያንዳንዱ ግለሰብ የሚመዘነው ዘመን በማይለውጠው በነበረው በሚኖረው አምላካዊ ሚዛኑ ነው እንጂ የኛ የቡድን ወይ የዘር መለያ ወይ ጎራ በሱ አይን ፊት እንደሌለ ነው የሚሆነው። አንዴ በሱ ፊት ተመዝነን ከወደቅንና ለቅጣት ከተወሰነብን ምን አለም ቢሰለፍ፣ ምን ተአምር ቢሰራ የሚያድነን ከቶ ሊኖር አይችልም፤ ደግሞ በዛው መጠን በሱ ፊት አንዴ ተመዝነን ከተመረጥን ምን እሳት ቢዘንብ፣ የእልቂት መአበል መሀል ብንገባ ከቶ የሚነካን ሊኖር አይችልም።

እውነተኛው ኦሮሞ አባቶችህ ማንነት በየዋህነት፣ ሰው ወዳድነት እንዲሁም ቸርነት የሚታወቅ ሆኖ ሳለ፣ አይደለም ለሰው ከተፈጥሮ ጋር እንኳን ተስማምቶ ተዋህዶ የሚኖር የብልህ ህዝብና ባህል ማንነት ያላቸው ሲሆኑ፣ ይህም ዛሬም ድረስ በገጠሩ ጠልቀው ሲገቡ በግልፅ የሚታይ እውነተኛው የኦሮምያ ክልል ህዝብ ማንነት ያ ሆኖ ሳለ፣ ዛሬ ፈፅሞ መጤና ክፉ በሆነ ጨርሶም ማንነትህና ያባቶችህ ባህልና ስነልቦናም የሚጠየፈውን አፀያፊ ሀሳብና ተግባር አይን ያወጣ ገፊነት፣ ራስ ወዳድነት እንዲሁም ጥላቻን አንግበው በፍፁም አዲስ ማንነት በስምህ ይዘው ካንተ የወጡ በመሆናቸውና ላንተ ማደግ ነው የምንሰራው በማለታቸው ብቻ እንድትቀበላቸው

ሊነግሱብህ የሚሯሯጡ ዘረኛ ቡድኖች በስፋት በኦሮምያ ክልል በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ።

ይህም የተፈጠረው ክፉውና ከፋፋይ ለማንም ያልበጀው የኢትዮጵያ አስተዳደር ዘመን ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲያድጉ በኦሮሞ አባቶቻቸው ትውፊትና ባህል እንዲሁም ማህበረሰባዊ አስተሳሰብና ስነልቦና ተቀርፀው ሊያድጉ የቻሉ ሳይሆን ከልጅነት ጀምሮ በሚውሉበትና በሚቀርፃቸው ትምህርትቤት፣ በሚከታተሏቸው ሚዲያዎች በሚለቀቁ መርዛማ የመከፋፈልና ዘረኝነት፣ የመጠላላትና መለያየት ሰበካ፣ ወላጆቻቸው ምንም ማድረግ ሳይችሉ ባልፈለጉት ባላሰቡት መንገድ ተቀርፀው፣ የማያባራ አመፅና የከንቱዎች የስልጣን መሳሪያ እንዲሆኑ ባስገደዳቸው ትርክትና ስርአት ውስጥ የተቀረፁ በመሆናቸው ነው። ይህም በኦሮሞነት ስም ከእውነተኛው የኦሮሞ ማንነትና አስተሳሰብ ወጥተው ባልበሰለና ፍሬ በማያፈራ የግልፍተኝነትና ስሜት መንገድ ለእልቂት ህዝቡን እያሰለፉ ይገኛሉ።

ከምንም በላይ የሀይማኖትም ሆነ ባህል አንዳችም ምልክት በልባቸው ሳይኖር ሁሉን ነገር በስጋ እቅድ፣ በሮሮና ብሶት ወይ በጉልበት፣ በዘር በጎራ በማሰብ፣ ስሜትን ብቻ ማእከል ባደረገ አካሄድ ወጣቱንም ሆነ ሰፊውን ህዝብ በማንቀሳቀስ እየሄዱ ይገኛሉ። የስሜት ማእበል በመሆኑ ለነሱ ይመስላቸዋል እንጂ ከድክመት የወረደ የድክመት መንገድ ነው።

አይደለም ለህዝቡ ያንን ሁሉ የምኞት ጫፍ ብልፅግናን ከባዱን ሰላም፣ ደስታ ገነትን ሊያመጡለት ሀይልና ችሎታ ሊኖራቸው፣ ደጋፊ እንኳን ለማሰባሰብ የሰውልጅ ወገንተኝነት ተፈጥሮን ነው የሚጋልቡት።

የወገንተኝነት ተፈጥሮ ማለት፣ ልክ በሰፈር አካባቢ ወይ በከተማ የምንተያየው ግን ሰላም ብለነው የማናውቀውን ሰው ሩቅ በሆነ ቦታ ወይ ከሀገር ውጪ በሌሎች መሀል ስናየው ከዘመድ በላይ በደስታ

እንደምንቀራረበው፣ ይሄም አብዛኞቻችንን አጋጥሞን ሀይሉን እንደምናውቀው፣ ወይ የሆነ በቴሌቪዥን የምንሰማው ዘፈን ላይ የሰፈር ወይ የከተማችን ስም ከተጠራ እንዲሁ መደሰትና መነሳሳት እንደሚያድርብን እነዚህም ፖለቲከኞች በዘራቸው እነዚህን መሰል ሀያል የተፈጥሮ ስሜት ላይ ተንጠላጥለው ለድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርገው ሀሳብና ፖሊሲያቸው ተሰምቶ ሳይታወቅ እንዲሁ በድጋፍ እንዲጎርፉ አድርጓቸዋል። ይህም የድክመታቸው ጫፍ ነው።

ፍፁም ደካማ ይሁኑ እንጂ፣ ስራ ቢሉት ምንም የማይሰራ የ 4 አመት ህፃን እንኳን ቤትውስጥ ቢተዉት ሁሉን አጨቀያይቶ፣ አተረማምሶ፣ ሁሉን ውድ እቃ ሰባብሮ ማበለሻሸት እንደማይቸግረው ሁሉ እንዲሁ ለጥፋት የሚያንስ የለምና እነዚህም ዘረኛ ፖለቲከኞች ጥፋት ለመፈፀም ግን ከምንም በላይ ሀይልን የተሞሉ ናቸው። ለኦሮሞ ህዝብም ዘላቂ መልካም ሊያደርጉለት ፈፅሞ ባይቻላቸውም ለሌሎችም የሚተርፍ ከፍተኛ ጉስቁልናንና መከራን ግን ሊያመጡለት ይቻላቸዋል።

እውነት የኦሮሞ አባቶች አላዋቂ ወይ ሞኝ ሆነው ነውን ደግነትን፣ አቃፊነትን፣ ከሰው ከተፈጥሮው መስማማትን፣ የዋህነትን ከራስ በላይ ለሌላው አሳቢነትን ተላብሰው ለዘመናት የኖሩት? በበሰለ ባህልና ማህበረሰባዊ ጥበብ አዳብረው የገነቡት ዘመን የፈጀ ሀብታቸው ነው እንጂ።
ለምሳሌ አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ ሌላ ቤትም ሆነ አካባቢ የማያውቅ ደሀ ነዋሪ የሆነ የሰው ፍጡር በላይ በዛቦታ ላይ የበላይነት፣ ከሱ የበለጠ ጥቅማጥቅም፣ ቀዳሚነት፣ ንግስና በሰፈሩና በከተማው ይገባኛል እያለ ከጅማ፣ ከወለጋ ዘሩን ብቻ ተማምኖ የሌላውን እየተጋፋ በራስ ወዳድነት፣ አልጠግብ ባይ ጥቅመኝነት፣ በተገኘው መንገድ ሁሉ ተጋፍቶ ራስን ለመጥቀም እያሉ መጋፋትን የሚያከል ክፉ፣ ከባህል ውጪ፣ ከምግባር ውጪነት ከቶ ሊኖር ይችላልን? እንዲህ ያለ ከባህልም ከፈጣሪም የሚለይ ስብእናን መላበስ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?

ይህ የራስወዳድ ብልጣብልጥነት፣ ጊዜው ከፈቀደ ከመዝረፍ ከመጋፋት አለመመለስን የኦሮሞ አባቶች በባህላቸው ሳያውቁት ስለቀሩ ነው ያልተላበሱት? እውነተኛ ውጤቱን ስለሚያውቁትና የተሻለውን መንገድ ስለሚያውቁት ነው እንጂ።

በዚህ መልኩ ተሄዶ ምን አይነት መልካም ነገር ይሆን ለኦሮሞ ህዝብ የሚያስገኙት? ለሌላውም የሚተርፍ ውድቀት መከራን ነውንጂ።

ሰፊ ግዛትን? ወይ የአዲስ አበባ ከተማን? ወይ ሀብት? ዴሞክራሲ ነፃነት? ብልፅግናን? ገነትን? እነዚህን አንዱንም ሳይሆን በትንኮሳና ጥላቻ መርዝ መርጨት፣ ከሌላውም ጋር ትርጉም አልባ ደም መፋሰስን ነውንጂ። ይህ ዝምብሎ ፍረጃ አይምሰልህ ያካሄዳቸውን መንገድ ጫፍ ነው የምነግርህና እውነቱን ተመልከተው። ፈልገውትም ይሁን ሳይፈልጉት፣ የያዙት መንገድ መዳረሻ ጫፉ የታወቀ ነውና እውነቱን ልትመለከተው ይገባሀል።

እንደው መሰናከላቸው ሁሉ ጠፍቶላቸው ምኞታቸው ቢሳካ እንኳን ለሀሳባቸው እንዳችም እውነተኛ ዘላዊ መልካም ነገር የማያስገኝ ያልበሰለ ልፊያ ውስጥ ነው ያሉት።

ለነገሩ እነሱም የጀመሩት አካሄድና መንገድ ከኢትዮጵያ የሚለያቸው መሆኑንና ይህም የሚዘጋጁበት መሆኑን ያውቁታል። መዘዙንና ውስብስብነቱን፣ የውጤቱም ጭቃነት፣ የመንገዱንም ምናባዊነት ላንተ አይነግሩህም ወይም አይገነዘቡትም እንጂ። አንድ ቀን በህዝቡ መሀል ያልኖሩበት ችግር ሸሽተው በውጪ የኖሩት በሀገሩ ያለውን ሁኔታ ቀን በቀን አብረው እየኖሩበት ያልተረዱትን አፍ ያገኙ ዘረኛ ቀስቃሾች የሚያራምዱት ሀሳብና ከብሶት ጋር በደካማ መንገድ የሚነዙት ወሬ እንጂ በተግባር ሊሆን የማይችል የውድቀት ሀሳብ መሆኑ ግልፅ ነው።

የኦሮሞ ክልል ህዝብ ከመሀሉ የወጡ በስልጣን ያሉ በሀገራቸው ምድር ታሽተው በህዝቡ መሀል ኖረው በስልጣንና አመሩን መንገድ ኖረውበት ተረድተውት አንድነት ይሻለናል ብለው የሚናገሩትንማ ሊሰማቸው ፈቃደኛ አልሆነም።እውነታውን ውስጥ ሆነው የተረዱት ግን ከምንም በላይ እነሱ ናቸው። ከኦሮሞ ክልል ህዝብ ይልቅ ሌላውን እናስቀድም ብለው፣ ወይ ሌላው ህዝብ ከኦሮሞ ክልል ህዝብ በላይ እንዲወደን እንፈልጋለን ብለው አይደለም የዘመኑ ዘረኛ ጥቅመኛ ፖለቲከኞች የሚሰብኩትን የሚለያይ ነገርን አብዝተው የሚጠየፉት። ውጪ ሳይኖሩበት ከሚጮሁት ይልቅ ኖረውበት እውነታውን ለህዝባቸውም ጭምር የሚበጀውን መንገድ ስለሚያውቁት ነውኝ።

ሌሎችን አስቀይሞ ተጋፍቶ፣ ከሌሎች አጋጭቶ በግልፅ ወደመለያየት የሚመሩ ተግባራትን በትእቢት የሚሰብኩት እነዚህ የኦሮሞ ምድር ዘረኛ ፖለቲከኞች የሚንደረደሩበት የመለያየት ድርጊት ውጤቱ ግልፅ ነው። በራስወዳድነትና እውር ዘረኝነት ድንበራቸውን ገፍተው በአዲስ አበባ፣ በሰሜን እስከወሎ፣ ከደቡብ፣ ከሱማሌ ግማሽ፣ አእምሮ ያጣ ምኞታዊ ጉዟቸውና ሊያስፈፅሙም የተነሱበት መንገድ፣ እብሪት፣ የጉልበት ግድያ ትጥቅ፣ ትውልድንና ህፃናትን ጨምሮ በዚህ ዘረኝነት ስካር መርዞ መሳሪያ ማሰልጠን ሁሉ አሁን የሚታይ ተግባራቸው ነውና፣ አንተም የማይቀር እውነት የሆነው ውጤታቸውን አስቀድመህ ላታውቀው ይገባሀል።

መሬት ላይ ባለው እውነት፣ በተጠላለፈ በተወሳሰበ ድንበርና ወሰን፣ ገና ያልተሰመሩ ሰው ያልሰፈረባቸው ገደላገደሎች፣ ሜዳዎች ይህ ሁሉ ባለበት ሳይሆን ከዚህ በፊት በግልፅ የተሰመረ አንዲት መስመር ድንበር ባላት ኤርትራ ግጭት እንኳን ከሁለት መቶሺዎች በላይ በአጭር ቀናት ፀጥ ያሉበት ዘግናኝ እልቂት የሚታወስ ነው።

እጅግ በተወሳሰበው በኦሮሚያ ክልል ድንበር ዙሪያ ያውም ከአራቱም አቅጣጫ በሚነሳ ግፊያ ደግሞ ምን ያህል ህዝብ በከንቱ እንደሚረግፍ ለማሰብ የሚያስፈራ ግን ከወዲሁ ግልፅ ሆኖ የሚታይ ዘግናኝ እውነታ ነው። ወደዚህ ግልፅ ሆኖ ወደተቀመጠ ውድቀት ህዝቡን ይዘው የሚንደረደሩት የኦሮሞ ዘረኛ ፖለቲከኞች ያለእውቀትና አቅማቸው ባገኙት ዘር ላይ የተመሰረተ የባዶ ድጋፍ ሰፊውን ህዝብ በእውር አይናቸው ከገደል ሊወረውሩት አይሳናቸውም። ይህን እልቂት ሌሎቹስ በዙሪያው ያሉት የተለያዩ ክልሎች ሰባት ክልሎች የሚቹን ቁጥር ሲከፋፈል የተወሰነ የተወሰነ ይደርሳቸዋል። የሌላኛው ወገን እልቂት ግን ሙሉውን ለአንድ ቡድን የሚቀር ሸክምና ውድቀት ይሆናል።

ሰው ምን ምክንያት ሆኖት ወደዚህ ይሄዳል? በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት በደል ያልደረሰበት የለም። ሁሉም ተጎጂ ነው። ምናልባት ጥንት ያሉት ተበዳድለው፣ ተጎዳድተው፣ ተጨካክነው ቢሆን እንኳን ዛሬ ያለው ትውልድና ህዝብ እንደሆነ በተመሳሳይ ዘመን የተወለደ፣ እኩል ከተወለደ ጀምሮ ሁሉን ግፍ ሁሉን ችግር ሁሉን ደስታ እንዲሁ አብሮ እኩል ያየ፣ ተመሳሳይ መሪዎች የቆሙበት ያደኸዩት፣ ተመሳሳይ ችግር ያለበት የዘመን ወንድማማች ተመሳሳይ የተሻለ እድል ያለው እኩል አዲስ ትውልድ ነው።

ሮሮና ብሶት ጋላቢ ጥቂት ጨለማዎች ካለፈው ጨለማ ቀድተው እያጠመቁ ላያድኑት ይለያዩታል እንጂ ዛሬ ላይ ከትውልዱ እኩል ያልተበደለ፣ እኩል ያልደኸየ ከቶም የለም። ላንዱ የሚመጣ መፍትሄ ለሌላውም የሚሆነው፣ ለሌላው የተገኘው መድሀኒት ለዚህኛውም እንዲሁ መድሀኒቱ የሚሆነው። እንጂ አንዱ ተለይቶ የሚፈልገው ሌላው ተለይቶ ሌላው የማይፈልገው በሀገራችን ባሉ ዘሮችና ክልሎች ከቶ የለም። ይህም ላይኖር ይህን እኩል ከደኸየው መሀል ራስን እየለዩ መሯሯጡ ትርምስና እልቂት እንጂ ከቶ አንዳችም ትርፍ አይኖረውም። አምላክም አይወደውም። ጥቂት ጨለማዎች በስብከታቸው ይረብሻሉ እንጂ ሰማኒያ በመቶ ከሚሆነው

የኢትዮጵያ ህዝብ ገበሬው ሆኖ ሳለ፣ እንደው የአማራን፣ የኦሮሞን፣ የትግሬውን ገበሬና ድሀ ቤተሰቦቹን በኑሮ ደረጃቸው አንዱን ከሌላው የሚበላለጥ፣ የሚለያይ ሆኖ ነውን? ሁሉም በያለበት በድህነት ቤተሰቦቹን ይዞ በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ የሚኖር አይደለምን? እንዲያም ኑሮ ተቸግሮ ይማሩ ዘንድ የላካቸው የራሱ ልጆቹን ሰብስቦ የሚመርዝ ስርአትና በትምህርትቤቶቹ ሳይቀር ጠላትነትን የሚሰብክ ክፉ ነጣቂ ስብእናቸውንና ስነልቦናቸውን ወስዶበት ከሱ ባህልና አኗኗር፣ ከአምላኩ መንገድ ጭምር ተቃርነው እዳ እንዲሆኑ የሚያደርግ ዘረኛ ጠላት ተነሳበት እንጂ።

ለዚህ ሁሉ ቀውስ የዳረገን የእምነታችን ድክመትና ስንቱን ይዞ ያሻገረንን የአምላካችንን ክንድ መልቀቃችን ቢሆንም፣ በትርምሳችን ተጠምደን ይህንን እንኳን እንዳናስተውል ሆነናል። በፍቅር መኖር፣ ራስወዳድነትን መጠየፍ፣ ጥቅመኝነትን መጠየፍ ይህ ሁሉ ለሰማይቤት መግቢያ ብቻ መስሎ ይታየናል፤ ለራሳችን ምድር መድህኒትነት ጭምር እዚሁ ምድር ላይ መጥቶ መስበትኩን ማን አስተውሎት። ራሱን ብቻ እየተመለከተ የሚያደርገው መወራጨት ሌላውን ሲገፋ ሲያስቆጣ በትእቢቱ ታውሮ ራሱን ብቻ ለማሳደግ የሚሯሯጥ፣ አብሮ የሚኖር ወንድሙን በማይቀይረው ማንነቱ ከሱ ለይቶ አግልሎ ራሱን ሊጠቅም የሚሯሯጥ ሰው የእግዚአብሄርን መኖርና በሀያልነት ያለው ስልጣንን ዘንግቶት ነውን? የክርስቶስ ሌላ ማንነቱ የሆነውን ወንድማዊ ፍቅርን እየናደ የሰው ፍጡርን በማይቀይረው ማንነቱ እያገለሉ መኖር እውነት በእግዚአብሄር ማመኑን ፈፅሞ ትተነዋልንዴ?

ወይ ጭራሹኑ ፈጣሪን እስከነመኖሩ ክደነዋል እንዴ? እንደ ሌሎቹ ፈጣሪ የለም ብለን ነው የምናምነው? አንተስ ይህን የምታነበው መኖሩን ትቀበላለህ? ታዲያ እሱ ካለ፣ ፈጣሪ እሱም የአለም ሁሉ ባለቤት፣ የሀይል ሁሉ ጣራ፣ የሁሉ ወሳኝ ባለቤትና ንጉስ የሆነ እሱ እግዚአብሄርን እርዳታ አንፈልግም? እንዲህ የሁሉ ከሀሊና ባለስልጣን የሆነ “አንኳኩ ይከፈትላችኋል” ብሎ ሊረዳን ፈቃደኛ

የሆነ ንጉስ በሙሉ ሀይሉ እያለ እንዴት እርዳታውን እንዲልክልን አንጠይቀውም?በዚህ ጭንቅና ችግራችን በበዛ ጊዜ እንዴት በመሀላችን እንዲገኝና ሁሉን እንዲያስተካክልልን ልናስበው ልንጋብዘው አልፈቀድንም? የሱን መኖር ካመንን?

ታዲያ እሱን የሚያርቅን ወንድምን ለይቶ ማበላለጥ፣ ለይቶ የሚያስጠላ፣ ለይቶ የሚያስጠቅም በዘር መሯሯጥን ልንይዝ መረጥን? የክርስቶስን በሰወች መሀል መገኛ ገፁ የሆነውን የማያበላልጥ ወንድማዊ ፍቅርን ከራሳችን ሰብረን አውጥተን አሁን በሚታየው መልኩ ተገኘን?

“ታዲያ ምን ችግር አለው እንደምእራብ ሀገሮች በስጋ ትግል ራሳችንን ችለን እስካስኬደን እንኼዳለና” የሚል ሰው ሊኖር ይችላል፡፡  ነገር ግን የስጋ ትግል የሚባል ነገር ከቶ እንደሌለ አታውቅምን? ሁለት ጎራ ብቻ እንዳለ አታውቅምን?

አንዱ የእግዚአብሄር፣ ሌላው ደግሞ የሰይጣን፡፡ ከሁለቱ መሀል የሚባል ቦታ ፈፅሞ እንደሌለ፣ ሊኖርም እንደማይቻል አታውቅምን?

በጎችን እረኛቸው ጥሏቸው ቢሄድ አነፍንፈው ሲከታተሉ የነበሩ አውሬዎች ሁሉ ከቶ ችለው ዝም እንደማይሉ አታውቅምን? ከቶ የትኛው በግ ይሆን ማንም ሳይነካው ሊኖር የሚቻለው?

ምእራባውያን ፈጣሪን ክደው በብልፅግና የሚኖሩት ከሰይጣንም ከእግዚአብሄርም ርቀው ነውን? ጨርሶ ወዳንደኛው ስለተጠቃለሉ ነውንጂ፡፡ የተማረከን ወታደር ሲገድል የሚውል ማን ጠላት አለ? ቢያደርግም ሌሎች እጅ እንዳይሰጡ እንቅፋት ይሆንበታል እንጂ ለሱ ምን ጠቅሞት? በብልፅግና በሀብት ቢኖሩ ምን ቸግሮት? እነሱ እንደሆነ አልፈው ልጆቻቸውን የሚሆኑትን ፆታ የማስመረጥ መብትና ነፃነት በህግ ጥበቃ የሚደረግለት ባህል እስከመከተል ድረስ ሄደውለታል፣ ቤቱ ገሀነም እስኪደርሱ ባላቸው ጉዞ ንዳት ስለምን

ይነካቸዋል? ከመንገድ ጥለው እንዲጠፉ?

እኛም እረኛችንን ብንገፋው፣ ብናርቀው፣ ጋባዥ የማይፈልገው ርኩስ መንፈስ በነፃነትና ሙሉ ሀይሉ ነግሶብን ይፈነጭብናል። በሀገራዊም ሆነ በየትኛውም ትግላችን ውስጥ ስልጡን ሆንን ብለን ወይ ደግሞ ዝንጉ ሆነን አምላካችንን በመሀል እንዲገኝ ሳንጋብዘው፣ ከህይወትና ትግላችን አርቀነው ብንተረማመስ፣ ጋባዥ የማይፈልገው ሰይጣን በመሀላችን ተገኝቶ የምናያቸውን ነገሮች በሙሉ ያስደርገናል። ለዚህም ነው ዘረኞች በሄዱበት ቦታ ሁሉ የሚከተላቸው ሞትና ደም ለአፍታ ደርቆ የማያውቀው።

ጥላቻን በልባቸው ይዘው ዘር ለይቶ ጥቅመኝነትን ተዋህደው በዘረኝነት ተሰብስበው ግር ብለው በወጡ ሰወች መሀል ለሰው አእምሮ የሚከብድ አሰቃቂ ነገር ሁሉ የሚከሰተው ስለምን ይመስልሀል? እያንዳንዱን ሰው በተናጠል ብትጠይቀው ከቶ ሊያደርገው የማይችለውን የሚጠየፈውን ነገር በተሰበሰቡ ሰወች መሀል ተደጋግሞ ሲደረግ ለምን ይመስልሀል? በየግል ያላቸው የተሻለ ሰብአዊ አእምሮ ጠፍቶ በጋራ አንድ የሚያደርጋቸው ሰው በቁሙ የሚያስቃጥል፣ ዘቅዝቆ የሚያሰቅል፣ በስለት የሚቆራርጥ በስቃይ የሚደሰት አዲስ አእምሮ በአንድነት ይላበሳሉ እንጂ፤ በዛ የቡድን መንፈስ ላይ መሪነቱን የሚቀዳጀው መሀል ለመግባት ግብዣ የማይፈልገው ክፉ መንፈስ፣ እያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ እንደፈለገው ተመሳሳይ ሀሳብ የማስቀመጥ፣ ትእዛዝ በመስጠት ማስተባበር የሚያስችለው መናፍስታዊ ተፈጥሮውን በመጠቀም አንድ የጋራ አእምሮ አስይዞ በየግላቸው የሚጠየፉትን ቡሀላም የሚፀፀቱትን፣ እንደሌላ ሰው የሚኮንኑትን ተግባር እንዲሁም ሌላም ያለንግግር የተቀናጁ ጥርጣሬዎች፣ ድንጋጤዎች፣ ፍርዶች፣ ያንድላይ ሀሰተኛ ፍረጃዎች በአንድነት ያለንግግር ተግባብተው አሰቃቂ ተግባሮችን በአንድ አእምሮ ያሰራቸዋል። ሌላም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ማንኛውም ሰው ክርስቶስ የሚቃወመውን ነገር ሲያደርግ፣ የፍቅር ፍፁም ተቃራኒ የሆነውን ዘረኝነትን ሲሰብክ፣ ራሱን ጋብዞ

የሚመጣ መንፈስ ምሁሩን አእምሮ አልባ እስኪመስል ድረስ ተቆጣጥሮ ክፉ ክፉ ያናግረዋል፣ ያሰራዋል። የዚህ አይነት ክፉ ወንድምን ከሌላው መከፈልና ለይቶ ጥቅመኝነትን መስበክ ደግሞ አንዴ ባለቤቱ መንፈስ ከገባበት ነገሩን አራማጁ ሰው እንዳቀደው ኦሮሞና ሌሎች፣ በሚለው ክፍፍል ፀንቶ የሚያበቃና በዛው የሚቀጥል ሳይሆን አንዴ የክፍፍልና የወገንተኝነት መሪ መንፈስ ካስገቡት ልክ ከላይ እንደሙቱት መስታወት ከዋናው ስንጥቅ መስመር ተከትለው ሌላ የበዙ ክፍልፍሎችና ስንጥቅጥቅ እስከጥጋጥጉ እንደሚዛመት፣ ኦሮሞ ወይ አማራ ብለው ክፍልፍልን መርጠው ከላይ ራሳቸውን የከፈሉበት መንፈስ ወርዶ የወለጋ ኦሮሞ፣ የአርሲ ኦሮሞ እያለ እየቀጠለ መጨረሻ የሌለው ነቀርሳ መንፈስ መሆኑ የሚወራ ሳይሆን በተግባር የሚታይም መገለጫው ነው። ቀድሞስ ቢሆን በዚህ መሀል የሚነግስ መንፈስ ከዛ ዘር ወይ ከሌላው ዘር ምን የተለየ ጉዳይ አለውና? በቻለው መጠን የልዩነትና ባላንጣነትን፣ ወገን ለይቶ ጥቅመኝነትን መንፈስ አንግሶ ፍቅርን እስከተቻለው መጨረሻዋ ቅንጣት መስበር ነውንጂ። በፍቅር የሚመሰለውን ክርስቶስ የወንጌል ህሉ ጭምቅ መልእክት በፅኑ መዋጋት ነውንጂ።

ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው “ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።”

ምን ባለመንፈሳዊ ፀጋ ባለቤት፣ ምን ባለቅዳሴ፣ ባለማህሌት ብንሆን፣ ያ ሁሉ በዜሮ ተባዝቶ እምነት ከሌላቸው ሀጢያተኞች ጋር በአንድ ላይ እንወድቃለን።

ሀገራችን ከፊቷ የቆመው መከራ ግልፅ የሆነ ነው። ከክፋቱና ስፋቱም የተነሳ ከሌሎቹ ይልቅ በትንቢት መፅሀፍት ተዘርዝሮ የተገለፀ ሆኗል። በትንቢት ተገልጦ በብዛት መፃፉም መነገሩም፣ በኛ በሰይፍ ወዳቂዎች ላይ ቀድሞ ለመዘባበት ወይም ደግሞ ካለፈ በኋላ ቃሉ

መፈፀሙን ያዩ አማኞችን ለማስገረምና ማስደነቅ ታስቦ ሳይሆን በአሁኗ ሰአትና ደቂቃ ከደጃፉ የተሰለፍነው የእግዚአብሄር ልጆቹ አይተን እንድንበትና መከራውን እናልፍበት ጊዜውን እናሳጥርበትና እንተርፍበት ዘንድ ነው።

ይህንንም ማድረግ የምንችለው ከሁሉ ቅድሚያ የአምላክን በመሀላችን መገኘት በመናፈቅና የሚጠየፋቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ከመሀላችን በማራቅ ለሱ ጋባዥ በመሆን ነው። አምሳሉ የሆነውን የሁሉን ፍቅር አጥፍተን ዘረኝነትንና ከሌላው ተለይቶ ጥቅመኝነትን እስካልተውን ድረስም ይኸው ተግባር ግብዣው የሆነ ሌላው አካል ነግሶብን ትግል ኑሯችን መከራ ህይወታችን ሆኖ በጭቃ እየዋኘን ዘመናትን እናልፋለን። በዚህም ምክንያት ከየትኛውም ምድራዊ ትግላችን ፊት የእግዚአብሄር ህግ ከሁሉ በላይ አፅንተን መሰረት በማድረግ፣ ራሳችንን አስገዝተን እሱ በመሀላችን መሆኑን እናረጋግጥ፣ ከዛ በኋላ ባለው ማንኛውም እንቅስቃሴያችን እሱም ስህተቱን አርሞ፣ በጎደለው ሞልቶ፣ ያላሰብነውን ፈፅሞ የትኛውም ጠላት የማይቋቋመን ድል አድራጊዎች እንሆናለን፣ ለራሳችን አልፈን ለሌላው የህይወት ደስታ እንሆናለን። ችግሮቻችን ላንለያቸው የፈለግን ይመስል ስንዘምራቸው ስንደጋግማቸው የምንኖር ሳንሆን ሁሉ ተፈቶልን በሰላም የምንኖር እንሆናለን። ስለዚህም ያንተ ምርጫ አምላክህን ማስቀደም፣ በልጅት ሆኖ ከሚመጣው ሁሉ ይቅርታን ጥበቃን በመለመን የፀና ይሁን። ከሁሉ ዘረኛና እንቅስቃሴያቸው ራስን አግል። ከሌሎች ወንድሞችህ ጋር ግንኙነትህን አጠንክር አስፋ፣ በእኩልነትና ፍቅር ኖረህ አምላክህን አስቀድም፤ እሱን በርትተህ ያዝ። በምታደርገው ቀሪው የምድር ትግልህ ጠላቶችህ ከደጅህ ሳይደርሱ በቦታቸው ተነው ይደመሰሳሉ። አምላኩን ትጥቁ እንዳደረገው ንጉስ ዳዊት በዘመትክበት ሁሉ ካንተ ቀድሞ ድል በሜዳው ይጠብቅሀል።

ኢትዮጵያዊነት እንዲሁ በባንዲራ የሚገለፅ፣ ወይ ደግሞ በዘረኞች አንደበት "ተወሮ የተያዘ ምድር መጠሪያ"፣ ወይ ደግሞ የአፍሪካ አንድ ሀገር ቅርፅ፣ ተብሎ እንደሚነገረው አድርገህ አትየው። ይልቁንስ ከቀድሞም መነሻው በነበረው ፍልስፍና፣ የዥንጉርጉሮች በክርስቶስ አምሳል ሰብአዊነታቸው ብቻ በአንድነት በፍቅር የሚኖሩበት፣ እግዚአብሄር በፈጠረው ዥንጉርጉር ፍጥረት መሀል የሚገኝበትን የፍቅርና አንድነትን መልክ መላበስ በመሆኑ ብቻ እየው።

እግዚአብሄርን የረሱ ስልጣን እጅግ ያፈቀሩ ታጣቂዎች ህብረት በድህነትና ፍቅር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መሀል ከፍለው "ኦሮሚያ ክልል" የተባልክ መሆንህን አትርሳ! ኦሮሚያ ተብሎ የተከለለው ምድር ኢትዮጵያዊ መሆንህን አትርሳ ! ለልጁ "ተመልከት ያንተን ንብረት" ብሎ አክሱም የሚጠቁም፣ "ተመልከት ያንተን ሀብት" ብሎ ጣናን፣ አባይን የሚጠቁም፣ ተመልከት የርስትህን ጫፍ" ብሎ ከካርታ ላይ ኦጋዴንን የሚያሳይ፣ እሱራሱ እንዲህ ተብሎ ከአባቶቹ የተረከበውን እንዳባቶቹ ታግሎ ጠብቆ ለሚወደው ልጁ ሙሉ መብትና ባለቤትነትን የሚሰጥ ነህ።

አባቶቹ ደማቸውን ከፍለው የገዙትለትን ጥሎ ጠቦ የሚሸጎጥ፣ ከፍተኛ ቁጥርን ይዞ ሳለ፣ ከንቱ ስልጣን ፈላጊዎች በዘረኝነት፣ በሮሮ፣ ዘላለም የማይለቅ የተጎጅነት ትርክት በማልቀስ የሚጠምዱት፣ ዘግናኝ እልቂትን አልፈው ራሳቸውን አሳድገው ታላቅ እንደሆኑት እስራኤላውያን ሳይሆን፣ ዘላለም ሮሮ በመደጋገም፣ ተጎጅነትን በመተረት፣ የዘር ተጠቂነትን በማላዘን ሳይቀየሩ እንደኖሩት ጥቁር አፍሪካውያን እንድትሆን የሚያደርጉህን የምትከተል አትሁን። ትልቅ ቁጥርና ተፅእኖ ፈጣሪነትን ይዘህ ሳለ፣ ጥቂቶች ስልጣንን በመፈለጋቸው ብቻ፣ ሌሎች አናሳዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሊጎዱን ነው፣ እንዲህ ሊያደርጉን ነው በሚል ከንቱ ለቅሶ የያዙ የበታችነት ስሜት የተጠናወታቸው ጠባቦች የሚያሸከረክሩህ ሳይሆን፣ በሰፊ ሙሉ ቁመና ያለህ ትልቅ መሆንህን ተማምነህ በፍቅር አንድነት

ክብር የምትኖርባትን የእግዚአብሄር ምድር ኢትዮጵያን የሚያድነው ኢትዮጵያዊ እንዳትሆን ከቶ ምን ያንስሀል?

በኢትዮጵያ ይመጣል በተባለው መከራ፣ በየትኛውም በኩል ያሉ ዘረኞች ከየትኛውም ዘር ይሁኑ በቅስፈት ይመታሉ፣ እርስበርስ ይወድቃሉ። እግዚአብሄርም የዚህን ዘር ብሎ ከክፉ ከዘረኞች መሀል አንዱን ወዶ አይመርጥም፤ ማንኛውም አንዱን ወንድሙን ከሌላው ከፍሎ ለይቶ ጥቅመኝነትን የሚፈልግ፣ የክርስቶስ ምሳሌ የሆነውን መስፈርት አልባ ወንድማዊ ፍቅር ላይ የተነሳ ሁሉ በአንድነት ይወድቃል። እናም ተነስተህ ድል በሚሆንህ ፍቅርና አለመገላለል፣ አለመመራረጥ ሆነህ ከአምላክህ ከሌሎች ከየሁሉም የሆኑ ወንድሞችህ ጋር በህብረት ሆነህ አምላክህን ከሚመጣው ሁሉ ያድንህ፣ በፈቃዱ ያኖርህ ዘንድ በመማፀን ፅና፤ ከሚመጣው መከራ ሁሉ እንዲጠብቅህ ቅረበው።

መፅሀፉ እንዳለው፣ ከኢትዮጵያውያን ጋር እጆችህን ወደእግዚአብሄር ዘርጋ። የተተነበየው የሚመጣው መከራና እልቂት ያለንስሀ በሀጢያት ጨቅይተው በመጣባቸው አልፎም አሻፈረኝ ብለው በተነሱ የፍቅር ተቃራኒ ፅልመት የሆነ ዘረኝነትን በተላበሱት መሀል፣ እንዲቀር፣ የነሱ ጉዳይ ይሆን ዘንድ፣ **አንተ ራስህን አንፃ አድን። ሀገርን ለማዳን በከንቱ ምድራዊ ፖለቲካ ልፊያ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሄርና በሱ መንገድ ላይ ትጋ። እውነትም አለና፣ እንደ ልጁ ሆነህ፣ እጄን ያዘኝ በለው። ድህነት ከሀጢያት ለነፁት እንጂ የሆነ ፖለቲካ አቋም ለያዙት አይደለምና፣ በንስሀ ታጥበህ ራስህን ከሀጢያት ጠብቀህ ዘወትር ድህነቱንና ይቅርታውን በመለመን ተዘጋጅተህ ኑር። ስለዘራቸው፣ ስለ ፖለቲካቸው ሳይሆን ስለ ፍቅርና እግዚአብሄር ልጅነታቸው ባመኑት እግዚአብሄር ተጠብቀው ከሚተርፉ ጥቂቶች መሀከል ሁን።**

ለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።

# ለኢትዮጵያውያን

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ አንዲቷም ፊፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

ጊዜህን ሰጥተህ ከማንበብህ በፊት

“ፈጣሪ አለ” ወይስ ደግሞ “ፈጣሪ የለም” በሚለው ላይ ግልፅ የሆነ የራስህ እምነትህን ለራስህ ጠይቅ። አቋምህን ለይ! ከዛ ብቻ አንብበው

ለየትኛዋ ህይወትህ፣ ለማንስ ብለህ ከምታምንበት አቋምህ መወላወል ነው? ከሁለቱ ውጪ ፈፅሞ ሌላ በመሀልቤት የሚባል ነገር የለምና፣ ቀድመህ አንዱ ላይ ፅና። ሀይማኖቴ የምትለው ቢኖርህም ነገርግን በፈጣሪ መኖር ላይ አንድ እምነት የሌለህ ከሆንክም ጭምር በዚህ ፅሁፍ አጭሯን ጊዜህን አታባክን። ፈጣሪ መኖሩን የምታውቅና ያመንክ ከሆንክ ግን የሚከተለው ፅሁፍ ፈጣሪ ባለበት አለም ላይ ያለ ግልፅ ፅኑና የማንሸሸው ሀቅ ነውና ልዩነት አይኖረንም።

ሀይማኖት አለኝ ብሎ እርግጠኛ ሆኖ የፈጣሪን መኖር ግን መጠራጠርና እርግጠኛ አለመሆን አይነት የዘመኑ ፍፁም ተአምር እብደት አካል ከሆንክም ራስህን መርምር። ሰይጣን እንደድሮው ቀጥታ ሀውልትና ጣኦት በማስመለክ ሳይሆን ሀይማኖት አለኝ ብለው በርግጠኝነትና መተማመን እየተናገሩ ነገር ግን የፈጣሪን መኖር በጥርጥርና መወላወል ላይ እንዲሆኑ በማድረግ ነውና ነፍስን ባሪያው የሚያደርገው። ከአባትና አምላካችን ጋር የሚደረግን ግንኙነት፣ ህይወትን በሱ ፍላጎት ተንተርሶ መቃኘትን በመሰባበር፣

የአኗኗር ሁኔታን የፈጣሪን መኖር ከግምት ያልከተተና በዛ መልክ ቅርፅ ያልያዘ ማድረግ፣ ጣኦት ማምለክ ሳይጠበቅብን የምንክድበት ከክህደትም ትልቁ መንገድ ነውና። ፈጣሪ አለ ብሎ መናገር አለመናገር ሳይሆን ዋናው ነጥብ፣ ህይወታችን የፈጣሪን መኖር ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው ወይስ አይደምለ በሚለው ነው የኛ የልብ እውትን የሚለካው። አምላክም ያንን ነው የሚያየው። ከኛ ምላስ ምንም የለውም።

ስለዚህ መጀመሪያ ቆም ብለህ አሰላስለውና፣ የራስህን አቋም ከያዝክ በኋላ ብቻ ምንባቡን ቀጥል። በአለማችን ላይ ታላቅ ስልጣንና ሀይል ያለው፣ በሁሉ ሊወስን የሚቻለው ፈጣሪ አለ ካልክ በተፃፈው የማንስማማበት ምክንያት የለንምና ምንባቡን ቀጥለው። የፈጣሪን መኖር ከካድህ ግን፣ ማንም በግድ የሚጋፋህ አይኖርም፣ እንግዲህ ባንተ መንገድ ባዶ አካላዊ እርምጃችን የት እንደሚያደርሰን አብረን የሚሆነው ሁሉ እናያለን። ይህንንም በማንበብ የአጭር እድሜህን ጊዜ አታባክናት።

የዛሬው የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁለት ያጣ ሆኖ በመሀል ቤት በክስረትና ከሌላው በከፋ መከራ መሀል ደህይቶ ይገኛል። ኢትዮጵያንም ከሌላው አለም የሚለያት ችግሯ ይህ ብቻ ነው። ከሁለቱም ያልሆነች ሀገር በመሆኗ።

ወይ ከእግዚአብሄር አልሆነ ወይ ከ አጋንንት ወገን አልሆነ፣ በጦርሜዳ መሀል ሰፍሮ ሁለቱም ወገን የኔ ብለው ላይመድቡት በመሀል ቆሞ የሚገኝን አካል እንመስላለን፣ የሁሉም አቅጣጫ ጥይት ላለመመታት ዋስትና የሌለው።

ክርስቶስ የሰበከውና ከጨለማዊነት የሚያድን እምነትና የአኗኗር መንገድን ብንተውና የአምላክን መኖር የካድን፣ በዝሙት ባህል በሀጢያትና ባጠቃላይ በመፅሀፍ ላይ በተወገዘው ርኩሰት ስራ የተዘፈቅን ብንሆን ኖሮ ሰይጣን እንደምእራባውያን በምድራዊ

ኑሯችን ሁሉ በስጋ የምንፈልገውን ብልፅግና፣ ሀብት ወዘተ ሊሞላልን ምን ገዶት? ይሞላልን ነበር። ለእርድ የሚቀልቧትን በግ ተንከባክበው ቀልበው እንደሚያቆዩዋት ማለት ነው። ብዙ በሀገራችንም እንደሚታየው በጠንቋይ በኩል እንኳን ከእግዚአብሄር ከተለያዩለትና ከካዱለት ምን ገዶት ሀብት ሊነሳ? ስንት ብልፅግናን በምድር ሊያለብሰን መች ይሰስታል? መጨረሻው አያምርምንጂ።

ነው ወይስ ምእራባውያን በአፋቸው በመንፈሳዊው አለም መኖር አናምንም፣ በቁሳዊነትና ሳይንስ ብቻ፣ ወዘተ ምናምን ስላሉ ለሰይጣን አይመቹትም፣ ከነሱ የራቀ ነው ብለህ አሰብክ? እሱንም ጨምረው ፈጣሪን ቢክዱለት ደስታው እንጂ ምን ሊጎድልበት? ወደአምላክ ካልሄዱ ዞሮ የሱኑ አይደሉምንዴ?

ነፃ ሆኖ በመሀል ሌላ አኗኗር ያለ ይመስልሀልንዴ? ነው ወይስ ፈጣሪ መኖሩን ጭራሽ ከደኸዋል? ፈጣሪ አለ ማለት እሱ አስቦ የፈጠረበት እንድንኖር የሚፈልገው መንገድ አለ ማለት ነው። እኛም አኗኗራችን ወይ ያንን ይመስላል ወይ ደግሞ አይመስልም። በዚህም መሰረት ሁለት አማራጭ ብቻ ነው ያለው።

አንዱ የእግዚአብሄር፣ ሌላው ደግሞ የሰይጣን። ከሁለቱ መሀል የሚባል ቦታ ፈፅሞ ሊኖርም አይችልም። ከፈጣሪ አምላካችን እቅፍ ከወደቅን፣ ያለእረፍት ከስርስር በረሀብ የሚልከሰከሰው ሰይጣን አነፍንፎ ይለቅመናል እንጂ።

በጎችን እረኛቸው ጥሏቸው ቢሄድ ተርበው አነፍንፈው ሲከታተሉ የነበሩ አውሬዎች ሁሉ እያዩዋቸው ከቶ ችለው ዝም እንደማይሉ አታውቅምን? ከቶ የትኛው በግ ይሆን ከእረኛው ርቆ በመሀል ማንም ሳይነካው ሊኖር የሚቻለው?

ምእራባውያን ፈጣሪን ክደው በብልፅግና የሚኖሩት ከሰይጣንም ከእግዚአብሄርም ርቀው ነውን? ጨርሶ ወዳንደኛው ስለተጠቃለሉ ነውንጂ። ቢበለፅጉ ቢመቻቸው ምን ይገርምሀል? የተማረከን ወታደር ሲገድል የሚውል ማን ጠላት አለ? ቢያደርግም ሌሎች እጅ እንዳይሰጡ እንቅፋት ይሆንበታል እንጂ ለሱ ምን ጠቅሞት? በብልፅግና በሀብት ቢኖሩ ምን ቸግሮት? እነሱ እንደሆነ የእርክስና ጫፍና ማማ አልፈው ልጆቻቸው ሲያድጉ የሚሆኑትን ፆታ የማስመረጥ መብትና ነፃነት በህግ ጥበቃ የሚደረግለት ባህል እስከመከተል ድረስ ሄደውለታል፣ ቤቱ ገሀነም እስኪደርሱ በሚነዳቸው ጉዞላይ ስለምን ይነካቸዋል? ከመንገድ ጥለው እንዲጠፉ ብሎ?

እኛም እስካሁን ፈፅመን አልካድንምና፣ ጥንት የነበረን የኛ እምነትና በሀይማኖት የተመሰረተ መልካም ማህበረሰባዊ እሴትና ባህላችን ለሰይጣን አልተመቸውም፤ ሁሌም ቢሆን ባገኘው መንገድ ሁሉ ሊያጠፋን እንቅልፍ አይኖረውም።በውጪዎቹ መሳሪያነትም ሆነ በሌላም መንገድ እኛን ከማደህየት ማማረር፣ ወደሱ መማረክ፣ ሰላም መንሳት ፈፅሞ አይቦዝንም።

ፈጣሪም ከዚህ ሁሉ ስራውና ጥፋቱ እንድን ይጠብቀን ዘንድ ወደሱ በሙሉ እምነትና ልጅነት አልተገኘንለትም። ነፃ ፈቃድን የሰጠን አምላካችንም ይህን ጥሶ ሳንጠይቀው ዘሎ ሊረዳን አይነሳም። በየዋህነትና ፍቅራችን በፈተናም ቢሆን ለሱ ያለን የውስጥ ፍቅራችን፣ እንዲሁም እሱን ብለው በበረሀና ዱር በፍቅር እድሜያቸውን ስለኛ በመለመን የሚኖሩም ቅዱሳን ልመናም ደግሞ ምንም ብንደክምም ፈፅሞ አሳልፎ ሊሰጠን እንዳይችል አድርጎታል።

በዚህ መልኩ ወይ ከሰይጣን አልሆንን፣ ወይ ፅንተን ከእግዚአብሄር ልጅነት ህይወት አልሆንን አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ሆነናል። እኛ የዛሬዎቹ እግዚአብሄርንም እንደሆነ አጥብቆ አልያዝነውም፣ በየትኛውም ጊዜ ሀገራችን ችግር ላይ ስትወድቅ፣ ወሳኝ ጊዜያት ላይ

ስትደርስ ለአንዲቷም ጊዜ እንኳን፣ አይደለም የሱን እርዳታ ልንጠይቅ ዘለአለም ቢያሹት ጠብ በማይል ፖለቲካና፣ ኢአማንያዊ ርእዮት ጭቅጭቅ በመሯሯጥ የሱን መኖር ጭራሹኑ ለመርሳት የምንጥር ይመስላል። በሌላው ጊዜ ደግሞ፣ በህይወትና ባህላችን እሱን በማክበር፣ በቅዳሴው በፀሎቱ ከሌላው አለም የተሻለ ለሀይማኖት ክብር የመስጠት መልክ ይታይብናል።

ወይ እግዚአብሄርን በአፋችን እንደምንለው ልንጋብዘው ፈቃደኛ አልሆንን።

እሱ ፈጣሪም ቢሆን በምንም ምክንያት ከሌላው አለም አድልቶ ሳንጠይቀው መጥቶ ጣልቃ ስለማይገባ፣ ወይ እኛም "አንኳኩ ይከፈትላችኋል" የሚለውን በአፋችን የምንሰብከውን የሱኑ ቃልኪዳን አምነን በዋና የሀገራችን ጉዳይ ላይ ወሳኝ ጊዜያት ላይ ስንደርስ በአንድነት ምህላ እንኳን የሱን እርዳታ ለማግኘት ሞክረን አናውቅ እንዲያውም ሀሳቡም ኖሮን አያውቅ ነገር፣ ሀገር አቅጣጫ ልትቀይስ መሰረታችን ሊቆም ሲል መብራቱን አጥፍተን በጨለማ ካቆምን በኋላ ጨርሰን ወደለተለት ኑሯችን ስንመለስ መብራቱን መልሰን እናበራለን። ስንንገዳገድ ስንንገጫገጭ ስናማርር እንውላለን።

አምላክም አይተወን፣ በተበላሸ መሰረታችን ማደግና ምእራባውያንን መምሰልን ለይቶ ማየት ያልቻለ አስተሳሰብ አንግሰን፣ በማደግ ስም ምእራባውያንን መምሰልን ሙሉ መዳረሻው በሆነ ፖለቲካዊ፣ ትምህርታዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም የአኗኗር መንገድ ቅየሳችን፣ ማደግንና ከአምላክ ከመለየትን ነጥለን ማየት የሚችል ግንዛቤ ሳይኖረን፣ ከሁሉ ትልቁ አካላችን ነው የምንለው "እግዚአብሄር" በዚህ ጉዟችን ውስጥ ምንድነው ቦታው? ሚናውስ ምንድነው? አደግን ብለም በምኖረው የወደፊት ህይወት ውስጥ የሱ ቦታ የቱጋር ነው? የእድገትና ስልጣኔ መንገዳችንስ መዳረሻው ጋር ይህ ትልቅ የህይወታችን አካል የምንለው "እግዚአብሄር" እንዴት ሆኖ ነው የሚገኘው? ብለን አንዳችም ጊዜ ሳናስብበት፣ በአደባባዩና ፖለቲካዊ መድረኩ

“ፈጣሪ/አምላክ” የሚለውን ማንሳት በውስጠታዋቂ እንደ ነውርነት መቁጠሩን ባልገባን መልኩ የታመነበት ነገር ሆኖ ለመጓዝ እየተንገዳገድን እንገኛለን።

የህዝቡ ማህበረሰባዊ መሰረት፣ በህዝቡ ሁሉ ልብ ትልቅ ትልቅ ቦታ ያለውን አካል “ፈጣሪ” (እግዚአብሄር/አላህ ማንኛውም አማኝ ፈጣሪዬ ብሎ የሚጠራው አምላኩ)፣ የድፍን ህዝቡ ኑሮ ሁኔታ ላይ ከማንም በላይ ቦታና ተፅእኖ ያለው አካል የሆነን የህዝቡን ሰፊ ክፍል ከምንም ግምት ያላስገባ የሀገርና ህዝብ መንገድ ቅየሳ ወይም ፖለቲካ ከቶ ምን አይነት ጎደሎና ውሱን ስንኩል ነው? እንዴት ለዚህ አይነት ህዝብ ተጣጥሞ ይሰራል? ምኑስ ነው እንዴትስ ነው ዴሞክራሲ(የህዝብ ፍላጎት አስተዳደር) ተብሎ ሊጠራ የሚችለው? መላው ህዝቡ በነፍሱ ጭምር የተቀበለው አካሉ ከግምትም ያልገባበት ሂደት? ህዝብ ላይ የሚጭኑት ሆኖ ሳለ? ለምን ይሆን ለሌሎች ተለክቶ የተሰፋ ርእዮት ካልሆነ አንለብስም ያልነው? ለራሳችን መቀየስ ያቃተን? ፈጣሪን የምናከብረውስ ከሆነ እንዴትስ ከሱ መለየትን በመጠየፍ ይህንን ላለማድረግ አስቻለንና ዝም አልን? ጥቂቶች በራቸውን ዘግተው ካመጧቸው አማራጮች መሀል አንደኛውን ምረጥ ተብሎ ህዝቡ ካሉት የሱ ካልሆኑት መሀል አንዱን ሲመርጥ ዴሞክራሲ ተብሎ የሚጨፈርበት መንገድ ምኑ ነው የህዝብ?

በዚህም ምክንያት ጎደሎ ሆነናል።የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ከሌላው አለም ህዝብ አንፃር በግማሽ አእምሮው የሚኖር ህመምተኛ ህዝብ ነው። አእምሮው ለሁለት የተከፈለ፣ በሙሉ አእምሮው አተኩሮ የሚሰራበት፣ የሚቆምለት ነገር የሌለው ባለግማሽ አእምሮ ህዝብ ነው።

ልደግበት ብሎ የያዘው፣ ልተዳደርበት ብሎ የጨበጠው ርእዮትና መንገድ ፈጣሪን ያገለለ፣ በዛ መንገድ የሄዱ ሀገራት በሙሉ በግሎባላይዜሽን ስም ወደተመሳሳይ ባህል፣ ቋንቋ፣ ማንነት፣ ብሎም

እምነት(እምነት አልባነት) ሲቀየሩበት በአይኑ እየተመለከተ፣ ከፈጣሪ ጋር የመኖርን እምነትና ባህል ምናልባት በጊዜው ካለው ሰው ባይሆንም በሱ ከሚተካው ትውልድ ብሎም ከምድሩ አጥቦ የሚያወጣ መንገድ መሆኑን ስለሚመለከት፣ እንደግበት ተብሎ የተያዘውን መንገድ በግማሽ አእምሮው እንዲተጋበት ያደርገዋል።

በዚህም ምክንያት ለእድገት ሲሆን ግማሽ አእምሮ ያለን ህዝቦች ያደርገናል። ከሁሉ ነገር ምን ይቀድምብህል ቢባል ፈጣሪዬ ይላል። አእምሮው ህይወቱና ተግባሩ ከዚህ ጋር እንዲጣጣም ክፉኛ ይወቅሰዋል። ልጆቹንም እግዚአብሄርን እንዲያስቀድሙ ይነግራቸዋል፣ ስለወደፊቱ አስፈሪ ፍርድ፣ በክፉ ሀጢያታችን ምክንያት ወደፊት ስለምንገባበት ቅጣት አስፈሪነት ጭምር ሁሉ ይነግራቸዋል። የለተለት ህይወታቸው ግን ከዛ መንገድ በተቃራኒ መሆኑን ሁሉም ያውቁታል።

በስነልቦና መነፅር ብቻ ብናየው እንኳን አታድርግ የእሳት መንገድ ነው ብሎ የሚያምነውን፣ ይህንን ባደርግ ወደእሳት ፍርድ ወደጥፋቴ ይመራኛል ብሎ የሚያምነውን፣ ተብሎም የሚነገረውን ነገር በለተለት ኑሮው ማድረግን የተለማመደ ድንጋይ ጭንቅላትና ክፉኛ የተዛባ አእምሮን ይዞ የሚያድግ ትውልድን እንድንይዝ ሆነናል። ፈጣሪ ኖረም አልኖረም፣ ሀይማኖት ልክ ሆነም አልሆነም፣ እንዲሁ ስናየው የዚህ አይነት ልምምድን የሚያደርግ አእምሮ አቋሙ ብላሽ እንደሚሆን ምንም ክርክር የለውም።

የህይወቴ ሁሉ የመጨረሻ አላማ እግዚአብሄር ነው ብሎ ያመነ አእምሮ፣ ለዚህ የህይወት ግቡ የሚያግዘውና የሚረዳው ሆኖ ያልተቀረፀና ይልቁኑም ከቀንቀን ከዚህ እንደሚያርቀው ሆኖ የተዘጋጀን ሀገራዊ ራእይና የጉዞ መንገድ በሙሉ አእምሮና ልቡ እንዳይከተለው፣ ሆኗል። በዚህም ምክንያት ባለግማሽ አእምሮ ተብለን ብንጠራ ማጋነን አይሆንም።

ይህ የቅዱሱን መፅሀፍ ቃል ወይ እውነት ነው ብለን ነው መቀበል ያለብን፣ ወይ ደግሞ ውሸት ነው ብለን ነው ማመን ያለብን። ከሁለቱ መሀል ያለ ቦታ የለምና።

የቅዱስ ጳውሎስ ሮሜ መልእክት
“ ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። “

የጴጥሮስ መልእክት “ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ።”

የቅዱስ መፅሀፉ ቃል እንግዲህ እንዲህ ይላል። ዛሬ ላለን ለብዙዎቻችን ግር የሚልና የሚያስደነግጥ ቃል ነው።ይህ መጥፎ ንግግር ነው ተሳስቷል ልንል ነው? ወይስ የመረጥነው ብቻ ነው እውነት ለኛ? ነው ወይስ ሌላ ሀይማኖት በሌላ መፅሀፍ ላይ መስርተናል?

ክርስቶስም ወደምድር በመጣ ጊዜ ስለሚገዛው መንግስትም ሆነ ስለ አስተዳዳሪዎቹ ዋጋ ሰጥቶ አልተናገረም። ይሉቁንስ ሲጠይቁት "የቄሳርን ለቄሳር፣ የእግዚአብሄርን ለእግዚአብሄር " ብሎ ነበር የተናገረው። ቦታም ሰጥቶ ስለሱ አልተናገረም ነበር። ምክንያቱም ህዝቡ እግዚአብሄርን ከያዘና አምላኩን ከጠየቀው የምድራዊዎቹ ባለስልጣናት የቅንጣትም ያክል ሀይል ኖሯቸው የሚያስቀሩት ነገር እንደሌለ ያውቃልና፣ ይህን ሀይል እግዚአብሄርን መያዝ ነው ያስተማራቸው። ከዛ በኋላ አይደለም የምድር ባለስልጣናት፣ የዝናብ

ደመና ሳይቀር በህዝቡ ፀሎት እንደሚገዛ እሙን ነው፡፡

በሀገራችን ጉዳይ ስንለፋ፣ ወይ ስንንቀሳቀስ እንደው ለመሆኑ እግዚአብሄር ስለመንግስትና ስልጣን የሚለው ምንድነው? ብለን አስበነው እናውቃለን? ቆይ ግን በፈጣሪ አማኝ ነን የምንለው ምን ለማለት ነው? ለአፋችን ደስታ ብቻ ነውኮ የምንናገረው፡፡ ፈጣሪ አለ ብለን ተስማምተናልና፣ ታዲያ እንዲህ ላኑራቸው ብሎ ከፈጠረን ከሱ በላይ ስለሰውልጅ ህብረት ኑሮ መልክና መመሪያ መንገድ ማ የተሻለ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል ብለን እናምናለን? ታዲያ እሱ ምን ይላል ብለን እንዴት አስቀድመን ልንጠይቅ አልቻልንም?

እግዚአብሄር ስለመንግስትና ስልጣን የሚለው ምንድነው? ይህንን አስበነው እናውቃለን? ፈጣሪ አለ ብለን ተስማምተናልና፣ ከሱ በላይ ስለፈጠረው ሰውልጅ ህብረት ኑሮ መልክና መመሪያ መንገድ ማ የተሻለ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል ብለን እናምናለን? ታዲያ እሱ ምን ይላል ብለን እንዴት አስቀድመን ልንጠይቅ አልቻልንም?

እንደ እውነታው ከሆነ በላይ በስልጣን የሚቀመጠው አካል ልክ እንደመስታወት ህዝቡ በእግዚአብሄር ፊት ስላላቸው ቅቡልነትና መልስ ራሳቸውን የሚለኩበት ነፀብራቃቸው ነው፡፡ መልካም ሆነው በእግዚአብሄር ሞገስን ባገኙ ጊዜ መልካሙን ሊያነግስባቸው፣ አንዳንዴ ለፈተናም ወይም ደግሞ ሙሉ ህዝቡ በክፋትና ሀጢያት ዘቅጠው ርኩሰትን በያዙ ጊዜም የከፋውን፣ ከበዛም ጭራሹኑ ከሌላ መጥቶ የሚገዛ አጥፊን ሊያስነሳባቸው የሚቻለው እነሱም የራሳቸውን እምነት የሚያዩበት መንገድ ነው፡፡ ቢከፋቸውም በአንድላይ ወደአምላካቸው በማመልከት በሱባኤ በምህላ ፍፁም ሊንዱት ሊያፀኑት የሚቻላቸው ተራ ክፍል ነው፡፡ በዚህም መልኩ የተከወኑ በሀገራችን ብዙ ታሪኮች አሉ፡፡ ታላላቅ ባለስልጣናትም የድሀ በስጋ ደካማ የካህናትን ግዝት እጅግ አብዝተው የሚፈሩበት፡፡ ለጦርነት ከተው ሰንቀው ህዝብ አንቀሳቅሰው ዘምተው ከተንቀሳቀሱ በኋላ እንኳን በሜዳው ላይ በመሀል ካህናት ገብተው ካስቆሟቸው

ሁሉን ትተው የሚመለሱት።

እግዚአብሄር ለምድር ባለስልጣን ያን ያህል ቦታ አይሰጠውም። የእስራኤል ህዝብን በምድራችሁ አኖራችኋለው ብሎ ከግብፅ ካወጣቸው በኋላ በሱ አባትነትና ጠባቂነት በሰላም ለረዥም ትውልድና ክፍለዘመናት ያኖራቸው ያለንጉስ ነበር። ቡህላም ንጉስ ያነግስላቸው ዘንድ ቢለመኑት አህዮቹን ሊፈልግ የወጣን አንድ ብላቴና ሳኦልን ቀባላቸው። ልክ እንደዛሬዎቹ እንደኛ የእግዚአብሄርን መንገድና ሀሳብ ባለመረዳታቸው፣ ስልጣንና ንግስናን ወሳኝና ከሁሉ በላይ መሰረት በማድረጋቸው እግዚአብሄር በማዘኑ ነቢዩ ሳሙኤል የተናገረው ይህንን ነበረ።

“ ሳሙኤልም ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ወደ ምጽጳ ጠራ። የእስራኤልንም ልጆች። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስራኤልን ከግብጽ አወጣሁ፥ ከግብጻውያንም እጅ ከሚያስጨንቁአችሁም ነገሥታት ሁሉ እጅ አዳንኋችሁ። ዛሬ ግን ከመከራችሁና ከጭንቃችሁ ሁሉ ያዳናችሁን አምላካችሁን ንቃችሁ። እንዲህ አይሁን፥ ነገር ግን ንጉሥ አንግሥልን አላችሁት። ”

ብሎ ሳኦልን አነገሰላቸው። ቢነግስም ባይነግስም ለሰላምና ጥንካሬ መሰረቱ ዋናው ህዝቡ ከእግዚአብሄር ጋር ያለው ግንኙነት በመሆኑ አንግስልን ቢሉት ሊያነግስላቸው፣ ይቅር ተወው ቢሉት ያለንጉስ ሊያኖራቸው አምላክ ምንም ችግር እንደሌለበት ያሳያል።

ቅዱስ መፅሀፉ እንደሚናገረው፣ የስልጣን ሁሉ ምንጭ እግዚአብሄር ነው። ከላይ ያለ ስልጣን ደግሞ ህዝቡ ከአምላካቸው ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት የሚለኩበት መስታወት እንጂ ያን ያህል በህይወታቸው ላይ ለውጥ ለመፍጠር ስልጣን ኖሮት በሱ አቅጣጫ የሚሄዱለት እንዳልሆነ ብዙ ቦታላይ እግዚአብሄር ሲናገር ይሰማል።

ህዝቡ መልካም ቢሆን፣ ለእግዚአብሄር በመልካም የሚገዛ ቢሆን፣ መልካም መሪ ያነግስለታል። በዛው መጠን ደግሞ ክፉ የሚሰራ ከሆነ ክፉ መሪን ነግስበታል። በዚሁም አንድ መመልከቻነት፣ ህዝቡ ክፉ በበረታባቸው ጊዜ በአንድነት ለአመፅ ሳይሆን የሚነሱት፣ ወደአምላካቸው ነበረ በህብረት የሚያመለክቱት። አምላክም ለመቶ ሚሊዮኖች ብሎ አንድን ባለስልጣን ወይ መሪ ቢያነሳው ቢጥለው ምን ቢያደርገው የሚገርም ነገርም አይኖረውም፤ ጥንትም ቢሆን ያለንጉስ የእስራኤል ህዝብ ሲኖሩ ነበርና ቁልፉ የህዝቡ በእግዚአብሄር ዘንድ ያለው እምነት እንጂ ከላይ የሚሽከረከረው መሪ የስራችን ውጤት ነው። መልካም ብንሆን መልካም ሊያነግስልን፣ ክፉ ብንሆንም ያው ሊሆንን ስልጣኑ የእግዚአብሄር እንደሆነ ነው መፅሀፉ የሚናገረው። ያም ነበረ መንገዱ አማኝ ለሆነ ህዝብ።

አባቶች ሲናገሩም፣ ጥንት በኢትዮጵያ ክፉ ንጉስ ቢነሳባቸው፣ መከራም ባፀናባቸው ጊዜ ቀሳውስት ሽማግሌዎች ተሰብስበው ክንድህን አቅልልን ካለዛ በፈጣሪያችን ስም ልናወግዝህ ነው ቢሉት፣ መጀመሪያውኑ በእናንተው ክፉ ስራ አይደለምንዴ እኔን በላያችሁ ያነገሰባችሁ ከኔ ሳይሆን ከፈጣሪያችሁ ጨርሱ ብሎ መልሷቸዋልም ይባላል።

የምድር ባለስልጣን ምድራዊ በመሆኑ፣ አምላክም እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ አባት ሆኖ ያለንጉስ እንዳኖራቸው ቡህላም ንጉስ አስነሳልን ቢሉት እንዳፋቸው እንዳነገሰላቸው ሁሉ የምድር ስልጣን ከእግዚአብሄር የሚሰጥ፣ ለክፉው ትውልድ ክፉ ለበጎው ትውልድ በጎ የሚሆን የህዝቡ የአኗኗር ሁኔታ ነፀብራቅ መአረግ ነው።

ይህ ንግግር አምላክ የለም ብለው ለሚያምኑት እንጂ፣ አምላክ መኖሩን ለተቀበሉ እንግዳ አይሆንባቸውም። ምክንያቱም መቶ ሚሊዮን የእግዚአብሄር ህዝብ ላይ ስልጣን ኖሮት ሁሉን የሚያደርግ አካል፣ የእግዚአብሄር ልጆች ሆነው ሳሉ፣ ከውጪም ሆነ ከውስጥ የተነሳ ቢሆን በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ የማይገባቸውን

ሊያደርግባቸው ስልጣን ከየትም ሊያገኝ አይችልምና፣ ሌላም ደግሞ ያሁሉ የእግዚአብሄር ልጅ ስለመሪው ወደአምላኩ ቢያመለክት አንድ ሰው/መሪ ከዛ ሁሉ የእግዚአብሄር ልጅ በልጦ ፀንቶ ሊቆይ አይችልምና።

ባለስልጣን ብሎ ይናገራውቸ እንጂ እንደመፅሀፍ ቅዱሱ ውስጣዊ ትርጉም ገዢዎች ሳይሆኑ ተገዢዎች ናቸው። ህዝቡ በእግዚአብሄር በኩል በፀሎት የሚገዛቸው፣ ህዝቡ ወደእግዚአብሄር ካመለከተባቸው ለሰአት ሽራፊ ፀንተው ሊቆሙ የማይችሉ፣ ህዝቡ ከእግዚአብሄር መንገድ ወጥቶ ክፉዎችን ካነገሰበት እግዚአብሄር እስካለ ድረስ የሚፀኑ ታዛዥ አካላት ናቸው ገዢዎች።

የኛም የዛሬው ነገራችን ሁሉ እንዲሁ ነው። በሀገራችን ሁኔታና በፖለቲካው በአስተዳድሩ ጉዳይ አምላካችንን ለሽራፊ ሴኮንድ በእምነት ልንጠይቀው ወደን አናውቅም። በራሳችን መንገድ ስንንፈራገጥ ከጥንት ለእግዚአብሄር በነበረን ቅርበት ቂም የያዘ አጋንንት የሰፈረባቸው ዘረኞችና ከሀዲያን መስፈኛ ሆነን ይኸው ለውድቀታችን ስንርመሰመስ እንገኛለን።

ከሁሉ በፊት የኛን ከአምላካችን ያለን ግንኙነት አስቀድመን ልናስተካክል፣ በንሰሀ በይቅርታ ተመልሰን የረሳነውን አምላክና በሱ ፈቃድና መንገድ የመኖርን ባህልን መልሶ መገንባቱን ከምንም በላይ አስቀድመን ልንለፋና ልንሰራበት ይገባናል፣ ወደአምላካችን ቀርበን ይቅርታን ያወርድልንና ሀገራችንን ያስተካክልልን ዘንድ እጅግ ፀንተን ልንለምነው ይገባናል።

ይሄ እንደዘመኑ ፖለቲከኞች "አብሮ የመኖር፣ የእምነት እሴቶችን እንገንባ..." በሚል አነጋገር የተፃፈ ፈፅሞ አይደለም። ነገር ግን ሀያል የሆነ ፈጣሪ እራሱ በአካል ስላለ፣ ና እርዳን ድረስልን ብለን ልንጣራ ይገባናል ነው የሚለው። "እምነት መኖር ለሰላምና ሳይኮሎጂ ጥሩ ነው..." ምሚል ከሀድያን ጭምር የሚናገሩት ከንቱ የውስጠ ክህደት

ንግግር አይደለም። ራሱ እንደኛ ያለውን ሀያል ፈጣሪ እርዳታ እንለምን የሚል እንጂ !!!! አይኑ በኛላይ ነውና፣ ንግግራችን በሱ ቁጣ ቃል ከሚጀምር፣ በኛ የይቅርታ ልመና ቃል ይጀምር ለማለት ነውንጂ፣ በቃሉ አስቀድሞ የነገረን ቁጣው ከመምጣቱ በፊት እንለምነው ለማለት ነውንጂ።

ምነው እግዚአብሄር የለም እንዴ? ታዲያ ሁላችን ተሰባስበን በአንድነት በይቅርታ ብንለምነው ምን ይሁን ብሎ ዝም ሊለን ሚቻለው ይመስላችኋል? የሁሉ ባለቤትና ፈጣሪ ጌታ ሆኖ ሳለ ለኛ ምኑም ላልሆንነው ጥቃቅን ፍጥረቶቹ ጥቃቅን ነገር ለማድረግ ምን ቸግሮት? ስንት ሊረዳን ሊቀርበን የሚፈልግ አምላካችን ያለበሰንን ስጦታው የሆነ ነፃ ፈቃድ ስላለን እሱን አፍርሶ ጣልቃ ስለማይገባ "አንኳኩ ይከፈትላችኋል" በማለቱ እንጂ ቀድሞስ ሊረዳን ሊያግዘን መች ወደኋላ ብሎ ያውቅና?

ዛሬም ሀገራችን በምን ስጋት ላይ ብትሆን፣ ምንም ብንፍጨረጨር ብንጯጯህ ብንተጋ፣ ከመሰረቱ አንድ ከሚያደርገን ፈጣሪያችንና አባታችን ጋር በንሰሀ በፍቅር ተዋህደን ከሱ እርዳታን ካልጠየቅነው፣ መሰረታችንን ካላደስን የትኛውም መሪ፣ የትኛውም ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢመጣ ሊያድነን የሚቻለው አይኖርም። ቀድሞውንም ክፉ መሪዎች የታዘዙብን ከሀያሉ ነውና፣ ያንን ትእዛዙን ካላስለወጥነው በኛ በምድር ብናሳምር ያው ተመልሶ ትእዛዙ መፅናቱ አይቀርምና።

ለምድር ለምድራዊነትማ ምናልባትም ከአቢይ በላይ እንደሚናገረው ቅንነትን የተላበሰ፣ ሁለገብ፣ አስተዋይ፣ ዝቅ ብሎ ከፍ ማለትን የተካነ ትሁት መሪ አይገኝልንም ይሆናል፣ በሱ ሙሉ ባለፈልን ነበር። እንደሚባለውም ምናልባት ጀግና ሊሆን ይችላል፣ የትም ሊገኝ የማይችል ታላቅ ጀግና! ነገርግን ጦርሜዳውን የተሳሳተ ጀግና። ሙሉ ትጥቅና ጀግንነቱን ይዞ ጠላት በሌለበት በተሳሳተ ጦርሜዳላይ ሄዶ የቆመ የባከነ ጀግና! ምናልባት እስካሁን ስንት ነገር ሰርቷል፣ ስንት

አስታርቋል፣ ስንት ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ተአምር አከናውኗል ይባል ይሆናል። እውነት ነው፣ ነገርግን ይሄ ሁሉ መጠጋገን፣ ማከም ሁሉ በዚሁ ያለፈጣሪ መንፈራገጣችን ከቀጠልን አሁንም አይቀሬ በሆነው በትንቢትም የተነገረው በሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ፅኑ ነውጥ መደረማመሱ፣ መንደዱ፣ መፈንዳቱ ካልቀረ ዛሬ ምን ተአምር ቢሰራ ምን ትርጉም ሊኖረው? አፋፍ ላይ ልትወድቅ ያለችን እንቁላል በቀለም፣ በጌጥ ምን ቢይሳምሯት ምን ቢያሸበርቋት ተንከባላ ወድቃ መፈረካከሷ፣ መበለሻሸቷን ሊያስቀሩላት ካልቻሉ ያ ሁሉ ድንቅ ተግባር ለጊዜው እንጂ ምኗ ሊሆንላት ነው? እሱንም ሳይቀር ቀድሞ እያወቀው እዚህ ቦታ መርቶ እንዳመጣው የሚያምነው ፈጣሪውን የሁሉ ከሀሊ ፈጣሪያችን ዘንድ በአንድነት ፊታችንን አዙረን እርዳታውን እንድንጠይቅ በአባቶች በኩል እንኳን ካላስተባበረን፣ እውነት እንዲህ የሚለውን "ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።

" ቃል የተናገረ ሀያል ፈጣሪ እርዳታውን እንድንጠይቀው ይጠባበቀናል ብለው የሚተማመኑ ሰወች በበዙበት ሀገር ሆኖ ሳለ ሁሉም በጋራ የሚወደውን ፈጣውሪን ለሀገሩ በሱባኤና ምህላ እንዲለምን የሚያስተባብር ካልሆነ፣ ጦርሜዳውን የተሳሳተ መና ጀግና ነው ማለት ነው። አልሞ የማይስት የጀግኖች ጀግና የሆነ አንድ ሰው ቢኖር፣ ጠላት በመጣ ጊዜ ግን ትጥቁን ትተቱን ሁሉ ሰብስቦ ተጉዞ ጠላት በሌለበት መና ቦታ ላይ ቢገኝ ለማ ሊሆን? ከንቱነት፣ ውድቀት፣ ለጠላትም ብርታት ነውንጂ።

በመንፈሳዊ መነፅር የአለምን መንግስታት እንቅስቃሴ፣ የግሎባላይዜሽኑን መንገድ፣ የሀገራችንን ሁኔታ ሊያየው ካልቻለ፣ እውነትም ጦርሜዳውን ፈፅሞ የሳተ፣ ጠላት ባልዋለበት የወጣ የባከነ ከንቱ ጀግና ነው።

**የሩሲያው መሪ ቭላዲሚር ፑቲን እንኳን በዛ ውስብስብ ትርምስ የሀያላን ስጋዊ ሽኩቻ ውስጥ ተጠምዶ የሚኖር ሆኖ ሳለ፣ ከኛ የዘመኑ የሀይማኖት መሪዎች በተሻለ አዲሱን የአለም መንፈስ፣ እንዲሁም ግሎባላይዜሽን መንፈስና እውነተኛ ቀለም እንዲህ ሲል በደንብ ገልፆት ነበር።**

***“ ሀገራት ሁሉ እምነታቸው፣ ባህላቸው ሁሉ እየታጠበ ወደ አንድና ተመሳሳይነት እየተለወጡ ብዙ የአውሮፓ ሀገራትን ተመልክተናል። ድሮ ድንቅ ታሪኮች የነበሯቸው ልዩ ማንነት የነበሯቸው የአውሮፓ ሀገራት አሁን እንደምናየው ራስን ማጣትነትና፣ በቀደመው ክርስቲያናዊ ባህልና ታሪካቸው የሚያፍሩና የሚሸማቀቁ ትውልዶች እየተፈጠሩባቸው በአይናችን አይተናል። በዚህም መልኩ የአለም ሀገራት ሁሉ በአዲስ ማንነትና እምነትአልባነት ወራሪ ባህል የሚገፉበት አስፈሪ ወረርሽኝ ውስጥ እየገቡ ይገኛሉ። ”***

ብሎ ነበረ ባልተጠበቀ መድረክላይ ከሁላችን በበለጠ መረዳት የገለፀን። ቢያንስ የከፋውን ወራሪ መንፈስ አቅጣጫ ተረድቶታል፣ ምንም እንኳን እሱም ቢሆን ከስጋ መሯሯጥ ያለፈ መፍትሄን ሊፈይድ ባይቻለውም። የኛ መሪዎች ግን በምንም መልኩ አለምንና በውስጧ ያሉትን ወራሪ አጥፊ መንፈሶች ሊረዷቸው አልቻሉም። አለ ብለው ያመኑትን የሁሉ ፈጣሪና ወሳኝ የሆነው ታላቁን ሀይልም ከግምት ሊያስገቡት አልተቻላቸውም።

በስውር ያለ ጠላቱን መኖር ያላወቀ አካል እጅግ በከፋ መልኩ የጠላቱ ባሪያና ተጎጂ እንደሚሆነው ሁሉ፣ አብይም ቢሆን ለዚህ መንፈሳዊ ጠላት ከቦታ ሳይሰጥ፣ ሎሌዎቹ በሆኑ የውጭ ሀይላትን ለሚያስፈፅመው ጥፋቱ አይኑን ጨፍኖ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ሀገራችንን ጠምዝዞ በጠላት መዳፍ ውስጥ የሚያስገባት ይሆናል። በሚያደርገው ነገር ሁሉ ሀገራችንን ኢትዮጵያው የሚያጠፋና አሳልፎ የሚሰጥ ይሆናል። ይህም እንዲሁ ፍርሀትና ወሬ አይደለም። ገና ከጅማሬው እያደረገው ይገኛል። ሀገሪቷ ለመቶ አመታት በደህ

ጉልበቷ በደሟ ያሳደገቻቸው፣ ስሮቻቸውን አስፍተው አጥልቀው የዘረጉ የሀገሪቷ ምሶሶ የሆኑ ድርጅቶቿን በማይመለስ መልኩ በቋሚ ባለቤትነትን ለውጪ አካላት መስጠትን በውጪዎች አማካሪነት የመጀመሪያ እርምጃው አድርጎ ተነስቷል። በኢትዮጵያ ህዝቦች ለትውልዶች በስኬት ሊያወርሷቸው የተቻላቸው ብቸኛ የሀገር ሀብት የሆኑት እነዚህ ከመቶ አመት በላይ ትውልዶች ለኢትዮጵያ ብለው ገንብተው ለኛ ያደረሱንን አይደለም ጊዜ የደረሰው ባለስልጣን እኛም ልንሸጣቸው መብቱ ባልኖረው ነበር።

በስጋዊ እይታ እንኳን ምንም ምክንያት የሌላቸው፣ የውጪዎች ጫናና ተፅእኖ ስላየለ ብቻ የምናደርጋቸው ተግባራት ኢትዮጵያን እንደጨው አሟሙቶ በሁሉ ነገሯ፣ አለሙን መስላ እምነቷም ባህሏም በሙሉ መልኳ አለሙን እንድትመስለው፣ በቴክኖሎጂም፣ በኢኮኖሚም ተፅእኖ አሟሙቶ አጥፍቶ የሚቀላቅላት፣ የዘመኑ መሪ ክፉ አስካጅ ክፉ መንፈስ ስራ ነው። በስጋም ወደበለጠ ባርነትና ፀያፍ ብዝበዛ፣ ባለቤት አልባነት የሚመራ ነውንጂ እሱም ቢሆን ለኢትዮጵያ እውነተኛ ጥቅም ኖሮት አይደለም።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሀገራችን እጅ ሆኖ፣ በራሳችን ያሳደግነው ከሀገራችን አልፎ የአፍሪካ ኮከብ የሆነ፣ ካሉት እጅግ ትርፋማ፣ ባለተስፋ የሆነ ጠንካራ ድርጅት ሆኖ ሳለ ምንም ችግር ሳያጋጥመው ለቋሚ ለሽያጭ ለውጪ ዜጎች መቅረቡ፣ አይደለም እሱ ሊሸጥ፣ ይልቅ አልፎ የሌሎች ሀገር አየርመንገዶችን በፐርሰንት ባለቤትነትን እስከመያዝ የደረሰ ጠንካራ ሆኖ ሳለ እሱን ራሱ ለሌሎች መሸጡ ምን ይሆን ትርጉሙ? ምን የምንዛሬ እጥረት፣ ምን ችግር ቢመጣ እንዴት ተሸጦ ይበላል? በገንዘቡስ ከዚህ በላይ ትርፋማ ተቋም ሊሰራበት ነውን? ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በላይ? ህዝቡ ተቸጋግሮም ቢሆን ይህን ጊዜ ያልፈዋል እንጂ ወደፊት ተስፋው የሆነን ዘርን ገበሬው በማይበላባት ሀገር እንዲህ ያለ ስራ ምን ማለት ነው? ለተፅእኖ፣ ለባእዳን፣ ላሰፈሰፉት ተንበርካኪነት ነውንጂ።

የቀድሞውን ጨምሮ ሁለቱም የአየርመንገዱ ሀላፊዎች አምርረው እየተቃወሙ ድምፃቸው ታፍኖ በግርግር ለውጪዎች መተላለፉ ምን ትርጉም ያለው ነው?

በደሀ ሀገር ላይ ይህንን የመሳሰሉ ተቋማት ሊኖሩ በማይችሉበት ሁኔታ ቀድሞውንም ይህን አይነት ድርጅት ሊቆም የቻለው ኢትዮጵያዊ ሰራተኛውና ሀላፊው ሁሉ ፅኑ በሆነ የሀገር ፍቅርና መስእዋትነት በሚሰራና በደስታ መስእዋትነት ከልቡ የሚደክምበት በመሆኑ ስለሆነ ነውንጂ፣ ተሸራርፎ ለውጪ ነጋዴ ተላልፎ ቢሰጥ ይህ ሀይሉ እንዴት እንደሚደክም መሪዎቹ ሳይቀር የሚመሰክሩት ነው። ለህዝቡም ኩራት የሆነና በነፃ ለብሶ፣ ለጥፎ ቢያስተዋውቀው የማይጠግብ ሀብቴ የሚለው የሀገሩ ነፀብራቅ በመሆኑ አልነበርንዴ? እንደ ግድቡ ያሉ ሙሉ በሙሉ በኛው ገንዘብ የተሰሩ ብለም የምንኮራበት ነገር ለመፍጠር፣ የሀገር ፍቅር ለማጠናከር ስንት ጥረት እየተደረገ፣ ገና ለገና ህዝቡ መርምሮ የማይረዳ በመሆኑ የዚህ አይነት ሀገር መሸርሸርና ምሶሶ ማፍረስ ውስጥ ለውስጥ ያለምንም ጠያቂ ሲሰራ እንዴት ያሳዝናል?

በኢትዮቴሌኮምስ በኩል? እያንዳንዱ ህዝብ ሁሉ በሳምንት እስከ ሶስቴ ካርድ በመግዛት የሚፈጀው ገንዘብ፣ ወደመንግስቱ ሄዶ ያው ተመልሶ መንገድ፣ ደሞዝ፣ ሆስፒታል፣ ዩኒቨርሲቲ የሚሰራበት በመሆኑ ነውንጂ ህዝቡ መች የገንዘቡ ብዛት ሳይታየው ቀርቶ ኖሯል? ታዲያ ይህንን ትልቅ ተቋም ለውጭ ነጋዴዎች በመሸጥ ይህንን ከትንሽ ከትልቁ ሁሉ የግብር ያክል በገፍ የሚሰበሰብ ገንዘብ ቀጥታ ወደውጭ ሀገር ፈሶ፣ የተረፈው ነጭ ነጋዴ መኪና ደራርቦ ሚገዛበት፣ ገንዘብ የተረፈው ባእድ ሀገር እኮኖሚ የሚሰባበት ማድረግ ምን ያህልል የመንፈስ ግርዶሽና ባርነት ነው? ያገልግሎት መሻሻል ያመጣል በሚል ስብከታቸው አስክረው ትልቅ ተፅእኖና ጫና ያለው የሆነውን የሚሰበሰበውን ገንዘብ መዳረሻ ወደራሳቸው ጋን ሲያዞሩ አጨብጭቦ መቀበል ምን የሚባል ነው?

ድርጅቶቹ በመስእዋትነት ለሀገራቸው የሚሰሯቸው ተግባራትስ? በመንግስት ትእዛዝ አደጋ በሚኖሩባቸው ጊዜያት፣ እልቂት ለማስቀረት የኢንተርኔት አገልግሎት በማቋረጥ፣ በፈተና ጊዜያት፣ በሌሎችም ብዙ መስኮች ገቢያቸውን ሰውተው ለሀገራቸው የሚያደርጓቸው ስራዎችስ? መብራት ሀይልስ ለግል ነጋዴዎች ተሸጦ በገጠር፣ በራቁ ቦታዎች ሁሉ በመስእዋትነት ለመዘርጋትና መገንባቱ ቀርቶ “ያተርፈኛል/አያተርፈኝም” በሚል ስሌት ሊቃኝ አይድል? ድህው እኩል ባለቤት የሆነባቸው ትልልቅ ግድቦቹን ጨምሮ ለውጪዎችና ጥቂቶች ይሸጥ እየተባለ አይደል?

ሌላው ተፅእኖ ቢቀር እንኳን በህግ የተፈቀደ ሞኖፖሊና ጥንካሬን የተላበሱትን እነዚህን ድርጅቶች በሀገር ድጋፍ ከያዙት ልቅ ሀይላቸው ለውጪ አሳልፎ ሰጥቶ በሀገራችን ላሉ ሌሎች ድርጅቶች፣ ለሀገራችን ሌሎች የግል ተቋማት ድቀትና የወደፊትም ቋሚ ስብራት እንዲሆን አይደል መቻኮሉ? የሀገር ባለቤትነታችንስ ምን ሊሆን ነው?

ይህ ሀገራት በብድር እዳ ሉአላዊነታቸውን ሲያጡ የሚገቡበት ግዳጅ፣ እንዲሁም ድርጅቶቻቸው ሲከስሩ የሚጥሉበት መንገድ ሆኖ ሳለ፣ ገና ለገና ህዝቡ መርምሮ አይመለከትም፣ ጊዜው ግርግር በመሆኑ ማንም ጠልቆ ልብ ሳይለው እንቀራመት ባሉ ባለተፅእኖ ሀገራት ውትወታ በራስ እጅ አሳልፎ መስጠት ምን የሚባል ነው? በዚህ መሰረት ሀገሪቷን ከስር መሰረቷ አሟሙቶ አጥፍቶ የመላው ስጋዊ፣ ክህደት መንፈስና አለም ውስጥ የማዋሀድ ሂደት አይደለምን? ለምን ብለን ሳንጠይቅ የቀድሞዎች ያቆሙትን ለማፍረስ እንሮጣለንንጂ፣ ሀገር ጎዳ የተባለው መለስ ዜናዊ እንኳን ደፍሮ ያላደረገው፣ ሀገር ሉአላዊነት ይደመስሳል ብሎ እጅግ የሚፀየፈው ተግባር አይደለምን? ክፉ ክፉው ሲሆን ብቻ ከሌሎች እንወስዳለንንጂ ቻይናስ ብትሆን ያንን የሚያክል ፅኑ ኢኮኖሚና ጥንካሬ ይዛ እያለች እጅግ በፍርሀት የምታርቀው ይህ ለውጪዎች መሸጥና፣ በጃዙር ምእራባውያን እጅ ለሚገባው ለነጋድያን ማሳለፍን አይደለምን? አይደለም እንደኛ ሀገር ያለች ትንፋሽ የሚበትነው

ኢኮኖሚና እውቀት ጥንካሬ ያላት ሀገር ላይ።

በዚህ መልኩ ጨምሮም በብዙዎች መንገዶች ኢትዮጵያዊነትን፣ እምነትና የእግዚአብሄር ልጅነትን፣ ለማጥፋት የሚታትረው መንፈስ፣ እኛም ሆንን መሪዎቻችን ለይተነውና እውቅና ሰጥተነው በመፃረርም ከአምላካችን ወገንነትን እርዳታን ካልያዝን መቼም ቢሆን በስውር እጃዙር አውሮ ዞሮ ዞሮ ውድቀታችን ላይ ያደርሰናል።

በስጋ አይን በሀገራችን ታሪክ በጥቂቱ በጥቂቱ የሚገኝ እንደ አቢይ ያለ ባለፍቅር ሰው፣ አዋቂ፣ ሁለገብ፣ ትህትናን የመረጠ፣ በሳል፣ ከእውቀትም ከልምድም በላይ መሰረት የሆነውን ቅንነት እጅግ የተላበሰ ሙሉ ሰው ብናገኝ እንኳን፣ መንፈሳዊውን የአለም አሰላለፍ ካላወቀ፣ እግዚአብሄርን ካልያዘ፣ የአለም ፈጣሪና ባለቤት የሁሉ ወሳኝ ለሆነው አካል ምንም ቦታ ሳይሰጥ፣ በስራው ሁሉ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ከሰራ ምንም ቢሆን ባልፈለገውና ባላሰበው መንገድ ሀገሩን እየገደለ፣ ሁሉ በጁ እየተፈረካከሸ ዞሮ ዞሮ ወደድቀት መሄዱ አይቀሬ ነው። ምንም ጥርጥር የሌለው የማይቀር ነገር ነው። አይደለም ለሀገር ለራሱም አይሆንም። እሱ በግሉ በቅንነት ቢሰራ እንኳን በዙሪያው የሚሰበሰቡ ሰወች፣ በዘር የሚጠራሩ ባለስልጣናት የመንግስቱን ሙሉ ስራ በሌላ መንገድ እንዳይሰሩት ምንም አያግዳቸውም። እሱም ራሱ ቢሆን፣ መረጃ የሚያገኘው፣ ምክር የሚያገኘው፣ ባጠቃላይ ኢትዮጵያን የሚያውቃት በዙሪያው በተሰበሰቡ ተመሳሳይ ሰወች በመሆኑ፣ በራሳቸው ተረት አየር ላይ ሊያንሳፍፉት፣ በምድር የሌለ ሌላ አለም ውስጥ ሊከቱት ይችላሉ። ከነሱ መንገድ በወጣ ጊዜ እንኳን ሊታዘዙት ሙሉ በራሳቸው መንገድ ሄደው እሱም በፍርሀት ሊያያቸው እንደሚችል ጥርጥር የለውም። ለዚህም መንገዳችንም ምስክር እንዲሆን መሪዎች ሁሉ ከህሊናቸውና ካመኑበት መሆን እንዳልቻሉ ያደባባይ እውነት ነው። ለዚህም ነው ሁልጊዜ ዛሬ ለተናገሩት ነገር ነገ በተፅእኖ ይቅርታ ሲጠይቁ ሲያስተባብሉ የሚታዩት። በአሰራርና አመራራቸውም ከዚህ የወጣ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። የትኛውም መሪ ቢሆን። ትልቅ ጎርፍ

ውሀ ላይ ተንሳፎ ውሀውን ወዲህ ሂድ፣ ወዲያ ሂድ ብሎ አቅጣጫ ሊሰጥ የሚቻለው ማነው? ከበታቾቻቸው ያሉ ተመሳሳይ ሰወችም በዚሁ መልኩ ነው የሚያኖሯቸው። በምድራዊነትና ስጋዊ ትርምሳችን በምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከዚህ የወጣ ውጤት ልናመጣ አንችልም። አለሙ የምድራውያን ብቻ የሆነ ይመስል፣ ሌሎች ሀያላን በመሀላችን የሌሉ ይመስል እንዲሁ አይናችንን ጨፍነን የምናደርገው ትርምስ ሁሉ የትም የሚያደርሰን አይሆንም።

ከጠላት ክፉ፣ የቅርብ እንደሚባለው፣ መኖሩ ያልታወቀለት ጠላት በፅኑ ጥፋት እንደሚያሰቃይ ሁሉ በራሳችን ፈቃድ "ብትኖርም እንርሳህ" ብለን ከሀሳባችን ያወጣነው አይናችንን የጨፈንልለት የጨለማው መንፈስ እንደልቡ ሲያሰቃየን ይኖራል፣ በያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን አብሮ ተቆራኝቶ፣ የገዛ አእምሯችን ጭምር ሆኖ ባሪያ ያደርገናል። በዚህም መሰረት አብይም ቢሆን በእይታና እርምጃው ሁሉ ይህንን ጠላት ሳያገናዝብ፣ ከፈጣሪው ህብረትን ከሁሉ አስቀድሞ ሳይዝ በሚያደርገው ስራ ሁሉ ውድቀትን ይሆናል የሚያመጣልን። የነካው ሁሉ እንደ አሽዋ ሸክላ የሚፈረካከስ ይሆናል፣ አእምሮው በሱ እጅ አይደለምና ዛሬ ሌላ ሰው ነገ ሌላ ሰው ያደርገዋል፣ ባላሰበው መንገድ ህዝቡን ሀገሩን የሚጎዳ ይሆናል፣ ጥረቱ ድካሙ ህልሙ ሌላ የተግባሩ ውጤት ደግሞ ተአምር በሚመስል መልኩ ፍፁም ሌላ ይሆናል። ልቡም በከንቱ ይሸፍታል፣ አይኑ ይጋረዳል ስራው ሁሉ ያለፈቃዱ የጥፋት ይሆናል። እንደዛ ያለ ቅን አሳቢ ከለት እለት በመልካም ሀሳብ በፅኑ የሚደክም ደግ ሰው በዚህ መልኩ ፍሬው መና ሲሆን ማየት ልብን ሰብሮ በእንባ ያረጥባል። ነገር ግን በዚህ ሰይጣን ስልጣኑን ባፀናበት አለም ውስጥ ፈጣሪን በግልፅ ሳይዙ፣ የሚሰሩ ድርጊቶችም ህዝቡን ከአምላኩ ያርቁ አያርቁ ገድ ሳይሰጡ መኳተን ትላንትም፣ ዛሬም ነገም የማይቀየር እውነቱና ውጤቱ ይኸው ነው። ወደድንም ጠላንም እግዚአብሄርን ያልያዙ፣ ህዝባቸውን ይዘው ከፊቱ ያልቀረቡ መሪዎች ይኸው ናቸው። ያውም ድፍን ህዝቡ ሙስሊሙም ክርስትያኑም አባቴን አገኛለሁ ብሎ የተከተለው መንገድ ቢለያይም ሁሉም አንድ

ፈጣሪውን አምላኪ በሆነበት፣ በህያሉ ፈጣሪና በሚወዳቸው ልጆቹ መልህ የቆሙ ናቸው። ቁስላችን ስብራታችን ናቸው፣ በዘመናቸው የሚፈጠረውንም ትውልድ በክህደት መንገድ በማነፅ ጊዜ ባለፈ ቁጥር ይበልጥ ከአምላክ እየራቅን እንድንሄድ አድርገው ሞታችን ጋር የሚያደርሱን ናቸው።

መሪማ አለ፣ እውነትም ለህዝቡ የሚያዝን ለህዝቡ ፍላጎትና አላማ መቃናት እንቅልፍ የሌለው። በጥንት ጊዜ የኢትዮጵያ ክርስትያን ህዝብ በእምነቱ አብቦ ጠንክሮ ይኖር የነበረበት ጊዜ ሰፊ ነበር። በተሰቀለልን ክርስቶስ እውነተኛ ፍቅር የተነኩ፣ እጅግ የወደዱት ቤተልሄም ድረስ በመሄድ፣ ቀራኒዮ ድረስ ኢየሩሳሌም ድረስ በእግራቸው በመጓዝ የኖረባትን ምድር በህይወት ዘመናቸው ለመረገጥ ራሳቸውን ለአደጋ ሰጥተው በመሄድ በወንበዴዎች፣ በዘራፊዎች፣ በብዙ ነገሮች ህይወታቸውን ያጡ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን አይቶ ዓፄ ዘረያዕቆብ ሊያስቆማቸው ባይችል እንኳን በሶስትመቶ ግመል አፈሩን ጭኖ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ህዝቡን ሊታደግ የሚሰራ መሪም የነበርን ጊዜ ነበር። እንደ ቅዱስ ላሊበላ ያሉት ደግሞ ራሷን ኢየሩሳሌምን አስመስለው በሀገራቸው በሰፊው በመገንባት፣ እስከነ ዮርዳኖስ ወንዝን ሳይቀር በመስራት ዳግማዊ ኢየሩሳሌምን እዚህ በመስራት ህዝባቸውን ይታደጉ ነበር። እነሱም በሄዱ ቁጥር አፈሩን ለህዝባቸው ጭነው መምጣት የተለመደ የጥንት ነገስታት ስራ ነበር። መቼስ እነሱ እንደው "እምነት ነው የሚያድነው፤ ባይሄዱም ችግር የለውም" የሚለው እኛ የዘመናችን ትምክህተኞች እንደጅሎች አይተን ልንመፃደቅባቸው እንደምንሯሯጥ ግልፅ ነው። ካለማወቃችን ደግሞ ትቢታችን! እነሱማ መች ይህ ጠፍቷቸው? ለነሱማ መፅሀፍ ቅዱስ ትምህርታቸው፣ ሳይንሳቸው፣ እውቀታቸው፣ የስልጣኔ አርማቸው ሆኖ እስከ 43 አመታት በሚደርሱ ትምህርቶች የተራቀቁበት ናቸው። ደግሞ እኛ የት የዋልንበትን? ለነሱ ይህንን አንነግራቸውም። እነሱም ቢሆን እዚሁ ሆነው እንደሚድኑ ጠንቅቀው ያውቁታል። መዳኑን አይጠራጠሩም፣ እንደኛ ብርቅ አይሆንባቸውም። ከመዳን ሀሳብ አልፈው ፍቅሩ

ቢፀናባቸው ነውንጂ። ክርስቶስ የረገጠው አፈር ቢናፍቃቸው እንጂ፣ የተጠመቀበትን ውህ መንካት በመናፈቃቸው እንጂ።

በጊዜው ከነበሩት የኢየሩሳሌም መሪዎች ይልቅ፣ የኢትዮጵያውያንን ይህንን ፅኑ ፍቅራቸውን የተመለከተው የሙስሊም መሪ ሳላህዲን ነበረ ይልቅ አዝኖ ለኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም በነፃነት እንዲሄዱ የፈቀደላቸውና የነጠቋቸውምን እስከዛሬም ድረስ ዴር-ሱልጣን የተሰኘውን ይዞታቸውን የመለሰላቸው።

ብዙ የኢትዮጵያ ንጉሶችም ህዝቦች ከልባቸው የሚያምኑባቸውን የሚወዷቸውን ነገሮች በማክበር ነበር የሚታወቁት። ለዛም ነበር የኢትዮጵያው መሪም፣ ጥንት ሙስሊሞች በስደት በመጡ ጊዜ ቃላቸውን ሰምቶ፣ ከልባቸው የሚፈልጉትና የሚያምኑበት መሆኑን አይቶ ጥበቃ ያደረገላቸው፣ ሀሳባቸውን እንዲሰሩ ያመቻቸላቸው። የህዝብ መሪዎች ስራቸው ይህ ነውና።

ዛሬ የድፍን አማኝ ህዝቡን ፍላጎት ሳይሆን፣ የአለምን ጨፍላቂ ተፅእኖና መንገድ በመከተል፣ ከሀገሬው ነዋሪ የራሱ ፍላጎት የበቀለ ስርአት ሳይሆን ከሀዲያን ሀገራት ህዝቦች ለግል ለራሳቸው ራሳቸው በሚመች በፍላጎታቸው ላይ ባቆሙት የአስተዳደር ርእዮት፣ ያልተሰፋልንን ካላለብናችሁ ብለው የሚታትሩ መሪዎች፣ ሌሎች አማኝ ሀገራት እንደዚሁ እንደኛ ሞክረውት ግን ተሳክቶላቸው እምነትና ማንነታቸውን አጥቦ ባዶ ያስቀራቸውን መንገድ፣ ባእዳኑን ያስመሰላቸውን መንገድ፣ አብይም ሆነ ማንም ቅን ሰው በሀገራችን ቢሞክረው የማይሳካ ነገር ነው። “የተባበሩት ምስራቅ አፍሪካ” መፍጠር፣ ከአለሙ መዋሀድ፣ ከሁሉ አላማ አስቀድሞ በኢኮኖሚ መበልፀግ፣ ወዘተ እንደ አቢይ በስጋ ብቻ ለሚያስብ ሰው የቅንነት የደግነት አላማ ቢሆንም፣ ልጆቹ የሆንን፣ አይኑ በኛላይ የሆነ ፈጣሪ ባለበት አለም ግን ከሱ የሚያርቀን፣ ማንነትና እምነታችንን፣ ሀገራችንን አሟሙቶና ቀላቅሎ ከሌላው ከሀዲ አለም ጋር አንድ የሚያደርገን ነገር ፈፅሞ በኢትዮጵያ አይቆምም። ሀገራችን ለሺ

ዘመናት የህዝቦቿ አስተዳደር ከፈጣሪ አምልኮ ቤት ጋር ተለይቶ አያውቅም ነበር። በሺ አመታት ቆይታ አንዴም፣ አንዴም እንኳን በጠላት እጅ ሳይወድቁ፣ ቅኝ ሳይያዙ በአለም ታሪክ በብቸኝነት መኖር ቀልድ አይደለም። ያለምክንያትም አልመጣም። በዚህ የምትታወቀው ሌላኛዋ ሀገር ሩሲያ እንኳን በሞንጎሎች ወረራ ጠፍታ ነበር። ይህም ከእግዚአብሄር ጋር የተሳሰረ አስተዳደር እስከ ሀይለስላሴ ጊዜ ድረስ የለመቋረጥ የቀጠለ ነበር። ነገርግን ሀይለስላሴ ልባቸው ወደእንግሊዝ ሸፍቶ የነሱን ገልብጠው፣ ሊቃውንት አባቶችን አትቀው ያለሀያሉ ፈጣሪ ሀይልነት ራቁቱን የቆመ አስተዳደር ሀገራችን አሀዱ ብላ ከጀመረችበት ከዛ ጊዜ ጀምሮ፣ የድፍን የህዝቦቿን አምላክ ፈጣሪያችንን ከአስተዳደሯ አግልላ፣ ከሀገራዊ ግቧ ሰርዛ በሌላ ተክታ ከያዘች ጀምሮ ኢትዮጵያ የቁም ቅዠት ውስጥ ገባች።

በቅፅበት ለባእድ ጦር ተንበረከከች ከሶስትሺ አመታት በላይ የቆየ ስርወመንግስቷ ብትንትኑ ወጣ፣ ከዛን ወዲህ ሁሉ ተገለባበጠ፣ ለትውልድ የሚፃፍ ታሪክ በአውሮፓውያን እይታ እየተቃኘ ተገለባበጠ። አባቶቻችን አማኞች በመሆናቸው፣ ወንጌል “የስልጣን ምንጭ እግዚአብሄር ነው” በሚለው ቃል የታመኑ፣ የፈጣሪን ቃል ፈፅመው የሚያምኑ በመሆናቸው ከአስተዳደራቸው ፈጣሪና አምላካቸውንና እምነትን ያቀረቡበት ምክንያት ይህ ሆኖ ሳለ፣ “በአምባገነንነት ለመንገስ፣ ጥያቄ እንዳይነሳባቸው” በሚል ተተካ። እሱንም ስትለቀው “ኢትዮጵያዊ” መንግስትና ሀይል ከሀገሯ ተኖ ጠፋ። አረመኔ ሰው በላ መንግስታት ተፈራረቁባት፣ ህዝቦቿን ፈጁት፣ የርስበርስ ጦርነት፣ የህዝብ ክፍፍል፣ ጥላቻ፣ ሀገራዊፍቅርና እምነት በደብዘዝ ሆነ፣ ይኸው የጊዜ ጎርፍ አድርሶን እኛም ዛሬ ላይም ቆመናል።

በሀገራችን አስተዳደርም እቅድም ሆነ በስጋዊ አላማ ከድፍን ህዝቡ አባት ፈጣሪያችን ለይተው በሚመሯት መሪዎች፣ በዚህም መልኩ በምናደርገው እንቅስቃሴ መዳረሻችንን ያለመመፃደቅና መታወር

ልናውቀው ይገባል።

በዚህ አካሄዳችን ቀጥታ መዳረሻችን ፍፁም የእምነት ጥፋትና ልቅ ግብረሰዶማዊነት ነው። ይህንን ምንም ሳትመፃደቅ ሐቁን ዋጠው። ያሁኑ መንገዳችን መዳረሻ የኢትዮጵያ ነገዋ ያ ነው። ከትላንት ወዲያ እንኳን በአፄ ሀይለስላሴ ዘመን በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በ አሜሪካም ጭምር እጅግ ከባድ ውግዘትና መጠየፍ የነበረበት ተግባር ነበረ ግብረሰዶማዊነት። የሀገራቱ ፖሊሶች በከፍተኛ ሀይል አለአግባብ ጭምር በዚህ ተከታዮች ላይ በመጠየፍ ድብደባና ግድያ የተፈፀሙባቸው ታሪክ መዛግብት የቅርብ ትውስታዎች ናቸው።

ዛሬም ይህንን የምታነበው አንተ ዛሬም ይሁን ነገ በዛ በእግዚአብሄርና ተፈጥሮ የተወገዘ ተግባር እንደማትገኝ ለራስህ ታውቀዋለህ። ካንተበላይ ደግሞ የዚህ አስፋፊዎችም ያውቁታል። ነገርግን እነሱም የሚሰሩት በሚመጣው ትውልድ ላይ እንጂ ባንተላይ እንዳልሆነ መች ገብቶህ? ትላንት በአሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመንን ጨምሮ በአውሮፓ ሀገራት በግብረሰዶማውያን ላይ ፅኑ መጠየፍና ጥቃት ሲፈፅሙ የነበሩ ዜጎች ልክ እንደኛው ነበሩ። ነገር ግን የነሱ ልጆች ናቸው ዛሬ ያንን በማፍቀር በማስፋፋት፣ በዛ በመጠመቅ፣ በማጥመቅ ትልቅ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙት።

የሩሲያውም ፕሬዝደንት "የአውሮፓ ሀገራት ባለፈው ክርስትያናዊ ታሪካቸው እንዲያፍሩና እንዲሸማቀቁ የሚያደርግ እጅግ ፈጣን የትውልድ ቅየራና አለማቀፍ ተመሳሳይ ባህል ተከላና ወረራ ውስጥ እንገኛለን" ብሎ የተናገረው ይህንን በመረዳቱ ነበረ። የኛም ልጆች ከኛ በምክር ከሚቀበሉት ባህልና እሴት ይልቅ ሙሉ ውሏቸውን በሚውሉባቸው ትምህርትቤቶችና ትርክቶች፣ ብዙው ጊዜያቸውን ካባቶቻቸው ምክር ይልቅ ሲሰብካቸውና ፍልስፍናቸውን ቅርፅ ሲያስይዙላቸው የሚኖሩት የውጪ ፊልሞችና ሙዚቃዎች፣ እንዲሁም ፅሁፎች መሆናቸውን ፈፅመን ልንክደው አንችልም። አስደንጋጩ የአለም ወደዚህ ፍጥነትና ጉዞ ካለው ህብረተሰብ ጋር

በመዳረቅ ሳይሆን ተተኪ ትውልዶችን በመያዝ በመሆኑ እንደኛ ያለነውም፣ በመጮህና በመቃወም የምናስቀረው ብቻ መስሎን፣ ሌሎቹም ሀገራት መስሏቸው አለሙ ሁሉ በሚገርም ፍጥነት እየተወረረ ነው። የኛም ነገ በመሪዎቻችን ማሸብረክ፣ በአስተዳደራችን የፈጣሪ እውቅና አለመኖር፣ በምናደርገው ስጋዊ ሩጫ የነገው ማንነታችን ያ መሆኑ ተቀበልነውም፣ አልተቀበልነውም ፅኑ ሀቅ ነው።

ይህ ፀያፍ ወረርሺኝ ገና ያልተረዳነው ህቡእና ረቂቅ የስርጭት ታክቲክና በግዙፍ መጠን በሀያላን የተደገፈ ስውር የወረራ እንቅስቃሴ በእስልምና ፀንተው እጅግ የሚጠየፉት፣ አጥብቀው የሚያወግዙት የአረብ ሀገራትን ስይቀር አንበርክኳል። ማን ይነግረናል ይህን ወረርሺኝ ፍጥነት? ባህሬን፣ እራቅ፣ ኩዌት፣ ካዛኪስታን፣ ታጂኪስታን፣... ብሎም ቱርክም ሳይቀር የዛሬው ትውልዳቸው ግብረሰዶማዊነትን በህግ ያፀደቁ ሀገራት ሆነዋል። ከኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮችና በጥንት ክርስትና ታሪክ ታዋቂዎቹ ቆስጠንጥንያ፣ ቆጵሮስ፣ ዮርዳኖስ፣ እስራኤል፣ አርሜንያ፣ የድንግል ማርያም ትውልድ ቦታ ሊባኖስ፣ ጆርጂያ፣ ሰርቢያን ጨምሮ፣... ብዙ ሀገራት ይህንን አይቀሬ ወረርሺኝ በህጋቸው አፅድቀው ይዘዋል። ከነሱ ይህንን ከሚጠየፉት ህዝብ በስውር ተፅእኖ ልጆቻቸውን ግን የዚህ ተገዢ እንዳደረጓቸው፣ እኛም እንዲሁ ቆመን ስንመፃደቅ፣ እኛ አናደርገውም ስንል፣ ሀገራችንን የምናሰረክባቸውን ልጆቻችንን ሌሎች በስነልቦና ቀርፀው እንዲያሳድጉልን አሳልፈን ሰጥተናል፣ እንደሌሎቹ ሙስሊምና ኦርቶዶክስ ሀገራት፣ ከፊት እያስፈራሩ እያስፎከሩን፣ ከኋላ ስራቸውን ይሰራሉ። የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ነውንጂ፣ ባሁኑ አካሄዳችን ከቀጠልን እንደተባለው የኛም የነገ እጣፈንታችን ያው ነው። እንደሰውኛ ያ ነበር ጉዟችን።

አለምም ይህንን ጠንቅቆ ያውቀዋል። እንግሊዝን፣ አሜሪካን ጨምሮ ትላንት የዚህ ተቃዋሚ የነበሩት ሁሉ ታሪካቸውን ቀይረዋል።

የጥቁር መብት ተሟጋች፣ የማንዴላ፣ የጋንዲ ታሪክ እንደሚታሰበው፣ የግብረሰዶማውያን መብት ተሟጋቾች ታሪክ ከነሱ ጋር ተቀላቅሏል። "ያለፈ ጨለማ ታሪክ" በማለት በቢቢሲ ዶክመንተሬ የድሮን ዘመን አስከፊነት በመዘከር መልኩ መተረክ ሁሉ አለም የተቀበለው ሆኗል። ህፃናት በታሪክ ትምህርታቸውም ጨለማው ዘመን ብለው ይማሩታል። ይህ ሁሉ ዛሬያችን ነው።

እኛም የተለየን አይደለንም። በዚሁ አካሄዳችን፣ ከቀጠልን፣ ብሎም ያሁኑ የአስተዳደር፣ የሀገራችን ምኞታችን ቢሳካልን በኛም ሀገር ያው እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የሌለው ነገር ነው። በተለያዩ ጊዜያት "የዴሞክራሲ መንገድ" በሚል ስም ተስፋ ያደረግናቸው እድሎቻችንን የሰባበረ አምላክ ምስጋና ይገባዋል። ጠማማ መንገዳችንና የወደቀ ምኞታችንን የነሳን አምላክ ምስጋና ይገባዋል።

97 እንደዛ እንዲያልፍ ያደረገ አምክላ ምስጋና ይገባልዋ። ያለወደብ ቆልፎ ያኖረን እግዚአብሄር ምስጋና ይገባዋል። ሀገራችን ለውጪዎች ሳቢ እንዳትሆን፣ ለብዙ ነገር እንዳይመርጧት እንዲህ ያደረገን አምላክ ምስጋና ይገባዋል። ለዘመናት "አለምን የረሳች፣ አለምም የረሳት" ምሚል ስያሜ እስክትጠራ ድረስ ዝግና ራሷን የሆነች አለም አድርጎ ያኖረን እግዚአብሄር ምስጋና ይገባዋል። እንደው ማን ይሆን በዚህ ዘመን እንዲህ ብሎ የሚያመሰግን? እውነታውን ቢያውቅ እንኳን ሊያመሰግን የሚደፍር? አንዳችም የለም። ይህ ምስጋና በጨለምተኛነትና ድፍን እድገት ጠልነት የተፃፈ ይመስል ይሆናል። ነገር ግን አይደለም። ፈጣሪን በልብነት የያዘ በሱ የተቃኘ ህዝቡን የመልለ አስተዳደር ማቆም ስንችል እኛ ግን የምእራቦቹን ቀጥታ ካልገለበጥን ብለን ራሳችንን እያሳመምን እንገኛለን። መንገድና ምኞታችን አምላክን የያዘ ይሁን እንጂ፣ ባይሆን እንደው ቢያንስ ቢያንስ በሂደት ከሱ የሚለየን የሚያርቀን አይሁን እንጂ፣ እንደው አሁን አምላክ ከኛ ጋር በምድራዊ ነገር ምን ፉክክር ኖሮት አደግን/አላደግን፣ ሀብት አገኘን ሀብት አጣን ለሱ ምኑ ሆኖ ያግደን ነበር? አይደለም ከዚህ ከአለም ሰው ሰራሽ ሀብትና እድገት አንፃር፣

ከፅኑ ከተፈጥሮና ፊዚክዝ ህግጋት ጭምር በላይ ብንሆን ምን ገዶት? ቅዱስ ያሬድ "የሰው ልጅ ከዋክብትን እስከማዘዝ ስልጣን እንዳለው ብታውቁ ኖሮ..." ብሎ የመሰከረው ስለኛ አይደለምንዴ? አምላክ የሱ ልጆች ሆነን ምን ሊያግደን? በአንዲት ቀጭን በትር ትሪሊዮን ኪሎ ቶን ባህር አንስተን መክፈል አስችለን ብንለው ምን ገዶት? የሞተውን እናስነሳ ብንለው ምን ገዶት? አለምን እንግዛ ብንለው ምን ገዶት? የትኛው አደግኩ የሚል እንሰሳ ሀገር በኛ ላይ በየትኛው ዘርፍ የበላይነት ሊኖረው? ሁሉን አሳልፎ በሰጠን ነበር። እንጂ የኛ የምድር ስራና ጉዳይ በአምላካችን ፊት ምን እንደው ምን ቦታ ኖሮት አምላክ እምቢ ሊለን? ግን እኛ ያንን መንገድ አልያዝንም። ገደል ላይ ተንጠልጥለን አባታችን በእጁ ይዞን፣ ልቀቀን እንሂድበት ብለን በድንፋታ እጁን የምንናከስ ህፃን እንመስላለን።

በምድራዊ መነፅር ብቻ እንይ ካልን፣ የኛም ነገ ይኸው ነው። ሰዶምነት፣ የርክስና መንገድ ነው። ከአለም የተለየን አይደለንም፤ ሁላችንም ባንድ ላይ ወደዛ እንሄዳለን።

ነገርግን እግዚአብሄር አለ። ይህንን ፈፅሞ አይፈቅደውም። የደከምነው፣ የረሳነው፣ የቃልኪዳን ምድሩን እሱን በማራቅ ወደዚህ ተፅእኖ የጣልናት እኛ አልቀንም ቢሆን ትቀጥላለች እንጂ፣ የሱ ቃልኪዳን ታጥፎ አትረክስም። በዱር በገዳማት ስላሉ ቅዱሳን ብሎ፣ በሀይማኖታቸው ስለታመኑ ልጆቹ ብሎ እጁን ይልካል፣ ለረከስነው እሳት ለተባረኩት መድህን ሆኖ ያርፍብናል። የተባለው ጠረጋም ሁሉ በኛ ይሆናል። ፈጣሪን የረሱ መሪዎቻችንም ምንም ቅን ቢሆኑ፣ ምን ደግ አሳቢ ቢሆኑ፣ ምን ቢጀግኑ የጦርሜዳውን ቦታ እንኳን ያላወቀ ሀያል ጀግና ምንም እንደማይፈይድ ለኛም እንደዛው ናቸው የሚሆኑን።

እኛም እነሱን በመቀያየር፣ በማመፅ ሳይሆን የምንድነው፣ በዚህች ቅድስት ሀገር ላይ እፎይታን የምናገኘው ወደአምላካችን ራሳችንን መልሰን በህብረት በፊቱ በቆምን ጊዜ ብቻ ነው መልካሙን

የሚያፀናልን። የእስራኤል ነገስታት አምላክ ዛሬም አልሞተም። ሲያርቁት የተሰቃዩት፣ ሲያቀርቡት ደስታን ሰላምን ያገኙት ያ ሁሉ የመፅሀፍ ቅዱስ ቃል ተረተረት አይደለም። ያ አምላክ ጥንትም ነበር፣ ዛሬም አለ፣ ነገም አለ። በትንቢቱ ፅሁፍም "ሀጢያታቸውን ስለታገሳቸው እንደሌለ ይቆጥሩታል" የተባልነው ሆነን ነውንጂ፣ በመፅሀፍ ቅዱስም ላይ አምላክ ሲናገር *"ፊቴን እሰውርባቸዋለሁ ፍጻሜያቸው ምን እንደ ሆነ አያለሁ፤ ጠማማ ትውልድ፥ ያልታመኑም ልጆች ናቸው።"* እንዳለው ሆኖ ነውንጂ ቅፅበት ለማትሞላው እድሜያችን የአለሙን ፈጣሪ ከደነው መከራችንን ከማየት ያለፈ ቀድሞስ የት ልንደርስ? ለቅፅበቷ እድሜያችን ኖርን ሞትን ምን ጥቅም ኖሮን?

ሰው ምን ቢያውቅ ምን ሀያል ቢሆን እግዚአብሄርን ካልያዘ ከንቱ ነው። ምን ቢደክም እግዚአብሄርን ከያዘ ግን ከሁሉ በላይ ሀያል ይሆናል የሚለው የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት ፍፁም እውነት ነው። ይህንንም አምነህ በህይወትህ ያልተገበርከው፣ ያልተቀበልከው፣ እንዲሁ ዝም ብለህ ያለፍከው ከሆንክ ክርስትያን አይደለህም። ያ ነው እውነቱ። የመፅሀፍ ቅዱስ ቃላት ሁሉ ወይ ትርጉማቸውን ስላላወቅን ይሆናል እንጂ ፈፅሞ እውነት ናቸው።መርጠህ የምትቀበል ከሆነ ክርስትያን አይደለህም። ስለዚህ ይህንን አውቀሃው ከከሀዲያን ወገን መሆንህን እወቀው። በመሀል ቤት የሚሆን እንደ ይሁዳ ብዙ ጊዜ የከፋውን ጥፋት የሚቆራኘው እሱ ነው። ነው ወይስ አስገድደውህ ነው ክርስትያን የሆንከው?

በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ ምንም አይነት መሪ ብታገኝ፣ ወደእግዚአብሄር እጆቿን ያልዘረጋች ከሆነች ምንም ቢሆን ከውድቀት አትላቀቅም። ሰሎሞን ጣኦት ቢያመልክም እንኳን፣ ቢሞትም እንኳን ስለ አባቱ ንጉስ ዳዊት ቃልኪዳን ብሎ አምላክ ዙፋኑን ከእጁ ሳይነጥቅ እንዳኖረው፣ ዛሬም ስለቅዱሳን ቃልኪዳን ብሎ ሀገራችንን እድል ሰጥቶ እየተመለከታት ይገኛል። ከሞት ቀስቅሶ የፈቀድነውን እናደርግ ዘንድ ነፃነት እናገኝ ዘንድ፣ መልካም

መሪ(በስጋ አይን)፣ የረፍት ጊዜ፣ የነፃነት ቀናት በመሀል አቀዳጅቶ ከተተነበየው ጥፋታችን አስቀድሞ እየመለከተን ይገኛል። ምልክት ምልክት ሊሆኑ የሚችሉ ማንቂያ ነገሮችንም እያሳየን ይገኛል። የነገሮችን ፍጥነት፣ አስደንጋጭ ክስተቶች አፋፍላይ መሆናችንን፣ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አልፎ አልፎ በሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ በጃችን ባለበት ጊዜ ጠቆም ጠቆም እያደረገን ይመስላል። በዚህ ጊዜም አንዳችም ገድ ሰጥቶት ይህንን መኖሩን የሚያምነውን ሀያል ፈጣሪ እንዲረዳው እንዲሆን ሊያስበው አልቻለም። በትግልና መፍጨርጨሩ ቦታሰጥቶ ሊጠራው አልቻለም፣ ጋባዥ የማይፈልገው ክፉ መንፈስ ግን በመሀላችን የጨቀየ ስራውን እያፋጠነው ይገኛል። ከሁሉ በላይ ደግሞም ወደፊት የምንመኘውና ልናገኝ ልንደርስበት የምንታገለው መዳረሻችን ይህ ታላቅ የአለም አካል የሆነ ፈጣሪን ይባስ የሚያርቅና ከመሀላችን ስሙን የሚደበዝዝ መሆኑ ነው። ምንም ቢሆን አሁንም ግድ የለንም። ይህም ትልቅ ትልቅ ዋጋ ያስከፍለናል። ከፊታችን ዞር ቢል ችለን ላንቆም ነገር ፈጣሪያችንን ገፍተነዋልና፣ ጠማማ መንገዳችንን አይቶ የትግስቱ ፅዋ ሞልቶ ሲሰወርብን፣ ለዘመናት ከቦ ሲጠብቅ የነበረው ክፉ መንፈስ የበቀል ጅራፉን ያሳርፍብናል። ተዘናግተን ባለንበትም ጊዜ በትንቢቱ ሰፍሮ የቆየውም የመከራና ጥፋት ቀን የሆነችው ፀሀይ ድንገት ትወጣለች፣ ለብዙዎቻችን ለኛ ግን ጨለማ ይሆናል።

"በምስራቅ ባለች ሀገር ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ጦርነት ይሆናል፣ ከጥቂት ሰወች በስተቀርም በሷ የሚተርፍ የለም" የተባለው ቀኑ በባለቤቱ ዘንድ ብቻ ተጠንቅቆ የሚታወቀው ጊዜ መሀል በአንዲቷ ቀን ራሳችንን እናገኘዋለን። የሞት ፈረሰኛ ይላካል፣ የረሀብ ፈረሰኛም ከኛ ዘንድ ሚሊዮኖችን ይመታል። በምሳሌ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት የተባለውም፣ እንደኛ ንሰሀና መመለስ ወይ ደግሞ ቸልተኝነትና ዝንጉነት በሶስት ወርም፣ ሶስት አመትም፣ ሰላሳ አመትም በየት እንዲተረጎም የሚያውቅ እሱ ይወስነዋል። ከግብፅ በወጣችሁ በ40 ቀን ትገባላችሁ የተባሉ እስራኤላውያን በክህደትና አመፀኛነታቸው 40 አመት እንዳደረጉት የኛም እጣፈንታ እልቂቱ ከተጀመረ በኋላ ሳይሆን ዛሬ ባለነው እጅ ይሆናል።

## በስጋ አይን ብቻ እንኳን ብንመለከት

አናስተውልም እንጂ በስጋ አይን የሚታየው ይበልጥ ምን ያህል አስፈሪ መሆኑን ባወቅን ነበር። በዚህ ሁሉ መሀል ሆነን መታወራችን ለአምላካችን እንዴት ይሆን የሚደንቀው?

በሀገራችን ሁኔታ ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው የዘር ፖለቲከኞች በየቦታቸው እየነገሱ ይገኛሉ። ምርጫ ሲካሄድ አንድ ፓርቲ ሳይሆን ሙሉ ሀገሩን የሚገዛው፣ እያንዳንዱ ባሸነፈበት አካባቢ ስልጣን የሚይዝ በመሆኑ፣ ከማንም በላይ አደጋውንና መከፋፈሉን ያገነዋል።

በአይን የሚታየውን ምድር ላይ ያለ ሀቅ ካወራን፣ በኦሮሚያ ከኦዴፒም ከሌሎችም ፓርቲ ይልቅ እየተንቀሳቀሰና ድጋፍን እያገኘ ያለው፣ ብሶትንና ወገኝተኝነትን ያለተቀናቃኝ እየጋለበ ሀሳቡ መታየት ሳይጠበቅበት እንዲሁ በወገንተኝነት ጥቅምና ተጎጂነት ስነልቦና ሞተርነት የነገሰው ኦነግ ነው። በሚመጣውም ምርጫ በክልሉ በሀሳብ ሳይሆን በዘሩና ወገንተኝነት ብቻ ምክንያት አሸናፊ እንደሚሆን ከወዲሁ በግልፅ የሚታይ ነው።

ለዚህም አፀፋ በአማራ ክልልም የዚህ ተፅእኖ ለመቋቋም የሚለውን በምክንያትነት በመያዝ ለሱው ተቀናቃኝ የሆነ የዘር ቡድን በመመስረቱ ያም የዚህኛውን ለመገዳደር ሲባል በክልሉ የበላይነትን ያገኛል። በሲዳማም የሲዳማዎች፣ በትግራይም የህወሀት ወዘተ... በያካባቢው ሁሉም በየራሱ የዘር ድርጅት በሶትና ተጋፊ ቅስቀሳውን እያጋለ ተካሮ ይነግሳል። የዛኔ ኢትዮጵያነትን እንርሳውና፣ ለቅዠት አላማቸው፣ ድንበርገፊነትና፣ ለከት ያጣ ራስወዳድ ጥቅመኝነታቸው ነፀብራቅ የሆኑ እቅዶቻቸውን በድንፋታና አእምሮቢስነት ያለእፍረት ወደፊት የሚጋፉ እብዶች የመንግስትን ስልጣን ይዘው፣ ልዩ ሀይል መከላከያዎችን በስራቸው ሲሆኑ በአጭር ጊዜ የኢትዮጵያ ምድር

እንደ አንዷት የሲኦል ክፍለሀገር እንደምትሆን ትንተና የማያስፈልገው ነጋችን ነው።

እስከዛሬስ ኢህአዴግ ምንም የዘር ድርጅቶችን አድርጎ በያካባቢው መድቦ የኖርን ቢሆንም፣ ልሰሙ ተሰየሙ እንጂ ሁሉም በእጃዙር በአንድ ትእዛዝ ስር በመሆናቸውና ሙሉ ተመሳሳይ አስተሳሰብ፣ መስማማትና አቋም የነበራቸው በስም ብቻ ያሉ በመሆናቸው አደጋና ችግሩ ትልቅ ቢሆንም፣ ቢያን ስከዛው መጠኑ እንዳያልፍ አድርጎታል።

አሁን ግን ጠላትነት የሚያገናኛቸው፣ በተፈጥሯቸው እርስ በርስ የሚጠላሉ፣ በግልፍተኝነት የተዋጡ፣ ያልበሰሉ የሳት እራትነትን የተላበሱ አባላት የሚመሯቸው የሚጠላሉ ቡድኖች ቦታ ቦታ ይዘው ሲቀመጡ፣ ቀድሞም ተንኳሽ ድንበር እጅግ ባፀያፊ መልኩ ገፊ የሆነው፣ በተሸሸጉ በጦረኞችና አማፅያን እንኳን ያለእረፍት ጥፋት ሲያደርሱ የኖሩ እንደ ኦነግ ያሉ ቡድኖች፣ በክልሉ ባለሙሉ ስልጣን ሆኖ፣ ባደባባይ የታጠቀ ልዩ ሀይል የተባለ መከላከያ በእጁ ትእዛዝ ስር ሲገባ፣ በአማራ ክልልም የዚህን አፀፋ በሚመስል ድንበር ለመግፋት ወደኋላ የማይሉ አዲስ እየተፈጠሩ ያሉ፣ በዙሪያ ካለው ስጋት አንፃር ህዝቡ ባይወድ እንኳን ለህልውና በሚል እሳቤ በግዱ ከሌሎች በተገዳዳሪነት የሚመርጣቸው ድርጅቶች በያካባቢያቸው መሰል ሀይል ሲላበሱ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ህወሀት፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ከኦነግም እርስ በርስም የድንበርና ወሰን ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ የገቡ፣ በሲዳሞም እንዲሁ፣ በሶማሌም፣ በአፋርም፣ በደቡብም፣ በሁሉም የዚህ አይነት ሁኔታ ሲነግስ፣ ይህም አይቀሬ መሆኑ አሁን ሲታይ ምን እንደሚሆን መገመቱ አስፈሪ ነው። ይህ እንዳይሆን ተማምነን የምንናገርበት አንዳችም ነገር ዛሬ እየተሰራ አለመሆኑ በስጋ በምናየው እንኳን ይህንን ለመናገር ያስገድደናል።

አሁን ባለው የጉዞ መንገዳችን ከቀጠልን ግን፣ ቆም ብሎ ለሚያስብ ማንኛውም ባለአእምሮ ፍጡር ግን ይህ ፈፅሞ ሊቀር የማይችል

የማይቀር ሀቅ ነው።

ማነው ሶሪያን አስፈሪ ምሳሌ ያደረጋት? ማነው የመንን አስፈሪ ምሳሌ ያደረጋት? ማነውስ ሯንዳን አስፈሪ ምሳሌ ያደረጋት?

በሶሪያ የነበረው ሁኔታ እንደሆነ በአንድነት ያለ ህዝብ ከመንግስትና ደጋፊዎቹ ጋር የነበራቸው አለመስማማት ቡሀላም አመፀኞችን ለመግታት የተደረገ እንቅስቃሴ ብቻ ነበረ። ቡሀላም ዱቺ ምክንያት ነበርች ተጋግላ እየከፋች የሄደችው። የስልጣን ሽኩቻ እንጂ እርስ በርስም የሚያጨካክን ጥላቻ የላቸውም።

በየመንም እንዲሁ በመንግስቱና በተቃዋሚዎቹ በሁቲ አማፅያን መሀል ነበር ችግሩና ጦርነቱ። ስልጣኑን ሊይዙ ወደው ተተጋገሉ እንጂ ልዩ ጥላቻስ የለባቸውም።

የሯንዳውም ቢሆን ሚሊዮኖችን ሊቀጥፍ ቢቻለውም፣ ሁለቱ ወገኖች ተመሳሳይ ቋንቋ የነበራቸው፣ የተከለለ የምድር ድንበር ክፍፍል ያልነበራቸው፣ በብዛታቸውም ተገዳዳሪ ሳይሆኑ ሰፊ ልዩነት የነበራቸው፣ በሁለቱም ወገን የየራሳቸው የሆኑ ጦሮች የሌሏቸው፣ ብሎም በቋንቋ አንድ የሆኑ በመሆናቸው ይህ ሁሉ ከሀገራችን የተሻለ ሁኔታ ላይ ያሉ ስለሚያደርጋቸው የሚቾቹ ቁጥር ከሚሊዮን ላላይልፍ ቻለ።

በሀገራችን ግን ከ 12 በላይ ቡድኖች፣ በቋንቋ የሚለያዩ፣ ጥላቻ እስካፍንጫቸው ሲሰበኩ የኖሩ፣ ካለፈው አብልጦ ዛሬም የሚሰበኩ፣ ሁሉም የኔ የሚሉት ያንዱ ተሻግሮ ሌላው እንብርት ድረስ የሚገቡ የቅዠት ወሰኖችና ድንበሮች በምናቦቻቸው ያሏቸው፣ በህዝብ ቁጥራቸው የሚቀራረቡ፣ ከዚህ በፊት አውርተዋቸው የማይጠግቡ ጨለማ ስነልቦናን የሚያላብሱ ብሶቶችና ጠላትነትን የሚሰብኩ ሮሮዎች ያሏቸው፣ የታጠቁ ገናም የሚታጠቁ፣ በመታወቂያ አልፎም በታርጋ ጭምር የተለዩ፣ ፈፅሞ የማይተማመኑ ቡድኖች፣ አንድን

ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ፉክክር ሳይሆን ሌላውን የኔ ነው ከሚሉት አጥፍቶ የራስ ጥቅምና ድንበርን ለማቆም በእብሪት የሚተያዩ የበረቱባት በቋፍ፣ አንዲት ትንኝ ብትጋጨው ሊሰባበርና ሊደረመስ የደረሰ በእንቁላል ቅርፊት የተገደበ ረዥም የግድብ ሀይቅ ስር ቆመን ድንጋይ የምንወራወር፣ የምናሾፍ ሀቦች እንመስላለን።

ይህም ዋናውን ስጋት አልገለፀውም። ዋናው ስጋት የውጭ ሀገራት በአለም ተፅእኗቸውን ለማስፋትና የቅኝ ግዛት ያህል ተፅእኖው ባለው መልኩ መስፋፋትን ለመፍጠር የሚያደርጉትን እረፍት የለሽ ሽኩቻ ፈፅሞ ያልተረዳን ህዝቦች መሆናችን ነው።

ቻይና፣ አሜሪካ፣ ሳውዲ፣ እራን፣ ግብፅ፣ ሩሲያ እነዚህ ሁሉ የሚያደርጉትን መፍጨርጨር፣ ከጀርባ የሚሰራውን ሁሉ ልብ ብለን የማናስተውል መሆናችን ደግሞ የበለጠ ሟች ያደርገናል።

ከዚህ በፊት በብዙ ቦታዎች እንደታየው ሀገራት ሌሎችን ሀገራት ብድርን በመጠቀም መክፈል በሚያቅታቸው ጊዜ ሉአላዊነታቸውን አሳልፈው እስከመስጠት የሚያደርሱ ሁኔታዎችን ሲያደርጉ እንመለከታለን።

ምነው ልቦናችን ደነዘዘ? ቻይና የራሷ 1.437 ቢሊዮን ሳይሆን 1.427 ትሪሊዮን የውጪ እዳ እያለባት ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካ ሀገራት እጅግ ብዙ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብድር ወይ እርዳታ ሰጠች ሲባል እንዴት ብለን ጠይቀን እናውቃለን? እንደማይከፈል እርግጠኛ የሆኑባቸውን ብድሮች በመስጠት የሀገራትን ሀብትና ንብረቶች በመበዝበዝ፣ አልፎም ብድር መጠኑ እጅግ ሲገፋ ሉአላዊነትን አሳልፎ በመስጠት በእጃዙር ቅኝግዛት መያዝን የተካኑበት አይደለምንዴ? ሽሚያቸው ፉክክራቸውስ ለዚህ አይደለምንዴ?

ብድራቸው የጠቅላላ ጂዲፒያቸውን ሀምሳ ፐርሰንት በላይ ባደረሱ ጊዜ ሉአላዊነት እስኪጠፋ ድረስ በጃዙር ብዝበዛውና ሀገር አሳልፎ

መስጠቱ የብዙዎች እጣፈንታ ሆኗል። ሙሉ የባህር ወደባቸው፣ ትራንስፖርታቸው፣ አልፎም በአንዳንዶቹ የፖሊስ ሀይላቸውን ጭምር ቻይናውያን በባለቤትነት የሚያስተዳድሩባቸው ድሀ የአፍሪካና የሌላው ሀገራት እጅግ የበዙ ናቸው።

በስሪላንካ ከተማው ታላቅ አለማቀፍ አየርማረፊያ በቻይና ጉትጎታ እንዲሰራ ተስማምተው፣ ለዚሁም የሚሆን በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብድር እሰጥሻለሁ ብላ፣ ገንዘቡም ተመልሶ እንዲገባ ፕሮጀክቱ በቻይናውያን ድርጅቶች ተሰርቶ ከተረካከቡ በኋላ፣ ትርፋማ ይሆናል የተባለው ምንም እንቅስቃሴ የሌለበትና ክስረት የሞላው ሆኖ ብድሩን የመክፈያው ጊዜ ቢደርስ፣ ሀገሪቱም ልትከፍል የማይቻላት ቢሆን ምንድነበር የተደረገው? ሙሉ መሬቱንና አየርመንገዱ ለቻይና ተላልፎ እንዲሰጥ ነበር የተደረገው። እንዴት ትርፋማ ሊሆን እንደሚችል ቀድሞም እቅድ የነበራት ቻይናም፣ በእጇ ከገባ በኋላ በቀን እጅግ የበዙ በረራዎች የሚካሄዱበት ትርፋማ አየርመንገድ በመሆን እያገለገለ ይገኛል።

ከዚሁም ካለንበት በጅቡቲ እንኳን ወደቧን እጅግ ዘመናዊ አድርጎ የመስራት ፕሮጀክትን ቻይና አቅርባላት፣ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ለዚሁ በብድር ሰጥታ ስራውን በመጀመር፣ ይሄውም ገንዘብ ተመልሶ እሷጋር እንዲመጣ በቻይናውያን ኩባንያዎች ሰርታ ጨርሳ ካስረከበች በኋላ የጅቡቲ ዋና ተጠቃሚ የሆነችው ኢትዮጵያ በሌሎች አማራጭ ወደቦች፣ መጠቀም እድል በማግኘቷ የተጠበቀውን ገቢ ሊያስገኝ ባለመቻሉ፣ የብድር ቀኑ ሲደርስ ቀጥታ ከነሙሉ መሬቱና ወደቡ ለቻይና በባለቤትነት እንዲተላለፍ ነበር የተደረገው። የኛንም ሀገር በዚሁ መልኩ ከዛው ጋር ተያይዞ በብዙ ቢሊዮን በሚቆጠር በከፍተኛ ብድር የተሰራው ከጅቡቲ አዲስ አበባ የኤሌክትሪክ ባቡር መንገድ ምንም ጥቅም እይሰጠ የማይገኝ ክስረት ሆኗል። ቢስተካከልና መስራት ቢችል እንኳን አማራጭ ወደብ በኤርትራ በርካሽ በመገኘቱ ውደፊትም ያለስራ የተኛ ክስረት ሆኖ ይገኛል። የኤርትራው ወደብ ባይስተካከል እንኳን በዚሁ በጅቡቲ

በኩል ሰርቶ ትርፋማ እንዳይሆን፣ የጅቡቲውን ወደብ በጃቸው በማስገባታቸው የማያንቀሳቅስ የወደብ ታሪፍን በመጫን ሊቆጣጠሩት ስለሚችሉ በነሱ መልካም ፈቃድና ሴራ እጅ ውስጥ ገብቷል።

የአዲስ አበባውን ባቡር ጨምሮ ብዙ እንደተጠበቁት ትርፋማ ያልሆኑ ምናልባትም እንዳይሆኑ የተደረጉ ፕሮጀክቶች የወሰድነው ብድርም ለወደፊት መክፈል ባለመቻላችን፣ ወይ ሙሉ የሙብራት ሀይሉን፣ ወይ ቴሌኮምኒኬሽን ካምፓኒውን እና ሌሎችም አሳልፈን ለቻይና መስጠታችን የማይቀር ይመስላል። የአፍሪካ እንዲሁም በአብዛኛው የምስራቁ ክፍል በዚህ መልኩ በቻይና መዳፍ ውስጥ እየተጠቀለለ መግባቱ ያስደነገጣር አሜሪካም ይህን ለመስበርና በራሷ ለማድረግ ብዙ መፍጨርጨሮችን ስታደርግ ቆይታለች። ኢትዮጵያም ለብዙ ከንቱ ፕሮጀክቶች የወሰደቻቸው ብድሮች ቀኑ በደረሰበት ወቅት፣ ከባድ ሁኔታ ውስጥ በገባንበትም ወቅት ለቻይና መዳፍ ሳንገባ በፊት በእጅ አዙር ይህ ነው በማንለው ምክንያት በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ወደሀገራችን ገብቷል። የአሜሪካ የአረብ ወኪሏ በሆነች ሳውዲም በኩል በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር እንዲሁ በነፃ ስጦታ ተሰጥቷል።

ከነዚህም ሁሉ እንደምንመለከተው የአለም ነገር ሁሉ፣ ከጀርባም የሚካሄደው እጅግ የተወሳሰበና ጨርሰን በማናውቀው መልኩ እንደ ምንም በማይቆጥሩን ድሀ ሀገራት ላይ ብዙ ግፍና ጨዋታን እንደሚያደርጉብን ነው። የአሜሪካና ምእራብ ሀገራት፣ ከቻይና ርሱሲያና ሌሎች መሰል ሀገራት ጋር የሚያደርጉት ፉክቻ መሀል የብዙ ሚሊዮኖች ደም የሳል። በዚሁም ሳያበቃልን በሳውዲና በኢራን መካከልም በሚደረገው ትግል እጅግ የብዙዎች ደም ዘወትር ይፈሳል።

ከሁሉም ከዘር ውጥረቱም ሆነ ከየትኛውም በላይ ባጉል መንገዳችን እየሄድንበት ላለነው ለጥፋታችን ቀን መቃረብ ዋናው አመልካች

የሆነውም የነዚህ ሀገራት በኢትዮጵያ ዙሪያ ከበው መገኘት ነው። ሞት በበዛበት አሞራዎች እንደሚሰበሰቡ ከየትኛውም የአለማችን ክፍል በላይ እነዚህ ሀገራት ጦሮቻቸውን በጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ሱማሊያ፣ ሱዳን ኬንያ አስፍረው ኢትዮጵያ በአካባቢው ተፅእኖ ለመያዝ በሚተጉ ሀገራት ፍጥጫ ላይ ትገኛለች።

የኛ ጦርነት ሳይሆን የሚያሰጋን፣ ልክ አንዱ ትንሽ ቡድን በሚነሳበት ጊዜ ከሀሳቡና ከአቅሙ በላይ የሆነ የገንዘብ ድጋፍና የመሳሪያ ሸክም ከተፋጠጡት ሀገራት በአንዱ ይሰጠዋል። ይህንን የተመለከተ ሌላኛው ሀገር ደግሞ፣ የዚህኛውን ሀገር ወዳጁን አጎልብቶ ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት ለማደናቀፍ ለዚህኛው ጠላት ተመሳሳይ ያደርጋል። እንደ ኦነግ ያሉ በግብፅ፣ በተለያዩ የአረብ ሀገራት እጅግ የሚረዱ ቡድኖችም ከታሰበው በላይ አጥፊነትን እንዲላበሱ ያደርጋቸዋል። ቆይቶም ለሌሎቹ ቡድኖች በዚሁ መልኩ ከሌሎቹ ሀገራት እርዳታ መስጠቱ የማይቀር ነው።

በየመን ሁቲዎችን እራን በስልጠና፣ ጦር መሳሪያ፣ ሚሳኤል ጭምር በማስታጠቅ በምትረዳበት ጊዜ ሳውዲና መሰሎቿ ደግሞ ሌላኛውን ቡድን በተመሳሳይ በመሳሪያ ጋጋታ፣ በአየር ጥቃት ድጋፍ፣ ወዘተ በማገዝ የማያቆም የማያልቅ ፍፁም አውዳሚ የሆነ ጦርነት በየመን እስከዛሬ ሳያልቅ ይታያል። ህዝቡ በመሀልቤት ያለ ቆጣሪና መራማሪ በእሳት መሀል ይረግፋል። አልፎም በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ በልመና እስከመሰማራትም ደርሰዋል።

የኛ በብዙ ቡድን በጥላቻ በህዝብ ላይ ህዝብ በሚነሳ ጦርነት ደግሞ ምን እንደሚሆን ከአምላክ ከእርሱ በስተቀር ሊገምተው የሚቻለው ሰው የለም።

ከወዲሁም በኤርትራ የተባበሩት የአረብ ኤሚሬትስ የጦር ካምፕን ጨምሮ ሌሎችም፣ በጅቡቲ ቻይና በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በውጭ ሀገር ያሰፈረቻቸው ወታደሮቿ፣ የፈረንሳይ FFD ጦር፣ የጣልያን፣

የአሜሪካ CJTF-HOA ጦር ካምፕ፣ ጃፓን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ወዲህ በታሪኳ ኖሯት የማያውቀውን የሌላ ሀገር ጦር ካምፕ ጭምር በዚህቺው በጅቡቲ አስፍራለች። ከጎረቤታችን ሱማሊያም ጭምር ቱርክ ሳትቀር ከሁሉም ትልቁን የጦር ካምፒን እያዘጋጀች ትገኛለች። እንግሊዝም በኬንያ፣ ሌሎችም ሌሎችም ተሰባስበው ምስራቅ አፍሪካን ከበው ይገኛሉ።

አንድ ግጭት በሚነሳ ቁጥር በነዚህ ሁሉ ያሰፈሰፉ ተሻኳቾች ሀያላን ቡድን ቡድን ይዞ ጣልቃገብነት መሀል ለማይበርድ እርስበርስ እልቂት እንደምንንደረደር ጥርጥር የለውም። እንደ ኦሮሞ እስላማዊ ነፃ አውጪ ግንባር የመሳሰሉት በአረብ ሀገራት ድጋፍና መተማመን የተቋቋሙት፣ ብቻ እንኳን በአረብ ሀገራት መሀከል በሚደረገው ፉክክርና እርስበርስ ግፊያ ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍሉ መገመት ይቻላል።

የየመን ከሶማሊያ የከፋ ግጭት እንዴት ነው የተፈጠረው? እንደመነሻው የመንግስቱና የአማፂዎች ፀባቸው ቢሆን ጦርነቱ በንፅፅር እንዴት የተባረከ የሚባል ነበር። ነገርግን ሳውዲ መንግስቱን የቀረበች፣ ኢራን ሁቲ አማፅያኑን የቀረበች እለት፣ ይህ የየመኖር የራሳቸው ግጭት በቅፅትበ ወደሲኦል ተቀየረ፣ አይተውት ስሙን ሰምተው የማያውቁትን መሳሪያ እርስበርስ ላይ መልቀቅ ጀመሩ፣ ህዝቡ ከጦርነት ይልቅ በረሀብና መቀጨጭ አለቀ፣ ቢንቢ በሁለት እጅ በጭብጨባ መልኩ እንደሚጨፈለቅ በመሀል ቤት በሁለት ሀያላን መሀል ተጨፈለቁ፣ ህዝቡ አልቆ በምድሯ ማንም ባይኖር እንኳን ሀያላኑ በሙሉ ጤናቸው በየሀገራቸው እስካሉ ድረስ እንደ ትኩስ ጦርነት የመቀጠል ሙሉ ችሎታን ይይዛል።

በኛም ዙሪያ ዝግጅቱ ያው ነው። የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ ብቻ እንኳን በሰሜን ኤርትራ ላይ፣ በደቡብ ሞቃዲሾ፣ በምስራቅ ሱማልያ በርበራ ላይ ጦሯን በኢትዮጵያ ዙሪያ አቁማ ትገኛለች። ሳውዲ አረቢያም በጅቡቲ እንዲሁም በኤርትራ ጦሮቿን አስፍራለች።

ቻይናም በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦሯን በጅቡቲ ማስፈሯ እጅግ አስፈሪ ሁኔታ ነው። ምክንያቱም በታሪክ አጋጣሚ ሁሉ፣ ለጥፋታችን ከተነሳ ሀይል ጋር ሁሉ በማበር ለውድመታችን ስትከንፍ የኖረች ሀገር ነበረች። ሰኢድ ባሬ ሶማሊያን አደራጅቶ በተነሳና በወረረን ጊዜ፣ ሞቃዲሾን አልፎ እስከሀረር ሊደርስ ተጠግቶ በግፍ በተነሳ ጊዜ ቻይና ከሱ ጋር የተሰለፈች ሀገር ነበረች። ዳግመኛም ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ባነሳች ጊዜ ኤርትራን በማገዝ በኢትዮጵያ ላይ ስትነሳ የነበረች ሀገር ነች።

ይባስ ብሎ በዚህ አሜሪካ ከሶስት በላይ ጦር ካምፖቿን ባሰፈረችበት ምስራቅ አፍሪካ፣ አልፎም ደግሞ ለረዥም ጊዜ ከአጋሮቿ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በምታደርግበት ቀጠና፣ የታሪክ ጠላቷና ተቀናቃኛ ሩሲያ በኤርትራ እንዲሁም፣ በሱዳን የጦር ካምፖችን የቀይ ባህር የጦር ሀይሎችን የማስፈር እንቅስቃሴ ውስጥ ትገኛለች።

ይህም ሁሉ ስካር በምስራቅ አፍሪካ ምን ሊፈጠር እንደሆነ አለም ሁሉ በአግራሞት እየተመለከተ እንዲጠብቀው አድርጎታል።

በትንቢቶችም እንደተነገረው፣ ቅድሚያ በኢትዮጵያ ምድር ፅኑ መናወጥ ከሆነ በኋላ፣ አለምም ወደባሰ ዘግናኝ ፍጭት ውስጥ እንደሚገባ መጠቆሙም ይህንን የሚመሰክር ይመስላል። በስጋ አይንም ስናየው በኛ ጦርሜዳነት በወኪል የሚጀምሩት የእብሪት ጦርነት ብሶም ወደነሱ የማደግ እድሉ ከፍተኛ እንደሆነ መገመት እንችላለን።

ከዝህም ባለፈ አክራሪ ቡድኖች በአረብ ሀገራትና ሶርያ የተቆጣጠሯቸውን መሬቶች በሙሉ ተነጥቀዋል። አይኤስአይኤስም በኢራቅ የመጨረሻውን ይዞታውን ተነጥቋል። በሱማሊያና ምስራቅ አፍሪካ ያሏቸው ይዞታዎቻቸው ጋር በጉያችን እንደሚሰበሰቡ የሚጠበቅ ነው። እስላማዊ ነፃውጪዎች ጭምር በሀገራችን በተለያዩ

ዘሮች የሚንቀሳቀሱበት ጊዜም በመሆኑ፣ በዚህ መንገድ መከራችንን እንደሚበዛ መገመት ቀላል ነው።

ከምርጫ በኋላ የሚኖረው ስጋት እንዳለ ሆነ፣ ከዛ በላይ ግን አደጋ የሆነው በየጊዜው የሚከሰቱት ድንገተኛ ጥቃቶች ናቸው። በሯንዳው ጭፍጭፍ በአንድ ሰው መገደል እንደፈነዳው፣ የዚህ አይነት እልቂቶች ድንገት ሊፈነዱ የሚችሉ ናቸው።

የዚህ አይነትም እጅግ አስጊ ፍንጮች በሀገራችን በተደጋጋሚ ታይተዋል። በአጣዬው የኦሮሞ አክራሪዎች ጥቃት በአንድ ቀን ብዙ ሰወች ሲገደሉ ቤተክርስትያናት ሲቃጠሉ፣ ሲዘረፉ በግልፍተኝነት በሌላ ቦታ በበቀል በኦሮሞ ተወላጆች ላይ ተመሳሳይ ነገር ቢከሰት ኖሮ ከፍተኛ በዚህ መመላለስ በአንዴ ወደለየለት እልቂት ድንገተኛ ፍንዳታ የመግባት እድላችን እጅግ ትልቅ ነበር። ዳግመኛም በመተከል የአማራ ተወላጆች ተራ ደሀ ነዋሪዎች ህፃናትን ጨምሮ በአንድ ቀን በመገደላቸው፣ ወዲያውም በጃዊ በበቀል የተነሳሱ ሰወች ተመሳሳይ ተራ ደሀዎች ላይ ግድያ መፈፀማቸው እጅግ አስፈሪ ገፅታን ይዞ ሊቀጣጠል ሳለ በእግዚአብሄር እርዳታ የቆመ ነገር ነበር።

አምላክም በዚህ መልኩ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ፍንጮችን እያሳየን ይመስላል። ወደልቦናችን ተመልሰን በንሰሀ ፀድተን እውነትም ያለውን ሀያል ፈጣሪ እርዳታውን ካልጠየቅን፣ ምህረቱን ካለመንን፣ በሙሉ አእምሯችን ሆነን አምላካችንን በሁሉ አስቀድመን ለሀገራችን መድሀኒትን ካላወረድን ምንም ትርጉም የለንም። ሀይማኖታችንም፣ ሀገራችንም፣ ምናችንም ትርጉም የለውም ማለት ነው።

ድፍን ኢትዮጵያውያን ያለንበት ስነልቦና እጅግ የወደቀ ነውና፣ አማኝ ሆነን ሳለ ባልገባን መንገድ ኢአማናዊ ኑሮን መኖራችን እጅግ

ጎድቶናል። ስለምን ብለን ያንን እናደርጋለን?

እስኪ አስበው፣ ከወንበርህ ስር ወይ ከአጥርህ ካብ ላይ የተመለከትካት ቁጫጭን እስቲ አስባት....

የህይወት ዘመኗን ምን ያህል ከንቱነት። ከተወለደች እስከለተሞቷ ካንተ ጊቢ ወይ ከዛ ካነሰች ቦታ ሌላ ልታይ የማይቻላት፣ ህልውናዋ ትፈጠር አትፈጠር ማንም ሳያስተውላት ሳትታይ የምትጠፋ፣ ወይ ደሴ፣ ወይ ጅማ፣ ወይ ባህርዳር የትኛውንም ቦታ ማካለል አይደለም፣ ቀኑን ሙሉ ስትጓዝ ብትውል ከሳሮች ወጣገባ አቆራርጣ ሁለት እርምጃ ሚሞላ ልትሄድ የማይቻላት ቁጫጭ የህይወት ልፋትና ብክነት ከንቱነት።

የኛስ ህይወት ቢሆን? ይህን የምታነብ አንተም በህይወት ዘመንህ ከምድር ስፋቷ አንፃር እንደዚቺው ቁጫጭ የአለምን የቁርሳሿን ቁራሽ ቁራሽ ቅንጣት ሳታካልል፣ በምድር ዙሪያ ምን ተራራ ቢኖር፣ ምን ጥቅጥቅ ያለ ደን ቢኖር፣ ምን ጥልቅ የአእላፋን አለም ባህር ቢኖር፣ ምን የበረዶ ከተማ፣ የአሸዋ ተራራ ቢኖር አንተ ግን ከ3 ወይ 4 ከተማ ያለፈ እሱንም ከአስፋልቷን ጥግ ተከትሎ ካሉት ውጭ እንኳን ሳታይ ባጭር አካባቢ በጠባብ ቤት ሆነህ ሰፊዋን አለም ሳታያት ሳታይህ ከንቱ ቅንጣት ሆነህ ለምታልፍባት፣ ጊዜ ወደፊት እልፍ ወደኋላ እልፍ በሆነበት፣ ከህዋና አለም የጊዜ ስፋትና እድሜ አንፃር ያይን ጥቅሻ ቅፅበት በማበልጥ እድሜ ታይተህ ለምትጠፋባት፣ ከንቱ ፍጥረት ባዶ ለሆንክባት ከቶ ለምን ይሆን የመኖርህ ትርጉም? ስለምን ተፈጠርክ? ይህችስ አለም ምንህ ናት? ይህንን ፅሁፍ አንብቤ ወጥቼ ስሻገር እንኳን መኪና ነክቶኝ የከንቱዋ ህይወቴ ፍፃሜ እንዳይሆን መተማመኛ እንኳን በራሴ የሌለኝ ከንቱ ሆኜ ሳለሁ ታዲያ የኔ አሁን መተንፈስ ምንድነው ትርጉሙ?

እንዲህ ቅንጣት ብናኝ ማኗም ላልሆንክ፣ የማታውቃትን ህዋና አለም ትላንት መጥተህ በሷ ውስጥ የእግዚአብሄርን አለመኖር ስነግራት

እንዴት ይሆን የሷ ግርምት? የኔስ በሷ እንዲህ ደቃ ሆኖ ለቅፅበት መኖር ምንድነው ትርጉሙ?

ሁሉን አውቆ አዘጋጅቶ፣ በውስብስብ ጥበብ ተሰርቶ ያለቀለት አለም ላይ አምጥቶ ፈጥሮ ያስቀመጠኝ እሱ የሁሉ አዘጋጅ፣ እኔንም በራሱ እቅድ እንድኖር ፈልጎ ምንም በማላውቀው መንገድ ቁጭ ያደረገኝ ፈጣሪ እሱ፣ እሱ ራሱ ካልሆነ ትርጉሙን ከቶ ማን ያውቀውና?

ቢዚህ ፅሁፍ የቀረበውን የትንቢት ቃሉንም በንቀትና በሹፈት የምመለከትበት ምንም መተማመኛና ምክንያት ሊኖረን አይገባም። ለየትኛው ህይወታችን ብለን? የት ተንቀሳቅሰን ላወቅናት አለምና ህዋ? የትቀድሜ የት ቆይቼ በጊዜ ሂደቷ ጠንቅቄ የማውቃትን ነው በእግዚአብሄር ቃል፣ በነዚህ ትንቢቶች የማፌዝ፣ ምን ተማምኜ ህይወቴስ ይህ ሆነ አልሆነ ምን ትርጉም ኖሯት ነው ትንቢቱን በልበሙሉነት የምፃረረው?

ታዲያ ስለየትኛዋ ህይወቴ ብዬ ነው እሱን ሳላስቀድም የምኖረው? ማን የትኛው ባለትርጉም ሰው እዳ ኖሮብኝ ነው ፈጣሪ ማለት ያሳፍራል፣ እሱን በአስተዳደሬ በሀገሬ ጉዳይ ቦታ አልሰጥም ብዬ ካለልቤ የምባክነው? ስለምን ብዬ ነው እሱን "እኔን ፈልገኸኝ የፈጠርከኝ ጌታዬ ሆይ ተቸግሬአለሁና እርዳኝ" ብዬ የማልጠራው? ቀድሞስ ማ ፈልጎኝ ተፈጠርኩና? በዚህች በከንቱዋ ህይወቴ የማን ፖለቲከኛ ወይ ነጭ እዳ ኖሮብኝ ነው ፈጣሪዬን በአደባባዬ መጥራትን የምሸማቀቀው?

ኢትዮጵያዊ ነኝ! ፈጣሪዬን አስቀድማለሁ! የህይወቴ ፍልስፍና፣ ያለኝ ባህሌ፣ እሴቶቼ ሁሉ ከጥንት ጀምሮ ከሱ ለመዋሀድ የማደርገው ጥረቴ ነፀብራቅ ነው! ፈልጎኝ "አንተ እራስህ፣ አንተኑ እንድትኖር እፈልግሀለሁ" ብሎ ሳይሳሳት የፈጠረኝ አምላኬን አልክድም!

ዴሞክራሲ ማለት የብዙው ህዝብ ፍላጎት አስተዳደር ነው ከተባለ፣ ዘጠና ዘጠኝ በመቶ አማኝ የሆነ፣ “ከሁሉ በፊት አምላኬ ይቀድምብኛል” ብሎ በማሰብ በውጪ ድርጅቶች በተሰራ አለማቀፍ ሰርቬይ ከሁሉም ሀገራት ለተከታታይ አመታት ኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠችበት ህዝብ፣ እንዴት ሆኖ የጋራ ግቡ National Interest ላይ ይህ ፍላጎቱ አንዳችም ግምት ውስጥ ሳይገባ፣ በሱ ፋንታ ልጆቹ ከልጅነታቸው ጀምሮ የኢአማናዊነትን ትምህርት በብቸኝነት በመማር፣ ጎን ልጎን እንኳን የፈጣሪ ምንነት፣ የሱ ፍላጎቶች እቅዶች ወዘተ የሀይማኖት ዶክትሪኖች ልዩነት ቢኖርም ሁሉም ፈጣሪን የሚያመልክ በመሆኑ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች በሙሉ ተመርጠው እንዲሰጡ ያልተደረገበት፣ ድፍን ህዝቡ ባልፈለገው መንገድ ያለአማራጭ ተቀርፀው ማንነቱን እንዲጠየፉት አድርጎ በሚተርክ ቀጥታ ከውጭ በተገለበጠ መንገድ የሚማሩበት፣ የሚተካውን ትውልድ ለሌሎች አስሮ ያስረከበ ህዝብ፣ ይህም ሁሉ ከራሱ ድህ ገቢ በሚሰበሰብ ታክስ ገንዘብ ተደግፎ አዲስ ተፃራሪ ሀይማኖት ያለ ማወዳደሪያ የሚማሩበት ሀገር ሆኗል። እንደ አሜሪካ ያሉ በቅዱሳን መፅሀፍት ዓይን የሀጢያት ማማ በሚባሉ ሀገራት እንኳን ወንጀልና ክልክል የሆነው ሴተኛዳሪነት፣ እዚህ ግን ብዙ ህዝቡ የሚጠየፈው ሆኖ ሳለ በልቅ የተፈቀደ ልቅ ስራ ሆኖ የነገሰበት መንገድ ዴሞክራሲ (የብዙ ህዝብ ፍላጎት አስተዳደር) ተብሎ ውሸት የሆነ ዴሞክራሲ ሀገራችንን አውሮ ሲገለን ያሳዝናል።

የአንድ ፈጣሪ ልጆች አንዱን የጋራ አባታችንን ለማመስገንና ለማምለክ ስለእውነት በመሰለን መንገድና አምልኮ ስንተጋ ቆይተናል።

ሁለት የአንድ አባት ልጆች ያጡትን አባታቸውን ፍለጋ ወጥተው በሚችሉት ሁሉ ስለአባታቸው ፍቅር ቢተጉ፣ ወደሱ ያቀርበናል ብለው ከልባቸው ባሰቡት በተለያየ መንገድም ወደአባታቸው ለመቅረብ ሊለፉ ይችላሉ። ታዲያ የጋራ አባታቸው ከልባቸው

እስከሆነ ድረስ አንዱን ሊያገኘው የሚባክን ቅን ልጁን ከሌላው አሳንሶ ወይ አብልጦ አያየውም፤ ሁለቱም በቅንነትና አባት ፍቅር ከልባቸው አባታቸውን ለማግኘት እስከጣሩ ድረስ አባታቸው አንዱን ከሌላው ለይቶ አያርቀውም። ይልቁንስ በእውነት ልብ ሆነው አባቴ ብለው ቢፈልጉት መንገድ የሳቱትን አቃንቶ እንደአብርሀም ወደቤቱ መንገድ ይመራቸዋል እንጂ።

ከሙስሊምም ሆነ ከክርስትያን ቤት ተወልደው በገባቸው መንገድ ስለእውነት ፈጣሪያቸውን ለመቅረብ የሚጥሩ የዋህ ቅን ልጆችንም እግዚአብሄር አንዱን ከሌላው አብልጦ አያያቸውም። ማንኛውም በቅን ልቦና ስለእውነት ከልቡ በመሻት አባቱን ለማግኘት በፍቅር የሚተጋን ልጁን የጋራ ፈጣሪያችን አይጨክንበትም። ፈጣሪ ጋር ለመቅረብ ከትውልድ እድል ይልቅ የልብ ቅንነትና የዋህነት እንዲሁም ከልብ በሆነ ፍቅር አባትን ለመቅረብ መሻት የበለጠ ዋጋ አለው።

ሁሉ ህዝብ አማኝ በሆነበት ሀገራችን፣ ያውም ሙሉው ህዝብ በሀይማኖት የአብርሀም ልጆች በሆኑበት ሀገር የእውነት ዴሞክራሲ (በህዝቡ ፍላጎት መተዳደር) ይኑር ከተባለ ህይወታችንን እስከመስጠት የምንታመንባቸው እምነቶቻችን በሚጋሯቸው አካሄዶች ላይ ብቻ ተመስርተው፣ በሚያስፈልጋቸው መንገድ ሁሉ የሚታገዙበት መንገድና ስርአት ነበረ ለሀገራችን መዋቅር መሰረቱና የጀርባ አጥንቱ ሊሆን የሚገባው። ከዚህ ውጪ የሆነ ብሎም ከዚህ የሚፃረር፣ ከውጪዎች የተገለበጠ መንግስት ቅኝግዛትና ማንነት ቅየራ እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም።

ሲሆን የጋራ የምስጋና ቀን አውጆ በሀገሩ ባቆመ ነበር። የኛ ሀገር የታደለች በመሆኗ፣ ሁሉም አማኞቿ ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩባት፣ አልፎም የእስማኤልና የአብርሀም ተከታዮች ሆነው በስጋ የጋራ አባታቸው የሆነውን የአብርሀምን አምላክ ቀጥታ ለማምለክ የሚጥሩ በመሆናቸው በዚህ ተመስርቶ ፈጣሪን የማክበር የህይወት እስከሞት

ምኞታቸውን ባገዛቸው ነበር። መንግስት ሲባል የህዝብ አገልጋይ እስከመሆኑ ድረስ ማለት ነው፤ አይደለም እንደኛ ሀገር በተቃራኒው ከትውልዳቸው የፈጣሪን እውቀት አመንምኖ የህይወት አላማቸውን ደብዛውን ለማጥፋት የሚጥር ስርአት ሊሆን።

እውነተኛ የኢትዮጵያ መንግስት ቢኖር ኖሮ እነዚህ በአምላካቸው ህግጋትና ያለፉ ታሪኮች፣ አምላካቸው በሚያዛቸው ነገሮች የሚለያዩ ቢሆኑም፣ አንድ አምላክ የሆነ እሱም የሰራቸው ፈጣሪያቸው መሆኑን ሁሉም በፅኑ የሚያምኑ ክርስትያኑ የሙስሊሙን ፈጣሪ፣ ሙስሊሙም ደግሞ የክርስትያኑን ፈጣሪ የሆነውን የጋራ አንድ ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩ በመሆናቸው ለአንዲት ቀን እንኳን ፈጣሪ በሚለው መጠሪያው ተሰብስበው፣ ሁለት የጋራ አባታቸውን በመሰላቸው መንገድ ለማምለክ የሚጥሩት ህዝቦች ተገናኝተው ባንድላይ "ፈጣሪያችን ሆይ" ብለው በጠሩት ነበር።

እስኪ አስበው!

ሀገሩ ሁሉ ወጥቶ፣ ፈጣሪያችን አባታችን ሆይ ብለው ጠርተውት በጋራ ወደሱ ሲመለከቱ። አባት ምን ይሰማዋል? ሌላ ባእድ አምልኮን ፈልገው ሳይሆን፣ በቅንነትና እውነት ፈጣሪያችንን እናገኝበታለን ባሉባቸው መንገዶች የተከፋፈሉ ልጆቹ ለአንዲት ቀን በአንድላይ ሁሉም በሚስማሙበት ማንነቱና መጠሪያው "ፈጣሪያችን፣ አባታችን" ብለው ወደሱ ሲጣሩ! የአባታቸው የአብርሀም አምላክ ምን ይሆን ምላሹ? ልጆቹ ፈልገውት በአንድነት ወጥተው የተጣሩ ዕለት የፍቅር አምላክ ምን ይሆን ምላሹ? ይህንንስ በእንባ ሳይዋጡ ማሰላሰል ይሳናል። ሲሆን ሲሆን ለኛ ህዝብ የዚህ አይነት የጋራ የተቀደሱ ቀናትን ከሀይማኖት አባቶች ጋር በመነጋገርና ሁሉም ሀይማኖት በሚስማማባቸው ምስጋናዎች ፈጣሪን አክብረን ሁሉም ሀይማኖት ውስጥ በልጦ በሚሰበከው ፍቅር ሆነን አምላካችንን በጋራ በማመስገን እምነታዊ ሀይልን የምናገኝበት፣ በመንፈስና በስነልቦና እድሳት አብበን ሌሎች ሀገራዊ ግቦቻችንን

በንፁህ አእምሮና ሰላም የምንሰራበትን መንገድ የሚያመቻች መንግስት ነበረ እንደኛ ላለችዋ ሀገር ይገባት የነበረው። አይደለም የገዛ ልጆቻችንን በተቀዳ ርእዮትና ኢአማንያትን በራሳቸው እምነት ለራሳቸው ያዘጋጁትን በገለበጠ ትምህርት ስርአት በልጅ አእምሮ ግቶ የገዛ ትውልዳችንን አእምሮና ነፍስ እንዲህ የሚያመክን ሊሆን!!! ምናልባትም ሀገራችን የቀናት ቀን ይህ የጋራ ሁላችን ምንወደው አባታችንን ደስ የሚያሰኘው፣ ለኛም ፍቅር ሰምላና አንድነት የሆነው የምስጋና ዕለት ወደፊት አንድ ቀን ይታወጅ ይሆናል።

መንግስት ድፍን ሙሉ ዜጎቹ የህይወት እስከሞት አላማቸው በሆነው በአምላካቸው አምልኮና ምስጋና ጉዳይ ከሆነ፣ ይህንን ካላሳለጠ፣ ካላስተባበረ፣ ለነሱ ካለፋላቸው ታዲያ ለነማን ይሆን የተሾመው? ያውም መቶ ፐርሰንት በሚባል ደረጃ በብዛት አማኞችን በመያዝ ከአለም ሚደርስባት በሌለች ሀገር ላይ!

በኢትዮጵያ ሁሉም ሀይማኖት ቢሆን ፈጣሪው የሆነውን ለማምለክ በቆመበት፣ ያውም ሁሉም እምነት አብርሀማዊ በሆነበት የአንድነት ምድር፣ በቤተ አምልኮ ውስጥ ከሚደረገው ስነስርአት ውጪ በአኗኗር ፍልስፍና፣ ህግጋት፣ ማህበረሰባዊ ቅርፅ ወዘተ እጅግ ተመሳሳይ የሆኑ እምነቶች ባሉበት ምድር፣ ፈጣሪ ብሎ አምላክን ጠርቶ በአንድነት በሁሉም እምነት በሚደገፉ ክፍሎች ላይ የተመሰረተ ኑሮን መኖር ለኛ እጅግ ቀላል ነበረ።

የኛ ሀገር ህዝብ በሙሉ አእምሮው አተኩሮ ሀገሩን ማሳደግ ይችል ዘንድ፣ ከልቡ የመጀመሪያ ግብ እሱም ፈጣሪውን ከሁሉ አስቀድሞ የሚኖርበት ግብን ያቀፈ ሀገራዊ ግብ የተቀረፀበት (ማንንም ለማስደሰት ብሎ ሳይሆን ሀገሩ ፍፁም የሱ የህዝቡ ሆና የሚኖርባት ናትና)፣ ትልቁ አካሉ የሆነው ፈጣሪው ቦታ ያለበት የሚመሰገንበት፣ የሚለመንበት፣ ህጉ ተከብሮ የሚደሰትበት አስተዳደራዊ እንዲሁም ህዝባዊ የሀገር መዋቅር የሌለው መንግስት በኢትዮጵያ በቃልኪዳኗ ምድር ከቶ በሰላምና ክብር ሊኖር አይችልም።

የሀገራችን ህዝብ ከፊቱ የሚጠብቀው የእግዚአብሄር ፍርድ የሚታይበት ፅኑ መከራ፣ ለዘመኑ ነዋሪ ብቻ እንግዳ ሆነው እንጂ ለጥንት ኢትዮጵያውያን የሚጠበቅ የሚታወቅ ነበር። ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የሚገዛ የተባለለት ያለፈው አፄ ቴዎድሮስ አልነበረም። ከአሁኑ አንፃር የዘመነ መሳፍንቱ ክፍፍልማ እንዴት ያለ ምርቃታችን ነበረ! ቢነሳ ያው ንጉስ በንጉስላይ፣ ደስ ያለው ይሄኛውን ደስ ያለው ያኛውን በሀሳብና ምርጫው የሚቀላቀልበት፣ የማይለውጠው የዘር መስፈርት ያልቆመበት፣ መና ሀይማኖት ያልገባበት፣ ከንቱ ርክስና በተራው ህዝብ ላይ ያልነገሰበት ጊዜ አልነበረችምን? ይህቺንማ የቀድሞ ዘመን የትም የተለመደች አኗኗር ማንስ ትኩረት ሰትቶ ሺ ዘመናትን አልፎ በትንቢት ሲናገራት ይኖር ነበር? የኛ የዛሬው አለ እንጂ ንጉስ በንጉስ ሳይሆን ህዝብ በህዝብ ጥላቻ ተሰባብኮ የሚነሳበት፣ ህፃን ልጅ ሁለት ጠጠር በእጁ ግራናቀኝ አድርጎ እንድሚያጋጭ ሀያላን ከበው አንድአንድ ይዘው ሊያፋጩ ያሰፈሰፉበት፣ የእግዚአብሄር ህልውና ከትውልዱ ልቦና ሳስቶ ጥላቻና ርስሰት ይህይወት አካል የሆነበት፣ እግዚአብሄር የጋራ አባት በመሀል ተገኝቶ ልጆቹን ያስተካክል፣ መልካሞቹን እንኳን ይደግፍ ዘንድ ስሙ የማይጠራበት፣ የአጋንንት መርመስመሻ የምንሆንበት የሰቆቃ ጥግ ደጃፍ ላይ ሆነን እንኳን አንዳችም ልብ ብሎ የሚያስተውል የሌለበትን ፅኑ መከፋፈል እንጂ ከሰሜን እስከደቡብ ተሻግሮ ኢትዮጵያ ተብለው የማይጠሩትን ጭምር አቅንቶ አንድ አድርጎ የሚገዛውን ያንን ታላቅ ንጉስ ነውንጂ ለሺ ዘመናት ሲነገርለት የኖረው። ወላፈኑ ሩቅ ጭምር በሚፈጅ በእግዚአብሄር ቁጣና መቅሰፍት ጠማሞች ሁሉ ከዙሪያው ከተጠረጉ በኋላም ስለሚደርስ ይህን ማድረግ ተአምር አይሆንበትም።

ዛሬም ያለነው ተመለስንም አልተመለስንም፣ በንሰሀ ከሀጢያት ነፅተን የምንጠብቅ ኖርንም አልኖርንም አምላክ ያለው ጊዜው ሲደርስ ሁሉም የሚሆን ይሆናል። ስለዚህ ከፈለገ ሁሉም እንዳልሰማ ሆኖ ኑሮውን ቢቀጥል ይችላል፣ አሿፊውም በዚህ መልእክት እያሾፈ

ይቀጥል፣ ኢአማኒውም በራሱ ፈቃድ መርመስመሱን ይቀጥልበት፣ ጊዜው ሲደርስ ግን ሁሉም አምላክ ባለው ፀንቶ ይፈፀማል።

**"ፌዘኞችም: ፌዝን: ይፈቅዳሉ? ሰነፎችም: እውቀትን: ይጠላሉ?: ወደ: ዘለፋዬ: ተመለሱ: እነሆ፥ መንፈሴን: አፈስስላችኋለሁ: ቃሌን: አስተምራችኋለሁ። በጠራሁ: ጊዜ: እምቢ: ስላላችሁ፥ እጄን: በዘረጋሁ: ጊዜ: ማንም: ስላላስተዋለ፥ ምክሬን: ሁሉ: ግን: ቸል: ስላላችሁ፥ ዘለፋዬንም: ስላልፈቀዳችሁ: እኔም: ስለዚህ: በጥፋታችሁ: እስቃለሁ: ጥፋታችሁም: በመጣ: ጊዜ: አላግጥባችኋለሁ። ድንጋጤ: እንደ: ጐርፍ: በደረሰባችሁ: ጊዜ፥ ጥፋታችሁም: እንደ: ዐውሎ: ነፋስ: በመጣ: ጊዜ፥ ጭንቅና: መከራ: በወረደባችሁ: ጊዜ። የዚያን: ጊዜ: ይጠሩኛል፥ እኔ: ግን: አልመልስም: ተግተው: ይሹኛል፥ ነገር: ግን: አያገኙኝም። እውቀትን: ጠልተዋልና፥ እግዚአብሔርንም:: መፍራት: አልመረጡምና: ምክሬን: አልፈቀዱምና፥ ዘለፋዬንም: ሁሉ: ንቀዋልና: ስለዚህ: የመንገዳቸውን: ፍሬ: ይበላሉ፥ ከራሳቸው: ምክር: ይጠግባሉ። አላዋቂዎችን: ከጥበብ: መራቅ: ይገድላቸዋልና፥ ሰነፎችንም: ቸልተኛ: መሆን: ያጠፉቸዋልና። የሚሰማኝ: ግን: በእርጋታ: ይቀመጣል፥ ከመከራም: ሥጋት: ያርፋል።"**

የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ ይህ ፅሁፍ ሰው መንገዱን አስቦ ባላቀደው መንገድ እርስዎ ዘንድ ደርሷልና፣ ለሎች ሀላፊነታቸውን ተወጥተው ይህ እርስዎ ጋር በመድረሱ፣ እርስዎም በቅንነት ለሌሎችም እንዲደርስ ሀላፊነቱን ያሳልፉ፣ በመክሊትዎ በችሎታዎ ሁሉ ያግዙ። ይህንን ተመልክቶ በንሰሀ ወደአባቱ የሚመለስ ይኖራልና፣ የሚወደው የጠፋውን ልጁን ያገኘው የእውነት አባትም ዋጋዎን አይረሳም። ከራስዎም እንዳይዘናጉ።
ልኡል እግዚአብሄር ከሁላችን ጋር ይሁንለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።
///

# ለፕሮቴስታንቶች

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ እንዲቷም ፈፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

እኛ የሰው ልጆች ከታች በራሳችንና በፈለግነው መልኩ እንለያይ እንጂ እግዚአብሄር በኛ ልዩነት ተፅእኖ ስር ሆኖ አንዱን ከሌላው ለይቶ አይመለከተውም።

የአምላካችንም መልእክት ሲመጣ እንዲሁ ለሁሉ ለፈጠራቸው ልጆቹ ይሆን ዘንድ ነው። ለዛም ነው ይህ መልእክት ለእርስዎም የሆነው።

ይህንን የመልእክት ክፍል ለፕሮቴስታንቶች ሲፃፍ፣ እውነትን ከልባቸው ለሚፈልጉት፣ ለቲፎዞነት ሳይሆን እምነቱንም እውነተኛ አምላክን ለማወቅና ለመቅረብ ከልባቸው እየፈለጉ ብቻ ለሚከተሉትና፣ ኢየሱስ ክርስቶስን በእውነት ልባቸው ለሚወዱት፣ እንዲሁም መፅሀፍ ቅዱስ የሚለውን ለመከተል የሚተጉትን ታስቦ ነው። እንጂ እንዲሁ ሀይማኖቱን በድፍን እንደ አምላክ ፍፁም አድርገው በንቀትና ጥላቻ ሌሎች ክርስትያኖችን ለሚመለከቱት፣ በራሱ አዳኝ የሆነውን የመፅሀፍ ቅዱስን ቃል በመተማመን ፈንታና ሌሎች ክርስትያኖችን እምነት በቅን ልቦና ለመመርመር ፈቃደኛ በመሆን ፋንታ እንዲሁ ሌሎች የሰጧቸውን ትርክት አፅንቶ በመያዝ ሳይመረምሩ በጭፍን ጥላቻ ራስን ፃድቅ በማድረግ የሚመኩትን፣ ባዕዳንን ሀገራትን ስራ በሁሉ ነገር ትክክለኛ የማድረግ ስነልቦና ውስጥ ሆነው፣ እውነትን ለማግኘት በቅን ልቦና ለመመርመር ልባቸው ፍፁም የተደፈነውን፣ ስለ እውነት ብለው መርምረውት የማያውቁትን፣ ሳይቀየር ተጠብቆ የኖረውን የጥንት ክርስትና እንዲሁም የራስ ሀገር እምነት ማንኳሰስ ቀሏቸው ራሳቸውን ለናቁ አይደለም።

ለዚህ አይነቶቹ መጀመርያም ማንም ገድ ሰጥቶት አይፅፍም።

ይልቁንስ መዳን ማለት በምድር ከተከፋፈሉት ሀይማኖቶች የአንዱ አባል ሆኖ በመመዝገብ ብቻ የሚገኝ ሳይሆን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን በእውነት ልብ በመውደድ፣ የህይወት ዘመንን በሱ ፍቅር በሚደረጉ ተግባራት፣ እሱ ባቆመልን ህግጋት፣ ቃሉን ምክሩን በመከተል፣ በፍቅር የሱ የሆነውን ነገር ሁሉ በመውደድ፣ ነው ብለው ለሚያምኑ፣ የኔ ሀይማኖት ሰወች ናቸው በሚል ብቻ በሰወች ከሚባሉ ንግግሮችንና አስተሳሰቦች ይልቅ መፅሀፍ ቅዱስን ምን ጊዜም መተማመኛ ለሚያደርጉ የተፃፈ መልእክት ነው።

አጠቃላይ የዋናው መልእክት ይዘት ዛሬ ላለን ለሁላችንም ከባድ የመከራ ቀን ስለመጣ ለንሰሀና ለፀሎት ከዛሬም አሁን ተግተን እንድንነሳ የሚነግር ነው። ሌላ ጥያቄም ከቶ የለውም።

የዚህ አይነት ጥያቄ ደግሞ ከማንም ይምጣ ከማን ለጠያቂው ልፋትና ድካም ምላሽ ሊሆን የሚችል ጥቅም ወይም አንዳችም ትርፍ ሳይኖረው እንዲሁ በህዝብ በፍቅርና የሁሉ ድህነት ምኞት ብቻ ተነስቶ በብዙ ሀብትና ጊዜ መስእዋትነት የቀረበ ነው።

ይህ እውነትም ሆነ ውሸት፣ ማንም ክርስትያን እንደሚያውቀው፣ ንሰሀ መግባት አያከስር/አያሰክር በማንም ተጠይቆ ቢደረግና ቢደጋገም ማንንም አይጎዳም። ቢበዛ ቀድሞም በየትኛዋ ደቂቃ እንደሚወስደን ለማናውቀው ሞት ዝግጁ ቢያደርገን ነውንጂ። ቅዱስ ቃሉ ትንቢትን አትናቁ ይላልና፣ ለመልካም የሚጣራ መልእክት ሲመጣ አምላካችንን ከሚመጣው ክፉ ነገር ይጠብቀን ዘንድ ልንለምነው ይገባል።

ለሰራነው ሀጢያት በፀፀት ይቅርታና ንሰሀ ተመልሰን፣ እንደልጅ ንፁህ ልብ በመያዝ ልጆቹን በእውነት ቃሉ በሚወድ አባታችን ፊት ቆመን ከሚመጣው እንዲጠብቀን፣ ወደመልካም መንገድ እንዲመልሰን ልንጠይቀው ይገባናል። ንሰሀ ገብተን በንፅህና ሆነን፣ ተግተን ወዳጅ አባታችንን ልንለምነው ይገባናል።

(አምላካችን ቸር ነው፣ ከክፉ ነገር ይጠብቀናል፣ ምንም አልሆንም፣ እኔ ከክፉ ነገር የተጠበቅኩኝ ነኝ...) ይህ የብዙዎቻችን መልስ ሊሆን ይችላል። ነገርግን ልክ እንደዚሁ እንዳለን ወይም ነን የምንለውን ሆነን ሳለን ነው የአምላክ ፍርድ ከፊታችን የመጣው። እኛም አማኝ ነን ባልንበት፣ ክፋውም ክፉ ነው በተባለበት፣ አሁን በያዝነው መልክ ነው የአምላክ ቁጣ ከፊታችን የሚጠብቀን፣ ከምንም በላይ እሱ ያውቀናልና።

ስለዚህም ምንም አማኝ ነን ብንልም እንኳን እስከዛሬ ከፀለይነውና ከተጋነው የበለጠ መትጋት ይኖርብናል ነው ጠቅላላ መልዕክቱ። ዛሬ ሁላችንም አሁን ካለንበት የበለጠ ወደአምላካችን ይቅርታን ለምነን ከሚመጣው ያድነን ዘንድ ምክንያት ልንሰጠው ይገባናል።

በቻልነው መንገድ ሁሉ ራሳችንን በመፈተሽ ወደአምላካችን ለመቅረብ እጅግ መጣር ይኖርብናል። እምነታችን በቁስና ለስጋ ተገዥነት ወድቀን በንግግር ብቻ ለስሙ እንደምእራባውያን የምንይዘው ሳይሆን በቻልነው መንገድ ሁሉ ከህይወታችን ጋር በማቆራኘት፣ በፍቅር ፆምና በስግደት ስጋዊ ምኞታችን በጥቂቱም ቢሆን በመሰዋት ራሳችንን በትህትና ማስገዛትን እየተለማመድን የምናመልክ ካልሆነ ላልተን ላልተን እንደነሱ ቅዱስ ጳስሎው ስለመጨረሻው ዘመን ሰወች ሲናገር "የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል” እንደተባሉት ልንሆን ነውን? ሀይማኖት ህጉን አፅንቶ እንደማህበረሰብ በጋራ የእለተለት ህይወታችን ላይ ገብቶ ተፅእኖ ከሌለው ክርስቶስ እራሱ ሲናገር “ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።” እንዳለው

ወደፊትም በእምነት ኖረን ብለን ተሸውደን ለፍርድ ቀን ግን “በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።” ብሎ እንዳስጠነቀቀው እንዳንሆን ልንጠነቀቅ ይገባናል። መፅሀፍ በዚህ መልኩ ሳይታወቀን፣ በመልካም ምግባርና ሀይማኖት የቆምን መስሎን በባዶነት እንዳንኖር በክርስትና ስም ካሉ የበዙ መንገዶችን ከእውነተኛው ለይቶ ማወቁ ከባድ ነውና ይህንን ለዚህ ይረዳን ዘንድ መፅሀፍ ሲጠቁመን ስብከታቸውን ወይ ጌታ ጌታ ማለታቸውን ወይ የአምልኮት መልክ መያዛቸውን ሳይሆን ከሱ ይልቅ የሚለያቸው የመጨረሻዋ ፍሬያቸው እንደሆነች ይነግረናል።

መፅሀፍ ሲነግረን “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?” ብሎ ከሁሉ የከበረውን መስፈርት ይጠቁመናል። በኢንተርኔት ከአለም አንደኛ ክርስትያን ሀገር ብለን ብናስስ ቁጥር አንድ ላይ አሜሪካን ያመጣልናል ሆንም ግን የአለም አዲሲቷ ሰዶምና ገሞራነትን የተላበሰችና ለሌላው የምትሰብከ፣ ምድራዊነትና የስጋዊነት ከየትኛውም ቦታ ከየትኛውም ዘመን በላይ የነገሰባት፣ ህፃናት የወደፊት ፆታቸውን እንድመርጡ የሚበረታቱባት፣ ቁሳዊነትና ዘማዊነት ባጠቃላይ ክርስቶስ የሚፀየፋቸው ነገሮች የነገሱባት የምድራችን ክፍል መሆኗን ሁላችንም የምናውቀው ነው።

ታዲያ ክርስትና በሰፊው ቢስፋፋና በብዛት ቢሰፍን ፍሬው ይህ ነውን? ከፍሬያቸው ታውውቋቸዋቅላችሁ ብሎ በተናገረው ምን ልንላቸው ይሆን? እንደዚህ ካሉት የላሉ ቢበዙ እንኳን ማህበረሰብን ክርስቶስ በነገረን መልኩ የማይገነቡ፣ ባዶ ሆነው ሳለ፣ ነገር ግን ወደፊት “በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?” ብለው ይጠይቁኛል፣ አላውቃችሁምም እላቸዋለሁ ካላቸው መንገዶች ልንጠበቅ በቻልነውም መጠን ክርስቶስን በፍቅርና ተግባር ከኑሯችን ያዋሀደን መንገድ ልንከተል ይገባናል።

በዚህ የሰፈረው ትንቢት ማብራርያ በመፅሀፍ ቅዱስ በነብዩ ኢሳያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ወንጌላዊ ማቴዎስ... በብዙዎቹ ቅዱሳን የተነገረ ቢሆንም በዚህ ሲቀርብ ግን ተተርጉሞና ተጠንቶ፣ ተጠብቆ እንዲሁም በብዙ የኢትዮጵያዋ ቤተክርስትያን ባሉ ቅዱሳት መፅሀፍት በብዛት በመገኘቱና፣ ብዙዎቹም ለቅዱሳን አባቶቻችን በመላእክት አንደበት ስለተነገሩም በመልአክት ድርሳን መፅሀፍት፣ ለቅዱሳን በራዕይ ተገልፀው የተፃፉም ብዙ በመኖራቸው በገድላት እንዲሁም በራዕይ መፅሀፍት የተቀመጡ፣ በ ጥንት ኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ሊቃውንትና አባቶች በልዩ መልክ ተጠንተውና ተላልፈው የደረሱን በመሆናቸው ምክንያት ብቻ የቤተክርስትያኗ ጭፍን ተቃውሞ እንዲሁም አንዳንዶችም ላይ ባለ ህቡዕ ጥላቻ ምክንያት ለመካድና፣ ላለመቀበል የሚወስኑ ብዙ ናቸው።

ብዙ የፕሮቴስታንት ሰወች እንዲሁም ሰባኪዎች እነዚህን ፕሮቴስታንታዊ ከተባለው አምልኮ በመንገዱ ለየት ባለ መልኩ እና ስርአት ክርስቶስን የሚያፈቅሩ የኢትዮጵያ ክርስቶሳውያን ክርስትያኖች እንደ አህዛብ፣ ክርስቶስን እንደማያውቁ አዛብቶ የመመልከትና የመናገር፣ እንዲሁም በሰባክያን ዘንድ ከክርስቶስ ማዕከላዊነት ይልቅ እኛ/እነሱ በሚል አስተሳሰብን ማዕከል በማድረግ ለምዕመናን አዛብቶ የመናገር ችግር በብዙ ፕሮቴስታንቶች ስላለ ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን በምታደርጋቸው ነገሮች፣ ከክርስቶስ በታች በምታከብራቸው ቅዱሳን የተነሳ የዚህ አይነት ምልከታና ስብከት በአንዳንድ ፕሮቴስታንት ላይ የተዛባ ተፅእኖ አሳድሯል። ይህ ፅሁፍ የተፃፈው መሰል የቡድን ልዩነት ወሬዎችን ሳይሆን መፅሀፍ ቅዱስን በመከተል እውነተኛውን በክርስቶስ ፍቅር ላይ የተመሰሰረቱ ተግባራትንና ያቀፈ ህይወትን ለመኖር ችለን ከሚመጣው እንድን ዘንድ ነው።

እውነት የማይፈልጉትን ተዋቸው።

አንተ ግን ይህንን ትድንበት ዘንድ የቀረበልህን ትንቢት ጨምሮ ይህች የጥንት ኢትዮጵያዊ ቤተክርስትያን የያዘቻቸውን ነገር ሁሉ በጭፍን ጥላቻ አይን ለማየት አትቸኩል። አምላክም ቢሆን "ትንቢትን ሁሉ አትናቁ" ብሎ ተናግሯልና።

ግን እነሱ እንደሚሉት የትኛው ነው ከክርስቶስ የሚያርቀው?

ድንግል ማርያምን ማክበር?

እንዴት ሆኖ?

አንድ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ ከቡር የሰው ልጅ አንድን ግኡዝ ቁስ "ይህ ቁስ እጅግ የከበረ ነው እኔ በጄ ልነካው የሚገባኝ አይደለሁም" ሲል ምን ያህል ከባድ ነገር ነው?

ታላቁ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ሲናገር ከኔ በሁዋላ የሚመጣው የጫማውን ጠፍር እንኳን ልፈታ የማይገባኝ ብሎ ነበረ ኢየሱስ ክርስቶስን የገለፀው።

የእግሩ መርገጫ የሆነውን ጫማ በእኔ እጅ ሊነካ የማይገባው ብሎ አክብሮ በማወደስ የክርስቶስን ክብር እጅግ እጅግ ከፍ አድርጎ ገለፀው።

ታዲያ የክርስቶስ መርገጫ በመሆኗ ምክንያት ጫማው እንዲህ ከከበረች፣ ታዲያ የወለደችው እንደልጅ እናቴ ብሎ ሚወዳት እሷማ እንዴት ያለ ክብር ይሰጣት! አምላካችን የሆነ ክርስቶስ የግሩ መረገጫ በመሆኗ ምክንያት በጫማው ላይ ያለች ጠፍር "በቅዱስ ዮሐንስ ለመነካት የምትከብር" እስከመባል ክብርና ውዳሴ

ከተሰጣትና የሷ በክብር መታየት ለክርስቶስ ክብር መግለጫ ከሆነና ይህም ከተገባት ፤ ታዲያ ኢየሱስ እራሱ አክብሮ “እናቴ” ብሎ የሚጠራት፣ ከእቅፏ ሆኖ በእናት ፍቅር አይኗን እያየ፣ ጠረኗን እየናፈቀ ፣ ሰማያዊ አምላክ ሆኖ ሳለ እንደልጅ አቅፏት ጡቷንም ጠብቶ ያደገውን፣ የሚወዳትን በአሳዳጅ ገዳዮች መሀል በስጋት እያነባች በበርሀ ለበርሀ በስደት በእናት ፍቅር ስትደከምለት የተመለከታትን፣ ሲያያት እናቴ ብሎ እንደልጅነቱ በናፍቆት ሮጦ ሲያቅፋት ያደገ እናቱ፣ ከእናትም የራሷ ቤት እንኳን የሌላት እጅግ የድሀ ድሀ ሆና ያሳደገችው እንዴት ያለ ክብር ልንሰጣት ይቻለን ይሆን? ታዲያ ይህንን አስባ በክርስቶስ ፍቅር በተዋቀሩ ተግባራትና ህግጋት በዘመናት ርዝመት የደረጀች ቤተክርስትያንን ማንቃሸሹ ምን ይሆን ትርጉሙ?

ሚረግጣት ጫማውን እንደዛ ያከበሩ ቅዱሳንስ የሚወዳትን እናቱን ምን ብለው ሊናገሩላት፣ አወድሰውስ ይጠግቡ ይሆን?

በሉቃስ ወንጌል እራሷ “ትውልድ ሁሉ ብፅእት ይሉኛል” ብላ የሚከተሉትን እውነተኛ ክርስትያኖችን ትውልድ ተናግራ ነበር። ከጥንት ጀምሮ በዚህች ጥንታዊት ቤተክርስትያን ብፅእት ብለው ማርያምን እያወደሱ በመንፈስ ቅዱስ የተነገረውን ያንን ቅዱስ ትውልድ መሆን ነው “ክርስቶስን የማያውቁ” እንዲሉ ያደረጋቸው? ከራሱ ክርስቶስ እናት በላይ ስለ ክርስቶስ መከተል እናውቃለን እያሉን ነው?

ይልቁንስ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ድንግል ማርያምን አክብራ በመያዟ በታሪክ ለሺዎች አመታት በሀገሩ ምንጊዜም ክርክርም፣ ጥያቄም፣ አልፎ ስድብም፣ ቢመጣ እንኳን በድንግል ማርያም ዙሪያ ያርፋል እንጂ አልፎ የመዳን መሰረት በሆነው የክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት ላይ ሳያርፍ እንዲቆይ አድርጎታል። በዚህም መልኩ በፍፁም እምነት የተቀበሉት የክርስቶስ አዳኝነት፣ አምላክነት ለጥያቄ ሳይቀርብ፣ ያንን በልባቸው ቀርፀው አልፈው በውዳሴ ላይ ይገኙ

ነበር፣ የሱ የሆነውን ሁሉ ማክበርና ማወደስ፣ ያለወንድ ዘር ሙሉ በሙሉ ስጋዋን የለበሰ እናቱንም ጨምሮ። አባቶች በጥበብ ለዋናው ቤት እንደ አጥር በር አድርገው የማርያምን ክብር አቁመውት ነበርና። ከቶ ማን አጥሩን በር ሳያፈርስ የዋናውን ቤት ሊቆረቁር ይቻለዋል? የክርስቶስን አምላክነት ፍፁም አምኖ ተቀብሎ፣ በልብ አፅንቶ ከዛ ተሻግሮ በፍቅር የሱ የሆነውን ሁሉ ወደመውደድና ማክበር የተሻገረ ወደኋላ ለመመለስ ብዙ ይፈጅበታልና። ሲጀመር ሀይማኖት ጥቅሙ ይህ አይደል? የኢየሱስ ክርስቶስን አምልኮ የሚያፀኑ የአኗኗር ስልቶችና ህግጋት ስብስብ፣ ምእመኑን ለድነት በሚመራ መልኩ የተቀረፀ በዘመን የደረጁ ስርአቶችና ህግጋት ስብስብ መሆኑ አይደል?

በመፅሀፍ ቅዱስ እንደተፃፈው፣ አብርሀም ሳራ በሞተችበት ጊዜ ለረዱት ለኪጤ ሰወች እንደሰገደ፣ በለዓም ለመልአኩ በግንባሩ ወድቆ እንደሰገደ፣ ኢያሱም ወደምድር በግንባሩ ወድቆ ለ ሊቀመልአኩ እንደሰገደ፣ ሩትም በግንባሯ ወድቃ ለቦዔዝ እንደሰገደች… ሁሉ ዘርዝረን አንጨርሰውምንጂ እነዚህ ሁሉ የአምልኮ ሳይሆን የክብር ስግደት ሰግደው እንዳሳዩ፣ ያውም የአምላክና የጌታችን የሚወዳት ቅድስት እናቱ ለሆነችው ለክብሯ መስገድ ምኑ ይሆን ርክስና? የአምላካችንን ወላጅ እናት ከነዚህ ሁሉ አሳነሷትን? በስጋ አይን እንኳን ብናየው፣ በማህበረሰባዊ እሴት ግንባታ፣ በኢትዮጵያ አንድ ታላቅ ወንድ ካህን በአደባባይ ተንበርክኮ በግንባሩ ተደፍቶ ለቅድስት ድንግል ማርያም ለክብሯ ሲሰግድ ማየት ለሴቶች ምን ትርጉም ነው ያለው? ለሴቶች ክብር አንዲት አርማ የሆነች ካህናቱ ሊቃውንቱ ለክብሯ የሚሰግዱላት መኖሯ ለ ማህበረሰባዊ ስነልቦና ምን ይሆን ትርጉሙ? ክርስቶስ በጥንት በጥፋቷ በታወቀችው ሄዋን በኩል መድህኒት ሆኖ መምጣቱስ ምንን ሊያስተካክል ነው? በዚህ ደረጃ እንኳን ለሺዎች ዘመናት በዚህ መልኩ የታነፀች እምነት መኖሯ ምን ያህል ስጦታ ነበር ለኛ ዛሬ ላለነው?

የሰው ልጅ አእምሮ ሀያል ነውና፣ ታውረን ይህንን ልንንቅ ካልሆነ በስተቀር፣ ሆመቼም 40 አመት እስከሚፈጁ ትምህርቶች ተምረው፣ ሳይንሳቸውም፤ ድላቸውም፤ ምርምራቸውም ሆኖ የእግዚአብሄር ነገርን በመመራመር፣ በፍቅርና ናፍቆት ተሞልተው በመሻት፣ በዚህ መልኩ ለሺ ዘመናት የኖሩበትን ውጤት እንዲሁ ከምድር ተነስተን የምንቅ ከሆነ ከባድ ግርዶሽ ውስጥ ነን ማለት ነው።

ለክርስቶስ ክብር የሚሆኑ ምስጋናዎችን በቅኔ፣ በቅዳሴ፣ በማህሌት፣ በድጓ... እስከ 40 በላይ በሚፈጁ ትምህርቶች እየተማሩ አርቅቀው በትጋት እየኖሩ፣ ለሱ ካላቸው ፍቅራቸው የተነሳ ብሎም የሱ ወገን ለሆኑትም ክብራቸውን ቢገልፁ፣ የሱ የሆነችውን እናቱን ቢያከብሩ፣ ምኑ ይሆን ግራ የሚያጋባው?
እውነት የማይፈልጉት ልባቸው የጠመመው በራሳቸው መንገድ ይሂዱ። አንተ ግን ይልቅ ሰዎችን ሳይሆን መፅሀፍ ቅዱስንና በክርስቶስ ፍቅር ተነሳስተው የሚደረጉ የተቀረፁ ተግባራትን ተከተል።

አንተ ግን ይህንን ትድንበት ዘንድ የቀረበልህን ትንቢት ጨምሮ ይህች የጥንት ኢትዮጵያዊ ቤተክርስትያን የያዘቻቸውን ጥልቅ ነገሮች ሁሉ አንዲትም ሳይመረምሩ እንዲሁ በጭፍን ጥላቻ አይን ለማየት የምትቸኩል አትሁን፣ በመፅሀፍ ቅዱስ መንገድ ክርስቶስን በፍፁም ፍቅር የሚያምኑ ሁሉ ከክርስቶስ ልጅነት የሚከለክላቸው የለምና። አምላክም ቢሆን “ትንቢትን ሁሉ አትናቁ” ብሎ ተናግሯልና።

ሌላስ እነሱ እንደሚሉት የትኛው ይሆን ከክርስቶስ የሚያርቀው? ለመላእክት የአምልኮ ሳይሆን የክብር ስግደት መስገዱን ነው? ምን አይነት ትርጉም የሌለው ንግግር ነው የሚናገሩት?

ማነው ለመልአኩ ሀያል ክብርንና ማንም የማይቋቋመው አስፈሪ ሞገስን ያለበሰው?

ድንገት አንድ መልአክ በፊቱ ቢገለፅ፣ ሞገሱን ተቋቁሞ ችሎ ሊቆም የማይችልና በግንባሩ የሚወድቅ ሁሉ በምድር ሆኖ “ለመልአክ አልሰግድም” እያለ ሲመፃደቅ ማየት እንዴት ይገርም ይሆን? የምላስ ሀይል ብቻ ከፍ ያደረጋቸው አላዋቂዎች

ነው ወይስ እግዚአብሄርን “እንዲህ ሞገስ አልብሰህ ፈጥረህ አሳትከኝ?” ብሎ ሊከሰው ነው?

የኢትዮጵያ አባቶችና እናቶች፣ "ቅዱስ ገብርኤል ይከተልህ"፣ "ቅዱስ ሚካኤል ይጠብቅህ"... ብለው ሲመርቁ ቢሰሙ፣ የዘመኑ አላዋቂዎች "ይህ ለመልአክት አይባልም"፣ "ክህደት ነው"፣ "በመፅሀፍ ቅዱስ የሌለ ነው"... ወዘተ ብለው ሊመፃደቁባቸው ይሯሯጣሉ።

ለመሆኑ ውጊያቸው ከማንጋር ነው?

ከአባቶቻችን ከአብርሀምና ከይስሀቅ ጋር ነው? ካልሆነስ የእግዚአብሄር ውድ ልጁ ከሆነው፣ "እስራኤል" የሚለውን መጠሪያ ከአምላክ ከተቀበለው ያዕቆብ ጋር ነው ውጊያቸው? ያዕቆብ ልጆቹን በመረቀ ጊዜ በመፅሀፍ ቅዱስ ዘፍ 48-21 "ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ፥ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ" ብሎ ለተናገረው ቃል ሊከሱት የሚመፃደቁን ምን እንበላቸው? ነው ወይስ ውጊያቸው ክብራቸው የእግዚአብሄርን ፊት እስከማየት ከፍ ካለው ከመልአክት ጋር ነው?

ከንቱ ተዋጊዎች ብሎም የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ህዝብ በልመናው "ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፣ እባክህን ከጠላት ውጊያ ጠብቀኝ"፣ "ቅዱስ ገብርኤል ሆይ ከመከራ ሰውረኝ"... ብሎ በዚህ መልኩ መልአክትን ቢማፀን ዛሬ ራሳቸውን ያፀደቁ አላዋቂዎች ሊተቹና ሊሳደቡ ሲመፃደቁ ይታያል። ወይ በአባቶቻችን ዘመን ሎጥ መልአኩን ጌታዬ ሆይ ብሎ በልመና ቢማፀን "የተናገርካትን ከተማ እንዳላጠፋት እነሆ በዚህ ነገር የለመንከኝን ተቀብያለሁ" ብሎ የመለሰለትን፣ ሊሄድባት

ያሰባትንም መንደር ከጥፋት የታደጋትን መልአክ "ስለምን ልመናን ትቀበላለህ? መች ስልጣን ሰጠሁህ፣ መች ፈቀድኩልህ" ብለው ይቃወሙት ይሆናል። ምናልባትም መልአኩ ኢያሱ ዘንድ በመጣ ጊዜ በመፅሀፍ ቅዱስ እንደተፃፈው "...እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና። ጌታዬ..." የሚለውን ባዩ ጊዜ በመልአኩና በኢያሱ ላይ ሌላም ሌላም ነገር እንናገር ሳይሉ የሚቀሩ አይመስሉም።

የዚህ አይነቶቹን መከተል ራስን ማውረድ ነው። ለራሳቸው ፍርድ ተዋቸው፣ መፅሀፍ ቅዱስን አስቀድመህ ተከተል። ትላንት ከትላንት ወዲያ በተነሱት፣ ያውም እምነትን እንደሁለተኛ ወይ ከዛ በታች አድርገው በሚኖሩ ውጪዎች ባህል ሳይሆን፣ ለሺ አመታት ያውም ሳይቋረጥ ባህሏም፣ ምርምሯም፣ ጥበቧም ይኸንኑ አድርጋ፣ አምላክን ክርስቶስን ከጥንትም መሰረቷ አድርጋ በዚህ መልኩ በዘመን ሂደት የተቀረፀው ባህሏን፣ የኢትዮጵያ ክርስትናን ባህል መላበሱ ከብዙ በብዙ ይልቃል። ሲሆን ሲሆን፣ ይህችው ያንተው ሀገር የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን መልክህ፣ ሀብትህ፣ ለዘመናት ያንተው አያት ቅድመአያቶችህ በእውነት ከክርስቶስ የተዋሀዱባት ማንነትህ፣ በአፍሪካውያን በአለምም ሁሉ ፊት ቀደምት ያንተው መከበሪያህ ነበረች። እሷም አምናም፣ ትላንትም፣ ዛሬም ነገም የተቀላቀሏት፣ የሚቀላቀሏትም ሁሉ እኩል ሀብት ናት።

በነሱ አፍ ሌላስ የትኛው ነው ከክርስቶስ የሚያርቀው?
ሮብ ሮብ ሲሆን፣ እያዘኑ አንተን በዚህ እለት ያለጥፋትህ ሞት ፈረዱብህ? በማለት በዚህስ ቀንስ ምግብ አልበላም ብሎ ራስን ከምቹ ምግቦች ከስጋ ከወተት ቆጥቦ እስከ 6 ና 9 ሰአት እድሜልክ በራስ ፈቃድ መፆሙ?

አርብ ሲሆን፣ በሀዘን በዚህ እለት ያለሀጢያትህ ከወንበዴዎች አባቴን ጋር ሰቀሉህ? ብሎ እንዲሁ ቀኑን በማሰብ ከልጅነት ጀምሮ እድሜ ልክ በዚህ እለት ምግብ ለግማሽ ቀን ሳይበሉ ቡሀላም በፆም ምግብ

መዋል ነው ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚያርቀው?

የዚህ አይነት ከንቱ ጠማማነትን በመያዝ ሌላውን ከድህነት ይልቅ ጎራ ይዞ በድንቁርና ውሸት መከራከርን የሚመርጡትን ተዋቸውና አንተ ግን ራስህ በንሰሀ አፅድተህ፣ የሰራኸውን ላትደግመው ለራስህ አምነህ እንደልጅ በፍቅር ሆነህ አምላክህን ምህረትን፣ ከሚመጣው መአት መጠበቅን አንዴ ሳይሆን ዘወትር ለምነው።

ራስህንም በአምላክህ ዘንድ ዝቅ አድርገህ፣ ዘወትር ተግተህ ለምነው፣ ራስህንም ዝቅ አድርገህ፣ አይደለም ከሱ ከሀያሉ ጌታ፣ አገልጋዮቹ ከሆኑ ከመልአክቱም ስር በትህትና ወድቀህ ለምናቸው፣ ወደክርስቶስ እንዲለምኑልህ ለምናቸው። መልአክትን ለምኑልን ብሎ መጠየቅ አዲስ ነገር ሳይሆን በመፅሀፍ ቅዱስም መከራ በፀና ቁጥር ቅዱሳን የሚያደርጉት የትህትናና ራስን ዝቅ የማድረግ ተግባር ነውና፣ ያውም በመፅሀፍቅዱስ ላይ ከሁሉም የመጀመርያ ፅሁፍ በሆነው መፅሀፈ ሔኖክ ላይ ጭምር በመከራ ልመና የፀኑ ሰወች ወደአምላካቸው እየለመኑ እንደገናም "እናንተ በሰማይ ያላችሁ መላእክት ልመናችንን ወደእግዚአብሄር አግቡልን" እያሉ ሲማፀኑ ጭምር ቃል በቃልም ሰፍሯልና።
ለነገሩ ከነሱ ማን ይህንን መፅሀፍ ይቀበለውና?

ፕሮቴስታንቲዝም ሲመሰረት፣ የመፅሀፍቅዱስን ስብጥር እንዳዲስ ሲያደራጁ መፅሀፍት በዘመናት በተነሱ ጥፋቶች በመጥፋታቸውና በመበታተናቸው በነጮቹ እጅ መፅሀፈ ሔኖክ በትክክል ተሟልቶ ባለመኖሩ የተገኙትን 66 መፅሀፍት በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ አደረጓቸው። ቡሀላም በቅርብ በውጪዎቹ 1947 ሙትባህር አርኪዎሎጂስቶች ወጥቶ በጥናት ጊዜው ከሺ ሰባትመቶ አመታት በላይ አካባቢ መሆኑ የተመሰከረለት እውነተኛ የጥንት መፅሀፈ ሔኖክ በመገኘቱ ቡሀላም ሲስተያይ በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ውስጥ ብቻ ተጠብቆ ካለው መፅሀፈ ሔኖክ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ በይፋ የተዘገበና አለምን ያስገረመ ታሪክ ሆኗል። ቡሀላም

ለክርስትያኖች የሚቀርብበት መንገድ እየተጠና፣ አንዳንድ ቦታላይም እየተያያዘ እየተሸጠ፣ በብዙ አጥኚዎች ጥናት እየተደረገ ይገኛል።

ታዲያ በዘመናት ተጠብቃ ተከልላ ሳትወረር ሳትበረዝ በቅድስና የኖረች በጃንደረባው አማካኝነት ከሁሉ ቀድማ መቀበሏ በመፅሀፍ ቅዱስ የተመሰከረላት፣ ከየዘመኑ ጋር አብሮ ለማስኬድ ብላ እምነቷን ሳትነካካ እንዳለ ያኖረች፣ ይህንንና መሰል ቅዱሳት መፅሀፍትን ጠብቃ በክብር ያኖረች እንቁ ክርስትያን ሀገር ውስጥ እየኖሩ፣ መፅሀፉን ፈልገው ካጡት ውጪዎች ጋር አብሮ መቸገር “ያባይ ልጅ ውሀ ጠማው” የሚያስብል፣ አሳዛኝ ያዲሱ ትውልድ የውጪ አምላኪነት ህመሙ ይመስላል።

ከኦርቶዶክስ ተዋህዶም እምነት ቢሆን እንደዚሁ ስለሌሎች ሀይማኖቶች በጥላቻና ድፍንነት፣ በጎራ ያዥነትና አለመመርመር በከንቱ የሚናገሩትን ሚያጥላሉትን ተዋቸው። በሌሎችም ሆነ በፕሮቴስታንት ሀይማኖት ያሉት የዚህ መሰል ያለምርመራ ሀሰት ተናጋሪዎች ለማንም አይጠቅሙም። እውነትን ከመፈለግ ይልቅ ክርስቶስን ከመፈለግ ይልቅ የሀይማኖት ጎራን እንደአምልኮ ይዘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን እንዲሁ በጥላቻ ብቻ በመስበክ የሚከራከሩትን አሁንም ተዋቸው። ይሁዳ በመልእክቱ በስሙ ጠርቶ የመሰከረለትን ነብዩን ሄኖክ፣ ወንጌላዊው ጳውሎስ ሄኖክ ከክብሩና ቅድስናው የተነሳ ሞትን እንኳን ሳይቀምሳት በእግዚአብሄር መወሰዱን፣ አምላክንም ደስ እንዳሰኘ የመሰከረለትን ሄኖክ እንደው ማን ነን ብለው፣ እንዴት ቢመፃደቁ ይሆን አንቀበልም የሚሉት? የሚቀበሉስ ቢኖሩ፣ ነብዩ ኤርሚያስን ተቀብሎ ትንቢተ ኤርሚያስ መፅሀፍን መጣል ምን ማለት ይሆን? ነብዩ ኢሳያስን ተቀብሎ ትንቢተ ኢሳያስንስ መፅሀፍን መጣል ምን ማለት ይሆን? ባካል ያላገኙት ከሄኖክ ከሺ ዘመናት በኋላ የመጡት ሀዋርያት፣ እነ ቅዱስ ጳውሎስ፣ እነ ይሁዳ በዘመናቸው ያነበቡትን፣ ሄኖክንም አውቀውት እንዲመሰክሩለት ያስቻላቸውን መፅሀፍ መጣል መቃወም እንዴት ያለ መመፃደቅና ክህደት እንደሆነ ራሳቸው የካዱት

ይወቁት።

አንተ ግን አባትህ ክርስቶስን፣ እውነትን ለማወቅ ብቻ አላማህ አድርገህ ኑር። ከሚመጣው እንዲጠብቅህ ለምነው።

የሚጠብቀን ውድቀታችን እጅግ የከፋ ነውና በሁሉ መንገድ እጅግ ተግተህ በሁሉ መንገድ በእንባ ለምነው። እውነትም መከራው ከሌላው አለም ኢአማንያን ይልቅ በኛ ይፀናልና። ከመጀመርያው በወንጌል ተጠማቂ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጀምሮ መቶ አይደለም፣ ሺዎች አመታትን በክርስትና፣ በእግዚአብሄር ተአምራት መሀል የኖርን፣ ምሳሌ በሚሆኑ የክርስቶስ ቅዱሳን ገድልና ታሪክ በዝቶ በሚነገርበት፣ ቅዳሴ ያለማቋረጥ በሚፈስበት ሀገር ላይ ሆነን በክህደት መንገድ ስንጓዝ፣ በውድቀት በርክስና መንገድ ስንነጉድ የቅጣት መከራችን እንዴት እንደሚበዛ መፅሀፍ ቅዱስን አንብቦ የሚያውቅ ክርስትያን ሁሉ እንግዳ አይሆንበትም። ምክንያቱም በመፅሀፍ ቅዱስ ወንጌል አንዴ ብቻ ሳይሆን ሁለቴም ሳይሆን ሶስት ቦታ ላይ በማቴዎስ በማርቆስ እንዲሁም በሌላ አገላለፅ በሉቃስ ወንጌል ላይ ይኸው ቃል ተደጋግሞ የተፃፈ ነውና

“ወዮልሽ ኮራዚ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና። ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። ... ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል።"

በዚህ መሰረት የተተነበየው ጥፋትና መከራ በኛ ላይ እንደሚፀና ምስክር ነው። ሁላችንም እጅግ ተግተን ተባብረን ወደአምላካችን ልንጮህ ይገባናል። ለቅዱሳን ልጆቹ ስለገባቸው ቃልኪዳኖች ብሎ ይምረን ዘንድ ልንለምነው ይገባናል።

# ለሙስሊሞች

**ሙሉው ሳይፈፀም ይህ የመጨረሻው ሰፊ ጥሪ ነው**

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ አንዲቷም ፈፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

ሀይማኖት ሁሉ ስለ ህይወት፣ ስለመፈጠርና መኖር ምክንያትና ግብ፣ ስለ ቀጣይ ታላቅ ፍርድ የሚናገር በመሆኑ ማንም ሰው በሀይማኖቱ የሚያሾፍና የሚቀልድ ባለመሆኑ ሁሉም ሰው በሙሉ አእምሮው አመዛዝኖ፣ ከልቡ በመሻት ነው ሀይማኖቱን የሚይዘው። ዛሬ በኢትዮጵያ እንዳለነው ትውልድ ልል፣ ቸልተኛ አማኞች ሳይሆን።

ቅን ሙስሊሙ በተቻለው ሁሉ ሊቀርበውና ለማምለክም የሚተጋው የክርስትያኖችን ፈጣሪ ነው። ቅን ክርስትያኑም ሁሉ በተቻለው መጠን ሊቀርበውና ሊያመልከው የሚተጋው የሙስሊሞችን ፈጣሪ ነው።

የአንድ ቤት የአንድ ፈጣሪ ልጆች አንዱን የጋራ አባታችንን ለማመስገንና ለማምለክ ስለእውነት በመሰለን መንገድና አምልኮ ስንተጋ ቆይተናል። የጋራ አባታችን አንዱን የሚጥር ቅን ልጁን ከሌላው አብልጦ ወይ አሳንሶ አያየውም። በእውነት ልብ ፈልገው አባቴ ብለውት ቢፈልጉት እንደአብርሀም ወደቤቱ መንገድ ይመራቸዋል እንጂ። ማንኛውም በቅን ልቦና ስለእውነት ከልቡ ፈልጎ አምላኩን ለማግኘት በፍቅር የሚተጋ ሰው የጋራ አባታችን አይጨክንበትም።

ነብያትና ትንቢቶች በክርስትናም ሆነ በእስልምና ሀይማኖት ያሉ፣ በደንብ የሚታወቁ የእምነቶቹ ክፍሎች ናቸው። ቅዱሳን ለሆኑ

ሰወችም ስለወደፊቱ እውነት ገልጦ የሚነግራቸው እንዳሉ ይታመናል። በክርስትና ብዙ የተፈፀሙ፣ ወደፊት ገና የሚፈፀሙ ትንቢቶች በፍርድ ቀን ስለሚፈፀመው፣ ስለ እስራኤላውያን መበትንና መሰብሰብ ወዘተ በደንብ ግልፅ ሆነው የተፃፉ እንዳሉ ሁሉ፣ በቁራኑም ስለወደፊቱ ፍርድ ቀን ምን እንደሚሆን፣ ስለ ሀይማኖት ክህደት መስፋፋት፣ መልካም ሰው መጥፋት ወዘተ ተፅፏል። በዚህም መልኩ ትንቢት ለሁላችንም አዲስ ነገር አይደለም።

ዛሬም በእኛ ዘንድ ተፅፈው ያሉትንና ከፍፁም ጥፋትና ውድቀት፣ ከፉ መከራ እልቂት እንድንባቸው ዘንድ ከሺ አመታት ጀምሮ በብዙ የተለያዩ ቅዱሳን በአንድነት እኛን በሚገልፅ መልኩ የተገለጡ፣ ዛሬ ያለን ህዝቦች ይሄኛው ያኛው ሳይል ሁላችን በንሰህና ተመልሰን በፀሎት ፀንተን እንድንባቸው ዘንድ የተፃፉልንን አቅርበንላችኋል።

በተመሳሳይ በአሁኑ ወቅት ልንድንበት የተፃፉ መልእክቶች በናንተ ዘንድ ቢኖሩ ልክ እንደኛው በወንድማዊ ፍቅርና፣ በእውነት ካመኑበት አደጋ ሁሉ ይድን ዘንድ በወንድማዊ ፍቅር እንዳቀረብንላችሁ እናንተም በለሁላችን ታሳውቁንና ታቀርቡልን እንደነበረ በፍፁም አንጠራጠርም።

ይህም የተፃፈው ለሁላችንም የአባታችን ልጆች ነው። ከእናንተም ሆነ ከኛ ከማንኛችንም መሀል ከሚመጣው ለመዳን ከሁሉም የሚጠበቀው ወደ ፈጣሪ ተመልሶ፣ በፍፁም ልብ ለሰራው ሀጢያት በፀፀትና ንሰሀ ፀድቶ ያቅርታንና ጥበቃን ከፈጣሪያችን መለመን ነው።

በዚህ ፅሁፍም ሌላ የሚጠየቅ ነገር ከቶ የለም። ይህንንም አመናችሁትም አላመናችሁትም ብታደርጉት የምትከሰሩበት ነገር የለም። ንሰሀ በመግባት፣ ይቅርታና ጥበቃን ከፈጣሪ ከመለመን ንሰሀና ፀሎት እንደሆነ ኢያከስር/ኢያሰክር

አይደለም በዚህ ወቅት በማንኛውም ጊዜ ጥያቄ የሌለው ጠቃሚ ነገር ነውና። ይህንንም አንብቦ ያንን ተግቶ የሚያደርግ ሰው ምን ሊጎዳ? ይህንን ካነበቡ በኋላ ሞት በስንት አመት ወይ ወር ወይ ቀን ወይ ሰአት ወይ ደቂቃ እንደሚመጣ ምን መተማመኛ የሌለን በመሆኑ ቢያዘጋጀን እንጂ ሌላ ምንም ጉዳት እንደሌለው ግልፅ ነው። ቀድሞም ወደአምላክ ለመመለስ ዛሬ ነገር የለውምና።

ከምንም በላይ ደግሞም የትንቢቶቹ የቀደሙ ክፍሎች በትክክል ቃል በቃል የተፈፀሙ እውነቶች ስለመሆናቸው በማስረጃዎች ተደግፎ ታሪክ የሚመሰክርላቸው በመሆኑ፣ ቀሪዎቹም ክፍሎች በዛው መልኩ መፈፀማቸው ይቀጥላል።

ማወቅ አለማወቅ መዳኛ ሆኖ አያውቅም። ነገርግን እምነትና የህይወት ተግባር ነው ለድህነት ምንጭ። ይህንን ይወቁም አይወቁም በመልካሙ መንገድ ለፈጣሪያቸው ቀርበው፣ ሀጢያትን አርቀው፣ በንሰሀ ፀድተው የተገኙ ሁሉ በፈጥአሪ ጥበቃ ስር ይሆናሉ። በኛም በተለያዩ ቦታዎችና መንገዶች የኖርንና ያደግን ሆነን በፈጣሪያችን ህግጋትና አገላለፅ፣ ቀድሞም በፈጣሪያችን ዙሪያ በተሰሩ ታሪኮች አቀባበል ብንለያይም፣ የሱ መገለጫ በሆነው ፍቅርና መልካም ተግባራት፣ ባህሪያት በአንድነት የምንስማማ በመሆኑ፣ በፍቅር አንድነት ሆነን በየገባንና በያመንንበት መንገድ ፈጣሪያችንን ለመቅረብ በመሞከር ልንኖር፣ በመፀለይ ልንገኝ ይገባናል። በሚመጡትም አስፈሪ ጊዜያት በብዙዎች መሀከል ጠላትነት በመፍጠር የተለያዩ ፀቦችና ግፊቶች ቢመጡም ከሁሉ በላይ ፍቅርና ሰብአዊ መተሳሰብን በማስቀደም በምናምነው ፈጣሪ ህግጋት ከምንም በላይ ለመፅናት በመሞከር ልንታግስ ይገባናል። ሁላችንም ወደእውነተኛው የፈጠረን አምላካችን ለመቅረብ መጣር፣ በሱም ፈቅድና ትእዛዛት ለመኖር ይበልጥ መጣር ይጠበቅብናል።

በተዋህዶ ክርስትናም ቢሆን የአምላክ ፍርድ እንዲሁ በኛ አይን ፈርደን የምናውቀው፣ ሀይማኖ ለይተን እንኳን ይህ ይፀድቃል ይህ ይሞታል ፈፅሞ የምንለው አይደለም። አዲስ ነፍስ፣ ህፃን ሲወለድ መወለጃውን ስፍራ እሱ መርጦ ሳይሆን ፈጣሪ በወሰነው ቦታ ነፍሱ ትመጣለችና፣ ወይ በጥንታዊ እስልምና በምትታወቀው መካ፣ ወይ በጥንታዊዋ ተዋህዶ ክርስትና ምትታወቀው በላሊበላ፣ ወይ ደግሞ ምናልባትም ከአለምና ሰውልጆች ጋር ተያይተው የማያውቁ የአማዞን ጫካ ጎሳዎች መሀል ሊወለድ ይችላል። መርጦ አልመጣምና በዚህ ምክንያት ብቻ በፈጣሪው ፊት ከሌላው የሰው ፍጡር ተቀድሶ ወይ ረክሶ በውልደቱ የሚፈረድበት ሳይሆን ለኛ ደቃዎቹ የ ፍትሀዊነትንእውቀት የሚያመዛዝን አእምሮ የፈጠረው ፈጣሪ እሱ ደግሞ በእፁብ ልኡል ፍትሀዊነት ፍርዱን እንደሚሰጠው ይታመናል። መፅሀፍትም በባዶ ኖረው ከሞቱት ይልቅ ፈጣሪ በይፋ በሚሰበክበት መሀል ኖረው ራሳቸውን ያረከሱና የካዱት ላይ ፍርዱ እንደሚፀና ይናገራሉ።

በዚህም መሰረት የሰው ልጅ የተም ሆነ የት ፈጣሪውንና አባቱን ለማወቅ እጅግ በመጣር፣ በቅንነት በተገለጠለት መልኩ ወደ አባቱ ለመቅረብ ቢጥር፣ ፈጣሪውን ለማግኘት በቅንነት፣ ለህሊናውና ላመነበት ራሱን አስገዝቶ ልባዊ ቅን ትኩረት ወደፈጣሪው አድርጎ ዘወትር ቢጣራ ፈፅሞ የሚመለከተው ፈጣሪ አባቱ እንደማይጨክንበት እሙን ነው። ስለዚህም ሁላችንም እርስበርስ በቅንነትና ሁሉም እምነት በሚሰብካት በፍቅር ሆነን ልንፀና ይገባናል።ካልሆነ ግን ሞት እንደሆነ በፊታችን ፀንቶ ቆሟልና ምርጫው የኛ ይሆናል።

በተዋህዶ ክርስትናም ሆነ በኢስላም አንድ፣ ፍፁም ከአንድ አምላክ ሌላ አምላክ ፈፅሞ የለም። እሱም ሁላችንንም በጥበቡ በአንድነት ያፀናን ፈጣሪ አንድ እሱ ነው።  በግለሰብ ደረጃ የዋህና በቅንነት እውነትን ብቻ ፈላጊ ሙስሊም ሆነህ፣ እሱም የዋህና በቅንነት እውነትን ብቻ ፈላጊ የሆነ ክርስትያን ወንድምህ ጋር ስትታዩ ሁለት

አባታቸውን የሚፈልጉ የአንድ አባት ወንድማማቾች እንጂ ሌላ መልክ ልትሰጣጡ አይገባችሁም። በእኩል አመዛዛኝ አእምሮ ተፈጥሮ ያላችሁ እኩል ፍጡራን ናችሁና በቅንነት ስለእውነት በአባት ፍቅር እስከሆነ ድረስ ይህን ልባችሁን የሚመለከት እውነተኛ አንድ አባታችሁ ወደ እቅፉ መርቶ እንደሚወስዳችሁ ጥርጥር የለውም።

ይህም መልእክትና ፅሁፍ በፍቅርና በቅንነት ብቻ ሆኖ ሁላችን እንድን ዘንድ ለእርስዎ የደረሰ ነው። ከሚመጣው ሁሉም እንደ እምነታችን ድክመትና ምግባራችን ውድቀት ሳይሆን እንደ ይቅርታውና ቸርነቱ ሁላችንንም በጋራ ይጠብቀን።

# ለ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናን

**ሙሉው ሳይፈፀም ይህ የመጨረሻው ሰፊ ጥሪ ነው**

**"ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ቃሌ ግን አያልፍም።" ማቴ24:35፣ሉቃ 21:33፣ማር 13:31**
**ሁሉም ላይ ተደጋግሞ የተፃፈ ፅኑ የስላሴ ቃል**

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ከቃሉ አንዲቷም ፈፅሞ በማትታበል በአንድ አምላክ ስም**

ኦርቶዶክስ ክርስትያንነት በዘመኑ ምእመን አያያዝ፣ ልክ ጨዋታውን አይተውለት የማያውቁት ግን ሲጠየቁ ብቻ ስሙን አስታውሰው “የዚህ ቡድን ደጋፊ ነኝ” እንደሚሉት አይነት አያያዝ ሆኗል ሀይማኖቱን የያዛት።

ብዙውም መልካም ክርስትያን ሳይቀር በዚህ መልእክትና ይዘት፣ እንዲሁም ትንቢት ግር ሊለው ይችላል። የቤተክርስትያን ሰወች ከሚባሉትም ሳይቀር ይህንን አፈታሪክ ብሎም ተሞኝቶም የሚያይ ብዙ የዋህ ይኖራል።

ነገርግን ይህ በሀገር ደረጃ ከደረስንበት፣ የመሪዎችና አባቶች ክፉኛ በጠላት ፅኑ ሴራ መዳፍ ተይዞ መውደቅና የቤተክርስትያን ሰብሳቢና ባለቤት አልባነት ያስከተለው የምንጋራው ፍፁም ውድቀታችን ማሳያ ነው እንጂ ይህ ነገር ፈፅሞ የፀና እውነትና የዘመኑ ምእመናን ልናውቃት ደንታ ኖሮን የማያውቀን የሀይማኖታችንም ደማቅ እውነትና የልዑል እግዚአብሄር የማያልፍ ቃል ነው።

ደንዝዘን፣ በዋዜማው አጋንንት ልባችንን ሰውሮት ካልሆነ በስተቀረ ከነዚህ እንደው የትኛው ይሆን ልዩ ባእድ የሆነብን?

የቅዱስ ራጉኤል ድርሳን? ይህን መፅሀፍ ነው የማናውቀው? ነው ወይስ ካድነው? የመልአኩን ቃል ካድነው? እምነት ቀይረናልን? ወይስ ለኛ ሲባል ቤተክርስትያኑም ፈርሶ፣ ድርሳኑም ተቃጥሎ አዲስ

አርቶዶክስ ተዋህዶ ይመስረትልን? ነው ወይስ የካድነው የቅዱስ ዑራኤልን ድርሳን ነው? የእግዚአብሄር መልአክ እስከነ ንግስና ስሙ ጠቅሶ የመሰከረበትን ቃል?

አምላካችን ክርስቶስ በመልካም ልጅነት እናቴ ብሎ የሚያፈቅራትን ድንግል ማርያም ቅዳሴዋን የደረሰው አባ ሕርያቆስንስ ልትክደው ተነስተሀልን? ነው ወይስ ቅዳሴውን ቀድሞም አትቀበለውም ነበር? የእዝራሱቱኤል ትንቢታዊ ፅሁፍ ተተርጉሞ ኢትዮጵያውያን እንድናውቀው በማሰብ ወደሀገራችን አስቦ የላከው እርሱ መሆኑ አልተፃፈምን?  ነው ወይስ የቁመት የሰአታቱን ውዳሴ አባት አባጊዮርጊስ ዘጋስጫ? እሱስ እንግዳ ሆነብህ? እሱስ ብዚ ጊዜ ስለዚህ አልተናገረምን? መፅሀፈ ምስጢር ብሎ ፅፎ ባስተማረበት መፅሀፍ ንጉሱን በስም ጠቅሶ እንደውም አልፎ ከነገሰ በኋላ ሮም ድረስ ሄዶ ስለሚያደርገው ሀይማኖታዊ ድል ሳይቀር በሙሉ ምዕራፍ ተብራርቶ አልተፃፈምን?

ወይስ የኢትዮጵያ ሊቃውንት መፅሀፍ ቅዱስ ትርጓሜ ላይ የወደፊት ትንቢት በሰፈሩባቸው ቦታዎች እግዚአብሄር በገለጠላቸው መንገድ ስለብዙ የወደፊት ተፈፃሚ ትንቢቶች አብራርተው አልፃፉምን? ክርስቶስ በዚህ ዘመን ስለሚሆነው የተናገረውን አልፎም በሀገራችንም የሚሆነውን በሚነግሰው ንጉስ የሚፈፀመውን ጭምር አላሰፈሩትም?

ራስህን እንድትታዘብ ተባዝተው በእጅህ ያሉትን ለመጥቀስ ነውንጂ በብዙ መፅሀፍት፣ እንደነ ገድለ ፊቅጦር ባሉ፣ በምንኩስና ፋና ፊልክስዩስ፣ በግብፃዊው አባት ሲኖዳ ራዕይ፣ በሳቤላ ራዕይ፣ በተአምረ ኢየሱስ፣ በፍካሬ ኢየሱስ.... በስንቱ በስንቱ የተጠቀሱትንማ ማን ችሎ ሲዘረዝር ይውላል? የተመቸንን ብቻ እየመረጡ መያዙ ክፋት ነው ትርፉ። እስራኤላውያን እንኳን የጥፋታቸውን፣ የመበተናቸውን የመከራቸውን ትንቢት የሚናገረውን መፅሀፍ ይዘውት ቆይተው ነበር።

የእስልምናው መፅሀፍ ቁራን እንኳን ወደፊት የመካዋ የካእባ በኢትዮጵያዊው ሰው መፍረስ ይናገራል።

አምላክን ስለእውነት የሚፈልግ፣ ልቡ ብሩህ የሆነስ እንደ ቅዱስ ያሬድ ያለውስ፣ ያለንባብ፣ ያለድምፅ ሰበካ ዛፍ ከምትወጣ ትል ብቻ አይቶ ይማራል። ያላደለው ግድ መስሎ ስለታየው ብቻ ያለ ፈጣሪ ፍቅር ሀይማኖት የተቀላቀለው ደግሞ፣ አይደለም በዚህ ሁሉ መፅሀፍ አውርሰውት በሰውነቱ ቢነቅሱት፣ ወይ ደግሞ እንደይሁዳ ከአምላክ ጋር ቢያከርሙትም እንኳን ትርፉ ባዶ ነው።

እኛም አውቀን ልባችንን አንዝጋው። ምን መሀይም ብንሆን በየዋህነት አምላክን ከልባችን ብንፈልገው፣ ስለሱ ልናውቅ ብንሻ ወዳጅ አባት ነውና የማይገልጥልን፣ የማያደርግልን ነገር ፈፅሞ አንዳችም አይኖርም። ቀድሞስ የሁሉ ፈጣሪና ባለቤት ከኛ ኢምንት ደቂቃን ከቶ ምን ይፈልግና?

በዚህ ወሳኝ ጊዜ እንዲህ መሆናችንን ልብ ገዝተን ልናስተውለው ይገባል። ልንነቃ ይገባናል። የተተነበየ ቀን ሲቀርብ ነገሩ ሁሉ እንዲህ ነውና። ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳን “ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ” ብሎ ለራሱ ትንቢቱን ነግሮትሳለ፣ እሱ ግን ትንቢቱ እስኪደርስ ከልቡ ተሰውሮ ሁሉ አልቆ የተባለችው ዶሮ ሲሰማ ነበረ ያንን ትንቢቱን ልብ ብሎ በፀፀት ያለቀሰው።

ሌላም ወደፊት ሀሳዊው መሲህ እኔ አምላክ ነኝ እያለ እንደሚመጣ ተብራርቶ ተፅፎ ሳለ ግን ጊዜው ሲደርስ እጅግ እንዲሁ ልብ ያላሉ የበዙ ተከታዮች፣ አለም ሁሉ አምላኪው እንደሚሆን ሁሉ እኛም ዛሬ በዚህ በተጠቀሰው ትንቢት ደጃፍ ላይ በመሆናችን ብዙዎች ደንዝዘን ልባችን ታውሮ እንገኛለን። በኢትዮጵያ የብዙ የክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ቅዱሳን ቃልኪዳን አለና እኛም አዘውትረን የሱ የክርስቶስ ባሪያዎች በመሆናቸው አክብረናቸው በትህትና የምንለምናቸው ቅዱሳን ልጆቹና መላእክትም ስለኛ ክርስቶስን

ቢለምኑት አልጨከነብንምና አሁንም የተወሰኑም ልብ ብለው ይድኑ ዘንድ ይኸው ባልታሰበ መንገድ ይሄ ፅሁፍ እርስዎም ጋር ደርሷል።

በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ተጠብቀው ለእምነቷም መሰረት የሆኑ ብዙ መፅሀፍትና ሀብቶች አሉ። ብዙ ምእመኗ ግን በነሱ የሰፈሩትን እንኳን ተማምኖ ለማመን ይቸግረዋል። ታዲያ መፅሀፍቷን ካላመንክ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መሆንህ ምኑ ነው? ነው ወይስ እንደ ምእራባውያን እምነት በአፍ ብቻ እግዚአብሄርን እየጠሩ፣ የመረጡትን ብቻ ከመፅሀፍ ቅዱስ እየወሰዱ በርክስና ህይወት እንደሚኖሩት መኖር ይሻላል? ማመን ወይ መካድ እንጂ በሁለቱ መሀል ሆኖ እኔ ክርስትያን ነኝ ማለት ግዴለሽነት ነው። ብዙዎቹ ለራሳቸው የሚመቻቸውን ብቻ ነው የሚቀበሉት። ሀይማኖት እንደ አጃቢና ማድመቂያ ሆኖ የፈለግናቸውን ብቻ በፈለግነው መንገድ ወስደን ለምድራዊ ምኞታችን ማዳመቂያ ነው የምንጠቀምበት። ለሰንካላው የአምላክን ህልውና ከምንም ሳንቆጥር በስጋ ፍትወት ለምንቃዠው አላማችን፣ ከአምላክ የሚያርቅ ይሁን የሚያቀርብ ገድ ሰጥቶን ለማያውቀው፣ በዚሁም ምክንያት ለመፈትፈት ግብዣና ገድ የማያስፈልጋቸው ልክስክስ አጋንንት ለሚጋልቡት፣ ለዚሁም ምልክቱ ሞትና ደም ለሚቀድመው ፖለቲካችን ማሟሟቂያ ብቻ የኢትዮጵያ ትንሳኤ የምትለውን ቃል እንዲሁ አጃቢ እናደርጋታለን።

## ለመሆኑ ትንሳኤ ማለት ምን ማለት ነው?

በመነሻነት በቅዱሳት መፅሀፍት የተፃፈውና በብዙው ኢትዮጵያዊ “የኢትዮጵያ ትንሳኤ” ተብሎ የሚታወቀው ይህ ትንሳኤ ግን እውነታው ምንድነው? ሁሉም ማለት እስኪያስደፍር ድረስ፣ መልካም ክርስትያኖችም ጭምር ይህንን ነገር አዛብተው ነው የተረዱት።

ማንም አሁን ቢጠየቅ መልካሙም ክርስትያን ጭምር የኢትዮጵያን ትንሳኤ በአእምሮው ያለው:

( ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ የበለፀገች ሆና ከአለም ሀገራት ተርታ መሰለፍ፣ በኢኪኖሚዋ ጠንካራ መሆን፣ መከላከያዋ እጅግ ብርቱ፣ በአለም ሀገራት ላይ ተፅእኖ ፈጣሪ ሆና፣ ህዝቦቿ በሀብትና ደስታ የሚኖሩባት፣ አለም ሁሉ ወደሷ የሚሰደድባት ክብሯ የተጠበቀ ኢትዮጵያ፣ ዴሞክራሲና ነፃነት እንዲሁም ሳይንስና ህክምና ቁንጮ ) ይህ ነው ሁሉም “የኢትዮጵያ ትንሳኤ” ብሎ የሚገልፀው።

ልክ ይኸው አገላለፅ ፣ ብዙዎች ከአለም የሚሰደድባት፣ የነፃነትና ዴሞክራሲ (ህዝብ በብዛት ሆኖ የፈለገው ማንኛውም ነገር የሚታወጅበት)፣ የሀብትና ጥንካሬ ቁንጮ የሆነችዋን አሜሪካን አይገልፃትምንዴ? እውነት 27 አመት ማንም ሳያስገድዳቸው በአንዷት ዋሻ ቆመው በፆም በስግደት እንደቅዱስ ዮሀንስ በበረሀ ከምኞት ወደው ርቀው ያለፉት አቡነ ተክለሀይማኖት ይሄ አጓጉቷቸው ትንሳኤ አሉት?

ጣልያን በዚህ መልኩ ያደገች ጠንካራ ብዙዎች ለመድረስ በባህር የሚሰጥሙላት ሀገር ነች። የኛን የትንሳኤ ምኞት ሀገር ትመስላለች። የአለም ቁንጮ ሆና የጣልያን እቃ ሲባል እራሱ ክብሩ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ታዲያ ምነው በአንድ ቀን ተመሳሳይ ህልም ያዩት መቶዎቹ የሮም ቅዱሳን ስለራሳቸው ሀገር ስለሮም ጣልያን ስለዚህ ትንሳኤዋና ሀያልነትዋ አልታያቸው? ምንሆነው ነው እትብታቸው ስለተቀበረችበት ምድራቸው ይህ ሁኔታ አልተናገሩ? ምነው አልፈው ስለ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ተናገሩ?

የሮሙ ቅዱስ ጳውሎስስ ቢሆን ምነው ስለዚህ የሮም መፃኢ ሀያልነትና አሁን ስላለችበት ትንሳኤ አልተናገረ? የቆስጠንጥንያው ዮሀንስ አፈወርቅ አልታየውም ይሆን እንዴ የሀገሩ ትንሳኤ? የቆስጠንጥንያ ወደ ኢስታንቡል መቀየር፣ የቱርክ ሀያል ሀገርነት፣

በኢኮኖሚና ስልጣኔ እጅግ ገዝፋ ከዩሮፕያን ዩኒየን አባል ለመሆን እስከመሰለፍ እንደምትደርስ? ከዙሪያዋ ያሉ ዛሬ እንደሚታየው ወደሷ ሊሰደዱ ሲሻሙ? አይ ቅዱስ አባታችን፣ አልታየውም ነበር እንዴ የሀገሩ ህዝብ ነፃነት? ዴሞክራሲ ነውና ብዙ ህዝብ ስለጠየቀ የወሲብ ንግድ የሚደግፍ ህግ መውጣቱ? ቁጥጥር አድራጊ አካል መቋቋሙ አልታየውምን?

አዩዩ... ምነው የመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዳሴዋን የደረሰው የቆስጥንጥንያ ብህንሳው ኤጲስ ቆጳስ አባ ሕርያቆስ፣ ለእእዝራ ሱቱኤል የተነገረውን የቅዱስ ዑራኤልን ዜና፣ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ትንቢት ወደኢትዮጵያ አስተርጉሞ ያመጣው እሱ እራሱ አልነበረምንዴ? ታዲያ ምነው ስለራሱ ክህነት ቦታ ቆስጠንጥንያ (የዛሬዋ ቱርክ ዋና ከተማ ኢስታንቡል) ሀያልነትና ትንሳኤ፣ ሀብት መትረፍረፍ፣ ከውድቀት ተነስቶ የአለም ሀያል ሀገር መሆን ምንም አልተናገረ?

ይህ ለምን የሆነ ይመስላችኋል?
እውነተኛ ክርስትያኖች ሆይ ፈፅሞ አትሳሳቱ! እንደዛ ያለ የኢትዮጵያ ትንሳኤ የለም። ትንሳኤ ቃሉ ራሱ የሚያመለክተው ከነበረበት የወደቀና የተዋረደ ሁኔታ ወደበፊቱ ወደነበረበት ክብር መመለስ ማለት ነው። የኢትዮጵያ የቀድሞ ማንነትም በእግዚአብሄር በረከትና ሀይል ተጠብቆ መኖርና በመልካም ስራና ክርስትያናዊ ህይወታቸው ምክንያት በአምላክ ተወዶ መኖር ማለት ነው። ትንሳኤ ማለት “ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሄር ትዘረጋለች” የሚለውና “ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይመራሉ” ይሚለው የዳዊት ትንቢት የሚፈፀምበት በአምላክ መነፅር የታየ ታላቅ የእግዚአብሄር ህዝብነት ነው። ህዝቡ በእምነት ወደአምላኩ የሚመለስበት ሀገሪቱም በአምላክ የምትባረክበት አኗኗር ነውንጂ በስጋ ሀብት፣ በብረት ሀይል ግዝፈት መመካት፣ በወርቅና ብር መትረፍረፍ ከመቼ ወዲህ ነው በቅዱሳት መፅሀፍት ትንሳኤ ተብሎ የሚፃፈው? ለሱ ለሱማ የነአሜሪካ ይህ ምጡቅ ሀያልነትን አያሰፍረውም ነበር?

እንዴት ያለ መታወር ነው? ከመቼስ ወዲህ ነው መልአክ ትንሳኤ ብሎ ይህንን እንደ አሜሪካ ያለ ስጋዊ ሀያልነት የምስራች ብሎ የሚናገረው? አምላክስ ቢሆን በራእይ የሚገልጠው? በነቢያት የሚያስነግረው?

አሁን እንደሚወራው የኢትዮጵያ ትንሳኤ ተብሎ ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ በልፅጋ፣ ጥሩ መንግስት ይዛ፣ ህዝቦቿ በነፃነት የፈለጉትን ሆነው፣ የዴሞክራሲና ነፃነት ጥግ የሚባለው ግብረሰዶማዊ ጋብቻ ተፈቅዶባት፣ አምላኳን በካደ ሳይንስ የበላይ ሆኗ... እውነት ይህ እንዴትስ ይሆናል?

እምነት ያለው ወደአምላኩ ተመልሶ፣ አውቆ ከሀዲውና ጠማማው በፍፁም ጥፋት ከተጠረገ በኋላ የሚመጣ የቀና የእግዚአብሄር ህዝቦች ከአምላካቸው ጋር በአንድነት የሚኖሩበት ትንሳኤ ነው የኢትዮጵያ ትንሳኤ።

እንዲጠፋ የፈለጉትን ነገር ማስረሳት እጅግ ከባድ በመሆኑ በሌላ ነገር መተካት ግን ውጤታማ የማጥፋት ስልት ነው። ለዚህም ነው በውጪ ሀገራት የክርስቶስን ልደት በ x-mass ትንሳኤውን በ Easter በመተካት በአላቱ ደምቀው ቢከበሩም እንኳን ከሀይማኖታዊ በአልነት ወደ ተራ ፌስቲቫልነት ተቀይረው በመከበራቸው ህፃናት እንኳን ትውልዱ የማ ልደት ነው ሲባሉ እንኳን በአእምሯቸው የገና አባት እንጂ ክርስቶስ እንዳይታያቸው ድረስ ተገልብጦ ሲወድቅ ይታያል።

በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ትንሳኤ በሁሉ የታወቀና በኢትዮጵያውያን የሚጠበቅ በመሆኑ ሊረሳ የማይቻል በመሆኑ ሌላ መልክ ባለው ሌላ ትንሳኤ ተቀይሮ እንዲታሰብ ሰይጣን የሚያደርገው ውጊያ ነው ይህንን መዛባት የፈጠረብን።

የዚህም ውጤቱ ከትንሳኤው በፊት ለሚመጣው መከራና ጠረጋ በእምነት የተዘጋጀን ሳንሆን በተሳሳተ መልኩ መልኩ ተሰልፈን፣ በመቅሰፍት እንድንወድቅና እንድንጠፋ የታሰበ ትልቅ አደጋ ነው። ይህም ሁሉ የመጣው በሀይማኖታችን እጅግ ደክመን መፅሀፍቶቻችንን መመርመር በማቆማችንና ይህንንም በማድረግ ለህዝቡ ያገለግላሉ ተብለው የሚጠበቁት የእምነት አባቶች የድርብርብ ጥቃትና ማዳከም ኢላማ በመደራጋቸው ነው።

ነገርግን ሁላችንም ይህንን አውቀን፣ ከሚመጣው መከራ አምላክ እንዲጠብቀን በመማፀን በእምነትና ንሰሀ ወደ አምላካችን ቢያንስ ለኛም ባይሆን ለቤተሰቦቻችን ልንለምንና እንዲያድነን ምክንያት ልንሰጠው ይገባናል።

በተለያየ መልኩ የሚመጣ ሰይጣን በብዙ መልኩ ሊያዳክመን ብዙ ነገሮችን አድርጓል። በኢትዮጵያና በቤተክርስትያኗ ላይ ያደረገውም ውጊያ አሁንም አብሶ የሚያደርገው ውጊያ ከምንም በላይ የበረታ ነው። ለዚህም የውጭ ጠላቶችንና ዘረኛ መንግስታትን መሳሪያ አድርጎ ተጠቅሞባቸውል።

በዝባዥ ሀያላን ሀገራት ከጥንትም በአፍሪካ ማንነት ያለው ህዝብ መሆን፣ እራሱን ማክበሩ ለመገዛትና ባርነት እንዳይመች ስለሚያደርገው በኢትዮጵያና እምነቷ እንዲሁም ታሪኳ ላይ ትልቅ ዘመቻና እቅድ ተደርጎ ለማጥፋት ተሰርቶበታል። ይህም እንዲሁ በወሬና ለራስ ችግር ሌላን ለመውቀስ ተብሎ የሚነገር ሳይሆን እራሳቸው የዚህ ተግባር ባለቤቶች አይን ባወጣ መልኩ በመፅሀፍ “Abyssinia: The Powder Barrel” በሚል ርእስ እቅዱን አሳትመው የኢትዮጵያ ዘውድ ክብር፣ የቆየ እንቁ ከህዝቡ የተዋሀደ ክርስቲያናዊ እምነት፣ ባህል አፍሪካ እንዳይገዛና ቀና ብሎ እንዲሄድ ሊያስተባብር የሚችል አደገኛ ፈንጂ በመሆኑ በዚህ እንዲተባበሯቸው ለማስተባበር በተለያዩ ሀገራት ሲያሰራጩት የነበረው መፅሀፍ ዛሬ በኢንተርኔት ላይ ምስክር ሆኖባቸው ይናገራል።

ከዚህም ባለፈ በመንፈሳዊ መልኩ፣ ሰይጣን የእግዚአብሄርን ህዝብ ለመበተን፣ ትውልዱን ለማጥፋት ፈፅሞ አይተኛምና አምላክን በማክበር፣ በራቸውን ዘግተው ወራሪን በእምነት ሀይል በመመከት ለእግዚአብሄር ተገዝተው የኖሩ ህዝቦችን ለመጣል የሚመጣ ጠላት ሁልጊዜም አይተኛም።

በነዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ክርስትና ላይ እጅግ ከፍተኛ የማይታመን ድብቅ ጥፋት ተሰርቷል። የማጥፋት ሁሉ የመጨረሻው ተግባር ጥግ ሊባል እስከሚችለው ድረስ በስኬት ሊያደርጉን ተችሏቸው፣ ከህዝቡ መፍዘዝና ለእግዚአብሄር ካለው ቸልተኝነት የተነሳ ጠላቶች ቤተክርስትያናችንን የማፈራረስ እቅዳቸው እጅግ ወደስኬት ከመድረሱ የተነሳ ለፈሊጣዊ ንግግር እንኳን ለግነት “በቋንቋ አንግባባም” የሚባለው በአካል እስኪፈፀምብን ድረስ ደርሶ ቤተክርስትያንና ምእመኑን በቋንቋ ጭምር ተለያይቷል። ግእዝን ፈፅሞ የማይሰማ፣ አባቶች ስንት የደከሙበት የተራቀቁበት ወርቃማ የቅኔ፣ የዝማሬ፣ የቅዳሴ፣ የምስጋና፣ የፈጣሪ ፍቅር ውጤቶች ምኑም ያልሆኑ ሊረዳቸው የማይችል ትውልድ ተፈጥሯል፣ አሁንም ወደባሰው እጅ እየተሸጋገረች ትገኛለች።

የኢትዮጵያ ጠላቶች ይህንን ድንቅ የሺ አመታት ክርስትና ሀብት ማቃጠልና ማጥፋት ሳይጠበቅባቸው፣ ባልተጠበቀ ስልት የቋንቋውን ትምህርት በማግለል የሚመጣው ትውልድ ምኑም እንዳይሆኑ፣ እንዳይረዳቸው፣ ስሜት እንዳይሰጡት፣ ባዶ እንዲሆን ተደርጎ ተቀርጿል። በኛ ትምህርት ስርአት እንዳይካተት አድርገው ሲቀርፁልን፣ በራሳቸው ምድር ግን ልጆቻቸው እስከ ዶክትሬት ደረጃ ተራቀው እንዲማሩበት አድርገውታል። ቅዳሴ እንኳን ልቁም ቢል ምንም በአእምሮው ሳይረዳ እንዲሁ ከመንፈሳዊ ከበረከቱ ብቻ ተካፍሎ እንዲመለስ የሆነ ምስኪን ወላጅ አልባ ትውልድ ሆኗል። ያኔ ጥንት እንግሊዞች ከእግዛዚብሄር ይልቅ ቀድመው በንጉሱ አእምሮ ላይ ሲነግሱ የኢትዮጵያን ትምህርት ስርአት በአዲስ ሲተካ፣

እንግሊዞች የኢትዮጵያ መሰረት የሆነው የግዕዝ ቋንቋ ለትውልድ እንዳይተላለፍ፣ እንዳይካተት ከፍተኛ ተፅእኖና ተግባር ነበራቸው። ለማካተት የነበረውንም ጥረት፣ በውጪ አስተሳሰብና ትምክህት ጠምቀው ያመጧቸውን ምሁራን ተብዬዎች በመጠቀም፣ ማንነታቸውን ተጠይፈው ቋንቋውንና ይዘቱን እንደኋላቀርነት ምንጭ አድርጎ በመስበክ እርግፍ አድርገው በመተው፣ ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ የመሳሰሉት ተክተው እንዲሰጡ በማድረግ በስልት ኢትዮጵያዊውን የአፍሪካ ባለታሪክ ኮከብ ህዝብ የእምነትና የጥበብ ሰንሰለቱ እንዲበጠስ ጥረዋል።

ይህም ሁሉ ሆኖ በአምላክ ቸርነትና ቅዱሳን ፀሎት ከህዝቡ ልብ አምላክን ሊወጡት ስላልተቻላቸው ዛሬ የኢትዮጵያ ክርስትያን ሁሉም ሲጠየቅ ከሁሉ ነገር የማስቀድመውና የማስበልጠው እግዚአብሄርን ነው ይላል።

ነገር ግን ህይወቱና የህገሩ አላማ ከዚህ የተቃረነ ሆኖ ተቀርፆበታል። ባላሰበው ባልፈለገው መንገድ የአምላክን ህልውና የካደ፣ ኢአማኒነትን የሚሰብክ፣ የእምነት መጥፋት መዳረሻው የሆነ የትምህርት ስርአት፣ የአስተዳደር ርእዮት በጥቂት ሰወች ስልጣን፣ ባልተስማማበት መንገድ ተጭኖበት ይኖራል።

የሰው ልጅ አንድ አእምሮ ነው ያለው። ማንም ቢሆን ከሁሉ የሚቀድምበት ፈጣሪው እንደሆነ ይናገራል። በዛው አእምሮው ደግሞ በህይወቱና ጉዞው ሌላን ነገር ሙሉ በሙሉ አስቀድሞ ይጓዛል።

የአእምሮ ሁኔታ እጅግ ወሳኝ ነውና፣ እንዲህ መከፈሉ፣ ወደአንድ አለማድረጉ በፈለገው መስክ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል። ወይ አምላኩን እርግፍ አድርጎ ትቶ ሙሉ የአእምሮ ሀሳብና ችሎታውን የኢኮኖሚ እድገት፣ ሳይንስ ልዕቀትን ብቸኛ ግብና ቀዳሚነት ወዳደረገው ርዕዮት አልገባ ወይ ደግሞ አምላኩን

እንደሚለው አስቀድሞ፣ ሁሉን ሌላውን ከሱ በታች አድርጎ ውጤታማ አልሆነ። በተፈጥሮው በሁለት መሀል መዋለል ላይ ሆኖ በሙሉ ሀይሉ ሊሰራ የማይችለው አእምሮ በትክክል ተንቀሳቅሶ እንድናድግ ያልሆንነውም ለዛ ነው።

ወይ እንደባቢሎን ሙሉ ክደን ትልቅ ስልጣኔላይ አልተገኘን፣ ወይ እንደሶሎሞን አምላክን አስቀድመን ትልቅ ጥበብና ስልጣኔ ላይ አልተገኘን፣ ከሁለት ያጣ ሆነን ደርቀን ቀርተናል።

ወይ ፈጣሪን ክደንላቸው አጋንንት የምድርን ሀብትን፣ ብልፅግናን፣ አልሰጡን፣ ወይ ለፈጣሪ አባታችንን ተገዝተንለት በምድር ባለው ላይ ሁሉ በሾመበት ቃሉ እንደ ጥንታችን ባለጥበብና ፀጋ አላደረገን።

የዛሬ ሁኔታችን ሲገለጥ በትክክል የሚከተለውን ይመስላል።

አንተም የእግዚአብሄርን መኖር ፍፁም የምታምንና፣ አባታችንም ከሁሉ ነገር ይቀድምብኛል የምትል ከሆነ ብቻ ከዚህ በሁላ ያለውን አንብበው። ያንን የተቀበለ በሚከተለው የማይስማማበት አንዳችም ምክንያት የለምና
ለመደህየታችን፣ ለኋላቀርነታችን ግን ቆይ በማን ይሆን የሚፈረደው?

እስቲ ስለእውነት በሀቀኝነት እንመልከት፣

ዛሬ በሀገራችን ሀብትን ያገኘ ሰው፣ ብር የበዛለት ሰው፣ ይበልጥ ወደእግዚአብሄር ሲቀርብ ነው የምናየው ?ወይስ ይባስ ሲርቅና የሚወልዳቸውም ልጆቹን ከእግዚአብሄር በሚያርቅ መልኩ ሲቀርፅ?

ታዲያ ማን ልጁን የሚወድ ከሱ የሚያርቀውንና ወደ ጠላት እጅ

ሚመራ ነገርን ይሰጠዋል? ታዲያ እግዚአብሄር እውነት የሚወደን ከሆነ እንዴት ከሱ እንድንርቅ ያደርገናል? ሀብት ሰጥቶ ስለምን ያርቀናል?

ስነልቦናችን ሀብት ሲያገኝ አምላክን የሚያርቅ አድርገን ከቀረፅነው፣ ይህንን ለመገመግምና ለማስተካከል የማንጥር ከሆነ ታዲያ አምላክ ምን ያድርገን?

ትቶን እንዳይተወን ደግሞ፣ በልባችን እንደምናፈቅረው ያውቃል፣ እንደምንወደው ያውቃል፣ ከሱ መራቅን ፈልገን ተግባራችንን በዛ መልኩ እንዳላደረግን ያውቃል። ታዲያ እንዴት ይተወን? በድህነትም ቢሆን ልጆቹ አድርጎን በአለም ለነገሰው ለሰይጣን እንዳንወድቅ ይጠብቀናል እንጂ።

ነው ወይስ “ዞርበልልን አንፈልግህም፣ ልቅቀን ተወን፣ እንደግበት” እንበለው? ቆርጠን በአንድነት እንደዛ ብንለውኮ ምንም ችግር የለበትም፣ ልክ እንደሌሎቹ ሀገራት በሀብት ገነው፣ የሰዶምን ተግባር አውጀው፣ የሰይጣን አምልኮን ፈቅደው እንደሚኖሩት ሀገሮች መሆን እንችላለንኮ። ድሮውንስ በግል እንኳን በጥንቆላ የሚገኝ ሀብት እንደዛ አይደልንዴ የሚመጣው? ደሞ ለምድር ሀብት!

ነገርን ግን ሁለት ሀይል ብቻ ነው ያለው። ይሄኛውን ርቀን ሄደን ጥበቃውን ስናርቅ፣ ሌላኛው አነፍናፊ መዳፍ ውስጥ ነው ራሳችንን የምናገኘው። ከሁለቱ ሌላ የለም።

አምላክ ከኛ ምን ችግር አለበት? ሀብቱን እድገቱን ልዕልናውን ቢሰጠን? ምን ቸግሮት? ኢምንት ቅንጣት የሆንን ፍጡራን ምን አገኘን ምን ያዝን ምን ግድ ኖሮት? ምንም አይቸግረውምኮ። ጥንት እንደዛ ሆነን የኖርንባቸው ወርቃማ ጊዜያትም ነበርኩንኮ።

በተለያዩ ጊዜያት በ 1997 ጨምሮ ምነው አምላክ በሀገራችን ላይ

መልካም እንዲሆን አላደረገም? ብለን ስንቴ ይሆን የወቀስነው? ምን ለመሆን? እንደ አሜሪካ ባለ የዴሞክራሲ፣ የግለሰብ ነፃነት፣ ሊብራሊዝም፣ የሳይንስ ሊቅነት ወዘተ ለመሄድ?

በብዙ የአውሮፓ፣ የምስራቅ ክርትያን ሀገሮች ተተግብሮ ያየነው፣ በጊዜ ሂደት ሁሉንም ወደተመሳሳይነት መልክ የሚመራ፣ ባህልን፣ አማኝነትን፣ ሀይማኖትን፣ እጥብ ጥርግ አድርጎ አፅድቶ በአዲስ ማንነት፣ ልቅ ስነልቦና፣ ለስሜት ተገዥነት፣ ቁስ ገንዘብ አምላኪነት የተመሰረት በሁሉም ቦታ ፍፁም ተመሳሳይ አዲስ ማንነት ሲቀርፅ ያየነው እንደ ኮሪያ እንደ ጃፓን፣ እንደ ቱርክ የመሳሰሉ በባህል እምነትና አስተሳሰባቸው ፍፁም የተለያዩ የነበሩ ሀገራትን ትውልድ ወደ ፍፁም ተመሳሳይ አሜሪካ መሰል ስነልቦና ህግጋትና ባህል እየቀየረ እየተመለከትነው ያለውን ርዕዮት

አንዲትም ሳይቀየር በዴሞክራሲ ስም በሀገራችን ነግሶ ስለምን አንተን አጥፍቶ አላሳደገንም ብለን በአይናውጣነት ጠይቀን እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም።

በዚህ ንግግሬ ኋላቀር፣ ፀረ ዴሞክራሲ፣ ዘመኑን ያልዋጀ... መስዬ ታየሁህ አይደል? “አምላክን ከሁሉ የማስቀድም ነኝ” ብለህ ካልተስማማህ እንዳታነበው አስቀድሜ ነግሬህ ነበረ። ላስቀድም ካልክ ግን እውነታው ይህ ነው።

ጨርሰህ ሳትሰማኝ አትፍረድብኝ ወንድሜ፣ እኔም ዴሞክራሲን እንዲሁ ዝምብሎ መቃወም የያዝኩ አይምሰልህ። በዛ ስም ሆነንጂ ዴሞክራሲ እራሱ አልነበረምና ቀርቦልን የነበረው፣ ይልቅ በሱ ስም ከትርጉሙ በተቃራኒ ሰይጣናዊነትን ይዞ የመጣ ነውንጂ።

እስቲ ልጠይቅህ፣ ዴሞክራሲ ማለት የብዙው ህዝብ ፍላጎትን ማክበት አልነበረምን?

ብዙ የሰርቬይ ድርጅቶች እንደሚሰሩት ኢትዮጵያውያን ከአለም አንደኛ የሆኑበት ነገር አለ "ለአምላኬ ከሁሉም በፊት ቦታ እሰጣለሁ" በሚለው አስተሳሰብ። ሙስሊምም ሆነ ክርስትያን የኢትዮጵያ ህዝብ ከአለም አንደኛ የራሱ እምነት ያለው ህዝብ ነው።

ይህ ሆኖ ሳለ፣ እናሳንሰውና 90% ህዝቡ ሁሉ ፈጣሪዬ ከሁሉ ዋና አላማዬ ነው የሚል ሆኖ ሳለ ዴሞክራሲ ቢሆን ኖሮ እንደህገር የጋራ አላማውን የሚቀርፅለት አስተዳደሩ እንዴት ፈጣሪን አንዲት ጊዜ እንኳን አክብሮ ቦታ ሰጥቶ ሊይዘው አልቻለም? ሙስሊምም ሆነ ክርስትያን በአምልኳቸው አንድ የሚያደርጓቸውን ነገሮች ላይ ተመስርቶ ለአምልኳቸው እንዲረዳቸው የሚችል እንዴትም አንዳች፣ አንዳች ነገር ሊያመቻች ወይ ሊሰራ ተጠየፈ? የድፍን ሙሉ ህዝቡን የመጀመርያ ፍላጎት እቅድ አላማ የሆነውን ነገር እንዴት ሊጠቅስ አልቻለም? ይሄ ነው ዴሞክራሲ? ጭፍለቃ?

እሺ ማመቻቸቱ ይቅርና፣ እንዴት ዴሞክራሲ ሆኖሳለ፣ ግን ድፍን ሙሉ ህዝብ የሚቃወማቸውን የረከሱ ተግባራት ሊያውግዝለት አልቻለም? ሙሉ ሀብ እምነት ያለው በሆነበት ሀገር፣ የወሲብ ንግድ (ሴተኛዳሪነት) ሙሉ ህዝቧ የሚጠየፈው ሆኖ ሳለ፣ በህግ የተፈቀደ እንደማንኛውም ያለ አድርጎ የብዙሀኑን አንገት ማስደፋት ነው የብዙሀኑ ህዝብ አስተዳደር የተባለለት ዴሞክራሲ መስፈን?

እንደ አሜሪካ፣ ካናዳ ያሉ የርኩሰት፣ የ ሰዶምነት ምልክት ተብለው በሚወሰዱት ሀገራት እንኳን ለትውልድ ስነልቦና ሲባል በህግ ደረጃ ወንጀል ተብሎ ክልክል የሆነውና በፍርድቤት ክስ የሚያስቀጣው የወሲብ ንግድና ሴተኛዳሪነት እንኳን በሀገራችን ህጋዊ መብትና ልቅ ስራ ያደረገው ነው የብዙሀኑ አስተዳደር/ዴሞክራሲ?

ሁሉ ህዝብ ፈጣሪዬ ብሎ የሚጠራው አምላክ እያለው፣ ይህ የብዙሀኑ አስተሳሰብ ፍላጎት ሆኖ ሳለ ልጆቻቸው "ፈጣሪ የሚባል ነገር የለም፣ በዝግመት ከቁሳት ወጣችሁ፣ እምነት ኋላቀር ነው"

የሚል ትምህርት በመንግስት ደረጃ ከህዝቡ በሚሰበሰብ ታክስ ወጪው ተሸፍኖ በብቸኝነት እንዲሰጥ ማድረጉ፣ የማይፈልጉት አይነት እምነት ያላቸው ልጆች እንዲኖሯቸው የሚያስገድድ ስርአት ነው የብዙሀኑ አስተዳደር/ ዴሞክራሲ ማለት?

ዝገመተለውጥህ ስለተነካብህ እንደኋላቀር አይተህ እንደምታጉረመርም ይጠበቃል፣ ግን ጥፋትና የተጋፊነት ጫኝ ተግባር ያደረገው የዝግመተለውጥ ትምህርት መሰጠቱ ሳይሆን፣ በህዝቡ ታክስ በመንግስት ተደግፎ፣ በብቸኝነት መሰጠቱና ሁሉም የሚያምኑበት፣ ከህዝብወሳኝነት/ዴሞክራሲ ፍፁም ተቃርኖ የኢትዮጵያ አማኝ ህዝቦች ልጆቻቸው እንዲማሩት እጅግ የሚፈልጉት የክርስትና/እስልምና የሰው አፈጣጠር ሂደትና የፈጣሪው ማንነት ይህንን ይመስላል ተብሎ ጎንለጎን እንደማስተያያ እንኳን እንዳይሰጥ በጉልበተኝነት ማገዱ፣ ብሎም ይሄ ሁሉ ከህዝቡ በሚሰበሰብ ገንዘብ የልጆቻቸውን አእምሮ ባልፈለጉት መልኩ ተተኪያቸውን መቅረፁ፣ ህዝቡ በሚፈልጉት ባህልና እውነት ሳይሆን ቀራጮቹ በፈለጉት ባህልና የአስተሳሰብ መልክ ትውልድ መቅረፁ ነው።

በሰው እምነትና ፍልስፍና ላይ አይደለምንዴ አስተዳደርም፣ ትምህርትም ምንም ነገር በመሰረትነት የሚቆመው? ሰዉ ለራሱ “ሰው ምንድነው? ከየት መጣ? ሰው ምን ያስፈልገዋል? ምን እናድርግ?” የሚለውን ተመስርቶ፣ ያ ታይቶ ለምሳሌ “ሰው ማለት ሙዝ ለመብላት የተፈጠረ ነው” ብለው ከደረሱበትና ካመኑ፣ ትምህርት ስርአቶች ሙዝ ማምረት ላይ አተኩረው በመስራት፣ ያንንም ማሻሻልን አላማና ግብ አድርገው ይቀረፃሉ፤ አስተዳደሮቹም ህዝቡ ያለችግር ሙዝ መብላት እንዲችል ለማስቻል በቻለው መንገድ ሁሉ የሚተጋ ይሆናል። በዚህም መንገድ ህዝቡ ያለችግር ሙዝ በተሻለ ሁኔታ በመብላት በደስታና ስኬት ይኖራል። ይህ አይደለምንዴ እውነታው መሆን ያለበት? ካልሆነማ ሌላ የተጫነ ከንቱ ነገር ነው ማለት ነው። ማንን ለማስደሰት ብለው ያንን

ያደርጉታል?

እኛስ ከራሳችን እምነትና መንገድ፣ የህይወት ግብ ተፃራሪ የሆነን እዳ ስለምን ብለን እንሸከማለን? ሁሉን የፈለግነውን የማድረግ ሙሉ ችሎታና መብት እያለን? ማንን ለማስደሰት ብለን ያንን እናደርገዋለን?

በ 1997ም ሆነ በሌላ ጊዜያት እንግዲህ ይህን ነው ካልነገሰብን ብለን የምናማርረው። እንዲሁ ሙሉውን ያልተረዳነውን ነገር በራሳችን ለማወጅ እሽቅድድም። እውነት አለ ካልን ለአምላክ ውዳሴ ምስጋና ነውንጂ ልናቀርብ የሚገባን፣ ባሰብነው መንገድ ለመንጎድ ስላላስቻለን።

ስለዚህ አምላክህን የምትወደው ከሆነ አሁን ቀና ብለህ "በ97 ምርጫም ሆነ በሌሎች ጊዜያት የተመኘሁት እንዲሳካ፣ እንዲፈፀም ስላልሆነ አመሰግንሀለሁ" ብለህ እስቲ አመስግነው። አምላክህን ለመውደድ መራቅ ላለመፈለግ ልብ ያለህ ከሆንክ እስቲ ደፍረህ እንዲህ በለው!

ያ አካሄድ አምላክን እናስቀድማለን፣ ዋናው የህይወት አላማችን እሱ ነው ለምንል በነፍሳችን ለምናምን ህዝቦች ነውንጂ፣ ለሌሎችስ ይጣጣም ይሆናል። ወይ ፍፁም ከደን ቁጭ ማለቱን ማን ከለከለን? እውነቱን ስለምናውቅ፣ የፈጠረም የምናመልከው አባት ስላለን ነውንጂ። እንዲያ ከሆነ ግን እውነቱ ይህ ነው።

ከሱ ከጌታችን የሚያርቅ ያልሆነ የመንግስትና አስተዳደር ስርአትን፣ የትውልድ ልቅነትና ሀይማኖት ቸልተኝነት ላይ ያልተመሰረተ፣ መቶ አመት ብንኖርበት ከአምላክ ከማራቅ ይልቅ የሚያቀርበን የሆነ የመንግስት ስርአትን ይዘን በፊቱ ብንቆም አምላካችን ያለአንዳችም

ማንገራገር ከአለም ሁሉ በላይ ሊያደርገን ምንም ጥርጥር አልነበረውም ነበር። እሱ እንደሆነ ዝቅ ብሎ በኛ ምድራዊ ታላቅነትና ሀያልነት ላይ ምን ችግር ኖሮበት ቦታ ሰጥቶ ትሆናላችሁ/አትሆኑም ይለናል? ይህ ለሱ ምኑ ነው? ሀገራዊ ኢኮኖሚያችን በሺ ተቆጠረ/በትሪሊዮን ተቆጠረ ለሱ ምኑ ነው? ለኛ ለልጆቹ ደስ ያለንን የጠየቅነውን ያለምንም ችግር ያደርግልናል እንጂ። ግን እኛ ከሱ ፍቅርና ቅርበት ይልቅ የመጀመሪያ ግባችን አድርገን የኢኮኖሚ ግዝፈትን ስንይዘው፣ አልፎም በሌሎቹ በምስክርነት የመንገዱ መዳረሻ በታየ መልኩ ከምንወደው ከሱ በሚያርቀን፣ እንደው በርትተን ከኛም ባይሆን እንኳን ከትውልዶቻችን የሱን ክብርና ፍቅር፣ ለሱ ያለንን ቅርበት አጥቦ የሚያጠፋ መንገድ መሆኑ ባደጉት ሀገራት የተመሰከረውን አካሄድ ስንይዝ ግን፣ እውነት የሚወደን ከሆነ ሊያቆመን ግድ ይለዋል። ያ ግን ገደብ አለው፣ ብዙዎችቻን ክደን ልቀቀን ብለን ብንታገለው፣ አልመለስ ብንል ግን ይህች ቅድስት ሀገር የኛ የበዛነው ከሀዲያን ብቻ ሳትሆን የተባረኩ ቅዱሳን ልጆቹ ፀንተው እየኖሩ ያሉባት ናትና፣ ከቅዱሳን አባቶቻችን ቃልኪዳን ያላት ናትና፣ አሉና ስለነሱ ሲል ቤቱን የምንረብሸውን እኛን ለራሳችን አሳል ፎይሰጠናል። በሀገራዊ ክህደት ጉዟችን ወጣቱ እርስ በርሱ ይበላላል፣ በክህደት ርእዮት ራሱን ያጠመቀ ወጣት ሌላ እርስ በርስ መከፋፈያ ቢያጣ "ማሸነፍ" እና "ማቸነፍ" በሚለው ቃል ሳይቀር እርስ በርስ ሲገዳደል አይተናል፣ ያንንም ተግሳፅ አይተን ያልተመለስን የርሬዎቹ በምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ወደውድትቷችን ከቀን ቀን እንነጉዳለን። እኛም ለራሳችን ተላልፈን የተሰጠን እንሆናለን፣ ወጣቱ በየምክንያቱ ያልቃል፣ ይተላለቃል፣ የቻለው በዘር፣ በመዋለዱ ዘሩ ቢዋሀድበት እንኳን ቋንቋ ለይቶ ይገዳደላል። በዚህም መልኩ መንግስት ለመመስረት በምናደርገው ምዘናችን፣ መስፈርታችን ሁሉ እስክናመልከው ድረስ ለምናፈቅረውና ለምናስቀድመው፣ እሱም በአምሳሉ እስኪፈጥረን ድረስ የሚያፈቅረን፣ አልፎም እስኪሰቀልልን ድረስ ከሚያፈቅረን አምላካችን ያርቀናል? ወይስ አያርቀንም ብለን ለአንዲትም ሴኮንድ ቆመን ማሰብ እስከተቻለን ድረስ፣ ወደጥፋታችን የምንነጉድ ይሆናል።

አንድ አገልጋይ ገበያ ሲወጣና የሚገዛውን ሲመርጥ፣ ለራሱ የሚመች ሚመቸውን ብቻ እየመረጠ፣ “ጌታዬ ይወደው ይሆን? ጌታዬን ያስቀይመው ይሆን?” ሳይል ቢያደርግ፤ የጌታው ምላሽ ምን ይሆን? ይህ ተግባር አገልጋዩ በጌታው ላይ ራሱን ሲያነግስ እንዴት ያለ ንቀትና ትእቢት ነው የሚያመለክተው?

የሰው ልጅ እንግዲህ፣ የአምላኩ የበታች አገልጋይ ነው። አምላኩም ፍፁም የተቀበለው ጌታው ነው።

መሪ ብሎ ወይ ለሀገሬ ገዥ ልምረጥ ሲል፣ ስርአት ልምረጥ ሲል ከፈጣሪው የሚያርቀው፣ የሚለየው ይሁን/አይሁን ለጌታው ተስማሚ ይሁን/አይሁን ምንም ግድ ሳይሰጠው አምላክ እንደሌለው ኢአማኒ ፈጣሪውን ፈፅሞ ከሀሳቡ ቢያደርገው፣ ምን ይሆን ውጤቱ? ትርጉሙ?

ምን ይሆን ከጌታው የሚኖረው ምላሽ? እኛስ ከጌታችን ምን ምላሽ ይሆን የምንጠብቀው? ነው ወይስ ጭራሹኑ ስለመኖሩም ክደነዋል?

በመፅሀፍት ባህሪውን የምናውቀው ያ ፈጣሪ የፈጣሪ ምላሹ ፀጥ ብሎ ወደሰዶማዊነት፣ ወደ ኢአማኒ ትውልድ ማፍራት፣ ወደ ሰይጣናዊ ባህል መመረዝ ስንገባ ዝም ብሎ መመልከት ነው ብለን የምናስብ ከሆነ እጅግ እንገርማለን።

እውነት የሚወደን ቢሆን፣ መቼም ወደዚህ አይነት ልቅነት፣ አጥፊ ትውልድ ቀረፃ፣ አምላክን አስረሽ አስተዳደር እንድንገባ አይፈቅድልንም። በ 97ም ሆነ በሚመጣው ዘመን በድህነትና በችግር ሆነን ራሳችንን ሳንለውጥ፣ ልጅነታችንን ሳንክድ ቢቆይልን የተሻለ ይሆንልናልና ልጆቹ አድርጎ ያቆየናል።

እኛ ባልነው ሆኖ እድገት ብለን ወደምንጠራው፣ ዴሞክራዊ ብለን እንደናፈቅነው ወደምኞታችን በስኬት ገብተን ቢሆን ኖሮ፣ ከአምላክ ፈፅሞ የምንርቅበት ስለመሆኑ ለማንም አእምሮ ላለውና ፈጣሪ እውነትም አለ ብሎ ለሚያስብ ሰው የማይካድ ሀቅ ነው። ሁላችሁም የምታውቁት በዚሁ ተፅእኖ ከእምነት የተለያየው በውቀቱ ስዩምም ሁኔታችንን መርምሮ እውነታውን ተናግሯል፣ “የጊዜ ጉዳይ ነውንጂ ሁላችንም በፍጥነት ወደዛው ነው የምንሄደው” ብሎ ያለንበትን ሁኔታና መዳረሻችንን ገልፆታል። ፈጣሪ የሚባል ነገር የለም ብሎ አምኖ ለተነሳው ይህ የማይካድ እውነት ነው። ነገር ግን እሱ ስላለና ጣልቃም ስለሚገባም ይህ አይሆንም። ወይ በቅጣት፣ ወይ በንሰሀ ወደእውነት እንመለሳለን። አይቀርም። ይህንን የምታነበው የፈጣሪን መኖር የምታምን ብቻ ሳይሆን የምታውቅ ስለሆንክ ይህንን ፈፅመህ አትቃወመውም።

እኛ ጠልተነው ዝም ቢለን፣ የጥንት ቅዱሳን አባቶች፣ ለራሳቸው ህይወትና እድሜ ሳይሆን 27 አመት ቆመው ቢፀልዩ ለሀገራቸ፣ ለሚመጣው ትውልድ ጭምር ነውና፣ ስለነሱ ስለገባው የማይታጠፍ ቃልኪዳን ብሎ አምላክ እጁን ያነሳል።

ታዲያ በትንቢቱ እንዳለው እንዲህ የፀና መከራ እንዴት ይደርስብናል? የተሻለ እምነት ኖሮን?

በቅድስት ሀገር ይህንን የመሰለ እድል ይዘን ብንወለድ፣ እድልን ብቻ ሳይሆን እዳንም ይዘን እንደተወለድን እንዳንረሳ።

ከመጀመርያው በወንጌል ተጠማቂ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጀምሮ መቶ አይደለም፣ ሺዎች አመታትን በክርስትና፣ በእግዚአብሄር ተአምራት መሀል የኖርን፣ ምሳሌ በሚሆኑ የክርስቶስ ቅዱሳን ገድልና ታሪክ በዝቶ በሚነገርበት፣ ቅዳሴ ያለማቋረጥ በሚፈስበት ሀገር ላይ

ሆነን በክህደት መንገድ ስንጓዝ፣ በውድቀት በርክስና መንገድ ስንነጉድ ሌላው ያጠፋ ሲባል፣ እኛ ደግሞ "አውቆ ያጠፋ" በሚል ይሆናል የምንታየው። ሌላው አለም የማያውቅ ሲባል፣ እኛ ግን ፈጣሪን አግኝቶት ከፊቱ ቆሞ የካደው ነው የምንባለው። ታዲያ መከራውና ቅጣቱ በማን ይፀና ይሆን? በቅዳሴ፣ በስብከት፣ በቃልኪዳን በበረከት መሀል እየኖርን የአምላክን ስራና ክብር በአይናችን እያየን በግዴለሽነት የካድነው መከራችን እንዴት አይፀና? ይህም ሁሉ ቅዱስን አንብቦ ለሚያውቅ ክርስትያን ሁሉ እንግዳ አይሆንበትም። ምክንያቱም በመፅሀፍ ቅዱስ ወንጌል አንዴ ብቻ ሳይሆን ሁለቴም ሳይሆን ሶስት ቦታ ላይ በማቴዎስ በሉቃስ በማርቆስ ወንጌል ላይ ይኸው ቃል ተደጋግሞ የተፃፈ ነውና

<< በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና።

ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል።

በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና።

ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል። >>

በአይናችን ፊትለፊት ያየነውን አባታችንን ብንክደው፣ እነሱ ግን ሲወለዱ ጀምሮ ያልሰሙትን ያላወቁትን ነው የካዱት። በዚህም መከራው በኛ ይፀናል። ከልባችን ተመልሰን በፅኑ ልመና አምላካችንን ከሚመጣው እንዲጠብቀን ብንለምነው ግን ፈፅሞ ሊጨክንብን አይችልም።

ዛሬም በደላችን የፀና ነውና፣ መዳን ከፈለግን የቅዱሳን አባቶቻችንን፣ እናቶቻችንን ቃልኪዳን በሙሉ አንብበን ልናውቅ ይገባናል። ቃልኪዳናችንን እንወቅ!! ስለቅዱሳን አባቶቻችን ቃልኪዳን ብሎ እንዲምረን ፈፅመን ልንለምነው ይገባናል። ይህ እጅግ ታላቅና ፍፁም የአምላክ ተግባር ነውና

በመዝሙረ ዳዊት

105:8 ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥ እስከ ሺህ ትውልድ ያዘዘውን ቃሉን አሰበ፥ ለአብርሃም ያደረገውን፥ ለይስሐቅም የማለውን

ብሎ አምላካችንን ቢገልፀው

ዘፀአት 20፥6 ላይ “ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር…” ብሎ አምላክ እራሱ ተናግሯልና

ትእዛዙን ጠብቀው በፅድቅ ኖረው ቃልኪዳንን ለመጪው ትውልድ የተቀበሉትን እያሳሰብክ ከአምላክህ ፊት በንሰሀ ወድቀህ ራስህን ታድን ዘንድ ይህ ፅሁፍ መጥቶልሀል።

ቅዱሳን አባቶችና እናቶች ስለአንተ ዛሬ ስላለኸው ብለው ነውና ቃልኪዳኑን የተቀበሉት። አቡነ መልከፄዴቅ እንኳን ቀጥታ በዚህቹ ሰአት ላይ ያለነውን በፀጋቸው ያውቁን ነበርና አምላክ ለስጦታው ቢጠይቃቸው “ከዚህ በኋላ የሚመጣው ትውልድ ተጠራጣሪ መርማሪ ሆኖ የሚቃወም ነውና፣ እነሱ ይድኑበት ዘንድ በአይን የሚታይ እንድትሰጠኝ እለምንሀለሁ” ቸሩ አምላክ ቢፈቅድላቸው ይኸው በቅፅራቸው የተቀበረ አስከሬን ሳይፈርስ ሳይበሰብስ እስከቅንድቡ ፀንቶ እየኖረ በሳንቲሜትር ልዩነት ከፊል አካሉ ወጣ ያለው በስብሶ እስኪታይ ድንቅ ስጦታን አልብሷቸው ሄደ።

አዬዬ... ደጉ አባታችን፣ ለማያውቁን ልጆችዎ በፍቅር ይህንን ቢሰጡን፣ እያየን ለመዳን ከማመን፣ ብዙዎቻችን እያየነው ለመካዳችን መፋረጃ እንዳይሆነብን አቤቱ እንዴት ያስፈራል?

ጥንት አባቶቻችን ጠላት ቢመጣ በገድሉ በሰፈረው ከአምላክ የተቀበለው ቃልኪዳኑ መሰረት በእምነት ሶስት ጊዜ “አምላከ ጊዎርጊስ” ብለው ስለገባው ቃልኪዳን እግዚአብሄርን ቢለምኑት ከድልም ደማቅ ድል አልብሶ አድኗቸዋል።

ይህ ለጥፋት የተነገረ የትንቢት ቃል አይደለም። የዘመኑ ሰወች ሰምተው ይድኑበት ዘንድ ነውና። አዲስም አይደለም።

በትርጓሜ ወንጌል ላይ እንደተመሰከረው በግራኝ ዘመን የነበረውን የ 40 አመት የመከራ ትንቢት ሳይቀር በህዝቡ ልመናና መመለስ፣ በድንግልማርያም ምልጃ እንዳጠረ ሰፍሮ ይገኛል።

ስለአባቱ ዳዊት ቃልኪዳን ብሎ ንግሱ ሶሎሞን ከባድ ክህደት ቢሰራ ከዙፋኑ ያልነሳው አምላክ፣ ዛሬም በዝተው ስላሉት ስለውድልጆቹ ቃልኪዳን ብሎ እንዲምረን ፈፅመን ልንማፀነው ይገባናል።

ከሁሉ ከሁሉ ከሁልሉ በላይ ዛሬ ያለነው ትውልድ እንደስፖርት ደጋፊ በስም ብቻ የያዝነውን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነታችንን እንወቀው እንወቀው እንኑረው። በከፊል መርጠን የምንይዘው የምንንጠባጠብበት ሳይሆን፣ ወይ ፈፅመን እንሁነው/ ወይ ፈፅመን እንካደው። ከሁለቱ መሀል ቦታ የለምና፣ ያም ሆኖ በመሀል መሆን እጅግ የከፋ ነው። ጥንትም ቢሆን በሰማይ በመላእክት መካከል በነቅዱስ ሚካኤል ሰራዊትና በሳጥናኤል ሰራዊት ጊዜም ቢሆን መሀል መሆን አልጠቀመም። መሀል ላይ የሆኑት ተፈርዶባቸው ያየር አጋንንት በመባል የሚታወቁት ዛሬም ድረስ የሚያሰቃዩን እጅግ ክፉ የሰው ጠላቶች ሆነው የሚገኙት ናቸውና። የአየር አጋንንትነትን እንተው።

እግዚአብሄርን ከሁሉ አስቀድማለሁ፣ ከሁሉ እወደዋለሁ የሚል ሰው

ለኑሮም፣ ለህገሩም፣ በየትም በሚያደርገው ጉዞ ከሁሉ ነገር የአምላኩ ፍላጎት የሚቀድምበት፣ ለሁሉ ነገር ቅድሚያ መስፈርቱ ለዛ ለሚወደው አምላኩ መመቸት/አለመመቸት የሆነ፣ ከዛ በኋላ ባለው እንደፈለገው በነፃነት በሀያልነት መኖር የሚችል ሰው መሆን አለበት። ከዛ ውጪ ግን በአፉ ብቻ እንደይሁዳ እየሳመ ልቡን የሚያደማ የደግ አምላክ እግዚአብሄር ጠላት ነው። አባቱን ሳያውቀው ከረከሰው ሌላው አለም ይልቅ፣ አውቆት የሚክደው ነውና ልቡን የሚያደማው ቅጣቱ ፍርዱ እጅግ እጅግ የከፋ ነው።

እግዚአብሄር ፈትኑኝ እንዳለ ታውቃለህን?

ደግሞ አምላክ እንድንፈትነው ይጠይቃልን?

አዎን። እግዚአብሄር አድርጎታል። መዳኛችን የሆነች ቤተክርስትያናችን ትፀና ዘንድ ልጆቹን ትሰበስብለት ዘንድ እሱው ከሰጠን ገቢ አስራት እንድናስገባ አፅንቶ፣ አዎ አፅንቶ ሲነግረን ይህንን ቃል ተናግሯል። “በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር” ብሎ በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ተፅፏል።

ይህንን ፀንቶ የተፃፈ ቃሉ ሆኖ ሳለ አይናችንን አፍጠን የማንተገብር ህዝቦች ነን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ነን ዛሬ የምንለው።

የካድን መሆኑን ማወቅ በራሱ ትልቅ ነገር ነውና ከሀድያን እንደሆንን እንወቀው። ቀድሞስ እንዲህ ያለውን ፅኑ ቃል እየካዱ ሌላ ከዚህ የከፋ ክህደት እንደው ከየት ይመጣል? ኧረ እንደው ከዚህ የከፋ ክህደት መቼ አለና ነው ራሳችንን ክርስትያን ብለን ለማሾፍ

የተነሳነው? እስከዚህ ድረስ ታውረናል? በእሳት መሀል ሆነን ሳለን እንዳንወጣ ራሳችንን "አቤት ብርዱ፣ ቅዝቃዜው ደስ ሲል" እያልን ነዶ ማለቅን ያክል ነው የዚህን አይነት ብዙ ፅኑ ቃሎችን እየካዱ ክርስትያን ነኝ ማለት። ለበለጠ ቃጠሎ መንደርደር!

በኢትዮጵያ ገዳማት፣ የገጠር አብያተክርስትያናት ተዘጉ፣ መናንያን ተፈናቀሉ፣ ገዳማት ችግር ውስጥ ሆኑ የሚል ቃል የተለመደ ምንም ስሜት የማይፈጥርብን ሆኗል። እጅግ አስደንጋጭ ነው፣ ይህን ተላምደነዋል! ትናንሽ ማህበራት አንዳንድ ጊዜ ቁንፅል የቤተክርስትያን አገልግሎት ቁሶች፣ እጣንና ሻማ ሲያበረክቱ እንኳን የራሳቸውን ትተው የእግዚአብሄርን ስም መቀደሻ እንኳን የመስእዋት እጣን ስላገኙ በረዥም ምርቃት በደስታ አልፎም በእንባ የሚያመሰግኑ መነኮሳትና ካህናትን በቪዲዮ ማየት ለኛ ተራ ልማዳችን ሆኖልናል።

ይህም ሁሉ እኛው ቤተክርስትያናት የሚገባቸውን ዘርፈናቸው ለዚህ አብቅተናቸዋል። ዛሬ ክርስትያን ብለን ራሳችንን እየደለልን ግን ያላመንነው መፅሀፍ ቅዱስ እንዲህ ስለክፉር ዝርፊያችን ይናገራል። በአግራሞት ሆኖ ስለእኛው እንዲህ ይላል።

“ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም። የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኵራት ነው።

“እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።”

ይህን ሁሉ እንዲሁ የተባለ ሳይሆን በመፅሀፍ ቅዱሱ ቃል በቃል ያለው የእግዚአብሄር ቃሉ ነው። የመፅሀፍ ቅዱስን ቃል ወይ እውነት ወይ ሀሰት በል ከሁለቱ መሀል የሆነ ቦታ የለም። ለራሳችን ብለን የምንመርጠው፣ የምንለዋውጠውም አይደለም። ዛሬ ያለነው

እንደምናወራው ቅዱስ ህዝብ አይደለንም፣ በዚህ መፅሀፍቅዱሳዊ ቃል መሰረት የተረገምን እርጉማን ህዝቦች ነን። አዎ እንደለመድከው “እኔኮ ክርስትያን ነኝ፣ ያውም ከጥንት ያልተለወጠችው ተዋህዶ” ብለህ ራስህን ደልለው። በስሟ ከመጠራት ያለፈ ህግጋቷንና ስርአታን አክብረህ፣ ኑሮህን በሷ እንቁዎች ካላደረጀኸው እውነተኛ ማንነትህ አንተ ያልከው ሳይሆን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት እውነተኛው ማንነትህ ያ ነው። ከልዑል እግዚአብሄር ቃል ሌላ ከፍ ያለ መለኪያ አለኝ ካልክ እንግዲህ አንተ ታውቃለህ።

ይኸው ይህንን ዛሬ አነበብከው፣ ነገር ግን ከአሁን በኋላ እንኳን እንደማትቀየር እነግርሀለሁ። ግን የተፃፈ የራሱን ቃል በመካድ አይን ያወጣ ክህደትን እንደያዝክ እወቀው።

ለሀዋርያቱ “ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል” ብሎ በአንደበቱ የተናገረላቸውን ሀዋርያቱን ያስራብክ፣ እነሱ እንደሆነ ዝም የሚሉ አባቶች ቀሳውስት በየቦታው ያሉ ሊቃውንትን ከሰማይ አይወርድላቸው ነገር የነፈግክ አይደለህምን?

ርጉማን ያላቸውን ህዝብ ተግባር አምላክ ፅፏል። ከሱ ተገዳድረህ እኔ ቅዱስ ነኝ ብለህ ብትከራከረው፣ መብትህ ነው። ነገርግን በዚህ መንገድህ መጨረሻህን ማንም አይቀይርልህም፣ እሱም ውድቀት ነው።

ሰበብ ልትሰጥ ትችላለህ፣ ሰበብ የሌለው ክህደትና ጥፋት እንደሌለ ግን እወቅ፤ ማንም በድሎ ሰበብ የማይሰጥ የለም፤ ያንተም ሰበብ ከዚሁ አይለይም፤ አያድንህምም። ምናልባትም "በዘመናችን ቤተክርስትያን አስተዳደር ውስጥ ብዙ አጥፊዎች ተመድበው አሉ፣ ብሰጥም በትክክል አይውልም..." ብዙ ልትል ትችላለህ። ግን ይህንን የምታደርገው ስለአምላክህ፣ ስለእሱ የጥያቄ ቃል ብለህ እንጂ የትኛው ተራ ምድራዊ ፍጡር ሰበብ ሆኖህ አምላክህን ልታሳዝን ተቻለህ? እምነት ጎድሎ እንጂ፣ ለምሳሌ አንድ የዋህ ደሀ ካለችው

ቆርሶ ሄዶ "ይህቺስ ለአባቴ ቤት ትሁንልኝ፣ አምላኬ ሆይ ለሚዘርፈው እሳት ትሁንበት፣ ለቤትህም ዋጋ አድርግልኝ" ብሎ ለአምላኩ ነግሮ ቢሰጥ፣ እምነቱ ተአምር በሰራ ነበር። ከገንዘቡ ይልቅ ፀሎቱ ቤተክርስትያኗን ባጠራት ነበር፣ ይህ ጥቂት ስጦታ ለቤተክርስትያናችን መድህኒቷ በሆነ ነበር። ወይ ካልሆነ እንኳን እንደ ማህበረ ቅዱሳን ላሉት፣ በአይን ለሚታዩት ማን አስገብቶ ይሆን? በገንዘብ ካላመነ እንኳን ማን ይሆን የአምላኬ ቤት ብሎ በማህበር ሆኖ በተግባርና ቁሶች በማድረግ ያስገባ፤ የቤቱ ቅናት በልቡ ያለ?

ቤተመቅደሱን ቤተመቅደሱን በገንዘብ ልውውጥ ገበያ ቢያረክሱት ክርስቶስ በቤቱ ቅናት ጅራፍ አነሳ። እኛ የአባታችን ቤት ቅናት ሊኖረን ሲገባ ጭራሽ ላልናቸው ሰወች አስረከብናት፣ አልፈንም በንፍገት ቤተክርስትያኒቷን የዱር ቅዱሳንን መበደል ምን ይባላል? ከጦር፣ ከእሳት የበረታ ፀሎትንና እምነትን የታጠቅን ሆነን ሳለን?

ምን ታደርግ ወንድሜ ከእውነተኛው የተዋህዶ የቀናች ህይወትና አኗኗር መንገድ በምን ያህል የራቅህ፣ ወይ የቀረብክ እንደሆነ ወይ እንግዲህ በጊዜ ወደኋላ ተመልሰህ አታይና ራስህን አታወዳድር ነገር፣ ምን ማድረግ ይቻላል? የተፃፉ መፅሀፍትን እንኳን በክርስቶስ ፍቅር አምላኬን ልወቀው ብለህ የምታነብ አልሆንክ።

ደክመህ ለአምላክህ መገዛት አልተቻለህምንጂ ስለእውነት ግን እምነትህን እንደምታፈቅራት አንተ ታውቃለህና እባክህን ቢያንስ ቢያንስ እውነቱን ከሰማህ፣ ወይ በመሰል አጋጣሚዎች ባወቅክ ጊዜ ራስህን አቅና። በእውነትም ቅድስት ናትና የምትወዳት የምትወድህ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ልጇ ሁን። ፈትነኝ ያለህን አምላክህን ያጎልብኛል ብለህ አላመንከውም? ነው ወይስ ቃሉ ውሸት ነው? ወይስ ከዚህ በላይ ምን ይበልህ?

መቼስ ደክመን ነውንጂ፣ ለኦርቶዶክስ እምነታችን፣ ለአምላካችን

ፍቅራችን ልዩ ነው።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሆኖ አምላክ ክርስቶስን የማያፈቅር፣ አይደለም እሱን የወለደቺው ሚወዳት እናቱን ድንግል ማርያምን ሳይቀር በፍቅርና በስስት የማይመለከት የለምና፣ ስለፍቅራችን ድንግል ማርያም ብለን እንኳን እንመለስ።

መቼም ግን የድንግል ማርያም ፍቅሩ በልባችን አለና፣ እስቲ ቢያንስ የምንወዳትን ቅድስት ድንግል ማርያም እንመናት፣ እሙብርሀን የተናገረችን እስቲ እኛ ኢትዮጵያውያን ልጆቿ እንኳን እንመናት!
ሰላም ለኪ እንል የለምንዴ? በመፅሀፍ ቅዱስ በሉቃስ ላይ የሰፈረው ቃሏ ነውኮ ሰላም ለኪ!
በዛ ቃሏ የአምላክን ሀይልና አድራጊነት የመሰከረችው በምድር የሚያደርገውንም ጭምር ነውና
ኧረ እስቲ እንወዳታለን የምንላትን ድንግል ማርያም የተናገረችውን እንኳን እንመናት!

ሰላም ለኪ ፀሎቷ ላይ "ዘረዎሙ ለእለ ያብዩ ህሊና ልቦሙ" ማለትም "በልባቸው ሀሳብ የሚታበዩትን ሁሉ በተናቸው" ብላ የተናገረችው፣ እኛ አምላክን የያዝን እንደሆነ፣ በሴራም በስልጣንም በሀይልም ከፍ ብለው የሚታዩት ሁሉ ከእግራችን በታች እንደሚበታተኑ ቃል በቃል የሷ ንግግር ነው።
"ነሰቶሙ ለሀያላን እም መናብርቲሆሙ" ሀያላን የተባሉት ሁሉ በቅፅበት ከየመንበሮቻቸው ሊያነሳ የሚቻለው አምላክ
"አበዮሙ ለትሁታን" ለተዋረዱትና ዝቅ ዝቅ ያሉትን ሁሉ ከማንም በላይ ታላቅና ከፍ የሚያደርግ አምላክ
"አፅገቦሙ እምበረከቱ ለርሁባን" ይዘውነው ተርበን የማናድር አምላካችን። ፀሎት ሲያስተምረን "የአመት ወይ የወር ቀለባችንን" ሳይሆን "የእለቷን" ብቻ እንድንጠይቅ ያስተማረን፣ ነገን በሙሉ መተማመን በሱ አምነነው እንድንጥል የነገረን፣ በዛም መንገድ የሆነ የቃልኪዳን ፀሎትን ያስተማረን እኛ ግን ያላመንነው አባታችን።

“ወ ፈነዎሙ ራእቆሙ ለብኡላን” ባለፀጋዎችን በአንዲት ቅፅበት ራቁታቸውን ሊያስቀር የሚቻለው

በምድር እንኳን ይህን ሁሉ የሚቻለው አምላክ ነው ፈጣሪያችን እያለች ድንግል ማርያም በፀሎቷ የተናገረችውን የምትወደን ልጆቿ አላምናት አልን። ድንግል ማርያምን አላምንሽም አልናት። ይሄ መሪ ፀናብን፣ እነህዚ ሀይልን የያዙ አሴሩብን፣ ባለስልጣናት ሊያጠፉን ነው፣ ይሄን መሾም አቃተን ወዘተ እያልን እንተራመሳለን። ዘወትር እናለቅሳለን፣ ፖለቲካ እያልን ስንደናቆር ስንፍጨረጨር እንውላለን። ነገር ግን አንዲትም ጊዜ እንኳን እንዲህ ድንግል ማርያም የነገረችንን ያንን ሁሉ የሚቻለውን አምላካችንን በሀገራችን ጉዳይ መፍትሄ አድርገን በህብረትና በጋራ ይዘነውአናውቅም። ኸረ እስቲ ቢያንስ ያለችን ሀብታችንን ድንግል ማርያምን እንመናት። ይህቺን እጅግ አጭር ፀሎቷን በቀን አንዴ ብናደርሳት፣ ሁሌ ስንላት እያንዳንዷን ቃል ትርጉም በየተለያየ ቀን ልብ ብለን እናደንቅ ነበር። ይሂቺ አጭር ፀሎት እምነታችንን ባጠነከረችው ነበር። ከቀን ወደቀን ባላሰብናቸው መንገዶች ህይወታችንን ወደእምነትና አምላካችን በመራችን ነበር። እናም ይህችን 5 መስመር አካባቢ ፀሎት በቀን አንዴ ማለት ቀላል ናትና፣ እስቲ እንሞክራት። ቢያንስ ያለችን ሀብታችንን የፍቅር እናት ድንግል ማርያምን እንመናት። እሷን እንኳን ማመን ያቅተን???

አስራት ሀገሯ ቆይ የትኛው ነው? ኢትዮጵያ አይደለችምንዴ? ነገር ግን በዚህ ዘመን ከኛ ይልቅ በእጥፉ ለግብፅ ኦርቶዶክስ ምእመናን ስለምን ይሆን አብዝታ የምትገለጠው? ስለምንድነው እንደዛ በአደባባይ ሁሉ ከምእመኑ የማትለየው? ይህንን ስናይ እንኳን እንዴት ልብ አንልም?

እጅግ ብዙዎቻችን በአፍ ብቻ እምነት ያለን መሆኑ፣ አንደኛ ነን በማለት ብቻ፣ በስም አማኝ ብቻ የሆንን መሆኑ እንዴት አይታወቀንም? በህይወት በተግባራችን ፈፅሞ ሀይማኖት አልባ

መሆናችንን እንዴት ልብ አንልም? እንዴት ያንን ስናይ እንኳን ልብ አንልም?

ከዛሬ ጀምሮ እንደምትወደው የእውነት ክርስትያን ሁን

መኪና ስትሳፈር እንኳን “በሰላም አስገባኝ” አትበለው፣ ይልቅ እስቲ ደፍረህ አምነኸው “ፈፅሞ ያንተው ፈቃድህ ይሁንልኝ” በል ክርስትና ያ ነውና፣ ፈቃዱን ማስቀደምን፣ መቀበልን ተለማመድ ! ! ! “ፈፅሞ ፈቃድህ ይሁንልኝ፣ ግን ከተቻለ የይቅርታና ቸርነትህ እንዲሆን እለምንሀለሁ” ብለህ አምነኸው ራስህን ስጠው፣ ፈቅዱ ሞትህም ከሆነ በደስታ ለመቀበል እስካልቻልክ እውነተኛ እምነት የለህምና ራስህን በዛ መንገድ አንፀው፣ ይህንን ሳትረሳ በመኪናም ሆነ በስጋትህ ጊዜ አትዘንጋው፣ ራስህን ወደአምላክህ አለማምደው። አባት ሆኖ ሳለ ደካማ ልጁ አምኖት ከእግሩ ስር ሲሸጎጥ ልቡ ችሎ የሚጎዳ፣ ችሎም ዝም የሚል አባት የለምና፣ እሱስ እንደሆነ ከኛ ልጅነትን እንጂ ጎሎበት ለሱ ልንሰጠው የምንችል እሱም የሚፈልገው አንዳችም የሌለው ደግ አባት ልጁ ሁንለት እንጂ ሁሉን እንዳይሰጥህ ቀድሞስ ምን አጋጅ ምክንያት አለውና?

የብዙ ገንዘብ እጣ ሊወጣልህ ቢል፣ ጌታህን እንደባሪያህ “ለኔ አድርገው” ብለህ ትእዛዝን አትስጥ፣ “እባክህን አምላኬ ያንተ ፈቃድ ብቻ ይሁንልኝ፣ ለኔ ፈቃድህ እሱ ከሆነ ባዶ እጄን እንድትመልሰኝ፣ አንዳችም እንዳላገኝ አብዝቼ እለምንሀለሁ፣ ለኔ ያልከው ፈቃድህ ከሆነ እንደፈቃድህ ይሁንልኝ” ብለህ ፈጣሪህን ማመኑን የህይወትህ መርህ አድርገው።

ለሌላው ተግባር ብትሰንፍ ይህቺን፣ ይህቺን ብቻ አድርጋት፣ በቀን 3 ጊዜ 25 ሴኮንድ የማትሞላውን "አባታችን ሆይ" ፀሎት በላት፣ እጅግ ቀላል ነውና፣ እንድታስታውሳትም ከ3ቱ ምግቦች በኋላ ከቁርስ፣ ከምሳ.. በኋላ፣ ወደመስሪያቤትህ ወይም ወደትምህርትቤት በምትሄድበት ጊዜ በመንገድህ ላይ፣ ወይም በሌላም መልኩ ራስህን

ሳትጫን እንኳን እንዲሁ ብትላት ትልቅ እርምጃ ይሆንልሀል፤ በዚህ መልኩ በቀን 3ቴ ማለቱ እጅግ ቀላል ነውና በዚቹ እንኳን ጀምር፤ አታጓድላት እንጂ እንዲሁ እንደዋዛ የምትላት አጭር ቀላል ፀሎት እየቆየ በምናውቀውም፣ በማናውቀውም መንገድ በስነልቦናህና በህይወትህ ላይ ተፅእኖ እየያዘች ትመጣለች፣ በጊዜ ሂደት ልብህ ናፍቆ፣ ፈልጎ ጊዜ ሰጥተህ አተኩረህ የምትላት ትሆናለች። በመልካም መንገድም ህይወትህ መልክ ይይዛል። ይህቺን በቀን የሴኮንዶች ፀሎት በአፈፃፀሟ ላይ ሳትጨነቅ ቁጥሯን ብቻ ሳታጓድል በላት፣ ይህቺን ቀላሏን እንኳን ለማድረግ ፈቃደኛ ሁን። በእምነት ወደፊት ትልቅ እርምጃ ትሁንልህ።

ተፈጥረሀልና በእውነት ህይወት ኑር። ሁሉ በጅህ ሆኖልህ፣ ምንም ካንተ የማይጠብቅ ወዳጅ አባት አምላክ፣ ልክ አንተኑ፣ አዎ ራስህ አንተኑ አስቦና ፈልጎ ፈፅሞ ሳይሳሳት የፈጠረህ ጌታ እያለልህ ወደእሳት፣ ወደተራ ስጋ መንገድ አትጓዝ። ይህ ሀያል አምላክ፣ ከምንም በላይ በሚያከብረው፣ በማያልፈው ቃሉ ላንተ ፍቅሩን ገልጧልና፣ ወደሱ በተመለስን ጊዜ እንደአዲስ የተወለደ ልጁ በፍቅር እንደሚያቅፈን ደጋግሞ በቃሉ ነግሮናል። ከመንገዱ ገብተህ በደስታ ትኖር ዘንድ ፈልጎ ፈልጎህ ፈጥሮሀልና በዛው ኑር። ቀኑ ደርሶ ከሚመጣው መከራ ሁሉ ትድን ዘንድ በንሰሀ ፀድተህ፣ በፍቅር ፀንተህ፣ በእምነት ጠይቀው። ትኖርበት ዘንድ ከተሰጠህ ምድርህ በመቅሰፍት አትጥፋ።

ካልሆነ ግን ሞት እንደሆነ በፊታችን ፀንቶ ቆሟልና ምርጫው የኛ ይሆናል።

ለጥያቄዎች እንዲሁም ምናልባትም አንዳንድ ተጨማሪ መረጃዎች ካስፈለጉ https://www.facebook.com/amlake.ethiopia ላይ የሚገኘውን "አንድ" የሚለውን ፔጅ እየተከታተሉ ይጠብቁ።

ልኡል እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን !

